# ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

# ሕይወቱና ትምህርቱ

*ሁለተኛ እትም*

አዘጋጅ፡- ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

አዲስ አበባ

ግንቦት፤ 2003 ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

©

**All Rights Reserved**



*የመጀመሪያ ዕትም:- 1999 ዓ.ም.*

*ሁለተኛ ዕትም:- 2003 ዓ.ም.*



**አድራሻ:- ፖ.ሳ.ቁ. 20278**

**አዲስ አበባ**

**ስልክ ቁጥር - 0911 - 482865**
**0911 - 477244**

**Email - deaconyaregal@yahoo.com**




# መታሰቢያነቱ

## የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነት:-

እግዚአብሔርን ደስ ከማያሰኙ ተግባራት ርቀው፣ ቤተ ክርስቲያንን ከሚያስነቅፉ ነገሮች ተጠብቀው፣ ከክፋትና ከተንኮል ነጻ ሆነው፣ በንጹሕና በቅን ሕሊና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው ላለፉና አሁንም በአገልግሎት ላይ ላሉ፣ በአጠቃላይ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለእውነት ኖረው ለእውነት ለሞቱና በእውነት መኖርን ዓላማቸው ላደረጉ ሁሉ ይሁን::

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለእኔ ሳይገባኝ የዚህን ታላቅ ቅዱስ አባት ሕይወትና ትምህርት አዘጋጅቼ እንዳቀርብ የፈቀደልኝ ቅዱስ እግዚአብሔር ስሙ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ የተመሰገነ ይሁን። አሜን።

ይህ ጽሑፍ በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅቶ እስኪወጣ ድረስ ረቂቁን በየጊዜው በመመልከትና አስተያየት በመስጠት፣ እንዲሁም በማበረታታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገውን ዲ/ን ብርሃኑ አድማስን አመሰግናለሁ። እንዲሁም ጊዜውን መሥዋዕት በማድረግ ረቂቁን የተመለከተልኝንና አስተያየት የሰጠኝን ቀሲስ ዶ/ር ሰሙ ምትኩን አመሰግናለሁ።

የመጽሐፉን ኅትመት አማናዊ በማድረግ በኩል ዋናውን ድርሻ የተወጣውን አቶ ተሻለ ሞላን አመሰግናለሁ። እንዲሁም አማኑኤል ደጉን፣ ረቂቁን በመጻፍ፣ በአሳብና በምክር የረዱኝን ኢ/ር ኃይለዓለም ወርቁንና ዘውዱ ገ/እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ከእነዚህም በተጨማሪ ከአሳብና ከምክር ጀምሮ አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ የረዱኝን ሌሎችንም ሁሉንም የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ደጉን ዋጋ ይከፍላቸው ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን። አሜን።



# ማውጫ

## ክፍል አንድ

## የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወት


ገጽ

መቅድም ........ ፯

መግቢያ ........ ፲፪

ክፍል አንድ፡- የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወት

1. ከልጅነቱ ጀምሮ እስኪጠመቅ ድረስ ........ 14
2. ጥምቀትና ገዳማዊ ሕይወት ........ 16
3. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በገዳም (374 - 381 ዓ.ም.) .... 19
4. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ - ዲያቆን፣ ቄስና ሰባኪ በአንጾኪያ (381-397) ዓ.ም. ........ 20
5. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ - የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ (398 - 404 ዓ.ም.) ........ 29
6. የመጀመሪያ ስደት (ግዞት)፡- ቴዎፍሎስ ዘእስክንድርያ እና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ........ 55
7. ሁለተኛ ግዞት፣ 404 ዓ. ም. ........ 61
8. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በስደት ላይ ........ 71
9. ዕረፍት ........ 74
10. የቅዱሱ ሰውነት ወደ ቁስጥንጥንያ መመለስ ........ 76
11. አጠቃላይ ስብእናውና ጠባዩ ........ 82
12. የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሥራዎች ........ 87

# ክፍል ሁለት

## የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርቶች

### ትምህርት አንድ


ወደ ቤተ ክርስቲያን ስላልመጡ ምዕመናን ያስተማረው ትምህርት ........................ 95


### ትምህርት ሁለት


አጋንንት በሰው ሕይወት ላይ ሥልጣን አላቸው ስለሚሉና ስለ እግዚአብሔር መለኮታዊ መግቦት ያስተማረው ትምህርት - 3 ተከታታይ ትምህርቶች

መግቢያ ........................ 107
ክፍለ ትምህርት አንድ ........................ 109
ክፍለ ትምህርት ሁለት ........................ 129
ክፍለ ትምህርት ሦስት ........................ 139


### ትምህርት ሦስት


በዩትሮጲየስ ምክንያት ያስተማረው ትምህርት

መግቢያ ........................ 154
ክፍለ ትምህርት አንድ ........................ 160

ዋቢ ድርሳናት ........................ 168


## መቅድም

ቤተ ክርስቲያን ስንል በክርስቶስ በተፈጸመው ድኅነት አምነው ለቃሉ እየታዘዙ ኖረው አገልግሎታቸውን ፈጽመው ያለፉ እና አሁንም በዚህ ዓለም ገና በጉዞ ላይ ያሉ ክርስቲያኖች እያንዳንዳቸውና በማኅበር ያላቸው አንድነትና ኅብረት ማለት ነው። በቤተ ክርስቲያንም የተለያዩ ጸጋዎችና የአገልግሎት ድርሻዎች፣ እንዲሁም የተጋድሎና የሕይወት ደረጃዎች አሉ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስንልም በተለያየ ዘመን የነበሩና የተነሡ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ቤተ ክርስቲያን በስብከተ ወንጌልና በክርስቶስ ደም ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ የፈጸሙት ታሪክ ነው። የተለያዩ ዖታ ምዕመናን እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን የየራሳቸውን መስቀል ተሸክመው በተጋድሎአቸውና በሕይወታቸው ክርስቶስን ያከበሩት ማክበርና ቤተ ክርስቲያንን ያስጌጡት ማስጌጥ ነው።

በዚህ ዓለም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ጉዞዋ በባሕር ላይ እንደሚሄድ መርከብ ነው። ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ወደ ጌርጌሴኖን ማዶ እዲሻገሩ ያዘዛቸው በባሕር ላይ ነው። ባሕሩንም በታንኳ ሲሻገሩ «ጌታ ሆይ አድነን፣ ጠፋን» እስኪሉ ድረስ ከባድ ማዕበል አስጨንቋቸው ነበር። ማቴ. 8+18-27። ነገር ግን በዚህች ሐዋርያት ተሳፍረውባት የባሕር ማዕበል ሲያማታት በነበረችው ታንኳ ውስጥ መድኃኔዓለም ክርስቶስ አብሮአቸው ነበር። ስለሆነም ክርስቶስ ባለባት ታንኳ (ቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ተሳፍረው ከክርስቶስ ጋር የሚጓዙ ሁሉ ባሕር የሆነ ይህ ዓለም ማዕበል እንደሚያስነሳ አስቀድሞ ማወቅና ራሳቸውን ማዘጋጀት ይገባቸዋል። በመከራ ማዕበል መናወጥ ትክክል ያለመሆንና ከክርስቶስ የመለየት ምልክት አይደለም፤ ይልቁንም ሐዋርያት ሲፈተኑ የነበረው ክርስቶስ አብሯቸው እያለ ነው። እራሱ ክርስቶስም በፈቃዱ መከራ ተቀብሏልና ያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ እንደየአቅሙ ከዚህ የክርስቶስ መከራ ሊሳተፍ ይገባዋል። የክርስቶስን መከራ ያልተሳተፈ ከክብሩ አይሳተፍም። ሮሜ 8+17 ፤ 2ጢሞ. 2+12

ከውጭ ለሚነሣው ማዕበል የውስጥ መጋቢዎች የሚሆኑም አሉ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት አድርገው እንደሚይዙት ሲጨነቁ ለነበሩት ጠላቶቹ *« እርሱን አሳልፌ ብሰጣችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ»* በማለት ሲሸጠው ከጠላቶቹ ጋር የተስማማበትና ለክርስቶስ የነበረውን ቀረቤታ ለጽድቅ ሳይሆን አሳልፎ ለመስጠት የተጠቀመበት ይሁዳም ከክርስቶስ ጋር አብሮ ነበር። *«ጌታ ሆይ ከአንተ ጋር እንሞታለን»* ያሉ እነ ቅዱስ ጴጥሮስና ሌሎቹም ሐዋርያት እንደነበሩ፤ እንዲሁም ያላትን ሁሉ ገንዘብ አፍስሳ ሽቶ ገዝታ በጌታችን እራስ ላይ በማፍሰስና እግሩን የሳመች በሰንበዋ እስከታጠበው ድረስ የወጀደችው ማርያም እንተሰፍረት እንደነበረች

ሁሉ ይሁዳ ደግሞ ለሠላሳ ብር ጌታውን ሸጧል። ሕይወታቸውን እንኳ ሳይቆር መስጠት ምንም መስሉ ያልታያቸው ክርስቲያኖች እንደነበሩ ሁሉ ሐዋርያው እንዳለ እግዚአብሔርን መምሰል ከንቱ ለሆነ ለዚህ ዓለም ክብርና ብዕል ማትረፊያ የሚመስላቸውም ነበሩ።

በነቢያት ዘመንም ከእግዚአብሔር የተላኩ እውነተኞች ነቢያት እንደነበሩ ሁሉ እግዚአብሔር ሳይልካቸው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እያሉ በድፍረት የሚዋሹና ሕዝቡን ያሳስቱ የነበሩ ሐሰተኞች ነቢያት ነበሩ። ከጌታችን የማዳን ሥራውን ፈጽሞ ማረግ በኋላም በሐዋርያት ዘመን ከእውነተኛ ወንድሞች (ክርስቲያኖች) ጋር ተደባልቀው የስህተት ትምህርት ያስተምሩ የነበሩ «ቢጽ ሐሳውያን - ሐሰተኞች ወንድሞች» ነበሩ። ከዚያም ቀጥሎ በነበሩት ዘመናት ሁሉ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች እንደነበሩ ሁሉ መናፍቃንና ሐሰተኞችም በየጊዜው ነበሩ። አማኒና ጻድቅ ያልነበረበት ዘመን እንዳልነበረ ሁሉ መናፍቅ ያልነበረበት ዘመንም አልነበረም።

ከዚሁም ሁሉ ጋር የክርስቶስ ፍቅር ገብቷቸው ክርስትናና ከዚያ የሚከተሉ ኃላፊነቶችን - ክህነትን እስከ ጵጵስና ድረስ «አውቃለሁ፣ እበቃለሁ» ብለው፣ ወይም «ይገባኛል» ብለው ሹመት ፈልገውና ተካሰው ሳይሆን «እኛ አንበቃም ተውን» እያሉ ነገር ግን ለመንጋው የግድ መሪ ስለሚያስፈልገው «እናንተ ለዚህ ኃላፊነት ትበቃላችሁ፣ መንጋውን ጠብቁ» እየተባሉ አደራ ሲጣልባቸው የተሰጣቸውን ከባድ ኃላፊነት የሚጠይቀውን ዋጋ ሁሉ በመክፈል የተወጡ ብዙ ቅዱሳን አባቶች ቤተ ክርስቲያን አሏት። ስም አጠራራቸውና ዝክረ ሕይወታቸው ከምንም ነገር በላይ የሚጣፍጥና ሕሊናን የሚያረካ የተቀደሰ ታሪክ ሠርተው ያለፉ በዙሪያችን እንደ ደመና የሚከቡን ብዙ ቅዱሳን በሰማዕትነት፣ በሊቅነት፣ በምዕመንነት፣ በገዳማዊ ሕይወት፤ በሁሉም ፈርጅ አሉ።

በተቃራኒው ደግሞ እነዚህን ኃላፊነቶች ለራሳቸው ግላዊ ክብርና ዝና መጠቀሚያ በማድረግ የክርስቶስን ክብርና በደሙ የዋጃትን ቤተ የክርስቲያንን ደኅንነትና ዕድገት ሳይሆን የራሳቸውን ምድራዊና ጊዜያዊ ፍላጎት ማስፈጸሚያ መሣሪያ ያደረጉትም ብዙዎች እንደነበሩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መስታወት ሆኖ ያሳየናል። በጣም የሚያሳዝነው ነገር ግን እንዲህ ዘላለማዊውን ክብር የለወጡለትን የዚህ ዓለም ክብርና ዝና እንኳ ሳይቀር በድርጊታቸው ያጡት መሆኑ ነው። በዘመናቸው ከነበሩ ከጥቂት አዳማቂዎቻቸውና መሰሎቻቸው በስተቀር (እነዚያም ቢሆኑ ለጥቅማ ጥቅማቸው ሲሉ የሚወዷቸውና የሚያከብሯቸው ከመምሰል በቀር በውስጣቸው አይወዷቸውም) ከነበሩበት ዘመን ጀምሮ የተጠሉ ናቸውና። በዘመናት የሚነሣው ትውልድ ሁሉ ሥራቸውን በታሪክ መስታወትነት የተመለከተ ሲወቅሳቸውና ስማቸው በክፉ ሲነሣ ይኖራል። በአንጻሩ



እውነተኞችና ደጋጎች ደግሞ ሁል ጊዜ በደግ ሥራቸው በመልካም ሲነሱና ሲታወሱ ይኖራሉ፤ በዘመናቸውም ቢሆን የሚጠሏቸው እንኳ ሳይቀሩ ቅናትና ክፋት ቢሸፍናቸውም በውስጣቸው ግን ያመሰግኗቸዋል።

ስለሆነም በቤተ ክርስቲያን እውነተኞች ስለነበሩ ስህተተኞችና አስመሳዮች ያልነበሩ ሊመስለን እንደማይገባ ሁሉ ሐሰተኞችና ብልሹዎች ስለነበሩና ስላሉ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛና መንፈሳዊ አርበኛ የሆኑ ልጆች የነበሯትና የሚኖሯት መሆኑን መጠራጠር አይገባም። በዚህ ዓለም ሁሉም በአንድ ላይ ተቀላቅለው ይኖራሉ። እስከ መከር (የፍርድ ቀን) ድረስ ስንዴውና እንክርዳዱ፣ ምርቱና ገለባው፣ ሰነፎችና ልባሞች፣ ሁሉም ተደባልቀው ይኖራሉ። ይህም እስከ ዕለተ ምጽአት ይቀጥላል።

በዚህ ዓለም ያለቺው ቤተ ክርስቲያን በውስጧ የምትይዘው ጻድቃንና ፍጹማንን ብቻ አይደለም፣ ኃጥአንንም ጭምር እንጂ። ከእነዚህ ውስጥ በንስሐ ተመልሰው ከደጋጎቹ ጎራ የሚቀላቀሉ ይኖራሉ፤ እንደ ዲያብሎስ በክፋታቸው ጸንተው የሚቀሩም ይኖራሉ። ይህ ዓለም ግን ገና የሽግግር ጊዜ ነው። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የፍጹማን ጻድቃን ብቻ የምትሆነው የዚህ ዓለም ጉዞዋ አብቅቶ ለዘለዓለም ከክርስቶስ ጋር ተዋሕዳ በምትኖርበት በሚመጣው ዓለም ነው። በዚህ ዓለም ክፉዎች የሌሉባት ቤተ ክርስቲያን የምንፈልግ ከሆነ እንዲህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን የለችም። ቢያንስ እኛ ስንገባበት የፍጹማን ማኅበርነቷን ታጣለች።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሕይወቱና ተጋድሎው፣ ትምህርቱም ይህንን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በተጨባጭ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ይህ አባት እውነተኛና ትክክለኛ ዓላማን ይዘው፣ በትክክለኛ መንገድ ተጉዘው፣ ይህ የእውነት ዓላማና ሕይወት የሚጠይቀውን ውድ ዋጋ ከፍለው በሕይወታቸውም በሞታቸውም እግዚአብሔርን ካከበሩና ደስ ካሰኙ ከታላቆቹ ቅዱሳን አባቶቻችን አንዱ ነው። እንዲሁም ይህ ተጋድሎአቸውና ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን በሰዎችም፣ ያውም በዘመናት በሚነሡ ትውልዶች ሁሉ ከታወቀላቸው ጥቂት ቅዱሳን ሰዎች ውስጥ ነው።

እሾህና አሜኬላ በበቀለበት በዚህ ዓለም ኖረው ነገር ግን በሕይወታቸው ነውር ነቀፋ ካልተገኘባቸውና የዚህ ዓለም ጥላሸት ካላረፈባቸው ጥቂት ቅዱሳን አባቶች አንዱ ነው። ምንም እንኳ የቅድስናና የብቃት ደረጃ ሰው የቻለውን ያህል ይደርስበታል እንጂ መጨረሻው ይህ ነው ባይባልም ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሥጋ የለበሰ ሰው፣ ሰው እንደመሆኑ መጠን ሊሆነው የሚገባውን የሆነ፣ ሊደርስበት ከሚገባው የክብርና የቅድስና ጣራ የደረሰ ነው። ክርስትና በንጹሕ ሕሊና ሲረዱትና በንጹሕ መዝገብ ሲቀበሉት በሰው

ሕይወት ላይ ምን ያህል እንደሚያበራ በዚህ ቅዱስ አባት ሕይወትና ትምህርት በግልጽ እናያለን።

ቤተ ክርስቲያንን የመምራትና የማስተዳደር ኃላፊነት ምን ያህል ከባድ መሆኑንና በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥ በድል አድራጊነት ለማለፍ ምን መሆንና ማድረግ እንደሚገባ ያሳየናል። እርሱ አንድ የቤተ ክርስቲያን አባት እንዴት መሆንና ምን ማድረግ እንደሚገባው ፍጹም አርአያ ነው። እርሱ ለነበረበት ዘመን ብቻ ሳይሆን ትምህርቱና ሕይወቱ ሁል ጊዜም ሕያው የሆነ የሁሉም ዘመን መምህር ነው። በእርሱ ዘመን ከነበረው የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ለዛሬዋም ቤተ ክርስቲያን ብዙ አማናዊ ተመክሮና ትምህርት እናገኝበታለን።

በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ በዙሪያዋና በውጭ ያሉትን ክፉዎቹንም ደጋጎቹንም የየራሳቸውን ሚና ሲጫወቱ እናያቸዋለን። እንጻና ዘንድም ክፉዎቹን እንዳንመስል፣ ደጋጎቹን ደግሞ እንድንመስላቸው ያስተምረናል። ታሪክ ማጥናትና ማወቅ ዋና ጥቅሙ በታሪክ ከተፈጸሙት ታሪካዊ ስህተቶች ተምሮ እነዚያን ላለመድገም ነበር። ነገር ግን «ታሪክ ብዙውን ጊዜ የሚያሳየው ሰዎች ከታሪክ አለመማራቸውን ነው» እንደሚባለው እኛም ክርስቶስን በማመን እንጸና ዘንድ የወደቁትንና ክፉዎች የነበሩትን ሳይሆን ደጋጎቹንና የጸኑትን እንድናስብ የጸኑ ቅዱሳንን ሕይወት ማጥናትና ማወቅ በጣም ጠቃሚያችን ነው። በመጀመሪያ ራሱን አሳልፎ እስኪሰጥልን ድረስ የወደደንንና ስለ እኛ መዳን ሲል በመከራ መስቀል የጸናውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንመልከት። ከዚህም ጋር የክርስቶስ ፍቅርና ውለታ ገብቷቸው መስቀላቸውን ተሸክመው እርሱን በመከተል ከጸኑት ውስጥ ታላቅና ደገኛ የሆነውን የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ሕይወትና ትምህርት ማወቅ ጠቃሚ ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱን ሲያስቡት ሁል ጊዜ አስደሳችና ከውስጥ የጥንካሬ መንፈስን የመፍጠር ኃይል አለው። በእግዚአብሔር የሚያምን ክርስቲያናዊ የሆነ ሰው፣ ሰውን ሁሉ አስተካክሎ ለመውደድ እንዲችል ከመሆን በስተቀር ሌላ ግዴታም ሆነ ጌታ የሌለው መሆኑን ያስተምረናል። ነገሮችን ሁሉ የምናይበት ማዕዘንና የምንለካበት መስፈሪያና መለኪያም «የክርስቶስ ክብር» ብቻ እንዲሆን ያሳስበናል። ስለ አንድ ነገር አስቀድሞ ብዙ መናገር ምናልባት የማጋነንና የማጉላት ልማድ ተደርጎ እንዳይወሰድና ያንኑ የበለጠ ለማሳወቅ የተፈለገውን ነገር ዝቅ አድርጎ እንዳያሳይ ከመስጋት የተነሣ ስለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በመቅድሙ ላይ ብዙ አንበል። ወደ ውስጥ ገብተን ሕይወቱንና ትምህርቶቹን ስናነብ ራሳችን በራሳችን ጊዜ የራሳችን የሆነ ግንዛቤ እናገኛለንና።



ከነበረበት ዘመን እንስቶ በየዘመኑ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ጸሐፍያንና ሊቃውንት ብዙ የተጻፈለትን፣ እርሱም ሥራውና ትምህርቱ በጣም ብዙ የሆነውን የዚህን አባት የሕይወት ታሪክ ሙሉውን በትንሽ መጽሐፍ ወስኖ ማቅረብ የማይቻልና የማይታሰብ ነው። ከዚህም ጋር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን በሚገባ ለማወቅና ለመረዳት ከማንኛውም ያለፉ ቅዱሳን አበው በላይ ጥሉልን የሄዳቸውን እጅግ ብዙ የሆኑ የትርጓሜና ሌሎቹንም ሥራዎቹን (ጽሑፎቹን) ማንበብ ይጠይቃል። ቢሆንም ይህን መጽሐፍ ስለ እርሱ አግባብ ያለው ሥዕል እንዲያሳይ አድርጎ ለማዘጋጀት ተሞክሯል።

መጽሐፉን አንብበን ስንጨርስም « እግዚአብሔር ሆይ፣ እንዲህ ያለውን ቅዱስ አገልጋይህንና ባለሟልህን እንዳውቀው ስለፈቀድህልኝ አመሰግንሃለሁ» እንበል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅንም «ጸሎትህና ምልጃህ አይለየኝ፣ በፍቅርህም ተቀበለኝ፤ በፍጹም ኃይልህና በፍጹም ልብህ ያገለገልሃትና የተሰደድክላት ቤተ ክርስቲያንንም አስባት» እንበለው።

እስመ ኵሉ እምኔሁ ወኵሉ በእንቲአሁ ወኵሉ ቦቱ ወሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን። ሮሜ 11፥36

ሁሉ ከእርሱ፣ ሁሉ በእርሱና ሁሉ ለእርሱ ለሆነ ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን፣ ዛሬም ዘወትርም ሁልጊዜም ለዘለዓለሙ አሜን።

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ክፍል - ክፍል አንድ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ሕይወት የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከትምህርቶቹ ውስጥ የተወሰኑት ተተርጉመው የቀረቡበት ክፍል ነው።

በመጀመሪያው ክፍል ዜና ሕይወቱ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ተገልጾአል። ከልጅነት ጊዜው ጀምሮ እስከሚጠመቅ ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ ያሳለፈው ሕይወት፣ ከዚያም ከተጠመቀ በኋላ ያለው ሕይወትና የገዳማዊ ሕይወቱ ተገልጾአል። ከከባድ ትኅርምት የተነሣ ጤናው አደገኛ ሁኔታ ላይ በመውደቁ ከብሕትውና ዋሻው ወደ አንጾኪያ ተመልሶ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በዲቁና፣ ከዚያም በቅስናና በስብከት ያገለገለባቸው ዓመታት፣ እንዲሁም በዚህ ጊዜ ውስጥ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የነበረችበት ሁኔታ ተዳሰዋል።

ፈቃደኝነቱ ሳይጠየቅና ሳይፈልግ በድንገት የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ የተደረገበት ሁኔታና ከዚያም በምሥራቁ የሮማ ግዛት ዋና ከተማ በቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ከሆነ በኋላ ቤተ ክርስቲያንንና ኅብረተሰቡን ለማስተካከልና ወደ እውነተኛው መስመር ለማስገባት ያደረጋቸው ከባድ ተጋድሎዎች ተገልጸዋል። እነዚህ ሥራዎቹ ያስከተሏቸው ውጤቶችም እንዲሁ ተብራርተው ይገኛሉ።

የሕይወት ታሪኩ ስቦ የሚያመጣቸው ቤተ ክርስቲያን ነክ ተዛማጅ ጉዳዮችና ታሪኮችም አብረው ተዳሰዋል። በተለይም ደግሞ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ታሪክ ሲነሣ አብሮ የሚነሣው የእስክንድርያ ፓትርያርክ የነበረው የቴዎፍሎስ ጉዳይም ትክክለኛ ማንነቱን ለመረዳት በሚያስችል መልኩ ታሪኩ ዘርዘር ብሎ ይገኛል። ከዚሁም ጋር የቆጵሮሱ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ተዛማጅ የሆነው ታሪክም እንዲሁ በዚሁ መጽሐፍ ተመልክቷል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለእውነት በነበረው የማያወላውል አቋምና ለቤተ ክርስቲያን መብት መከበር ያሳይ በነበረው የጸና ሰብእና ምክንያት ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት በተውጣጡ የቤተ ክርስቲያን የውስጥና የዙሪያ ጠላቶች የደረሰበት አሳዝኝ ግፍ፣ ይህም በቤተ ክርስቲያን ላይ ያስከተለው ነገርም ተገልጾአል። እርሱም ለእውነት ኖሮ በሕይወቱም በሞቱም ክርስቶስን ገልጦና አክብሮ ያሳለፈው የሰማዕትነት ሕይወት ከመጀመሪያ ጀምሮ በስደት በተፈጸመው ሕይወቱ ግልጽ ሆኖ ይታያል።

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ካስተማራቸው የብዙ ብዙ ትምህርቶች መካከል ሦስቱ ተተርጉመው ቀርበዋል። አንደኛው ትምህርት ክርስቲያኖች ሆነው ሳለ ነገር ግን በክብረ በዓልና በዓመታዊ በዓላት ቀን ካልሆነ በቀር ወደ ቤተ ክርስቲያን የማይመጡትን በተመለከተ የተሰጠ ትምህርት ነው። ሁለተኛው ትምህርት ደግሞ ሦስት ተከታይ ትምህርቶችን የያዘ ሲሆን እነዚህም፣



«አጋንንት በሰው ሕይወትና በዚህ ዓለም ባሉ ነገሮች ላይ ሥልጣን አላቸው፤ የሰው ሕይወቱ በዕድሉ የተወሰነ ነው፣ ስለዚህ ሰው በራሱ ምርጫ ምንም ማድረግ አይችልም፣ እግዚአብሔር ሰይጣንን ለምን ፈጠረው? ለምንስ አላጠፋውም?» ስለሚሉና በእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃና መግቦት ላይ ጥርጣሬና ጥያቄ ባላቸው ሰዎች አስተሳሰብ ላይ የተሰጠ ጠንካራና በሳል ትምህርት ነው።

በዚህ ትምህርቱ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ በሁሉ የተገለጸ መሆኑን፣ አጋንንት ሥልጣን ቢኖራቸው ኖሮ ምን ያደርጉ እንደነበረና የእኛም ሕይወት እንዴት ይሆን እንደነበር ተንትኖ ያሳያል። የሰው መውደቅ ዋናው ምክንያት የራሱ የሰው ስንፍና እንጂ ሰይጣን አለመሆኑን በማስረዳትና ጥፋትንና ውድቀትን በሰይጣን ማመካኘት ዋናው የሰይጣን መሣሪያ መሆኑን በማሳየት ራሳችንን ከዚህ የውድቀት በር ከፋች ከሆነ ደካማ አስተሳሰብ እንድንጠብቅ ይመክራል። ሰው በእግዚአብሔር ኃይል ፈተናን መቋቋምና ድል ማድረግ የሚችል መሆኑን፣ ለዚህም ወሳኙ ዓላማና ውሳኔ መሆኑን ይገልጻል።

ሦስተኛው ትምህርት ደግሞ በዘመኑ የንጉሡ ቆንስላ (ከንጉሡ ቀጥሎ የነበረው ከፍተኛ ባለሥልጣን) የነበረው ሰው በአንድ ቀን ውስጥ በድንገት ከሥልጣን ተባሮ ሲገደል ሲሳደድ ሳለ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ጥገኝነት በመጠየቁ ሁኔታ በተፈጠረው ክሥተት ላይ ያስተማረው ትምህርት አንዱ ክፍል ነው። የዚህን ዓለም ሀብት፣ ሥልጣንና ክብር ጊዜያዊነትና ከንቱነት ይረዱ ዘንድ ሁል ጊዜም ያስተምር እንደነበረ ሁሉ በዚህ ክሥተት የተግባር ማሳያነት ደግሞ ይህንኑ በገሃድ በማሳየት ሰማዕያኑ ትምህርቱን የበለጠ ይረዱት ዘንድ አስደናቂ በሆነ ቋንቋና በግሩም አገላለጽ ያስተማረው ትምህርት ነው።

በሁለቱም ክፍሎች ላይ ለግንዛቤ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የታመነባቸው ማብራሪያዎችና ታሪኮች በግርጌ ማስታወሻ ተገልጸዋል። በግርጌ ማስታወሻዎቹም ሕይወታቸው አስተማሪ ነው ተብሎ የታመነባቸውን፣ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ግንዛቤን ለማዳበር ይረዳሉ ተብለው የታመኑና አስፈላጊ ሆነው የተገኙ ነገሮች ተካተዋል።

ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ምንጭ ተደርገው የተወሰዱት በአካል የሚያውቁትና አብረውት የነበሩት እነ ጳላድዮስ ከጻፉት ጀምሮ ዘመን ገጠም የነበሩት እነ ሶቅራጥስና እነ ሶዞመንና ሌሎችም ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጸሐፊዎች የጻፏቸው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ድርሳናት ናቸው። እንዲሁም ከዚያም ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ዘመናት መዛግብት አመሳክረውና ምንጭ አጣቅሰው በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወትና ትምህርት ላይ የተጻፉ የተለያዩ ድርሳናትም ጥቅም ላይ ውለዋል። የቅድስና ሕይወቱና ተጋድሎው እንዲሁም ትምህርቱ እጅግ በጣም ብዙ የሆነውን የዚህን ቅዱስ አባት ሕይወትና ትምህርት በተመለከተ ለአንባቢ በጣም ሳይበዛ፣ እንዲሁም ደግሞ ተጠቅሎ ጭብጡንና ፍሬ ነገሩን ሳያሳይ እንዳይቀር አድርጎ ለማቅረብ ቀላል ሥራ ባይሆንም በእግዚአብሔር ፈቃድና ርዳታ የሚቻለውን ያህል ጥረት ተደርጓል።

# ክፍል አንድ

## የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወት

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቤተ ክርስቲያን ካፈራቻቸው ሰባክያንና መተርጉማን ታላቁና ደገኛው አባት ነው:: ዛሬም ድረስ በመላው የክርስትና ዓለም ከፍተኛውን ክብር ይዞ ይገኛል:: እንከን የለሽና ደስ የሚያሰኝ የሕይወት አሻራ ትቶ ያለፈ፣ በሰባክያንና በመተርጉማን ተዘውትሮ የሚነበብና የሚጠቀስ፣ በሁሉም ዘንድ በፍቅር የሚታወስ እንደ እርሱ ያለ የለም:: ከዕረፍቱ በኋላ ከ5ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ጀምሮ በተጋድሎው፣ በትምህርቱና በሕይወቱ ቅድስና የሚያደንቁትና የሚወዱት የኋላ ዘመን (ከዕረፍቱ በኋላ) ክርስቲያኖች «አፈወርቅ»[1] የሚለውን ቅጽላዊ መጠሪያ ሰጡት:: ይህም ከመጠሪያ ስሙ (ዮሐንስ) በላይ ጎልቶ የሚታወቅበትና የሚጠራበት እስኪሆን የደረሰ ሲሆን ለቤተ ክርስቲያን ላበረከተው ሁለገብ የሆነ ታላቅ አስተዋጽዖም ተገቢ የሆነ አጠቃላይ መግለጫ ነው:: በዚህ በክፍል አንድ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ሕይወት እንደሚከተለው ከፋፍለን እናያለን::

### 1. ከልጅነቱ ጀምሮ ስኪጠመቅ ድረስ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በ347 ዓ.ም. የሶርያ ዋና ከተማ በነበረችው፣ ከአሕዛብ ወደ ክርስትና የሚገቡ ክርስቲያኖች መነኻሪያ ማዕከል በነበረችውና ክርስቲያኖች መጀመሪያ «ክርስቲያን» ተብለው በተጠሩባት በአንጾኪያ ከተማ ተወለደ:: አንጾኪያ የምሥራቁ የሮማ ግዛት ሁለተኛ ከተማ (ከቁስጥንጥንያ ቀጥሎ) ነበረች:: ዐራተኛው መቶ ዓመት የተለያዩ መናፍቃን (መነናውያን፣ ግኖስቲኮች፣ አርዮሳውያን፣ አቡሊናርዮሳውያን) እንዲሁም አይሁዶችና መምለክያነ ጣዖት የሆኑት ሁሉ በአንጾኪያ ከተማ ሁሉም የየራሳቸውን እምነት ለማስፋፋት ይሯሯጡበት የነበረ ዘመን ነው:: ኦርቶዶክሳውያኑ ክርስቲያኖች ራሳቸው በጳጳስ መላጥዮስና በጳውሊኖስ መካከል በነበረው ልዩነትና ክፍፍል ምክንያት ከሁለት ተከፍለው ነበር:: ስለዚህ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የወጣትነት ዘመን ቤተ ክርስቲያን በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ በነበረችበት ጊዜ ላይ ነበር::

[1] {(Chrysostomos - በግሪክ)፣ Golden mouth)}





አባቱ ሴኩንዱስ የታወቀ ታላቅ የጦር መኰንን የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ቅዱስ ዮሐንስ ገና ሕፃን እያለ ነበር የሞተው:: እናቱ አንቱዛ በሃይማኖቷና በምግባሯ እጅግ በጣም የተደነቀችና የተመሰገነች ክርስቲያናዊት ነበረች:: ገና በሃያ ዓመቷ ባለቤቷ በሞት ቢለያትም ማንኛውንም የሁለተኛ ጋብቻ ጥያቄ ሁሉ ባለመቀበል አባታቸው ጥሏቸው የሞቱትን ሁለቱን ልጆቿን:- ቅዱስ ዮሐንስንና ታላቅ እኅቱን በማስተማር ላይ አተኮረች:: አንቱዛ ክርስትና በሴቶች ሕይወት ላይ እንዴት እንደሚያበራና የሚያሳድረውን መልካም ተጽእኖ በተግባር በማሳየት በዛን ዘመን ከነበሩ ፍጹም ሃይማኖተኛ እናቶች ወገን የሚያስመድብ ሕይወት ላይ የደረሰች ነበረች:: የእናቱ የአንቱዛ የተቀደሰ ሕይወት በክርስቲያኖች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በአሕዛብና በታላላቅ የዘመኑ ምሁራን ዘንድ ሳይቀር የተደነቀ ነበር:: ሊባንዮስ የተባለው ዋነኛ የአሕዛብ ቀበለእምነት[2] ጠበቃ የነበረው የእርሷን ጽናትና ሕይወት ሲሰማ «አቤት! ከክርስቲያኖች ወገን እንዴት ዓይነት አስደናቂ ቅድስና ያላቸው ሴቶች አሉ!» ብሎ ለመገረም ተገዷል::

እናቱ አንቱዛ ልጇ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፍልስፍናንና የንግግር ጥበብን በዘመኑ ከነበሩት ታላላቅ መምህራን እንዲማር አደረገች:: እንዲሁም በልጇ አእምሮ ውስጥ ከልጅነቱ ጀምሮ የእምነትን ዘር ጥሩ አድርጋ ዘራች:: ይህም የእምነት ዘር በኋላ ለራሱና ለቤተ ክርስቲያን እጅግ ጠቃሚ የሆነ ብዙ ፍሬ አፍርቷል:: በእናቱ ተግሣጽና በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በዘመኑ ተንሰራፍቶ ከነበረው አሕዛባዊ ነገረ ዘርቅና ከንቱ አስተሳሰብ ተጠበቀ::

ሆኖም ግን እስኪያድግ ድረስ አልተጠመቀም ነበር:: ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ ከአሕዛብነት ወደ ክርስትና በሽግግር ላይ በነበሩበት በዚያ ዘመን የንዑስ ክርስቲያን ተጠማቂዎች ብዛት ከሕፃናት ተጠማቂዎች በጣም ይበልጥ ነበር:: ከዚህ የተነሣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት (እነ ቄርሎስ ጳጳስ ዘኢየሩሳሌም፣ ራሱ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እና ሌሎችም) ለንዑስ ክርስቲያኖች ከመጠመቃቸውና ወደ ቅዱስ ቁርባን ከመቅረባቸው በፊት የሚማሯቸው ወጥና መሠረታዊ ትምህርቶች አዘጋጅተዋል:: አንዳንድ ክርስቲያን ቤተሰቦች ሳይቀሩ የልጆቻቸውን ጥምቀት እስኪያድጉ ድረስ ያዘገዩ ነበር:: ይህም ለጥምቀት ካላቸው ከፍተኛ ክበሬታ የተነሣና ቶሎ መጠመቅ የጥምቀትን ጸጋ መልሶ የማጣት ሥጋት አለው ከሚል በዘመኑ ከነበረ የፍርሃት አስተሳሰብ የተነሣ

[2] (Heathenism, Paganism)

ነበር:: ይህም ዛሬ ብዙዎች ንስሐ መግባትንና መቁረብን ሊሞቱ እስኪጣጣሩ ድረስ እንደሚያዘገዩት ዓይነት አስተሳሰብ ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በኋላ ይህን ልማድ ትክክል አለመሆኑን በመግለጥ አጥብቆ ይኮንናል[3]::

በዘመኑ የነበረውን የንግግር ጥበብ ትምህርት (ክሂሎተ ነቢብ)[4] በዘመኑ ቁጥር አንድ ሊቅ ከነበረው ሊባንዮስ ከተባለው መምህር ተምሯል:: ፍልስፍና ደግሞ በአቴንስ ከነበሩ ዕውቅ መምህራን ተምሯል:: በአጠቃላይ እውቀቱ፣ በትምህርቱና በማስተዋል ችሎታው አብረውት ከሚማሩት ጓደኞቹ ሁሉ በላይ ነበር:: ይህም ትምህርቱ ወደፊት ለሚሰማራበት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጣም ጠቅሞታል:: ቅዱስ ዮሐንስ የሊባንዮስ ምርጥና ተወዳጅ ተማሪው ነበር:: ሊባንዮስ ሊሞት ሲል «ማን ቢተካህ ትወዳለህ?» ብለው ሲጠይቁት «ክርስቲያኖች ከእኛ ሰርቀው ባይወስዱብን ኖሮ የሚተካኝ ዮሐንስ ነበር» ብሏል::

ትምህርቱን እንደ ጨረሰ ለትንሽ ጊዜ ጠበቃ ሆነ:: ይህም ሥራ ለመንግሥት ሹመትና ሥልጣን ዋና በር ከፋች ነበር:: በፍርድ ቤቶች ውስጥ የንግግር ክህሎትንና ልዩ ተሰጥኦን ማሳየት ለታላላቅ ሹመቶች ከሚኒስትርነት እስከ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ድረስ ሊያደርስ የሚችል ዋና ጥርጊያ ጎዳና ነበር:: በፍርድ ቤት የሚያደርጋቸው ንግግሮች በሰማዕያኑና በመምህሩ በሊባንዮስ ሳይቀር ከፍተኛ አድናቆትን አስገኙለት:: ሆኖም እርሱ ግን በዚህ ደስተኛ አልሆነም:: ሞራላዊ ደረጃው በዘቀጠና በተበላሸ ማኅበረሰብ መካከል መኖር አስጠላው:: መጥፎውን ጉዳይ ጥሩ አስመስሎ በማቅረብ ገንዘብ ማግኘት የሰይጣንን ደመወዝ መቀበል ሆኖ ተሰማው:: ለክርስትና ያለው ዝንባሌና ፍቅር እየጨመረ መጣ:: የተሰጠውን ትላቅ ጸጋ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማጥናትና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማዋል አዘነበለ::

## 2. ጥምቀትና ገዳማዊ ሕይወት

ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥንቃቄና በጥሞና ማጥናቱ፣ የእናቱ አርአያነት ያለው የቅድስና ሕይወት፣ ከጳጳስ መላጥዮስ ጋር መተዋወቁ እና የገዳማዊ ሕይወት ዝንባሌ የነበረውና የዕድሜ እኩያው የነበረው የቅርብ ጓደኛው የባስልዮስ ተጽእኖ በሕይወቱ ላይ ቀስ በቀስ ለውጥ አመጡ:: ከደጉ በኋላ ወደሚጠመቁ ንዑስ ክርስቲያኖች በመግባት ከተለመደው የ3 ዓመት የትምህርትና የአመክሮ ጊዜ በኋላ በ23 ዓመቱ (በ370 ዓ.ም.) በጳጳስ መላጥዮስ ተጠመቀ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ፣ ይላል ዜና ሕይወቱን የጻፈው የሄልዮፖሊስ ጳጳስ የነበረው ጳላድዮስ[5]፣ «ፈጽሞ አልማለም፣ ማንንም አልረገመም፣ በሐሰትም አልተናገረም፣ ረብ ጥቅም የሌለው ነገር ታግሦ አልሰማም፣ ጥምቀቱ ይህን ዓለም ፈጽሞ የካደበትና ክርስቶስን ለማገልገል ራሱን የሰጠበት፣ ከዓለም ለክርስቶስ የተለየበት፣ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያደረገበት ነበር:: ለውጡም ፍጹምና ዘላቂ ነበር::»

በወጣቱ በቅዱስ ዮሐንስ ሥነ ምግባርና አጠቃላይ ሁኔታ ደስ በመሰኘቱና የዚህን ወጣት የወደፊት ታላቅነት የተረዳው የአንጾኪያው ጳጳስ መላጥዮስ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሰማራ ለማድረግ ስለፈለገ አናጉንስጢስነት (የአንባቢነተ መዓርግ) ሾመው:: እንደተጠመቀ የእርሱ ፍላጎትና ዝንባሌ ማን ወደ ገዳም ሄዶ በዚያ ገዳማዊ ሕይወትን መምራት ነበር:: ነገር ግን የእናቱ ጥብቅ ልመናና ተማጽኖ የገዳማዊ ሕይወት ፍላጎቱን ከማሟላት ለጊዜውም ቢሆን አዘግይቶታል:: እናቱ በሕይወቷ እስካለች ድረስ ተለይቷት እንዳይሄድ፣ ከዚህ ዓለም ከተለየች በኋላ ግን

[3] በሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች አገላለጽ ደግሞ እናቱ አንቱዛ የልጇን ጥምቀት ያዘገየቺው ከጥምቀት በኋላ ኃጢአት የመሥራት ስጋት በሚለው አስተሳሰብ ሳይሆን ያን ጊዜ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በኦርቶዶክሳውያንና በአርዮሳውያን መካከል በነበረው ትግል ትታመስ ስለ ነበር ኦርቶዶክሳውያን የሆኑት ጥርት ብለው ተለይተው እስኪታወቁ ድረስ ነበር ይላሉ::

[4] (Rhetoric)

[5] ጳላድዮስ በ368 ዓ.ም በገላትያ ተወለደ፤ ከ431 ዓ.ም. ትንሽ ቀደም ብሎ ዐረፈ:: በ20 ዓመቱ ገደብረ ዘይት ገዳም መነኰሰ:: ከ3 ዓመት በኋላ በግብጽ በረሃ የነበሩትን ታላላቅ ገዳማውያን አበው ሕይወት ለማየት ወደ ግብጽ ሄደ:: ሆኖም በሕመም ምክንያት ጤንነቱ በጣም ስለተጎዳ ከአንዱ የመነኮሳት ማኅበር ወደ ሌላው እየዞረ የገዳማውያኑን ሕይወትና ተጋድሎ ተመለከተ:: በኒጥሪያ በረሃ ከነበሩት በሽዎች የሚቆጠሩ መነኮሳት ጋር ያሉትን ሕይወታቸውን የተመለከተ፣ እንዲሁም የገዳማቱን መሥራቾች የእነ ቅዱስ እንጦንዮስን፣ ቅዱስ ጳኩሚስን፣ ቅዱስ ጳዉሊን፣ ቅዱስ አሞንን፣ ቅዱስ ፓምቦን ዜና ሕይወት እየሰማ 9 ዓመት ኖረ:: በቴቤያድ የነበሩትን መነኮሳትና መነኮሳይያትም፣ በአጠቃላይ በግብጽ የነበሩትን ዋና ዋና ገዳማት አይቷል:: በዚህም ሁሉ ያየውንና የሰማውን የቅዱሳን ገዳማውያንን ዜና ሕይወት የሚገልጽ "Historia Lausiaca" የሚባል መጽሐፍ ጽፏል:: ይህም በተለያየ ስያሜና ቅርጽ «ዜና አበው» ("Vitæ patrum") ፣ «መጽሐፈ ገነት»፣ ("Paradisus Patrum) ፣ «የበረሃ አባቶች ጥበብ» (Wisdom of the Desert Fathers)፣ «የአበው አባባሎች» ("Sayings of the Fathers") በሚሉ ስያሜዎች ይታወቃል:: በኋላም ቢታንያ ላይ ጵጵስና ተሾመ:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፓትርያርክ በነበረበት ጊዜ እርሱንም የሄልዮፖሊስ ሀገረ ስብከት ጳጳስ አደረገው:: በኋላም በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ በደረሰው ነገር እርሱም የመከራው ተሳታፊ ሆኗል፤ ለ11 ወራት በጨለማ ቤት ውስጥ ታስሯል:: በ405 ዓ.ም. በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ስለ ደረሰው ነገር መፍትሔ ለመሻት ወደ ንጉሥ አኖሬዎስና ፓትርያርክ ኢኖሰንት ለማሳሰብ ወደ ሮም የመጣ ሲሆን ወደ አርቃዴዎስ ከተላኩት መልእክተኞች አንዱ ነበር:: ነገር ግን እርሱና አብረውት የተላኩት ታስረውና ተንገላትተው ተመልሰዋል:: የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ሕይወት በዘመኑ አብሮ ተገኝቶ ያየ ሲሆን ዜና ሕይወቱን በጥያቄና መልስ ዓይነት አቀራረብ ጽፏል::

ወደ ገዳም ከመሄድ የሚከለክለው ምንም ነገር እንደሌለ አጥብቃ ስለ ተማጸነችው ከእናቱ ጋር ቆየ።

ነገር ግን ቤቱን ወደ ገዳምነት ለወጠው። ራሱን ከውጭው ዓለም ለየ፤ በዚያም ጽኑ የሆነ ብሕትውናን መለማመድ ጀመረ። በጣም ትንሽና አልፎ አልፎ፣ ያውም መናኛ የሆነ ነገር ለቁመተ ሥጋ ያህል ብቻ ይቀምሳል፣ መሬት ላይ ይተኛል፣ ቶሎ ቶሎ ለጸሎት ይነሣል። ተገቢ ወዳልሆነ ንግግር ላለመግባት አርምሞንና ጸጥታን ያዘ። በዚህም ድርጊቱ ቀድሞ የሚያውቁትና ይቀርቡት የነበሩት ጓደኞቹ ጠሉት። ነገር ግን ከሊባንዮስ ጋር አብረውት የተማሩት ሁለቱ ጓደኞቹ - መክሲሞስ (በኋላ የሴሌውቅያ ጳጳስ የሆነ) እና ቴዎድሮስ (የሞፕሶስቲያ ጳጳስ የሆነ) - እንደ እርሱ ገዳማዊ ሕይወትን በመምረጥ ገዳም ገቡ። መጽሐፍ ቅዱስን ከዲያድርስ[6] (በኋላ የተርሴስ ጳጳስ የሆነ) ተማሩ።

የቅዱስ ዮሐንስን የቅድስና ሕይወትና የተማረ መሆን ያዩት ሕዝቡና ካህናቱ እርሱንና ጓደኛውን ባስልዮስን (ምንም እንኳ ዕድሜያቸው በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ቢያንስ የሚፈለገውን 30 ዓመት ያልሞላ የነበረ ቢሆንም) ጵጵስና ሊሾሟቸው ፈለጉ። እርሱ ግን እኔ ለዚህ ከባድ ኃላፊነት አልበቃም፣ ለዚህ ከባድ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት የሚበቃውና የሚጠቅመው ወንድሜ ባስልዮስ ነው በማለት ባስልዮስ እንዲሾም ለማድረግ እርሱ ተደበቀ። ባስልዮስ ይህንን ሹመት የተቀበለው ጓደኛው ቅዱስ ዮሐንስም አብሮ የሚሾም መስሎት ነበር። ነገር ግን እርሱ ለጊዜው በመደበቁ ባስልዮስ ብቻ ተሾመ።

ከዚህ የጵጵስና ሹመት እምቢ ብሎ መቅረት የተነሣ ባስልዮስ ብቻውን በመሾሙና ዮሐንስ ባለ መሾሙ ባስልዮስ በጣም ስላዘነበት ክህነትን በተመለከተ (በእንተ ክህነት)[7] ለጻፋቸው እጅግ ተደናቂ ለሆኑ ስድስት ተከታታይ መጻሕፍት መጻፍ ምክንያት ሆነ። መጻሕፍቱ በእርሱና በባስልዮስ መካከል በሚደረግ ቃለ ምልልሳዊ ንግግር መልክ የተዘጋጁ ሲሆን የክህነትን ኃላፊነት ጠቀሜ እና ታላቅነት፣ ፈተናዎቹንና ከባድነቱን በበሰለ የንግግር ጥበብና በመጠቀ የአጻጻፍ ዘይቤ የገለጸበት ድንቅ መጽሐፍ ነው። የካህናት ዋና መሣሪያ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን አበክሮ ይገልጻል። የክህነትን ኃላፊነትና ክብደት በመገንዘብ፣ የክርስቶስን መንጋ በሙሉ ልብ በማፍቀር ራስን ለክርስቶስ አገልግሎት መለየት ለክህነት ወሳኝና ቁልፍ መሆኑን ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስን

[6] (Diodoros)

[7] (On the Priesthood)





የማያውቅና ያልተማረ እንዲሁም የክህነትን ኃላፊነት ክብደት ያልተረዳ ሰው ክህነት ሊቀበል የማይገባ መሆኑን ያሳስባል።

ዋና አርአያውና ምሳሌው አድርጎ የሚወስደው ቅዱስ ጳውሎስን ነው። ቅዱሱ አባት የሰባኪና የካህን ዋና ዓላማ ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ማስደሰት ነው ይላል። አንድ አገልጋይ «የሥራውን ጥሩነት የሚገልጹ መግለጫዎችን መንቀፍ የለበትም፤ ሆኖም ግን ምንም ዋጋ ሊሰጣቸውና በውስጡ ሊቀበላቸው አይገባም፣ ኋላም እነዚህ የድርጊቱን ጥሩነት የሚገልጹ ውዳሴዎችና መልካም ቃላት ቢቀሩበት ሊጨነቅና ዓላማውን ሊጠራጠር ወይም ሊለውጥ አይገባም። ከበሬታን ከትሕትና፣ ሥልጣንን ከሰዎች ጋር ከመግባባትና ራስን የተለዩ አድርጎ ካለመቁጠር ጋር፣ ሁሉንም እኩል ማየትን ከይሉኝታ ጋር፣ ነጻነትን ራስን ከማዋረድ ጋር፣ ጥንካሬን ከገራምነትና ለስላሳነት ጋር የያዘና ብቸኛ ዓላማውና ፍላጎቱ የክርስቶስ ክብርና የቤተ ክርስቲያን ደኅንነትና ብልጽግና የሆነ ሊሆን ይገባል» ይላል። ይህ መጽሐፉ የክህነትን ዘርፈ ብዙ ኃላፊነትና የአገልግሎቱን ክብደት በማሳየት ወደ ክህነት ሊገቡ ለሚፈልጉ ሁሉ ጥሩ ትምህርት የሚሰጥ ድንቅ መጽሐፍ ነው።

## 3. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በገዳም (374 - 381 ዓ.ም.)

እናቱ እንዳረፈች ከአንጾኪያ በስተደቡብ ወዳለ ተራራ በመሄድ በዚያ በነበረ ገዳም ከመነኩሳት ጋር መኖር ጀመረ። ከማኅበረ መነኩሳቱ ጋርም ዐራት ዓመት በጾም፣ በጸሎትና፣ ራስን በመግዛት መንፈሳዊ ተጋድሎ ኖረ። ሲሲኮስ ከሚባል አረጋዊ መነኩስ ጋር ሁኖ ገዳማዊ ሕይወትንና መንፈሳዊ ተጋድሎን ከዚህ አባት ጋር ሲለማመድ ቆየ። አረጋዊው አባት ሲሲኮስም ብዙ አምላካዊ ራእይን ያይ ነበር። ይህ አባት አንድ ሌሊት በራእይ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌልን፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ መክፈቻን ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሲሰጡት አየ፤ በዚህም የወደፊት ታላቅነቱን ተረዳ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ራሱን ከዚህ ዓለም [illegible] ለመሰወርና ብቻውን ዘግቶ ለመኖር በመፈለጉ ወደ ዋሻ ገብቶ በብሕትውና ሁለት ዓመት ኖረ። በዚያም በትጋሃ ሌሊት፣ ለራሱ ዕንቅልፍ በመከልከል፣ በቀዊም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በቃል በማጥናት፣ በጸሎትና በተዘክሮ ኖረ።

ገዳማዊ ሕይወትን « እውነተኛ ፍልስፍና» ይለው ነበር። በዚህ በገዳም በነበረባቸው ዓመታት ከ374-381- ድረስ የገዳም ሕይወትንና ድንግልናዊ ሕይወትን ታላቅነትና ጠቀሜ የሚገልጹ መጻሕፍትን ጻፈ። እንዲሁም ከበፊት ጀምሮ የትምህርት ቤት ጓደኛው ለነበረውና ገዳማዊ ሕይወትን

ከመረጠ በኋላ እንደ ገና በአንዲት ሴት ምክንያት ለተሰናከለው ቴዎድሮስ ምክርና ተግሣጽ የጻፈው በዚሁ ጊዜ ነው::[8] በ373 ዓ.ም. ንጉሥ ቫሌንስ ገዳማዊ ሕይወትን ለማጥፋት መነኵሳት ገዳማቸውንና ምንኵስናቸውን ትተው ወታደር አለዚያም የመንግሥት ሠራተኛ ይሆኑ ዘንድ አዋጅ ባወጀ ጊዜ ለገዳማዊ ሕይወት ተቃዋሚዎች መልስ ሦስት መጻሕፍትን ጻፈ:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህንን ዐዋጅ «ከሁሉ የከፋ ዐዋጅ» አለው::

## 4. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ - ዲያቆን፣ ቄስና ሰባኪ በአንጾኪያ (381-397) ዓ.ም.

በቀዊም፣ ለሌሊቱ ቅዝቃዜ ራሱን በማጋለጥ፣ በትጋሃ ሌሊትና መጽሐፍ ቅዱስን በቃል በማጥናት በአጠቃላይ ከባድ ከሆነ ትህርምትና ከተጋድሎ ብዛት የተነሣ ሰውነቱ በጣም ተጎዳ:: ትህርምቱና ተጋድሎው የሰው ሰውነትና ተፈጥሮ ሊሸከም ከሚችለው በላይ በመሆኑ የውስጥ የሰውነት ክፍሎቹ ከጥቅም ውጭ ወደ መሆን ደረሱ:: ሕይወቱም አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ ምክንያት ምንም ማድረግ ስላልቻለ ወደ አንጾኪያ ተመለሰ:: «ይህም የእግዚአብሔር ሥራ ነው»፣ ይላል ጳላድዮስ፣ «ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ይሆን ዘንድ በሕመሙ ምክንያት የብሕትውና ዋሻውን ትቶ ወደ አንጾኪያ ይመጣ ዘንድ አደረገው::» ይህ የብሕትውና ሕይወቱም በቀሪ ዘመኑ በሕይወቱ ላይ ቋሚ የሆነ መንፈሳዊ አሻራውን ትቷል፤ ወደ ውስጡም ዘልቆ ገብቷል::

ከዚያም ወዲያውኑ ጳጳስ መላጥዮስ በ381 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ[9] ዲቁና ሾመው:: በዚህም የጤንነቱ ሁኔታ በሚፈቅድለት መጠን በገዳም ያደርገው በነበረው ትህርምትና ሕይወት ኖረ:: የዲቁና ጊዜው ወደ ፊት በቤተ ክርስቲያን የሚጫወተውን ሚና አሳይቶታል:: እግዚአብሔር ላዘጋጀለት ሥራና ተግባር ዝግጁ ነበር:: «የወጣትነት የቤተ ክርስቲያን ፍቅርና ቅናት ከውስጡ ይወጣ ነበር፣ ጥልቅና ምጡቅ ትምህርትን ተምሯል፣ ሁለንተናው ለእግዚአብሔር በመቅናት የተመላ ነበር፣ በአንደበተ ርቱዕነትና በደግነት ሙሉ ነበር»[10]:: እንደ ዲያቆንነቱ በቅዳሴ አገልግሎት በመራዳት፣ በሽተኞችንና ድሆችን በመንከባከብ፣ እንዲሁም

[8] እርሱም የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ምክር ተቀብሎ ተመልሷል፤ በኋላም የሞፕሶስቲያ ጳጳስ ሆኗል::

[9] ጳጳስ መላጥዮስ በ381 ዓ.ም. ወደ ቁስጥንጥንያ ሄዶ ሁለተኛውን ዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በሊቀ መንበርነት መምራት እንደጀመረ ወዲያውኑ ዐርፏል:: ስለዚህ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ዲቁና የሾመው ወደ ቁስጥንጥንያ ከመሄዱ ከትንሽ ጊዜ በፊት ነው።

[10] (A. PEUCH, Saint Jean Chrysostome, P.4)





ወደ ክርስትና ለመግባትና ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ ያሉ ንዑስ ክርስቲያኖችን በማስተማር አገልግሎት ይሳተፍ ነበር:: የዲቁና ጊዜው የሕዝቡ ችግርና ፍላጎት እንዲሁም በሽተኞችና ድሆች የሚያስፈልጋቸው እንክብካቤና ርዳታ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጥሩ ዕድል ፈጠረለት::

በ386 ዓ.ም. ጳጳስ ፍላብያን ቅስና ሾመው:: በቤተ ክርስቲያን የሕይወት ጉዞና ታሪክ ውስጥ ወሳኙን ምዕራፍ የጀመረው በተለይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው:: በሚቀጥሉት ዐሥራ ሁለት ዓመታት ዋና ሥራው ማስተማር (ስብከት) ነበር:: ቅስና ከተቀበለ በኋላ የመጀመሪያ ስብከቱን ጳጳሱ ባለበት ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ደስ በሚል አንደበት የራሱን ብቁ አለመሆን በትሕትና በመግለጽ አስተማረ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ቀሪ ሕይወቱንና የሕይወት ዘመኑን ሁሉ ወደሰጠለት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወደ ማስተማር ሥራው ገባ:: የመስበኪያ ሰገነት ተወዳጅ ዙፋኑ ነበር:: ጣፋጭ በሆነው ትምህርቱ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ማብራት ጀመረች:: ጥልቅና አስደሳች የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮውና በእያንዳንዱ ትምህርቱ ላይ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን በተመለከተ የሚያስተምረው ትምህርት ተሰምቶ የማይጠገብ ተወዳጅ ነበር:: በአንጾኪያ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በገጠሩ ሳይቀር እየዞረ፣ የሰማዕታት በዓል ቀን ሲሆን አጽማቸው ባረፈበትና በስማቸው ቤተ ክርስቲያን በታነፀበት ቦታ ሁሉ፣ ለማዕትነት በተቀበሉበት ቀን የመታሰቢያ በዓላቸው ዕለት ያስተምር ነበር:: ብዙውን ጊዜ የሚያስተምረው ግን በቆስጠንጢኖስ እንደታነጸ፣ አመሠራረቱ ግን በሐዋርያት ዘመን እንደሆነ በሚነገረው በታላቁ ቤተ ክርስቲያን ነበር:: ብዙውን ጊዜ የሚያስተምረው እሑድ እሑድ ነበር:: በጾመ ኢየሱስ ግን ሁሉንም ቀን በተከታይ ይሰብክ ነበር::

በጾመ ኢየሱስ (ዐቢይ ጾም) የክርስቲያኖችን ተግባርና ኃላፊነት በተመለከተ በስፋትና በጥልቀት በተከታይ ያስተምር ነበር:: በኅብረተሰቡ የነበረውን ምግባረ ብልሹነት ሳያፍርና ሳይፈራ ገሠፀ:: በዘመኑ የነበረውን የቲያትር ቤቶችን፣ የፈረስ ሽቅድምድሞችንና ብዙ የግብረ ገብነት ዝቅጠትና አረመኔያዊ ተግባር የሚታይባቸውን የልዩ ልዩ ትርዒቶችን ከንቱነት ደጋግሞና አጥብቆ አስረዳ:: ክርስቲያን ከተባሉትም ውስጥ እንደ አይሁድና እንደ አረማውያን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ትተው ወደ እነዚህ የትርዒት ቦታዎች ይሄዱ ነበር:: በትምህርቶቹም በከተማው የነበሩ አሕዛባዊ ልማዶችንና አረመኔዊ ተግባር የሚታይባቸውንና ብዙ አስነዋሪ ነገሮችን የተመሉ ቲያትሮችን፣ የፈረስ እሽቅድምድሞችና የመሳሰሉትን በኃይልና

በአጽንዖት ይቃወም ነበር:: በእንዲህ ያሉ ተግባራት የሚሳተፉ ክርስቲያኖችንም ይወቅሳቸው ነበር:-

> «ከእነዚህ አንዱን (ክርስቲያኖችን) አሞጽ ወይም አብድዩ ማነው? ወይም ሐዋርያት ወይም ነቢያት ስንት ነበሩ ብላችሁ ብትጠይቋቸው ድዳ ይመስል ዝም ይላሉ፤ ነገር ግን ስለ ፈረሶች ወይም ስለ ተሽቀዳዳሚዎች ወይም ስለ ሌሎች ትርዒት አቅራቢዎች ወይም ስለ ተወዳዳሪዎች ብትጠይቋቸው የንግግር ጥበብ ከተማሩት ባላነሰ ግልጽነት፣ በጥንቃቄና በስሜት ሆነው ይመልሳሉ::»

ነውር ነቀፋ የሌለበት የተቀደሰ ሕይወቱ ለስብከቱ ኃይልና ግርማ ሰጠው:: ማስተማር በጀመረ በትንሽ ጊዜ ውስጥ በሕዝበ ክርስቲያኑ ልብ ውስጥ ዘልቆ ገባ:: የሕዝቡንም ፍቅር አገኘ:: በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉ የቤተ ክርስቲያኑ ግቢ በሕዝብ ይጣበብ ነበር::

በዚህ የአንጾኪያ ተግባሩ ላይ በ387 ዓ.ም. የተፈጠረ አንድ ክስተት የተሰጠውን ጸጋ አብዝቶና ደህና አድርጎ መጠቀምና የበለጠ መድከም ያለበትን ሁኔታ ፈጠረ:: የአንጾኪያ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ በቀረጥ መብዛት ምክንያት ተማርሮ ስለነበር የንጉሡን የቴዎዶስዮስ ቀዳማዊን (379-395 ዓ.ም)፣ የሚስቱንና የልጁን የአርቃዴዎስን ሀውልት በመሰባበርና ስባሪውን በከተማው በመጎተት እንዲሁም ሌሎች የተቃውሞ መግለጫ ድርጊቶችን በመፈጸም ተቃውሟቸውን ገለጹ:: ንጉሡም ከተማዋን በሙሉ አጠፋለሁ ብሎ ዛተ:: በዚህ ጊዜ ንጉሡን ለመማለድ አረጋዊው ጳጳስ ፍላቭያን ወደ ቁስጥንጥንያ ሲሄድ እርሱ ደግሞ ሕዝቡን በማጽናናትና በማረጋጋት ሥራ ላይ ተጠመደ::

ለብዙ ወራት በዘለቀው በዚህ የጭንቀት ወቅት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕዝቡን በማጽናናት፣ ጥፋታቸውን ራሳቸው እንዲገነዘቡ በመማለድ፣ እንዲሁም ክፉ ምግባራትን እንዲተው በመምከር ተከታታይ ትምህርት አስተማረ:: እነዚህም 21 ተከታታይ ስብከቶች «ትምህርት በእንተ ምክንያተ ሐውልታት»[11] ተብለው ይታወቃሉ:: እንዲህ የተሰየሙት ለስብከቶቹ ምክንያት ከሆነው ከንጉሡ ሀውልቶች መሰባበር ነው:: «እነዚህ ስብከቶች» ይላል አንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሊቅ «በታሪክ ተትተው ከተሄዱት ሥራዎች ተወዳዳሪ የላቸውም»:: ተስፋ ቆርጠውና ተሸብረው የነበሩትን የአንጾኪያ ከተማ ሕዝብ ካጽናናና ካረጋጋ በኋላ በሕዝቡ ዘንድ ተለምደውና ተንሰራፍተው የነበሩትን ስህተቶች ወደ ማስተካከል ቀጠለ:: በተለይም መሐላ መማልንና ሌሎች ስህተቶችን

[11] (Homilies on the Statues)





እንዲተው፣ እንዲሁም የዚህን ዓለም ጊዜያዊነትና ከንቱነት ያስተውሉ ዘንድ በአጽንኦት አስተማረ::

እነዚህ ትምህርቶች የተሰበኩት በ387 ዓ.ም. በጾመ ኢየሱስ (ዐቢይ ጾም) ነው:: የእነዚህ ትምህርቶች አንዱ ውጤት የሆነው ብዙ ቁጥር ያላቸው ብዙ አረማውያን ወደ ክርስትና መግባትና መጠመቅ ነበር:: አስጨናቂ የነበረው የችግር ጊዜ በቅዱስ ዮሐንስ ስብከትና ድካም በእግዚአብሔር ፈቃድ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ፍሬ ያፈራችበት ሆኖ አለፈ:: ንጉሡም በሽምግልና ዕድሜው ወደ ቁስጥንጥንያ በሄደው በጳጳስ ፍላቭያን ምልጃ ለከተማዋና ለሕዝቧ ይቅርታ አደረገ:: ንጉሥ ቴዎዶስዮስ ኃይለኛና ቁጡ የነበረ ቢሆንም ለቤተ ክርስቲያን አባቶች (ለጳጳሳት) ታላቅ ክብሬታ ነበረው:: በሌላም ጊዜ በተሰሎንቄ ሰዎች በጅምላ መጨፍጨፍ ምክንያት የሚላን ጳጳስ የነበረውን የቅዱስ አምብሮስን ተግሣፅ ራሱን ዝንበል አድርጎ በትሕትና ተቀብሏል::

በመጨረሻም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በ21ኛው ስብከቱ ላይ ጳጳሱ ፍላቭያን ከንጉሡ ዘንድ ምሕረትን ይዞ መምጣቱን ለሕዝቡ ተናገረ:: ከመድረኩም ለንጉሡ የተላከውን የምልጃ ደብዳቤ አነበበ:: ይህ ደብዳቤ ንጉሡ ቴዎዶስዮስን እንዲያለቅስ ያደረገው ሲሆን በማርቀቁ ሂደት የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እጅ ያለበት ይመስላል:: ይህ ተፈጥሮ የነበረው ችግር በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የማስተማር ሂደት ላይ ወሳኝ ሚና ነበረው:: በዚህ አስጨናቂ ወቅት ሳይለያቸው ስላጽናናቸውና ስላስተማራቸው ሕዝቡ ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የልቡናውን በር እስከ መጨረሻው የከፈተበትና ከዚያ በኋላ ምንም ነገር ቢላቸው የሚላቸውን ሁሉ ለመቀበል ልባቸው ለእርሱ የለሰለሰ መሬት የሆነበት ሁኔታ ነበር::

ለድሆች ምጽዋት መስጠትንና ችግረኞችን ማሰብን በአጽንዖት ያስተምር ነበር:: ለድሆች መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጎቶች በጣም ያስብና የሚቻለውን ሁሉ ያደርግ ነበር:: ሀብትና ሥልጣንን መከታ በማድረግ የሚፈጸሙ ግፎችን አጥብቆ ያወግዝ ነበር:: ድሀ ሲገፋ ካየ ከራሱ ከተገፋው ድሀ በበለጠ በማዘንና በመቆርቆር ግፍ ፈጻሚውን ማንም ይሁን ማን ይገሥጻል፤ የወሰደውን እንዲመልስ፣ ያደረገውን ጥፋት አውቆ ከክፉ ግብሩ እንዲመለስ ይመክረዋል:: እነዚህ ከ386-398 ድረስ የነበሩት ዓመታት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ወንጌልን በማስተማር ረገድ ከፍተኛ ሥራ የሠራባቸውና ዛሬም ድረስ ያሉትን እጅግ በጣም ጠቃሚና ተወዳጅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎችንና ሌሎች ተዛማጅ ጽሑፎቹን የሠራባቸው ወርቃማ ጊዜያት ነበሩ::
የሕይወቱ ቅድስናና የትምህርቱ ተወዳጅነት ተደጋግፈው ያማረና የሠመረ ውሕደት ፈጠሩ:: ከመቼውም ጊዜ በላይ ማንም ሊስተካከለው

በማይችል ሁኔታ በጣዕመ ስብከቱ የቤተ ክርስቲያንን የስብከት አደባባይ አስዋበ። በአጠቃላይ አንጾኪያ የነበረባቸው ዓመታት ብዙ ሥራ የሠራባቸውና በሕይወቱ ውስጥ ደስተኛ የነበረባቸው ጊዜያት ነበሩ ማለት ይቻላል። ብዙዎቹን የቅዱሳት መጻሕፍት የትርጓሜ ሥራዎቹንና ልዩ ልዩ ጽሑፎቹን የሠራው ከዲቁና ጊዜው አንሥቶ አንጾኪያ በነበረባቸው በእነዚህ ዐሥራ ስድስትና ዐሥራ ሰባት ዓመታት ውስጥ ነው።

## የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የነበረችበት ሁኔታ

የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ለሰማንያ አምስት ዓመታት ያህል (330-415 ዓ.ም) በኑፋቄና በመከፋፈል ስትታመስ ነበር። አርዮሳውያን ዋና ራስ ምታት የነበሩ ሲሆን ኦርቶዶክሳዉያኑም ከሁለት ተከፍለው ነበር፤ የዚህ ችግር መንስኤና ገጽታ ምን ነበር?

በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ከተሰበሰቡትና አርዮስንና አርዮሳዊነትን ካወገዙትና የጉባኤው መሪ ከነበሩት አባቶች አንዱ የነበረው የአንጾኪያው ጳጳስ ኤዎስጣቴዎስ ነበር። እርሱም አርዮሳውያንን በቃልም በጽሑፍም ይዋጋቸው የነበረ የቅዱስ አትናቴዎስ አጋዥና ጠንካራ ኦርቶዶክሳዊ አባት ነበር። ነገር ግን ከኒቅያ ጉባኤ ከትንሽ ጊዜ በኋላ አርዮሳውያን የመንግሥት ድጋፍ እያገኙ ስለሄዱ ኦርቶዶክሳዊያን አባቶችን በሰበብ በአስባቡ እያመካኙ ከየመንበራቸው ሲያሳድዷቸው ኤዎስጣቴዎስንም በ330 ዓ.ም. በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ትእዛዝ የአንጾኪያን መንበር እንዲለቅ ተደረገ። ያከብሩትና ይወዱት በነበረው አባታቸው ላይ በተደረገው ግፍ የአንጾኪያ ምዕመናን ጦር እስከማንሣት ሊደርሱ የነበረ ቢሆንም እርሱ ግን ይህን እንዲተውና በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታቸው እንዲጸኑ መክሯቸው ከብዙ ካህናት ጋር በፀጥታ ወደ ስደቱ ሄደ። የእርሱ ተከታዮች አንጾኪያ ላይ በስሙ «ኤዎስጣቴዎሳውያን» ተብለው በመለየት በአርዮሳዊውያን የሚሾሙባቸውን ጳጳሳት አንቀበልም እያሉ ቆዩ።

በኤዎስጣቴዎስ ጊዜ አንጾኪያ የኦርቶዶክሳዊነት ዋና ማዕከልና መነኻሪያ ነበረች። ነገር ግን እርሱ ከተሳደደ በኋላ በቦታው የተተኩት አርዮሳዊ ዝንባሌ የነበራቸውና አንዳንዶቹም በግልጥ አርዮሳውያን እየሆኑ መጡ። ቤተ ክርስቲያን ከአርዮሳውያን ጋር ከባድ ትግል ላይ በነበረችበት በዚህ ወቅትም እንደሚሾሙት ሰዎች ሃይማኖትና እንደ ነገሥታቱ ድጋፍ በአንጾኪያ መንበር ቶሎ ቶሎ መውጣትና መውረድ





ነበር። ኤዎስጣቴዎስ በስደት ላይ እያለ ከሞተ በኋላ በ360 ዓ.ም. ጉባኤ ተደርጎ በሁሉም ስምምነት መላጥዮስ ለአንጾኪያ መንበር በሊሰበት ተመረጠ። መላጥዮስ ቅንና ንጹሕ የሆነ ጽኑ ሃይማኖተኛ አባት ነበር። አዲስ የተሾመው መላጥዮስ የሕዝቡን ፍቅርና አክብሮት አገኘ። የወደፊቱ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ሁሉም ያከብሩትና ያመሰግኑት ነበር። በኤዎስጣቴዎስ ስም የሚጠሩት ግን መላጥዮስ በስምምነት ከተመረጠ በኋላም እንደ በፊቱ ዕውቅና አንሰጥም ብለው በልዩ ቡድንነታቸው ቀጠሉ።

ጠረኛ አርዮሳዊ የነበረው ንጉሥ ቁንስጣ ብዙ ጳጳሳትን እንዲገኙ በመጋበዝ ታላቅ ጉባኤ በአንጾኪያ ጠርቶ መላጥዮስ እንዲያስተምር አደረገ። ይህም መላጥዮስን ለመፈተን ነበር። ጳጳስ መላጥዮስም ጥልቅ የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀት ያለው መሆኑ ግልጽ ሆኖ በታየበት ሁኔታ ኦርቶዶክሳዊ እምነቱን መሠከረ። ሕዝቡም በትምህርቱ፣ እንዲሁም ንጉሡን ሳይፈራ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖቱን በመመሥከሩ በጣም ደስ ተሰኙበት[12]። አርዮሳውያንም እርሱን ለመበቀል ጊዜ አልፈጀባቸውም። አርዮሳዊው ንጉሥ ቁንስጣም ሰበብ ፈልጎ ገና በመንበሩ ላይ አንድ ወር እንኳ ያልቆየውን ጳጳስ መላጥዮስን በኦርቶዶክሳዊነቱ ምክንያት አሳደደው። ይህ የመላጥዮስ ስደት በአንጾኪያ ኦርቶዶክሳውያን መካከል ረዘም ላለ ጊዜ የዘለቀ መለያየት ለመፈጠሩ ምክንያት ነበር። ጳውሊኖስ የሚባል ቄስ ኤዎስጣቴዎሳዊያንን ሲመራ ፍላቭያንና ዲያድርስ ደግሞ በስደት ላይ ያለውን የመላጥዮስን መንጋ ይመሩ ነበር።

በአንጾኪያ በየቤተሰቡ ውስጥ አንዱ በመላጥዮስ ስም ይሰየም ነበር። ምስሉ በጣት ቀለበት፣ በቤት ግድግዳ ላይ ወዘተ ይሳል ነበር። ከጥቂት ወራት በኋላ ንጉሥ ቁንስጣ በድንገት ሲሞት ተተኪው ንጉሥ ጁሊያን የቁንስጣን የስደት ዐዋጅ በመሻር የተሰደዱትን አባቶች ወደየመንበራቸው እንዲመለሱ አደረገ። መላጥዮስም ወደ አንጾኪያ

[12] ቅዱስ መላጥዮስ አስተምሮ ሲጨርስ ምዕመናን የትምህርቱን ማጠቃለያ ጠየቁት። እርሱም ሦስቱን ጣቶቹን ወደ ሕዝቡ ካወጣ በኋላ አንደገና ሁለቱን ጣቶቹን ወደ እርሱ መልሶ «በሕሊናችን ሦስት አካላትን (Three Persons) እናስባለን፣ ነገር ግን አንድን አምላክ ብቻ እንደምናስብ ነው (አንድ አምላክ እንላለን» አላቸው። ("Three Persons are conceived in the mind but it as though we addressed one only".) ይህም አገላለጽ ዝነኛና የታወቀ ምልክትና መግባቢያ ሆነ። ቅዱስ መላጥዮስ ስለ ክርስቶስ ሃይማኖት ሲሉ ስደት፣ ግዞት፣ ግርፋት፣ ድብደባና ልዩ ልዩ ዓይነት መከራ ከተቀበሉ፣ ነገር ግን በዚህ ሂደት ካልሞቱ መስካሪ ሰማዕታት (ሰማዕታት ዘእንበለ ክዕወተ ደም - (Confessors)) ወገን የሚመደብ አባት ነው።

መንበሩ ተመለሰ:: ሆኖም ተፈጥሮ በጠበቀው ክፍፍል ምክንያት ሁኔታዎች አስቸጋሪ ሆነው አገኛቸው:: በ362 ዓ.ም. የእስክንድርያ ጉባኤ ልዩነቱን ለማስወገድና ዕርቅ ለመፍጠር ቢሞክርም አልተሳካለትም:: ሁለቱም ወገኖች ከያዙት አቋም ፍንክች የማይሉ ሆኑ:: ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ ይሞክሩ ከነበሩት ሰዎች ፌሊጥ ማጣትና አላስፈላጊ ግፊት የተነሣም ልዩነቱ ሰፋ፣ የሰላምና የአንድነትን ተስፋም እየራቀ ሄደ:: በሁሉም ስምምነት የተመረጠው ጳጳስ መላጥዮስ እስኪመለስ እንደመጠበቅ፣ ለተደጋጋሚ ጥያቄያቸው እጅ በመስጠት መላጥዮስ በስደት ላይ እያለ ካግሊያሪ የተባለ ከሌሎች ሁለቶች ጋር በመሆን የኤዎስጣቴዎሳውያን ቡድን መሪ የነበረውን ጳውሊኖስን ጳጳስ አድርጎ ሾመው:: ይህ ጥንቃቄ የጎደለው ድርጊት በጣም አሳዛኝ ነበር፤ ምክንያቱም ክፍፍሉን ካለበት ደረጃ የበለጠ በማክበድ መፍትሔውን የበለጠ አወሳሰበው::

መላጥዮስ አሁንም መጀመሪያ ከስደት መልሶት በነበረው፣ በክሃዲውና የጣዖት አምልኮ ዋና ጠበቃ በነበረው በንጉሥ ጁሊያን (361-363 ዓ.ም.) እንደገና ተሳደደ:: ሆኖም አሳዳጁ ንጉሥ ጁሊያን በድንገት' ስለተቀሰፈ በቦታው ጆቪኒያን (363-364) ነገሠ:: ንጉሡ ጆቪኒያንም ጳጳስ መላጥዮስን አንጾኪያ ላይ ተገናኘው፤ በታላቅ ክበሬታም አከበረው:: ወዲያውም በንጉሡ ትእዛዝ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ (328-373 ዓ.ም.) ወደ አንጾኪያ መጥቶ ከእርሱ ጋር ኅብረትና አንድነት እንዲኖረው የሚፈልግ መሆኑን ለመላጥዮስ ገለጸለት:: ነገር ግን መላጥዮስን መካሪዎች በክፉ መከሩትና ለቅዱስ አትናቴዎስ መልስ ሳይሰጠው ዘገየ:: ቅዱስ አትናቴዎስም ገና ለጽጽስናው ዕውቅና ካልሰጠው ከጳዉሊኖስ ጋር ኅብረት ያለው መሆኑ ተነገረ::

እንዲህም ሆኖ ቅዱስ አትናቴዎስ ለመላጥዮስ የነበረው በጎ አመለካከት አሁንም አልተለወጠም ነበር:: ሆኖም ቅዱስ አትናቴዎስ በመላጥዮስ በሃይማኖቱ ኦርቶዶክሳዊነት የነበረው እምነትና ለእርሱ የነበረው በጎ አመለካከት ከእርሱ በኋላ በእርሱ ቦታ በመንበሩ በተተካው በጴጥሮስ 2ኛ (373-378 ዓ.ም.) አልነበረም:: እንዲያውም ፓትርያርክ ጴጥሮስ በግልጽ መላጥዮስ መናፍቅ ነው ይል ጀመር:: መላጥዮስ በኦርቶዶክሳዊነቱ ሊቀበሉትና ዕውቅና ሊሰጡት ይገባቸው በነበሩት በእስክንድርያና በሮም በእነርሱው ለረጂም ጊዜ ጥያቄ ላይ ሲወድቅና ዕውቅና ሲነፈገው ቆየ:: በመላጥዮስ መሪነት የ26 ጳጳሳት ጉባኤ በአንጾኪያ መደረጉ ጥሩ ውጤት ያስገኘ ቢመስልም የጳዉሊኖስ ነው የተባለ በራሪ ጽሑፍ መሠራጨት በመላጥዮስ ኦርቶዶክሳዊነት ላይ ጥርጣሬ አስነሣ:: በዚህም ላይ አዲስና ያልተጠበቁ ችግሮች ብቅ አሉ::





የንጉሥ ጆቪኒያን ሞት አርዮሳዊነት ኃይል እንዲያገኝ በማድረግ አዲስ ስደት በንጉሥ ቫሌንስ (364-378 ዓ.ም.) እንደገና ተጀመረ:: በዚህም ላይ በእስክንድርያና በአንጾኪያ መካከል የነበረው የለዘበም ቢሆን የዘለቀ ፉክክር በጉዳዩ ላይ ራሱን የቻለ ሚና ነበረው:: በምሥራቅ ያሉ የተለያዩ ጳጳሳት የመላጥዮስን መሪነት በመቀበል ድጋፋቸውን ሰጡት:: በ379 ዓ.ም አንድ መቶ ሃምሳ ጳጳሳት በእርሱ ዙሪያ ተሰባሰቡ:: በ370 ዓ.ም ቅዱስ ባስልዮስ በቂሣርያ መንበር ላይ ተሾመ፣ የመላጥዮስም ጠንካራ ደጋፊ ነበር:: ልዩ በሆነ ተሰጥኦ ቅዱስ ባስልዮስ በምሥራቁ ክፍል በቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ለማምጣት አስቸጋሪ ያደረገውን የሁኔታውን ውስብስብነት በመረዳት በቅዱስ አትናቴዎስና በመላጥዮስ መካከል ሽምግልና ጀመረ:: ሆኖም መላጥዮስ አሁንም በንጉሡ ወደ አርማንያ ስለተሳደደ ሁኔታውን አስቸጋሪ አደረገበት:: የቅዱስ ባስልዮስ መልእክተኛ ከቂሳርያ ወደ አርማንያ፣ ከአርማንያ ወደ እስክንድርያ፣ ከዚያም ወደ ሮም መሄድ ነበረበት:: በሁኔታዎቹ አስቸጋሪነት ላይ የነበረው የመገናኛ ዝግመት ተጨማሪ መሰናክል ነበር::

ቅዱስ አትናቴዎስ በቅዱስ ባስልዮስ የሽምግልና ጥረት ውጤት ይገኛል ብሎ ተስፋ አድርጎ ነበር:: ምክንያቱም በ363 ዓ.ም አንጾኪያ ሄዶ ሳለ የገጠመው ነገር ቢኖርም ቅንና አርቆ አሳቢ የሆነውና ዓላማውና ሕሊናው ሁሉ ለክርስቶስ ሃይማኖት መጠበቅና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት እንጂ የግል ክብርና ሌላ ፍላጎት ለእርሱ ጉዳዩ አልነበረም:: ሆኖም ግን እርሱ ታላቅ የሆነ ተጋድሎውን ፈጽሞ በ373 ዓ.ም ስላረፈ የተጀመረው ጥረት ተቋረጠ:: ይባስ ብሎ በቅዱስ ባስልዮስ የተጀመረው የዕርቅ ጉዳይ ዋና አንቀሳቃሽና መልእክተኛ የነበረው ሰው የእነ ጳውሊኖስን ጎራ ተቀላቀለ:: የሮማው ፓትርያርክ የነበረው ዳማስቆስ እና ሌሎችም በአንጾኪያና በምሥራቁ ክፍል ያለውን የተወሳሰበ ሁኔታ ለመረዳት ካለመቻላቸው የተነሣ ችግሩን በማርገብ ፋንታ ያወሳሰቡት ሄዱ:: የሮማው ሊቀ ጳጳሳት ለጳዉሊኖስ ጵጵስና ዕውቅና በመስጠት፣ የእርሱ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን እንደራሴ ያደረገው መሆኑን ገለፀ::

ሁኔታዎች አሳዛኝ እየሆኑ ቢሄዱበትም ቅዱስ ባስልዮስ መፍትሄ መሻቱን አላቋረጠም:: ሮምና እስክንድርያም በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያንና በዙሪያዋ ያሉትን የተወሳሰቡ ግላዊና ብሔራዊ ጉዳዮችና ፍላጎቶች አልተረዱትም፤ እንዲሁም ኦርቶዶክሳውያኑ እየደረሰባቸው የነበረውን ስደትና እየተቀበሉት የነበረውን መከራ አልተገነዘቡላቸውም:: ይህንን ሁኔታ ለመፍታት መቀራረብና ጥሩ ኣስታራቂዎች ያስፈልጉ ነበር:: ሆኖም ይህ ባለመገኘቱ ችግሩ ቀጠለ:: በ378 ዓ.ም ቅዱስ ባስልዮስ

ሲደክምለት የነበረው መቀራረብ ደህና ሊባል የሚችል ውጤት አስገኘ:: መላጥዮስም ከተሰደደበት እንደገና በ378 ዓ.ም (ያሳደደው ንጉሥ ቫሌንስ ሲሞት) ተመለሰ:: ሆኖም በስደትና በመንገላታት እንዲሁም በልዩ ልዩ መከራ ለደከመውና በዕድሜ ለሸመገለው አባት በኦርቶዶክሳውያኑ መካከል የነበረውን ልዩነት ለማስወገድ ከባድ ሥራ ነበር:: በ379 ዓ.ም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት በአርዮሳዊነት ላይ ድል ማድረጉን ለማወጅ አንድ መቶ ሃምሳ ጳጳሳት የተገኙበት ጉባኤ በመላጥዮስ ሰብሳቢነት ተደረገ:: ይህም የእምነት መግለጫና የኦርቶዶክሳዊነት ድል ማድረግ በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ ዓለም አቀፋዊ ጉባኤ የቤተ ክርስቲያን ውሳኔ ሆነ::

የክፍፍሉ ፍጻሜ ቅርብ ነበር:: የአንጾኪያን ቤተ ክርስቲያን ከሁለት የከፈሏት ሁለቱም ኦርቶዶክሳውያን ስለነበሩ መፍትሔውም ከሁለቱ አንዱ ቀድሞ ሲሞት ወደኋላ የቀረው ሁለቱን ጠቅልሎ አንድነትን መፍጠር ነበር:: መላጥዮስ ይህ ጥሩ መፍትሄ እንደሚሆን አስቀድሞ ተገንዝቦ ስለነበር ይህንን አሳብ ለጳውሊኖስ አቀረበ:: ሆኖም ይህ የወንድማዊና የሰላም አሳብ ምንም ዓይነት የስምምነትም ሆነ ሁኔታውን የመፍታት ፍላጎት ባልነበረው በጳውሊኖስ ውድቅ ተደረገ:: መላጥዮስ በ381 ዓ.ም የቁስጥንጥንያን ጉባኤ በሊቀ መንበርነት መምራት ከጀመረ በኋላ በድንገት ዐረፈ:: ዕረፍቱም የታሰበውን የአንድነት ተስፋ በእንጭጩ አስቀረ:: አስከሬኑም ከቁስጥንጥንያ ወደ አንጾኪያ መጥቶ በታላቅ ክብርና ሥነ ሥርዓት ሆኖ ቀደም ብሎ የአንጾኪያ ጳጳስ በነበረው በሰማዕቱ በቅዱስ ባቢላስ አጠገብ ተቀበረ:: እርሱም ዕረፍቱ መቃረቡን የተረዳ በሚመስል መልኩ ከትንሽ ቀናት ቀደም ብሎ አንድነት የማምጣትን አስፈላጊነት በአጽንዖት ሲናገርና ሲያሳስብ ነበር::

ሆኖም በመላጥዮስ መንበር ፍላቪያን ተተካ:: እስክንድርያና ሮምም በፊት እንዳደረጉት ከጳውሊኖስ ወገን በኩል በመሆን ለፍላቪያን ዕውቅና አልሰጡም:: ልዩነቱም በዚሁ ቀጠለ:: በተለይ የሕይወት ዘመኑን ሁሉ ከአርዮሳውያን ጋር በመታገል የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጠበቃ የነበረው ቅዱስ አትናቴዎስ የነበረው ቅንና ደግ አስተሳሰብ፣ በግሉ የሚጠሉት እንኳ ቢሆኑ ኦርዶክሳውያን እስከሆኑ ድረስ ከማንም ጋር አንድነትና ሰላም ለመፍጠር የሚቻለውን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ የማይለው የእርሱ ማረፍና የተከታዮቹ የእርሱን አሳብና መንገድ አለመጋራት በእስክንድርያ በኩል ከአንጾኪያ ጋር ለነበረው ችግር ዋናው ምክንያት ነበር::

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ ጊዜ በአንጾኪያ ያስተማረ ነበር:: በአንጾኪያ በኤዎስጣቴዎስ የቀድሞ ታላቅነት ብቻ እንዲሁም ከሮም





በነበራቸው ድጋፍ የተኩራሩ ቁጥራቸው ትንሽም ቢሆን ችግር ሲፈጥሩ የነበሩ ኤዎስጣቴዎሳውያንን ድርጊታቸው ትክክል አለመሆኑን ያስረዳ ነበር:: የጳውሊኖስን የጵጵስና ሹመትም ሕጋዊና ዋጋ ያለው ነው ብሎ አይቀበልም ነበር:: የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ጊዜ አጥታው የነበረውን ሰላም እንድታገኝ ያደረገውም እርሱ ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የመላጥዮስ ተተኪ የሆነውን ፍላቭያንን ከእስክንድርያና ከሮም ጋር በ398 ዓ.ም. አስታረቀ:: የፍላቭያን ተተኪ አሌክሳንደር ደግሞ ኤዎስጣቴዎሳውያንን በ415 ዓ.ም. ወደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መለሳቸው:: በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያንም ከብዙ ጊዜ ልዩነትና ችግር በኋላ ፍቅርና አንድነት ሆነ::

## 5. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ - የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ (398 - 404 ዓ.ም.)

ነገሮች በተለመደው ሁኔታ ቢሄዱ ኖሮ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሚሆነው የአንጾኪያው ጳጳስ የፍላቭያን ተተኪ ነበር:: ነገር ግን በ397 ዓ.ም. የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ የነበረው ኔክታርዮስ[13] ዐረፈ:: በዚህ ጊዜ አሁን ክፍት በሆነው በሮማ ምሥራቃዊ ግዛት ዋና ከተማ በቁስጥንጥንያ መንበር ለመሾም በገሃድም ሆነ በስውር አጠቃላይ የሆነ ሽኩቻ ነበር:: ከትንሽ ወራት በኋላ በመንበሩ ለመተካት ሲናፍቁ የነበሩትን ጳጳሳት የሚያስደነግጥ ነገር ተሰማ:: ንጉሡ አርቃዴዎስ በሚኒስትሩ በዩትሮጲየስ ምክር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ከአንጾኪያ ከተማ ሕዝቡ ሳይሰማና ሳያውቅ በቶሎ ወደ ቁስጥንጥንያ እንዲሰደው የሚያዝ መልእክት ለአንጾኪያ ገዢ መላኩ ተሰማ:: የአንጾኪያ ምዕመናን አባታችንን አንሰድም ብለው ረብሻ እንዳያስነሱና ከእርሱም ሆነ ከሌላ የሚመጣን ተቃውሞ ዋጋ ቢስ ለማድረግ በዘዴ ከከተማው እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ ከቤተ መንግሥት በተላከ አጃቢ ኃይል በአስቸኳይ ወደ ቁስጥንጥንያ ተወሰደ::

የአንጾኪያ ገዢ የነበረው ሰው የንጉሡ ትእዛዝ እንደደረሰው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ከከተማው ውጭ ወደሚገኝ ቤተ ክርስቲያን አብሮት እንዲሄድ ጠየቀው:: በእርሱ ሠረገላ ላይ እንደተቀመጠለትም ወዲያውኑ በፍጥነት ወደ ቁስጥንጥንያ ሊወስዱት ተዘጋጅተው የሚጠብቁ መኳንንት ወደነበሩበት ወደ ቁስጥንጥንያ ወደሚወስደው ጎዳና ይዞት ሄደ:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክና በቅዱሳን መዝገብ የጎላና ደማቅ ስምና ክብር ሊያሰጡት ወዳሉት የፈተናዎችና የተጋድሎዎች መድረክ በዚህ ዓይነት ድንገተኛ ሁኔታ ተወሰደ::

[13] የቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘ ንዚናንዙ ወራሴ መንበር

ወደ·ትና ለምን እንደሚወስዱት ያወቀው ቁስጥንጥንያ ከደረሰ በኋላ ነበር። እንዲህ ባለ ሁኔታ ያለ ፈቃዱና ያለ ውዴታው፣ ፈቃደኝነቱ እንኳ ሳይጠየቅ በድንገት የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት እንዲሆን ተደረገ። የካቲት 26 ቀን 398 ዓ.ም. ብዙ ጳጳሳት ባሉበት በታላቅ ሥነ ሥርዓት በቁስጥንጥንያ መንበር ላይ 23ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ በነበረው በቴዎፍሎስ እጅ ተሾመ። ቴዎፍሎስም ያለ ውዴታው በንጉሡ በአርቃዴዎስ ትእዛዝ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለመሾም ተገደደ። ቴዎፍሎስ በቁስጥንጥንያ መንበር ላይ ለማሾም የራሱ ዕጩ አዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም ይህን ማድረግ እንደማይችል በመረዳቱ የንጉሡን ትእዛዝ ፈጸመ። በዚያም ላይ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን አልሾምም ለማለትና ለመበቀል አሁን እንዳልተመቸው አይቶ ጥሩ ወቅትና አጋጣሚ እስኪያገኝ ድረስ ጠላትነቱን በልቡ ጠበቀ።

ይኽ ለውጥ ድንገተኛ የመሆኑን ያህል ከባድም ነበር። ምቾትና ድሎት የዕለት ተዕለት ሕይወቱ በሆነበት፣ ኃጢአትና ግፍ እንደ ቀላል በሚታዩበት፣ በሰው ደምና ሕይወት ተረማምዶ ወደ ሥልጣን መውጣትና ሥልጣንን ማጠበቅ የጀግንነት መገለጫና ጀብድ ተደርገው በሚወሰዱበት ቤተ መንግሥት አጠገብ መሾም ቀላል ነገር አልነበረም።



ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በቁስጥንጥንያ መንበር ላይ ሲሾም የሚያሳይ ሥዕል





አዲስ የተሾመው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መጀመሪያ ያደረገው ነገር ከላይ እንደተገለጸው ለብዙ ጊዜ ዘልቆ የነበረውን የአንጾኪያን ቤተ ክርስቲያን ችግር መፍታት ነበር። በዚህም በአንጾኪያው ጳጳስ በፍላቭያንና በሮምና በእስክንድርያ መካከል ዕርቅና አንድነት እንዲፈጠር አደረገ። በዚህም የምሥራቁና የምዕራቡ የክርስትና ዓለም የቀድሞ አንድነት ተመለሰ።

የቁስጥንጥንያ ከተማ በታላቁ ቆስጠንጢኖስ በ330 ዓ.ም. የተመሠረተች ስትሆን የሮማ ግዛት ምሥራቃዊ መናገሻ ከተማ ተደረገች። እንዲሁም ከምሥራቃውያን የቤተ ክርስቲያን መናብርት የቀዳሚነት ደረጃ ተሰጣት (ከእስክንድርያ መንበር ቀዳሚ ሆነች)። በ381 ዓ.ም. የተካሄደው ሁለተኛው ዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የኒቅያ ጉባኤ አርቶዶክሳዊ ሃይማኖት በአርዮሳዊ ኑፋቄ ላይ ድል ማድረጉን ከማወጁ ጋር ለቁስጥንጥንያ (የአዲሲቷ ሮም) ሊቀ ጳጳስ በክብርና በመዓርግ ከጥንታዊቷ ሮም ቀጥሎ የሁለተኛነት ደረጃ ሰጠ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን ከባድ የእረኝነት ኃላፊነትና የክርስቶስ አደራ እንደ ተሸከመ በሥነ ምግባር ዘቅጦ ከነበረ ኅብረተሰብና የተበላሸ የሕይወት ልምድ ከነበራቸው የዘመኑ ባለጸጎችና ባለሥልጣናት ጋር ጽድቅንና ውነትን በኃጢአት ላይ ለማንገሥና የሚጠበቅበትን ተገቢ ሥራ ለመሥራት በመንፈሳዊ ቆራጥነት ተነሣ። ቤተ ክርስቲያን እውነተኛና ቆራጥ አባት በሚያስፈልጋት ወቅተ ላይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያዘጋጀው አባት ነበር።

የለውጥና የማስተካከል አስፈላጊነት በጣም ግልጽ ነበር። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የማጥራቱንና የማስተካከሉን ሥራ ከላይ ጀመረ።[14] እውነተኛእና ርቱዕ የሆነ ትምህርቱንና ገዳማዊ ሕይወቱን በቁስጥንጥንያ መንበረ ጵጵስናም ቀጠለ። በመንበረ ጵጵስናው ውስጥ የነበሩትን ውድና ጌጠኛ የውስጥ ዕቃዎችንና ቁሳቁሶችን በመሸጥ ገንዘቡ ለድሆችና ለሐኪም ቤቶች ጥቅም እንዲውል አደረገ። ለቤተ ክርስቲያን ፋይዳ ያልነበራቸውን ወጪዎች ሁሉ አስቀረ። ትህርምታዊ የገዳም ሕይወቱን በመንበረ ጵጵስናውም በመቀጠል ከእርሱ በፊት በመንበረ ጵጵስናው ግቢ ውስጥ ይደረጉ የነበሩ ድግሶችንና ግብዣዎችን አስቀረ። የእራትና ልዩ ልዩ ግብዣ ሲጠራም አይቀበልም ነበር። በመንበረ ጵጵስናው ግቢ ብዙ ሰው ማንጋጋትንና አጀብ ማብዛትን አስቀረ፤ ሌሎች ነገሮችንም በጣም አስፈላጊ ወደ ሆኑት ብቻ ቀነሰ። የመንበረ ጵጵስናውን ገቢና ገንዘብ ብዙውን ለድሆችና ለሐኪም ቤቶች አገልግሎት እንዲውል አደረገ። በፊት በገዳም ሲኖር ከነበረው ሕይወት ብዙም ያልተለየ ሕይወትን ቀጠለ።

ካህናትን በተመለከተ ደግሞ ምግባረ ብልሹና ሥርዓት የለሽ ካህናትን እንዲስተካከሉና ሥርዓት እንዲይዙ አደረገ። እርሱ ፓትርያርክ በሆነበት ዘመን የሕዝቡና የገዢዎቹ ብቻ ሳይሆን የከተማዋ ካህናትም ሕይወታቸው

[14] ጳላድዮስ ምዕ. 5

በምቾትና በመቀማጠል የተበላሸ ስለነበር የሰላ ትችትና ነቀፌታ ይሰማባቸው ነበር:: በተለይም ካህናትን በመጀመሪያ በድንግልና ለመኖር የወሰኑ ቤታቸውን የሚጠብቁና የሚራዷቸው ደናግል ሴቶች ጋር በአንድ ቤት የመኖር ልማድ ነበራቸውና ይህ ልማድ ተገቢ ያልሆነና ቤተ ክርስቲያንን የሚያስነቅፍ በመሆኑ ሊተው እንደሚገባ በአጽንዖት ነገራቸው:: ይህም ከካህናት መካከል ፍቅረ እግዚአብሔር የሌላቸውንና በራሳቸው ምኞት የሚነዱትን አስቆጣ::[15]

እንዲሁም ካህናት ከገንዘብ ፍቅር ርቀው የክርስቶስን መንጋዎች በትጋት እንዲጠብቁና ሕይወታቸውን ሥርዓት ባለው መልኩ በመምራት ለመንጋው መልካም አርአያ ይሆኑ ዘንድ ከአስተሳሰብ ጀምሮ ሕይወታቸውን ለመለወጥ ብዙ ደከመ:: ከዚያም በነውርና በወንጀል ድርጊታቸው ቤተ ክርስቲያንን ያስነቅፉ በነበሩ በሌሎች ካህናት ላይ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ወሰደ:: ሁለት ዲያቆናትን (አንዱን በግድያ ወንጀል ሁለተኛውን ደግሞ በዝሙት ምክንያት) ከክህነት መዓርግ ሻራቸው:: ከየአካባቢው ተጋብዘው የሚመጡ ሰባክያንን፣ «በነጻ የተቀበላችሁትን በነጻ ስጡ» ተብሏልና ወንጌልን በማስተማራችሁ ወደየመጣችሁበትና በቋሚነት ወደምታገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን ስትመለሱ ገንዘብና ምድራዊ ጥቅም አትቀበሉ ይላቸው ነበር:: ቀጥሎም ሌሊት በሚደረገው ጸሎት (ሊጦን) እንዲሳተፉ ካህናቱንና ሕዝበ ክርስቲያኑን አሳሰበ:: ይህም ሌሊቱን ሁሉ መተኛት የለመዱትን ሰነፎቹን ካህናት አስቆጣ::[16]

---

[15] የኒቅያ ጉባኤ (ቀኖና ቁጥር 3) እናት፣ እህት፣ አክስት ወይም ከመጠርጠር በላይ ከሆነች በስተቀር ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ዲያቆናትና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ከሴት ጋር በአንድ ቤት እንዳይኖሩ እንዲህ ዓይነት ልማድን ይከለክላል:: ሌሎች የኋላ ጉባኤያትም ይህንኑ እንዲተገበር አጽንተውታል:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ ልማድ ላይ ሁለት ትምህርቶችን አስተምሯል:: በርግጥ በጊዜው ያን ያህል የጎላ በተግባር የደረሰ ችግር አለመኖሩን ይገልፃል:: ሆኖም ግን ሐሜትና ነቀፌታ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ያስረዳል:: እንዲሁም እንዲህ ዓይነት ሴቶች ብዙውን ጊዜ በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዳሉት ወይዛዝርት የቅጥፈትና የብልጠት ሕይወት የሚመሩ እንደሆኑ አመልክቷል::

[16] በንጉሥ ቴዎዶስዮስ ቀዳማዊ ከኦርቶዶክሳውያን በስተቀር መናፍቃን በከተማዋ ውስጥ መሰብሰቢያ ቦታ እንዳይኖራቸው ስለተከለከሉ በቁስጥንጥንያ የነበሩ አርዮሳውያን በቡድን በቡድን ተከፋፍለው የረከሰ ምንነታቸውን የሚገልጽ መዝሙር እየዘመሩ ከከተማው ውጭ ወዳለው መሰብሰቢያቸው ይሄዱ ነበር:: በመዝሙራቸውም «ሦስቱ አካላት አንድ አምላክ ናቸው የሚሉ ወዴት ናቸው?» የሚሉና ሌላም ጥላቻን የሚቀሰቅሱ ብዙ ሻካራ ነገሮችን ይሉና ያሰሙ ነበር:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከቤተ ክርስቲያን ልጆች መካከል በዚህ የአርዮሳውያን ድርጊት የሚሳቡና ከእውነት መንገድ የሚስቱ እንዳይኖሩ ስለሰጋ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በተመሳሳይ ሁኔታ መዝሙር እየዘመሩ በከተማዋ እንዲዞሩ በማድረግ ለዚህ አጸፋዊ የሆነ ኦርቶዶክሳዊ ስልፍ አዘጋጀ:: ንግሥቲቱ አውዶክስያ ለዚህ ሥነ ሥርዓት መገልገያ ይሆኑ ዘንድ ከብር የተሠሩ የሻማ መቅረዞችን ሰጠች፣ ለዚህ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችንም በሙሉ ቻለች:: ምዕመናንም የብር መስቀሎችን ይዘው መብራት ያበሩ መዘመርና መዘዋወር ጀመሩ:: በዚህ ድርጊት ኦርቶዶክሳውያኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ የአርዮሳውያኑን ድርጊት እንደሌለ እስኪቆጠር አደረሱት:: በዚህ ጊዜ አርዮሳውያኑ በመቅናትና በመበሳጨት ኦርቶዶክሳውያንን በኃይል ማጥቃት በመጀመራቸው ከሁለቱም ወገን ደም ፈሰሰ:: በዚህም ንጉሡ አርዮሳውያን በኅብረት እንዳይሰበሰቡ አገደ:: ኦርቶዶክሳውያኑ ግን ይህን ማድረጋቸውን ቀጠሉ:: ሶዞ. 6፥18





መነኰሳትን በተመለከተ ደግሞ ያን ጊዜ በቁስጥንጥንያ ብዙ መነኰሳት ነበሩ:: ከገዳማቸው እየወጡ በየቤቱና በየመንደሩ የሚዞሩትንና ከተማ ለከተማ ይርመሰመሱ የነበሩትን መነኰሳት በገዳማቸው ተወስነው እንዲኖሩ አደረገ:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለመነኰሳት ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት ነበረው:: ማንኛውም ኢፍትሐዊ ነገር እንዳይደረግባቸውና በደል እንዳይደርስባቸው የሚችለውን ሁሉ ያደርግ ነበር፤ እንዲሁም የሚያስፈልጋቸውንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም ነበር:: ነገር ግን የምንኵስናን ሕይወት ያስድባሉ በማለት ገዳማቸውን ትተው ከተማ ለከተማ የሚዞሩትን አይወድም ነበር:: ወደ ቁስጥንጥንያ ከተማ በመምጣት ደጋጎችና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብዙ ገንዘብ ይሰጡ በነበሩ ብእሲተ ማውታዎች (ባላቸው የሞተባቸው ሴቶች)[17] ክርስቲያናዊ ደግነት የሚነግዱ መነኰሳትም ነበሩ::

ከካህናቱ በመቀጠልም ትኩረቱን ወደ መንጋው አደረገ:: በአንጾኪያ ሳለ ያደርግ እንደነበረው አሁንም ማስተማሩን ቀጠለ:: የባለጸጎችን ቅጥ የለሽ አኗኗርና መቀማጠል እንዲሁም የግብረ ገብነት ጉድለቶችንና በሴቶች ላይ ይታይ በነበረው መያዶ አለባበስ ላይ ደጋግሞ በአጽንኦት አስተማረ:: በተለይም ደግሞ በወጣቶች ላይ እንኳ ቢታይ የሚያስጠላ ዓይነት አለባበስ ዕድሜያቸው በገፋ ብእሲተ ማውታ (ባላቸው የሞተባቸው ሴቶች) ይታይ ነበርና እነዚህን ከዕድሜያቸው እንኳ የማይማሩትን የድርጊታቸውን ሕፀፅ በማሳየት ይታረሙ ዘንድ አስተማረ:: ከእነዚህ ሴቶች ውስጥ በቤተ መንግሥቱ ውስጥና በቅርብ ያሉ ነበሩ:: የቁስጥንጥንያ የላዕላይ መደብ አባላት ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ጠንካራ ትምህርትና ስለ ክርስቲያናዊ ሕይወት ጥንቃቄ ጠንከር ያለና ጥብቅ የሆነ ሥነ ምግባራዊ ተግሣፅና ቋንቋ ሰምተው የሚያውቁ አይመስልም::[18] አንዳንዶች ትምህርቱና ተግሣፁ እነርሱን ለመንካት የታለመ እንደሆነ ያስቡ ነበር:: በተለይም ተግሣፁ የበለጠ ተገቢና ትክክለኛ በሆነ መጠን ቁጣቸው እየጨመረ ሄደ:: ሕዝቡ ግን በሚያስተምራቸው ትምህርት እጅግ በጣም ደስተኞች ነበሩ::

ድሆችንና ችግረኞችንም አልረሳም:: በሊቀ ጵጵስናው የመጀመሪያ ዓመት ከመንበረ ጵጵስናው ወጭ በመቆጠብ አንድ ሐኪም ቤት አሠራ::19

---

[17] (widow)

[18] ከርሱ በፊት የነበረው ሊቀ ጳጳሳት ኔክታርዮስ የቤተ መንግሥት የቅርብ ሰውና የወይዛዝርትና የመኳንንት ወዳጅ ነበር:: ኔክታርዮስ ከቤተ መንግሥትና ከከተማዋ ታላላቆች ጋር የነበረው የቅርብ ማኅበራዊ ግንኙነት የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ትምህርትና ሕይወት በፊት ከለመዱት አንጻር የማይመችና ሻካራ ሆኖ እንዲታያቸው የራሱን አስተዋጽኦ ሳያደርግ አልቀረም::

[19] የመጀመሪያው ሐኪም ቤት (ሆስፒታል) ፋቢዮላ በተባለች ክርስቲያናዊት እንደተመሠረተ ጀሮም (ይሩማሊስ) ይገልፃል:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ በቂሣሪያ በጣም ትልቅ ሆስፒታል አሠርቶ የማስተዳደሩን ኃላፊነት ለአንድ የዚያው አገረ ስብከት ጳጳስ አደራ የሰጠውን የቅዱስ ባስልዮስን አርአያ ተከተለ::

የነበረው የሕክምና ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ስለ ነበር ሌሎች ሆስፒ ቤቶችንም አሠራ። በእነዚህ ላይ ሁለት ደጋግ ካህናትን ኃላፊ አደረገ። እንዲሁም ሐኪሞችን፣ ምግብ አብሳዮችንና [illegible] ማውታዎች ህመማንን እንዲንከባከቧቸውና በሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንዲረዷቸው፤ እንዲሁም ወደ ከተማዋ የሚመጡ እንግዶች ቢታመሙ የህክምና ርዳታ እንዲያገኙ አደረገ።

ስለ ምጽዋት በየትምህርቱ አዘውትሮ ያስተምር ነበር። በአንድ ወቅት ስለዚሁ ሲያስተምር እንዲህ ብሏል፦

> «የክርስቶስን አካል ልታከብሩት ትወዳላችሁ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ራቁቱን ሆኖ እያያችሁት አትለፉት፤ በየመንገዱ ራቁቱን ሆኖ በብርድ እየተሰቃየ አለና፤ እራቁቱን ሆኖ በብርድ እየተሰቃየ አልፋችሁት መጥታችሁ እዚህ በቤተ መቅደስ በሐርና በወርቅ ሳስጌጡ አትከብሩት። «ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ የተናገረው ክርስቶስ ራሱ «ተርቤ አይታችሁኝ አላበላችሁኝም» ያለው እንዲሁም «ከእነዚህ ከታናናሾች ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት» ያለውም ያው እርሱ ራሱ ነው። ወንድምህ በረሃብ እየተሰቃየና የሞተ ቅዱስ ደሙ የሚቀዳበት ጽዋ በወርቅ ቢለበጥና ቢንቆጠቆጥ ጥቅሙ ምን ላይ ነው? አስቀድመህ የወንድምህን ረሃብ በማጥገብና ጥሙን በማርካት ጀምር፤ ከዚያ በኋላ በተረፈህ ገንዘብ ቤተ መቅደሱንና ንዋያተ ቅድሳትን እንደልብ ማስጌጥ ትችላለህ።»

ባለ ጸጎችን ድሆችን የመርዳት ኃላፊነት እንዳለባቸው አስተማራቸው። ይህም ሁኔታ በጎዳናዎችና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ እና በሕዝብ መሰብሰቢያዎች ሁሉ የሚርመሰመሱትን ለማኞች እንዲበዙ አደረጋቸው። ነገር ግን በተራው ሕዝብ ዘንድ ቢወደድም ምግባረ ብልሹዎች በነበሩት ካህናትና በሀብታሞች እንዲሁም በባለ ሥልጣናት ዘንድ አልተወደደም። ተሾሞ ቁስጥንጥንያ እንደመጣ ባስተማረው አንድ ትምህርት ላይ «ለምቾት አዲሱን ለማንኳሰስ ቢሉ ያለፈውን ያመሰግናሉ» አለ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ንፍግ ኃጢአትን የሚያደርገውን ማንኛውንም ሰው ንጉሥና ንግሥቲቱም ቢሆኑ ሲገሥጽ መፍራት የሚባል ነገር አያውቅም። እርሱ የሚፈራው አንድ እግዚአብሔርን ብቻ ነው። ሰውን ይወዳል! ያከብራል! ግፈኛ ከሆነ ግን ሁሉንም ሰው ደሀ ነው፤ ንጉሥ ነው ሳይል ይገሥጻል። በተለይ ንግሥቲቱ አውዶክስያ በሴቶች የሚበዛበት ቅጥ ማጣትና ወግ የለሽ መሽሞንሞን፤ እንዲሁም ከልክ ያለፈ መደላደልና





መሞላቀቅ ላይ በስተማረ ቁጥር እኔን ነው እያለች ግብሯን ከማስተካከል ይልቅ እርሱን እንደ ጠላትና ተቃዋሚ የምትቆጥረው መሄድ ጀመረች።

ይህንን በተመለከተ ካስተማረው ብዙ ትምህርት መካከል በአንድ ወቅት ባስተማረው ትምህርት እንዲህ አለ፦

> «በዚህ ዓለም የምንፈራው ምንድነው፣ ሞትን? በጭራሽ፤ ለእኔ ሕይወቴ ክርስቶስ ነው፤ ሞትም እንዲሁ። ስደት ነው? ዓለምና በውስጧ ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። የሀብት መጥፋት ነው? ወደ ዓለም ምንም አላመጣንም፤ ከዓለምም ምንም ነገር ይዘን እንደማንወጣ የታወቀ ነው። የዓለምን ሽብርና ፍርሃት እንደ ቁም ነገር አልቆጥረውም፤ ሀብቱና ሕይወቱንም እንደ ኢምንት እየቆጠርሁ። ድህነትንም አልፈራም፤ ሀብትንም አልመኝም። ለሞት አልሸበርም፤ እናንተ በሃይማኖትና በምግባር እንድትጎለብቱ ምናልባት ትንሽም ቢሆን እንድረዳችሁ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ዓለም ስለ መኖር ወደ ፊት አላስብም። ስለዚህ የተወደዳችሁ ወገኖቼ ሆይ! የሆነ ባለው ነገር አትጨነቁ እላችኋለሁ።»

ከዚህ ሁሉ ድካምና የተበላሸውን የማስተካከልና የማደስ ትግል በኋላ ድካሙ ብዙ ፍሬ ማፍራት ጀመረ። ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ በቁጥርም በጥራትም እጅግ በዘላቂነቱ የበለጸገ መዓዛ ተላበሰ፤ ሕዝቡ ፈጣሪውን የሚወድና ለቃሉም የሚታዘዝ ሆነ፤ ነፍሳቸው በመንፈሳዊ ሐሴት ውስጥ ሆነች። ቀድሞ ይደረጉ የነበሩ አረመኔያዊ ድርጊቶችና ትርዒቶችም በጣም ቀነሱ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሕይወቱና በትምህርቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቁስጥንጥንያ መንበር ላይ እንደ ፀሐይ አበራ። በሕዝቡ፤ በንጉሡ፤ እንዲሁም ለትንሽ ጊዜም ቢሆን በንግሥቲቱ በአውዶክስያ ዘንድ ሳይቀር መከበርንና መወደድን አገኘ። በቁስጥንጥንያ መንበር በዝናውና በተወዳጅነቱ እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ። አባታዊና ሐዋርያዊ ትምህርቱን ጎትስ ለተባሉ አሕዛቦች እንዲዳረስ አደረገ። ለእነርሱ መጽሐፍ ቅዱስን በቋንቋቸው ተረጎመላቸው፤ እንዲሁም በአስተርጓሚ አማካይነት ብዙ ጊዜ ራሱ ያስተምራቸው ነበር። ከዚህም ጋር በዳንዩብ ወንዝ ለሚኖሩ የጎቲክና የሲጢያን ነገዶች የሚያስተምሯቸው ሰዎች ይልክላቸው ነበር። በአጭር ጊዜ ውስጥ የተወዳጅነትና የክብር ጫፍ ላይ ደረሰ።

በአጠቃላይ በአመጋገብና በአለባበስ ይታይ የነበረውን መቀናጣትና ድሎት ለማስተካከል አጽንቶ አስተማረ። የመነኮሳቱንና የመኳንንቱን እንዲሁም የካህናቱን ክፋትና ቅጥ የለሽ ምኞት ሰመድ አኗኗር በትምህርቱ ሁሉ ትክክል አለመሆኑን አጥብቆ በማጋለጥ ጠላቶችንም አፈራ። ሆኖም

ከታላላቆች የቤተ መንግሥት ሰዎችና ከባለጸጎችም ወገን የሚወዱትና የሚያፈቅሩት ብዙ ወዳጆች ነበሩት:: ከእነዚህም በጣም ደገኛዋ ብእሲተ ማውታ እና ዲያቆናዊይት፣ የንጉሥ ቴዎዶስዮስ ዘመድ የነበረችው ኦሊምፒያ[20] ነበረች:: ሌሎችም እውነተኛ ወዳጆቹ የነበሩ ብዙ የእውነት

[20] ኦሊምፒያ (Olympias) ከታላላቆች የቤተ መንግሥት ወገን የነበረች ስትሆን እንዳገባች ወዲያው ብዙም ሳይቆይ ባሏ የሞተባትና በትውልድ፣ በውበት፣ በሀብት፣ በሁሉም ነገር የተሰጣት ስትሆን እርሷ ግን የሁለተኛ ጋብቻን ጥያቄና ግፊት ሁሉ እምቢ ብላ በፍጹም መንፈሳዊ ተጋድሎ የኖረች ቅድስት ናት:: ንጉሥ ቴዎዶስዮስ ዘመዱ ለሆነ ሰው ሊያጋባት ደጋግሞ ቢለምናትም እርሷ ግን እምቢ አለች፤ እንዲህ በማለት፦ «እምላኬ በትዳር እንድኖር ቢፈልግ ኖሮ የመጀመሪያዬን አይወስደውም ነበር፤ ነገር ግን እኔ ለትዳር ሕይወት የምስማማ አለመሆኔን ስለሚያውቅ በቶሎ ከእስራቴ ፈታኝ፣ ከከባዱ ቀንበር ነፃ አደረገኝ፣ በሕሊናዬም ቀላልና ልዝብ የሆነውን የንጽሕናን ቀንበር አደረገልኝ::» በዚህ ጊዜ ንጉሡ ሠላሳ ዓመት እስኪሆናት ድረስ ንብረቷ ሁሉ እንዲያዝባት አዘዘ:: ቤተ ክርስቲያን መሄድ እስከማትችል ድረስ ከማንም ጋር እንዳትገናኝ በመከልከል እሽ ለማሰኘት ብዙ ግፊት ቢያደርጉባትም እርሷ ግን ሁሉንም በአኮቴት ተቀበለች:: ንጉሡንም «ከባድ ሸክም ሆኖ ሲያስጨንቀኝ የነበረውን ንብረት እንዲጠበቅ በማድረግህ መልካም አደረግህ፤ አሁንም ለድሆችና ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲሰጥ ብታደርግ የበለጠ መልካም ታደርጋለህ፤ እርሱን እኔ ራሴ ብሰጠው ከሚያስከትለው ውዳሴ ከንቱ ለመዳን የብዙ ጊዜ ጸሎቴ ነበርና::» አለችው:: እርሱም ጽናቷን አይቶ ንብረቷን እንደፈለገች እንድትጠቀምበት ነጻነት ሰጣት:: ከዚያም ራሷንና ሀብቷን ሁሉ ለሃይማኖታዊ አገልግሎት አዋለች::

የነበራትን ብዙ ሀብት ለድሆች፣ ለሐኪም ቤትና ለሀሙማን መገልገያ እንዲውል አደረገች:: እርሷ ግን በከባድ ትህርምትና በፍጹም ብሕትውና የኖረች ስትሆን በቅድስና ሕይወቷም በብዙ አባቶች የተመሰገነች ነበረች:: ጊዜዋንና ኃይሏን ሁሉ ድሆችና በሽተኞች የሚያስፈልጋቸውን በማድረግ እና ወደ ቁስጥንጥንያ የሚመጡ ጳጳሳትንና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ሁሉ ለመቀበል ሰጠች:: የመጡትም በሰፋፊ መሬት ወይም በገንዘብ መልክ ደህና ስጦታ ሳትሰጣቸው አይሄዱም ነበር:: ቤቷ የካህናትና ከተለያየ የዓለም ክፍል ወደ ቁስጥንጥንያ የሚመጡ የመነኮሳትና የመነኮሳይያት ቤት ነበር:: ቴዎፍሎስ ያባረራቸውን መነኮሳት የተቀበለቻቸውና ያሳረፈቻቸው እርሷ ናት:: ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፣ ቅዱስ አምፊሎቅዮስ ሌሎችም ብዙ ቅዱሳንና አባቶች ከእርሷ ቤት ዐርፈዋል:: ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይሆናቸውም ዘንድ ለብዙዎቹ አባቶች ብዙ ገንዘብና ሰፋፊ መሬት ሰጥታቸዋለች::

ሊቀ ጳጳሳት ኔክታርዮስ ለቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናዊት አደረጋት:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በቅድስናቸው በጣም ከሚያመሰግናቸው ሴቶች ዋነኛዋ እርሷ ነበረች:: በእርሱ ላይ በደረሰው ስደት እርሷም ብዙ መከራ ተቀብላለች:: የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ስደት ተገቢነት ተቀብላ አዲስ የተሾሙትን ጳጳሳት ዕውቅናእንድትሰጥ ለማስገደድ ብዙ ክስና የገንዘብ ቅጣት ቢደርስባትም በዓመፅ መንገድ ከተሾሙት ጋር ኅብረትና አንድነት አልቀበልም በማለት ብዙ መከራ ተቀብላለች:: ይህንን ሲሰማ ስደተኛው አባት በጣም ተደስቶአል:: እርሱም በስደቱ ጊዜ የሚያጽናኑ 17 መልእክታትን ልኮላታል:: እነዚህ መልእክታትም «ማንም ሰው ራሱን ካልጎዳ በስተቀር ማንም ሊጎዳው አይችልም» በሚልና በመሳሰሉ ርእሶች ላይ የተቀበለችውን መከራና እያደረገች ያለችውን ተጋድሎ የሚያበረታ እና የቅድስና ሕይወቷን የሚያመሰግኑ፣ መከራ የሚያደርስ እንጂ መከራ የሚቀበል ሰው እንደማይጎዳ የሚያስረዱ ጥልቅ ትምህርቶችን የያዙ ናቸው::





ሰዎች በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ነበሩ:: መጀመሪያ ላይ ራሷ ንግሥቲቱ አውዶክስያም አዲሱን ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ትወደው ነበር:: ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓቶችን አብራ ትከታተላለች፣ በክብረ በዓል ጊዜ ትገኝና ሲያስተምርም ትማር ነበር:: ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ የሚሆኑ የብር መቅረዞችንም ሰጥታለች::

ሆኖም ይህ የወዳጅነት ስሜት ብዙ አልዘለቀም:: ከላይ የተገለጹትና ንግሥቲቱን የሚከቧት ወይዛዝርት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ያስተጋቡ ነበር:: በዚሁ ላይ ደግሞ አውዶክሷ የአንዲትን ብእሲተ ማውታ የወይን አትክልት ቦታ ቀማቻት:: እርሱም እንድትመልስላት አውዶክስያን ማለዳት:: እርሷ ግን በዚህ የመደፈር ስሜት ተሰምቷት ተበሳጨች:: ይህ ሁኔታ በቤተ መንግሥትና በመንበረ ጵጵስናው መካከል የነበረውን ግንኙነት አሻከረው፤ ቀስ በቀስም ውስጥ ውስጡን ችግሩ የጎለመሰ ሄደ:: ሆኖም እነዚህ ነገሮች በሕዝቡ ዘንድ በይፋ ከመታወቃቸው በፊት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሳይፈልገው፣ ነገር ግን በታዛቢነት ቁጭ ብሎ ሊመለከታቸው የማይችል፣ መካካትን የግድ የሚሉ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ፋይዳ ያላቸው ሁለት ክሥተቶች ተፈጠሩ::

## አንደኛ ክሥተት

በመጀመሪያ በፊት ባሪያ የነበረው፣ በኋላ ደግሞ ሚኒስትርና ቆንስላ የሆነው ዩትሮጲየስ ሥልጣኑን አላግባብ መጠቀም አበዛ:: ከባለጸጎች የአንዳንዶቹን ንብረት በኃይልና በግፍ ቀማቸው፣ ሥልጣኔን ይቀናቀኑኛል ብሎ የሚሰጋቸውንና የሚጠረጥራቸውን ሁሉንም በሰበብ በአስባቡ እያባረረ አሳደዳቸው:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከአንድ ጊዜ በላይ ወደዚህ ሚኒስትር ራሱ በመሄድ የድርጊቱን ትክክል አለመሆንና በድርጊቱም ያዘነ መሆኑን በመግለፅ ከክፋቱ እንዲመለስ የድርጊቱ ውጤት ምን ሊያስከትል እንደሚችል ከማሳሰብ ጋር መከረው:: ነገር ግን ዩትሮጲየስ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ምክርና ተግሣፅ አልሰማውም:: ጠላቶቹ ቤተ ክርስቲያን ባላት የማስጠጊያና ወደ እርሷ የመጣውን ሰው አሳልፎ ያለመስጠት መብት እንኳ ቢጠቀመው ከእጁ እንዳያመልጡት ይህን የቤተ ክርስቲያን መብት የሚሽር ዐዋጅ አወጣ:: አሁንም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ ዐዋጅ ጠንካራ የሆነ ተቃውሞውን አሰማ::

በ399 ዓ.ም. ዩትሮጲየስ በአንድ ቅጽበት ከሥልጣኑ ተባሮ ሕይወቱ በሞት አፋፍ ላይ እስኪደርስ ድረስ በከፍተኛ ችግር ላይ ወደቀ::

በሥልጣን ዘመኑ በሠራው ሥራ ምክንያት በ[illegible] ሕዝቡና የግ[illegible] ጠላቶቹ በእርሱ ላይ ያላቸውን ስሜት [illegible] መጠጊያ ሲያጣ ሕይወቱን ለማትረፍ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሸሽቶ ገባ። የቤተ ክርስቲያንን ጥገኝነት የመስጠት መብት በቅርብ ጊዜ ራሱ ባወጣው ሕግ ለመሻር የሞከረ ሰው መሆኑን ሕዝቡ ስለሚያውቅ እርሱ እንዲተርፍ ያሰበ ሰው አልነበረም። ሕዝቡ በርሱ ላይ የነበረው ቁጣ ታላቅ ነበር። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ካለው ድንገተኛ ክሥተት የሚገኘውን ትምህርት ለሕዝቡ ጥቅም ሲል ከማሳየትና ከማመልከት ወደ ኋላ አላለም። በዚህ ሁኔታ ምክንያት በሰወደቀው ሚኒስትር በ[illegible] ዩትሮጲየስ የዚህን ዓለም ክብርና ሥልጣን ከንቱነት በተመለከተ ድንቅ በሆነ ኃይልና ብሩህ በሆነ አገላለጽ ሁለት አስደናቂ ስብከቶችን ሰበከ።[21] በዚህም የሕዝቡን ቁጣ በማረጋጋት፣ ቤተ ክርስቲያን የገባውን ሰው አሳልፌ አልሰጥም በማለት ከሞት እንዲተርፍ አደረገው። ሆኖም ዩትሮጲየስ ከጥቂት ቀናት በኋላ በሌሊት አመለጣለሁ ብሎ ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ በመገኘቱ ተይዞ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተገደለ።[22]

## ሁለተኛ ክሥተት

ዩትሮጲየስ ከሥልጣኑ እንደተባረረ ወዲያውኑ ከበድ ያለና የበለጠ አደገኛ የሆነ ሁኔታ ተፈጠረ። ጋይናስ የተባለ ከቤተ መንግሥት ዘቦች ውስጥ አንዱ የነበረ ትሪቢጊልድ የተባለው የጦር መኮንን ያስነሣውን ዓመፅ በኃይል ያከሽፍ ዘንድ ተላከ። ሆኖም ጋይናስ [illegible] ከትሪቢጊልድ ጋር በግልፅ [illegible] ለማምጣትና ሁኔታውን [illegible] የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን [illegible] የቤተ መንግሥቱ ግቢ ጦር [illegible] በቁስጥንጥንያ ከተማ [illegible] ተላልፈው እንዲሰጡት [illegible] ጋይናስን የመሸምገል [illegible] ተላልፈው የተሰጡት [illegible] በኋላም ነጻ እንዲሆኑና እን[illegible]

ከዚህ ክስተት በኋላ ጋ[illegible] ሳይቆይ አርዮሳዊ የነበ[illegible] መሪዎች ግፊት በ[illegible]

[21] (Homilies on Eutropius)

[22] ዝርዝር ታሪኩ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ ምክንያት - ስለ ዩትሮጲየስ - ባስተማረው ትምህርት መግቢያ ላይ ይገኛል።





ክርስቲያኖች አንዱን ለራሱና እንደርሱ አርዮሳዊ ለሆኑ ወታደሮች መገልገያ ይሰጠን አለ። አሁንም እንደገና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጳጳሳቱን ሁሉ ሰብስቦ ከእነርሱ ጋር ወደ ቤተ መንግሥት በመሄድ በዚህ ጉዳይ ላይ ኃይለኛና ጠንካራ የሆነ የሚያሳምን ተቃውሞውን በማቅረቡ ጋይናስ ጥያቄውን ለማንሣት ተገደደ። በዚህ ጉዳይ የቁስጥንጥንያ ሕዝበ ክርስቲያን በጣም ተቆጣ፤ በአንድ ሌሊትም ብዙ አርዮሳውያን ተገደሉ። ጋይናስ ከቁስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት ሸሽቶ ለጊዜው ቢያመልጥም ኋላ ድል ሆኖ ተገደለ።

ይህ ከተለመደው በላይ የሆነ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በመከራ የወደቁትን የመታደግና የደግነት አድራጎት እና በእነዚህ የጠላ ወረደ ክሥተቶች ሁሉ ያሳየው የጸና አቋምና የማያወላውል የመንፈስ ጥንካሬ በሕዝቡ ዘንድ የነበረውን ክብርና ተሰሚነት የበለጠ ያጠናከረው መሆኑ ግልፅ ነው። ከዩትሮጲየስ ውድቀት በኋላ የሮማን የምሥራቅ ግዛት በተግባር የሚመሩትን (ንግሥቲቱ አውዶክስያንና በእርሷ መሪነት በሥሯ የተሰበሰቡትን ደሌዎች) ቅናታቸውን የበለጠ ያባበሰባቸው ይህ ሳይሆን አይቀርም። በዩትሮጲየስ ከሥልጣን ሜዳ ላይ በአንድ ጊዜ ተንኮታኩቶ ወደ ጥልቅ መውደቅ ምክንያት ባስተማረው ትምህርት የዚህን ዓለም ሥልጣን፣ ክብርና ሀብት ከንቱነት በአጽንዖት ማስተማሩ ይህንን ሕይወትና ቁም ነገር ብለው በያዙት በገዢ መደቦችና በሀብታሞች ዘንድ አልተወደደም። በተለይም ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣንና መብት ላለማስደፈር ባደረገው ድርጊትና በነበረው የጸና አቋም ምክንያት ሥጋትና ጥላቻ አደረባቸው። እነዚህም ቁርጠኛ ጠላቶቹ እየሆኑ መጡ። ወደ እነዚህ ማኅበርም ከቤተ ክርስቲያን ነን የሚሉ ጥቂት ሥልጣን ፈላጊና አድር ባይ ሰዎች ተቀላቀሉ።

እውነትም እርሱ ባይሆኑ ቅጥረኛ የሆኑ ካህናትም ቅናት ያቃጥላቸው [illegible] [illegible] ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ የተለየ ጥላቻ ማሳደራቸውና [illegible] [illegible] ንግሥቲቱና [illegible] የዚህ [illegible] ቅናት [illegible] [illegible] አቋም ደስተኛ ያለመሆኗ ቁርጠኛ ጠላቱ ሆና ተነሳች።

ንግሥቲቱ አውዶክስያ ካሊትርጳ የምትባልን አንዲት ብእሲተ ማውታ መሬቷን ቀማቻት። ያቺ ሴትም ወደ ድሆች ጠበቃ ወደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መጥታ የደረሰባትን ነገረችው። እርሱም ንግሥቲቱን የድሀይቱን መሬት መመለስ እንደሚኖርባት በአጽንኦት አሳሰባት። እንዲሁም በሌላ ጊዜ የአንዲት ሌላ መበለት መሬት በመቀማቷ ምክንያት አሁንም እንዲሁ ከተግሣፅ ጋር እንድትመልስ ስላሳሰባት በሁለቱ መካከል ችግር እየተፈጠረ ሄደ። እርሱ የድሆች ጠበቃና ተቆርቋሪ፣ የቅርብ አሳቢያቸውና መጋቢያቸው ነበር።

## ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በኤፌሶን

በጥር 401 ዓ.ም. የኤፌሶን ካህናትና የአካባቢዋ ጳጳሳት ባደረጉለት ጥሪ መሠረት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ወደ ኤፌሶን ሄደ። ካህናቱና ጳጳሳቱ እንዲህ ብለው በተማጽኖ ላኩበት፦

> «ባለፉት ጊዜያት የቤተ ክርስቲያን ሕግጋትና እኛም ራሳችን በመልካም እረኛ እጦት ምክንያት ለከፋ ችግርና መዘበራረቅ ተጋልጠን ቆይተናል። በአንድ በኩል አርዮሳውያን በሆኑ ሰዎች፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእኛ ላይ ለመጠቀምና ለመሠልጠን ሲሉ ብቻ ሃይማኖታቸው እንደእኛ እንደ ሆነ ለማሳየት ብዙ በሚናገሩና በሚያስመስሉ ነገር ግን እንደ ጨካኝ ተኩላ አድቢዎች በሆኑና ኤጲስ ቆጶስነትን በገንዘብ ለማግኘት በሚጓጉ ሰዎች ችግር ላይ ወድቀን እንገኛለን። ስለዚህ ከእግዚአብሔር በተሰጠህ ጸጋና በተቀበልከው አደራ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትን ትሠራልን ዘንድና የሚገባውን ታደርግ ዘንድ ቅድስናህን እንለምናለን።»[23]

በዚህ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ታሞ የነበረ ቢሆንም ይህንን መልእክት እንደተቀበለ የእስያ አብያተ ክርስቲያናትን ሁኔታ ሲሰማ ለቤተ ክርስቲያን ባለው ቅናት ራሱን አበርትቶ የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ወደ ኤፌሶን ሄደ። በተለይ ዋና ጉዳይና መነሻ የነበረው አውሳብዮስ የሚባል ጳጳስ አንቶኒዮስ በሚባል ሌላ ጳጳስ ላይ ያቀረበው ክስ ነበር። ይህም ክስ አንቶኒዮስን በሰባት ዋና ዋና ወንጀሎች የሚከስ ሲሆን ሰባተኛው ክስ *«ጵጵስናን ለመስጠት እንደ ክብሩ ላቅነት መጠን ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ መቀበል ይገባል የሚል መሆኑንና ይህንንም እንደ ቀዋሚ ሕግ አድርጎ የሚያምንበትና የሚሠራበት ነው»*[24] የሚል ነበር። በዚህ ሂደት ጉዳዩ ሳይታይ ሁለት ዓመት ስለሆነው ተከሳሹ ጳጳስ አንቶኒዮስ ሞተ።

[23] ጳላድዮስ ምዕ. 14

[24] ዝኒ ከማሁ





ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ኤፌሶን ደርሶ ስባ ከሚሆኑ የየአገሩ ስብከት ጳጳሳት ጋር ጉባኤ አድርጎ ሳለ ከሳሹ ጳጳስ አውሳብዮስ ምንም እንኳ ገንዘቡን የተቀበለውና የሾማቸው ጳጳስ አንቶኒዮስ ቢሞትም ገንዘቡን የሰጡትና የተሾሙት ሰዎች በሕይወት ስላሉ ዛሬውኑ ምስክር እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ አለ። ሲኖዶሱም ማጣራቱ እንዲቀጥል በመወሰን ከሳሾችም ተከሳሾችም ያለ ጣልቃ ገብነትና ተጽእኖ ሁሉም ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ እንዲከራከሩ ተደረገ። ምስክሮቹ፣ እንዲሁም ጉቦ ሰጥተው ተሹመዋል ተብለው የተከሠሡት ስድስቱ ጳጳሳት እነ ማን መሆናቸው ተገለጸ። መጀመሪያ ላይ ተከሳሾቹ ክሱን ካዱ። ነገር ግን ምስክሮቹ እነርሱ በጣም የሚያምኗቸውና የሚቀርቧቸው ምዕመናን፣ ካህናት፣ እንዲሁም ሴቶች ሁሉም የተባባሉትን ነገር፣ ቀኑን፣ ቦታውን፣ የገንዘቡን መጠን ሳይቀር በግልፅ መሰከሩባቸው።

በዚህ ጊዜ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ያለ ብዙ ግፊት በራሳቸው ፈቃድ ማድረጋቸውን አመኑ፤ *«አዎ! ከመንግሥታዊና ከተያያዥ ግዳጆች ነጻ ለመሆን ስንል*[25] *ጉቦ ሰጥተን ጵጵስና ተሹመናል፣ ይህን የምናምነው ነገር ነው። እንዲህ በማድረጋችን የሚከተል ጥፋት ከሌለ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ይፈቀድልን ዘንድ እንለምናለን፤ ይህም የማይሆን ከሆነ ደግሞ የከፈልነው ገንዘብ ይመለስልን ዘንድ እንለምናለን፤ አንዳንዶቻችን የሚስቶቻችንን የቤት ዕቃ ሳይቀር ሰጥተናልና አሉ።»*[26]

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለዚህ ሲመልስ ከመንግሥታዊ ግዳጆች ነጻ ይሆኑ ዘንድ፣ እንዲሁም የሰጡትን ገንዘብ ከአንቶኒዮስ ወራሾች እንዲቀበሉ እንዲያዝላቸው ስለ እነርሱ ለንጉሡ ማመልከቻ እንደሚያቀርብላቸው በጉባኤው ስም ቃል ገባላቸው። ስለዚህ ጉባኤው ከአንቶኒዮስ ወራሾች ገንዘባቸውን እንዲቀበሉና ከቤተ ክርስቲያን እንዳይለዩ ሲወስን ነገር ግን በገንዘብ የገዙት «ጵጵስና» ዋጋ እንደሌለው

[25] ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ካህናትን ከመንግሥታዊና ከማኅበራዊ ግዳጆችና አገልግሎቶች ነጻ አደረገ። ነገር ግን መንግሥታዊ ግዳጆችን ለማምለጥ ሲሉ ከምዕመናን ወገን አንዳንዶቹ በቤተ ክርስቲያን ዝቅተኛ ቦታ የያዙ መገኘታቸው ሲታወቅ ይህ መብት ወደ ኋላ ላይ ለጳጳሳት ብቻ እና በመንግሥታዊ አስተዳደር ስምምነት ለተሾሙ ካህናትና ዲያቆናት ብቻ እንዲሆን ተደረገ። ቅዱስ ባስልዮስ ካህናት «በጥንቱ ሕግ መሠረት» ከቀረጥ ነጻ መሆን አለባቸው ይላል፤ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ አንድ ዲያቆን ቀረጥ እንዲከፍል በመደረጉ ስለ ሁኔታው አግባብ አለመሆን አጠንክሮ ይገልጻል።

[26] ጳላ.፣ ምዕ. 15

ተገልጸ ክህናት ሆነው እንደሚይቀጠሩ ተወስኗል። [illegible] በበደል ላይ በደል ከመጨመር በላዩ [illegible] መሆናቸውን ገልጸዋል። ከቤተ ክርስቲያን ሳይርቁ [illegible] ሞያ ቤተ ክርስቲያንን ሲያስገሉ ቆይተዋል። በእነርሱም ምትክ ያገባቸውና በጸጋ የበለጸጉ ሌሎች ስድስት ጳጳሳት ተሾሙ።[27]

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከቁስጥንጥንያ ወደ ኤፌሶን ሄዶ በዚያ በቆየባቸው ወራት ብዙ ለውጦች ተከሠቱ። በእነዚህ በኤፌሶን በቆየባቸው ጊዜያት የቁስጥንጥንያን መንበር ሴቬሪያን በተባለ የጋባላ (በሶርያ ውስጥ ያለች ከተማ) ጳጳስ ጊዜያዊ ኃላፊነት ሰጥቶ ነበር። ቀጣፊ፣ አቀላማጭና አድመኛ የነበረው ሴቬሪያን ግን ተለማኒነቱንና አደራውን ከዶ በንግሥቲቱ በአውዶክስያ እና ብልግና በተጠናወታቸው የቤተ መንግሥት ወይዛዝርት የሚመራ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከመንበሩ የሚወገድበትንና ከህዝቡ የሚለያይበትን መንገድ የሚያጠናና የሚያዘጋጅ የአድማ ቡድን መሠረተ።

አንቲኪየስ የተባለ አንድ የፕቶለሚያስ ጳጳስ ወደ ቁስጥንጥንያ መጥቶ ሲያስተምር በትምህርቱ ብዙ ሰዎች ስለወደዱት በዛ ያለ ገንዘብ ሰብስቦ ወደ አገሩ ሰብኮቱ ተመለሰ። ሴቬሪያን ይህንን የአንቲኪየስን ጉዳይ ሲሰማ የእርሱን ፈለግ በመከተል ወደ ቁስጥንጥንያ ሄደ። በዚያ በቤተ ክርስቲያን ሲያስተምር ተደናቂነት አገኘ። ደህና ሰው መስሎ በመቅረቡና በሰብከቱም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አቀረበው። ከአውዶክስያና ከቤተ መንግሥት ጋርም ተቀራረበ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በኤፌሶን ሳለ ሴቬሪያን ሕዝቡንና ንግሥቲቱን ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጋር አቀላማጭ በሆነ ዘዴው ለማጣላትና [illegible] የሚቻለውን ሲያደርግ ቆየ።

በአንድ ወቅት ሴቬሪያን ሲያልፍ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ [illegible] የነበረው ሴራፒዮን ተነሥቶ ለጳጳሱ እንደሚገባው [illegible]። ሴቬሪያንም በዚህ በጣም ስለተናደደ ሴራፒዮንን [illegible] ከቤተ ክርስቲያን እንዲባረር አለ። ጉዳዩ [illegible] ያልተነሣሁት ስላላየሁት ነው በማለት ነገሩን [illegible] የተሰበሰቡት ጳጳሳትም የሴራፒዮንን ይቅር [illegible] ሴቬሪያን ሊጣልዱትም ፈቃደኛ አልሆነም [illegible] ሴቬሪያን ግን [illegible]

[27] ሆኖም ክህነትን ገንዘብ በመክፈል መቀበል «ሲሞንያ ይባላል፤ [illegible] ከቅዱስ ጴጥሮስ በገንዘብ ለመግዛት በሞከረው በሲሞን መሠሪ የተሰየመ [illegible] የሐዋ. ምዕ. 8፥18-20። በ5ኛው መቶ ዓመት ደግሞ ይህን ነውረኛ ድርጊት «በክርስቶስ መነገድ» ("Christemporismus," "trafficking in Christ") ይሉት ነበር።





ውግዘት እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ሊልተባረረበት በቂ ሰላ ነገር አልተገለፀም በማለት ይህንን ለማድረግ የሚችለውን ነገር ሁሉ ይሰብቀም ጀመር። ሴቬሪያንም ጥላቻው የባሰበት ስለሄደ «ሴራፒዮን በክህነቱ ሆኖ ከሞተ ክርስቶስ ሰው አልሆነም» አለ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ይህን ሲሰማ «ሴራፒዮን በክህነቱ ሆኖ ቢይሞት ክርስቶስ ሰው አልሆነም ሊባል ነው?» በማለት ገሠፀው። ሴቬሪያንም በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ የነበረውን ቅናትና ጥላቻ የሚያመካኝበት አገኘ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከኤፌሶን እንደ ተመለሰ የኤልያስንና የኤልሳዕን ግንኙነት በተመለከተ ሲያስተምር አውዶክስያ ሲሻኝ ጣስ ዉጋኝ እንዲሉ ይህ እኔን ለመስደብ የተነገረ ነው አለች። ለዲያማ ሕይወታቸውና ለወረደ ምግባራቸው አለመምቻቸው ያሉ ካህናትም እርሱን የሚያስወግዱበትን ነገር አብሬው ማውጠንጠን ጀመሩ። ከእነዚህ ዋናው ሰው ሴቬሪያን ነበር። የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ትምህርት በእርሷ ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ እያስመሰለ ይነግራት ነበር።

ሆኖም እነዚህ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ጥላቻ ያደረባቸው የተለያዩ ወገኖች፣ ነገር በመጎንጎንና በማሾከውም መንገድ ቢሆን ያሰቡትን ከማሳካት ወደ ኋላ የማይል የነገር ልዩ ተሰጥኦ ያለው ሌላ እጅ እስካላገኙ ድረስ ብቻቸውን ያን ያህል አደገኛ አልነበሩም። ገመዱን ከያሉበት የሚጎትትና የሚወጥር! ከዚያም አንድ ላይ የሚገምድ ካላገኙ በስተቀር በኋላ ያስከተሉትን ውጤት ያህል ሊያመጡ የማይችሉ ነበሩ። ሆኖም ለእንዲህ ዓይነቱ ተግባር ራሱን ያዘጋጀና ብቁ የሆነ ችሎታ ያለው ሰው ማግኘም [illegible] በፊት ጊዜ ውስጥ ተገኘ። እርሱም 23ኛው የእስክንድርያ [illegible] ነበር። ቴዎፍሎስ ወደ ቁስጥንጥንያ መጀመሪያ [illegible] የሆነውን ነገር ማግኘም በማይታወቅበት ሁኔታ ነበር።

[illegible] በእስክንድርያ መንበር ላይ የተሰጣት [illegible] ቁስጥንጥንያ ላይ በሚሾሙት ዘንድ በጎ [illegible] እንዲሁም ይህ ትልቅ ስፍራ [illegible]

[illegible] በሁለቱ [illegible] የእስክንድርያና የቁስጥንጥንያ መካከል ጥላቻን እየፈጠረና ግንኙነታቸውን እያሻከረ ሄደ። ይህም ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት

ብዙ ችግር አስከትሏል። ወደ ፊት የምናየው በቴዎፍሎስ የተፈጸመው ድርጊት በቁስጥንጥንያ ምዕመናን ላይ ከፍተኛ ጠባሳን ጥሎ በማለፉ ክርስቲያኖች በአንድነት መንፈስ እርስ በርሳቸው እንዳይተባበሩ ትልቅ ዕንቅፋት ፈጥሯል። ይህ የእርስ በርስ ጥላቻና ሽኩቻ ለምሥራቁ የሮማ ግዛትም ያልበጀው ሲሆን በተለይም ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንዱ ሌላውን በስሩ ለማድረግ የሚያደርገው ግብግብ የምሥራቁ የሮማ ግዛት በመሐመዳውያን ሥር እንዲወድቅ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። ወደፊት ከዚህ በኋላ በመጡት ዘመናት በቤተ ክርስቲያን ብዙ ችግሮች የተፈጠሩት በዚህ የሥልጣን ፍቅርና ጥማት መንስኤነት ነው። ችግሮች ሲፈጠሩ እንኳ በመነጋገርና በውይይት እንዳይፈቱ እየሆኑ የከረሩ ሄደው ብዙ ችግር ሲያስከትሉ የኖሩት ውጫቸው በምንም ጭምብል ቢሸፈን ውስጣቸው የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን የሚያንጽ ሳይሆን የግል ክብርና ዝና ጉዳይ የሆነ ነው።

ይኸው የመንበር እኔ እበልጣለሁ ጉዳይም ቀጥሎ በ451 ዓ.ም. የሮሙ ጳጳስ የነበረው ርጉሙ ልዮን የእኔ መንበር ከሁሉም ይበልጣል፣ እኔ የክርስቶስ እንደራሴ ስለሆንሁ እኔ ያልኩት ነገር ሁሉ የክርስቶስ ቃል ነው በማለት ንጉሡ መርቅያን የእርሱን እሳብ ይደግፍ ስለነበር በዚህ በመመካት አንዲቷን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንድትከፈል አድርጓል። ሌሎችን የመግዛት ምኞትና የሥልጣን ፍቅር ከቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በዚህ ዓለም ከግለሰብ እስከ ማኅበረሰብ ሁሉም ሲታመስበት የኖረና ያለ ወደፊትም የመኖሩ ጉዳይ ብዙም የማያጠራጥር ክፉ ደዌ ነው።

## ቴዎፍሎስ ማነው?

ቴዎፍሎስ ከ385-412 ዓ.ም. ድረስ የነበረ 23ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ነው። ቴዎፍሎስ ተሰጥኦና ችሎታ እንደነበረው ይነገርለታል። ከዚህም ጋር ግን በጣም ጨካኝና የፈለገውን ነገር ለመፈጸም ማንኛውንም መንገድ ቢሆን ከመጠቀም ወደኋላ የማይል፣ ውጤቱን እንጂ ለውጤቱ መገኘት የሚጠቀመው ዘዴ ክፋትም ሆነ ደግነት የማያሳስበው ሰው ነበር። 23ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ በብዙ የታሪክ መዛግብት እንደተገለጸው፣ ሥራውም እንደሚያሳየው ሌሎችን በሥሩ ማድረግ የሚፈልግ፣ ክርክርና ነገር ወዳጅ፣ የሚያጠቃበት መንገድ ካገኘ ይሉኝታ እና ርኅራኄ የማያውቅ ጨካኝ ነበር። ቴዎፍሎስ እንደ እስክንድርያ ፓትርያርክነቱ ያዘጋጃቸው ከነበሩት የትንሣኤ መልእክታት ውጭ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያን ያህል ተጠቃሽ የሆነ ሌላ ሥራ ትቶ አላለፈም። አንድ ትልቅ «በ[illegible] ኦሪገን» ጥራዝ እንደጻፈ ይነገራል። የዚህ መጽሐፉ አንዳንድ ክፍሎቹ ተጠብቀው ይገኛሉ። ዋናው ቴዎፍሎስን በታሪክ የሚያስነሳው ትልቁ ጉዳይ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስደትና መከራ ጋር ያለው መሠረታዊ ቁርኝት ነው።





እስከ 399 ዓ.ም. ድረስ ዋና የኦሪገን (ኦርጌንስ)[28] አድናቂና የኦሪገናውያን አስተሳሰብ ደጋፊና ተከታይ ለነበሩት ወዳጅ ነበር። ኦሪገናዊ ከሚባሉት መነኮሳት ብዙዎቹ በጣም ከሚቀርቡት ወዳጆቹ ወገን ነበሩ። ከእነርሱ ውስጥ አንዳንዶቹንም በቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ቦታና የአገልግሎት መስክ መድቧቸው ነበር። ለምሳሌም አባ ኤስድሮስን[29] ሊቀ ካህናትና የመንበረ ፓትርያርኩ የውስጥ ጉዳይ ኃላፊ አድርጎት ነበር። ኤጲስቆጶስነት የሾማቸው ሌሎችም ነበሩ። በኦሪገን ምክንያት ዮሐንስ ጳጳስ ዘኢየሩሳሌምና ሩፊኖስ በአንድ ወገን (በኦሪገን አስተሳሰብ ደጋፊነት)፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስና ጀሮም ደግሞ በሌላ ወገን (በፀረ ኦሪገን አስተሳሰብ) ሆነው በፈጠሩት አለመግባባት ቴዎፍሎስ ወደ መጀመሪያዎቹ ጎን በመሆን ጀሮምን ጳጳሱን ዮሐንስን ሊያከብረውና ሊሰማው እንደሚገባው ነገረው፤ ቅዱስ ኤጲፋንዮስንም ስለ እግዚአብሔር ህልውና ባለው አስተሳሰቡ እግዚአብሔርን እንደ መዋቲ ሰው ያለ አካልና ህላዌ ያለው ብሎ የሚያስብ[30] ነው ያለ ይነቅፈውና ይተቸው ነበር። የኦሪገናውያን ተቃዋሚ የነበረውን ጳውሎስ የሚባል የግብጽ ጳጳስም ከግብጽ አባሮታል።

[28] (Origen)፣ ከ182 - 251 ዓ.ም. የነበረ ሲሆን የመጀመሪያው የሥነ መለኮት ሊቅ ነበር። አባቱ በሰማዕትነት የሞተ ሲሆን እርሱም ሰማዕትነት ሊቀበል ሊሄድ ሲል እናቱ ልብሱን ስለደበቀችበት ቀረ። እጅግ በጣም የተማረና የክርስትናን ትምህርት ወጥ በሆነ ሁኔታ ለመቅረፅ ብዙ የደከመ ነው። እጅግ በጣም ብዙ ጽሑፎችን ጽፏል፤ ዕድሜ ልኩን ለቤተ ክርስቲያን ደክሟል፤ የሞተውም ስለ ክርስቶስ ሲል በተቀበለው ድብደባ ምክንያት ነው። ለኋላ ሊቃውንት መነሻ የሚሆን ሰፊ ሥራ ትቷል። ሆኖም ግን አስተሳሰቡ ከፕላቶን ፍልስፍና ጋር የተደበለቀ ስለ ነበር ኑፋቄያዊ ስህተቶችንና ትምህርቶችንም ጥሎ አልፏል። ከዚህ የተነሣ እርሱ ከሞተ በኋላ በአንድ ወገን የእርሱ አድናቂዎችና የአስተሳሰቡ ተከታዮች፤ በሌላ ወገን ደግሞ የእርሱ አስተሳሰብ ጠላቶች በመሆን ለብዙ ጊዜያት በቤተ ክርስቲያን ውዝግብ ሲያስከትል ቆይቷል።

ቅ.አትናቴዎስ በታላቅ አክብሮት ይጠቅሰዋል፤በጥንቃቄና በቅንነት ሲተረጎም እንደሚገባውም ይገልጻል። ቅ.ጎርጎርዮስ ዘ ንዚናዙ፣ ቅ.ባስልዮስ ያደንቁታል፣ ቅ.ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ «የ3ኛው መቶ ዓመት የክርስትና ትምህርት ንጉሥ» ይለዋል። የሚቃወሙትና የሚነቅፉትም ነበሩ። ዋናዎቹ ተቃዋሚዎቹ መናፍቃን ቢሆኑም ከአባቶችም በተለይ ቅ. ኤጲፋንዮስና ቅ.ሜቶዲየስ በኃይል ይነቅፉታል። ያን ያህል የተማረና በቅድስና ሕይወቱና በትጋርምቱ «የእነ ቅዱስ እንጦንዮስ ፋና ወጊ» የተባለውና በጣም ትሑት የነበረው እርሱ ለተሳሳታቸው ዓይነት ስህተቶች መጋለጡንና የውዝግብ ምክንያት መሆኑን ሲያስቡት ኦሪገንን ባጣም የሚያሳዝን ሰው ሆኖ እናገኘዋለን። ኦሪገናዊነት በመለካውያን ጉባኤ (በ553ዓ.ም) ተወግዟል የሚሉ ብዙዎች አሉ፤ የዚያኑ ያህል ደግሞ የለም፣ አልተወገዘም የሚሉ አሉ። የኦሪገናዊነት ጉዳይ ዋናው ችግሩ ጉዳዩ ሲነሣ በራሱ ያለው ሃይማኖታዊ አንድምታና ፋይዳ ብቻ ሳይሆን በብዙ ግላዊ ጥላቻዎችና ድብቅ ዓላማዎች ተተብትቦ ይቀርብ ስለነበር ነው።

[29] (Isiodore) ቴዎፍሎስ በቁስጥንጥንያ መንበር ላይ ሊሾመው አዘጋጅቶት ነበር። የልጅነቱን ዘመን ያሳለፈው በኒጥሪያ ገዳም ሲሆን በሃይማኖተኛነቱ የተመሰገነ መነኩሴ ነበር።

[30] (Anthropomorphism) - Anthropos - man - ሰው ማለት ሲሆን morphe - form ደግሞ ቅርጽ ማለት ነው። ይህም እግዚአብሔር የሰው ቅርጽ አለው የሚል አመለካከት ነው።

## በግብጽ ገዳማት የተነሣው ውዝግብ

በዚህ ጊዜ ከላይ ለተገለጹት መነኰሳት ለቁምስናቸው መጠቀሚያ መሆን የቻለ የከፋ ውዝግብ ነበር። ጉዳዩም እግዚአብሔር እንደ ሰው ያለ ገጽ፣ አካልና አኗኗር አለው ወይስ ረቂቅና ሊገለጽ የማይችል[31] ነው? የሚል ነው። ይህ ጉዳይ ቴዎፍሎስን ከመነኰሳቱ ጋር፣ ከቅዱስ ኤጲፋንዮስም ጋር የሚያገናኝና መሠረታዊ የሃይማኖት ጉዳይ በመሆኑ በመጠኑ ምንነቱንና ታሪካዊ ሂደቱን በአጭሩ እንመለከት።

በ4ኛው መቶ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ የኒጥሬያ ገዳም መነኮሳት የተጋነነ ኦሪገናዊ አድናቆት ነበራቸው። የአንቶኒዮቹም የሲጤሲ ገዳም መነኮሳት ደግሞ እነዚን ከመቃወምና የኦሪገንን መጠን አለፍ ዘይቤያዊ የትርጓሜ ስልት በጣም ከመፍራት የተነሣ ወደ አንትሮፖሞርፊዝም አስተሳሰብ አዘነበሉ። ይህም ጉዳይ ወደ ፍልስጥኤም ገዳማት ተዛመተ።

ጉዳዩ በእንግሊዝኛው አንትሮፖሞርፊዝም ይባላል። ዋና አሳቡም እግዚአብሔር የሰው ቅርጽ፣ የውጭና የውስጥ አካላት ከነአሠራራቸው በአጠቃላይ የሰው ባሕርይ በሙሉ አለው፣ ህልውናውም እንዲሁ ነው የሚል አስተሳሰብ ነው። ይህ በጥንት ጣዖት አምላኪዎች በተለይም በግሪኮችና በሮማውያን አማልክት አገላለጽ ጎልቶ ይንፀባረቅ ነበር። የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች ጣዖታውያን አሕዛብ ረቂቅና መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን ለሰው ድክመትና ውጣ ውረድ የተጋለጠ፣ የተጋነነ ሰው ብቻ አድርገው በማሰባቸው ይነቅፏቸው ነበር።

እግዚአብሔርን እንዲህ ባለ ሁኔታ የሚገልጹ አባባሎች በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በብሉይ ኪዳን ተደጋግመው ይገኛሉ። መናገር፣ መስማት፣ ማየት፣ መተንፈስ ተነግረውለታል። እንዲሁም በዓይኑ ይመለከታል፣ መሬት የእግሩ መረገጫ ናት፣ በሰማያት ይቀመጣል ተብሏል። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሰውኛ አነጋገር ለእግዚአብሔር ሲናገር ሰው ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ በሚገልጽ ሁኔታ እንጂ እንዲሁ በቀጥታ እንደ ሰው ያለ አካልና ባሕርይ ያለው መሆኑን በቀጥታ አልተናገረም። የዚህ አገላለጽ ምሳሌያዊነቱ ግልጽ ነው። ሁሉን የሚያዩ ዓይኖቹ - ሁሉን ዐዋቂነቱን፣ ዘላለማዊ ክንዶቹ - ሁሉን ማድረግ ቻይነቱን፣ ቁጣውና ስድቶ - ኃጥአንን የሚቀጣ መሆኑንና ፈራጅነቱን፣ ሰውን ስለመፍጠሩ ተጸጸተ ሲባል ኃጢአትን ፈጽሞ የሚጸየፍ መሆኑን

[31] (Incorporeal)





የሚገልጽ አጽንኦታዊ አባባል ነው። ሰው በዚህ ዓይነት ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ ካልተገለጸለት በስተቀር የእግዚአብሔርን ዐዋቂነት፣ ሁሉን ቻይነት... ለመረዳት ሌላ መንገድ የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በእግዚአብሔር ቋንቋ ሳይሆን የእግዚአብሔር አሳብ ለሰው፣ በሰውኛ ቋንቋ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲሁ በጥሬው እንዳንወስዳቸው እራሳቸው ያስጠነቅቁናል። እግዚአብሔር መንፈስ፣ ሁሉን ቻይ፣ የማይታይ፣ ምሉእ በኩለሄ፣ ሊገለጽ የማይችል መሆኑን ያስተምሩናል። አንትሮፖሞርፊዝም በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉ ምሳሌያዊ አገላለጾችን እንዳሉ በጥሬው የመውሰድ ውጤት ነው።

የቤተ ክርስቲያን አባቶች በድርሳናቸው የመለኮታዊ ባሕርይ ረቂቅነት፣ እንዲሁም የሰው አእምሮ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ ደግነትና ወሰን የለሽ ፍጹምነት ለመረዳት የማይችል መሆኑን ሁሉም በአጽንዖት ገልጸዋል። እግዚአብሔርን ልንረዳው የምንችለው ከምናየው ሕይወትና ህልውና፣ ከራሳችንም ጭምር ነው። ሆኖም ግን የተፈጠረው ነገር ሁሉ ከመለኮታዊ ፍጹምነት የት የሌለ[32] ርቀት ስላለው ስለ እግዚአብሔር የሚኖረን እውቀትና አስተሳሰብ እርሱ እንደሆነው አድርጎ ሊስለውና ሊረዳው አይችልም። እርሱ ገደብና ወሰን የሌለበት፣ ሁሉን ይወስናል እንጂ የሚወስነው የሌለ ነው፣ እኛ ግን ሕሊናችንና አስተሳሰባችን ውሱን ነው። ስለዚህ ውሱን የሆነው የማይወሰነውን ሙሉ በሙሉ ሊረዳው አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔርን ማሰብና ህልውናውን መገንዘብ እንጂ ባሕርዩንና መርምረን ልንረዳውና ይህን ይመስላል ብለን ልንገልጸው አይቻለንም። ሰውና በዚህ ዓለም ላሉ ነገሮች የሚነገሩ ቃላት - አካል፣ ህልውና እና የመሳሰሉት - ለእግዚአብሔር ሲነገሩ ቃላቶቹ ያው ቢሆኑም ለሰው ሲነገሩና ለእግዚአብሔር ሲነገሩ ያለውን የንጽጽርና የአገላለጽ ልዩነት ማገናዘብ ውስጥ በማስገባት ነው።

በ4ኛው መቶ ዓመት በዘፍ. 1፥27 ላይ ያለውን በጥሬው በመያዝ አዲየስ የሚባል ሰው «እግዚአብሔር የሰው ቅርጽ አለው» ብሎ ተነሥቶ ነበር። ሆኖም ስህተቱ የለየለት ስለነበር፣ በጀሮም አገላለጽ «ደረቅና ትርጉም የለሽ ስህተት» በመሆኑ ብዙም ተከታይ አላገኘም፣ ቤተ ክርስቲያንንም አላወከም። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ በአንዳንድ የአፍሪካ ክርስቲያኖች ዘንድ ብቅ ማለት ጀምሮ ነበር። ከላይ እንደተገለጸው በቴዎፍሎስ ዘመን በግብጽ ገዳማት በመነኰሳቱ መካከል ውዝግብ

[32] (Infinite)

ፈጥሮ ነበር:: ቴዎፍሎስ በትንሣኤ መልእክቱ እግዚአብሔር ረቂቅ እንጂ እንደሰው ያለ ገጽና አኗኗር አለው የሚሉ የተሳሳቱ ናቸው በማለት ገለፀ:: ኋላም በእርሱ የተተካው ቅዱስ ቄርሎስ ይህን ስህተት የሚገልጽ አጠር ያለ ጽሑፍ አዘጋጅቷል:: የስህተታቸውንም ምክንያት ከመጠን ያለፈ አላዋቂነት መሆኑን ገልጾል:: በእነዚህ ላይ የጻፉ ሌሎች ሊቃውንትም ሁሉም ይህ የሞኝነት አስተሳሰብ ነው በሚል ውድቅ አድርገውታል::

እንግዲህ ሁለቱም ዓይነት አስተሳሰቦች ምንነታቸውና ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትክክል ነው ብለው የጻፉለትና ያስተማሩት በአንድ በኩል፣ እንዲሁም አልፎ አልፎም ቢሆን በሚነሡ ሰዎች ዘንድ ይንጸባረቅ የነበረው አንትሮፖሞርፊዝም በሌላ በኩል በአጭሩ ይህን ይመስሉ ነበር::

## የቴዎፍሎስ አሳብ መለወጥ

በ399 እና በ400 ዓ.ም መካከል ቴዎፍሎስ አመለካከቱ በድንገት ተለውጦ ከኦሪገን ተቃዋሚዎች ጎራ ተሰለፈ:: የዚህ ምክንያት የሆነው ለኦሪገናውያን ወዳጅነት ከነበረው ከአባ ኤስድሮስ ጋር በግሉ መጣላቱ ነበር:: ከኤስድሮስ ጋር የተጣላበት ምክንያት ይህ ነበር:: ከታላላቆች ወገን የሆነች አንዲት ብእሲተ ማውታ ለእስክንድርያ ድሆች ልብስ መግዣና ለሚያስፈልጋቸው ነገር ይሆን ዘንድ ከጥብቅ አደራ ጋር በመሐላ አጽንታ ለአባ ኤስድሮስ ብዙ ወርቅ ሰጠቼው:: እርሱም ይህን ነገር ለቴዎፍሎስ አልገለጠም:: ምክንያቱም ቴዎፍሎስ ይህን ብዙ ገንዘብ መቀበሌን ከሰማ ለሚያስገነባቸው ግንቦች ማሠሪያ ይወስደብኛል ብሎ ስለፈራ ነው:: ቴዎፍሎስ ግንብ ማስገንባትና ቤት ማሠራት በጣም ይወድ ነበር ይባላል:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ የሆነው ሶዞመን፣ አባ ኤስድሮስ ቴዎፍሎስን «ግድግዳዎችን ከመገንባት ይልቅ አማናዊ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆኑትን የድሆችን አካል ማከምና መርዳት የተሻለ ነው» እንዳለው ጽፏል::[33] የፔሉዚየሙ ቅዱስ ኤስድሮስ ደግሞ ቴዎፍሎስን «የወርቅና የሕንፃ ፍቅር ያደረበት፣ ፍቅረ ንዋይ የገዛው»[34] ይለዋል::

አባ ኤስድሮስም ያን በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ ለድሆችና ለችግረኞች አገልግሎት አዋለው:: ሆኖም ቴዎፍሎስ ይህንን ነገር በነበሩት መገብተ

[33] ሶዞመን 8፣12

[34] ("the gold-maniac and litholater." , "mania for building" and avarice) St. Isidore Pelus., Ep. i, 152





ዜና አማካይነት ሰማ:: በዚህ ጊዜ በኤስድሮስ ላይ በጣም ተቆጣ:: ለጊዜው ዝም ያለ መሰለና ከሁለት ወር በኋላ ካህናቱን ሰብስቦ *«ኤስድሮስ ሆይ፣ ይህንን ክስ በአንተ ላይ ከዛሬ አሥራ ስምንት ዓመት በፊት አንድ የሆነ ሰው አምጥቶ ሰጠቶኝ ነበር፣ ነገር ግን በጣም ሥራ ስለሚበዛብኝ ረስቼው ነበር:: አሁን ግን ሌሎች ወረቀቶችን ስመለከት ይህን አንተን የሚመለከት ክሥ የያዘ ወረቀት አገኘሁት:: አንተስ ራስህን ለመከላከል ምን ትላለህ?»* አለው::

ኤስድሮስም *«ነገሩ እንደተባለው ያን ጊዜ ቀርቦ ነገር ግን ተረስቶህ ኖሮ ነው መባሉ እውነት ነው ብለን ብናስብ እንኳ ይህን ክስ ያቀረበው ሰው ለሁለተኛ ጊዜ ቀርቦ ክሱን አይከታተልም ነበርን?»* አለው:: ቴዎፍሎስም አይ ሰውዬው ባህረተኛ ስለነበረ ሌላ ጊዜ አልመጣም አለ:: ኤስድሮስም *«ፓትርያርክ ሆይ፣ ያን ጊዜ ቶሎ ተመልሶ ባይቀርብም ከጉዞው በኋላ አልተመለሰም? በሚቀጥለው ዓመት፣ ወይንም በሚቀጥሉት ሌሎች ብዙ ያለፉ ዓመታት አልቀረበም? አሁንም ቢሆን ይህን ያህል ዓመት ቢቆይም ጨርሶ ከመቅረት ይሻላልና የሚገኝ ከሆነ ቀርቦ ያስረዳና ይከራከር ዘንድ ንገረው»* አለ::

በዚህ ጊዜ ቴዎፍሎስ በሰበሰባቸው ካህናት ፊት ነገሩ የማያዋጣውና የሚያሳፍረው ሆኖ ሲያየው ነገሩን ለሌላ ቀን ቀጠረ:: ቴዎፍሎስ ገንዘብ በመስጠት በኤስድሮስ ላይ የሐሰት ምስክር ለመግዛት ለአንድ ልጅ በእኅቱ አማካይነት ብዙ ገንዘብ ሰጠ:: የልጁ እናት ግን ይህን የዓመፃ ገንዘብ አልቀበልም ብላ ለኤስድሮስ በእርሱ ላይ በሐሰት ስለመመስከር ከቴዎፍሎስ እኅት እጅ የተቀበለቺውን ገንዘብ አሳየችው:: ገንዘቡንም አልቀበልም ብላ መለሰች:: የቴዎፍሎስ እኅትም በሕመም ተሰቃይታ ሞተች:: ከዚያም በምክንያት ለማባረር እንዳልሆነለት ሲያይ እንዲሁ «ኤስድሮስ ከቤተ ክርስቲያን የተባረረ ነው» በማለት አወገዘው:: በዚህ ጊዜ አባ ኤስድሮስ ለሕይወቱም ስለፈራ ወደ ቀደመ ገዳሙ ወደ ኒጥሪያ በመሸሸ በዚያ በበዓቱ ተቀምጦ ነገሩን ለፈጣሪው ሰጠ:

ወዲያውም ሳይቆይ ቴዎፍሎስ በኤስድሮስ ላይ ያገኘው ድል አስተማማኝ መስሎ ስላልተሰማው ምንም ምክንያት ሳይገልጽ ከታላላቅ የገዳም አበምኔቶችና አባቶች የተወሰኑትን ጳጳሳትን ሳይቀር ከየገዳማቸውና ከበረሃውም እንዲሰደዱ የሚያዝ ደብዳቤ ለአካባቢው ጳጳሳት ላከ:: እነዚህ መነኰሳት ከካህናቶቻቸው ጋር ወደ እስክንድርያ ሄደው እንዲባረሩ የተወሰነባቸው በምን ምክንያት እንደሆነ በልመና ጠየቁት:: እርሱ ግን ከአንድ ፓትርያርክ ቀርቶ ከማንኛውም ሰው በማይጠበቅ መልኩ በጥፊ መታቸው:: ከዚያም አሁን ያለው ጉዳይ ስለ

ኤስድሮስና ተያይዞ ስለተፈጸመው ሁኔታ ለመግለጽ መምጣታቸው ሆኖ ሳለ ሌላ ምክንያት ስላልነበረው በቁጣና በጩኸት እናንተ መናፍቃን ናችሁ፣ አሪዮሳዊ ናችሁ»[35] አላቸው።

## ቴዎፍሎስና የመነኮሳቱ ውዝግብ

ከላይ የተገለጸው በመነኮሳቱ መካከል ተፈጥሮ የነበረው ውዝግብ ቴዎፍሎስ አንዱን በአንዱ ላይ በማነሳሳት እነርሱን ጥሩ የሚያጠቃበት መሣሪያ ሆኖ አገኘው። ከመነኮሳቱ ጋር ስለተጣላ እንዴት አድርጎ እንደሚበቀላቸው ሲያስብ ነበር። ሆኖም ግን መናንያን ስለሆኑና ለምንም ነገር ስለማይጨነቁ የሚያጠቃበት መንገድ አላገኘም ነበር። ይሁን እንጂ ከመነኮሳቱ የተወሰኑት እግዚአብሔር ረቂቅ እንጂ ሰብአዊ ገጽ የለውም የሚሉትን ይህንን ከሚቃወሙት ጋር አጋጫቸው። መነኮሳቱም ረጋ ብሎ መነጋገርንና ጉዳዩን በውይይት መፍታትን ትተው ወደ ሁከትና እርስ እበርስ ወደ መሰዳደብ ሄዱ። የመለኮታዊ ባሕርይን ረቂቅነት የሚያምኑትን ነዚያኞቹ «አሪገናውያን» ሲሏቸው እነዚህ ደግሞ እነዚያን «አንትሮፖሞርፊስቶች» አሏቸው። ይህ የመነኮሳቱ መከፋፈል ለቴዎፍሎስ በቀል ምቹ ሁኔታን ፈጠረ።

## የመነኮሳቱ መባረር

በዚህም ሳይወሰን ቴዎፍሎስ እነዚህን መነኮሳት ለማውገዝ ወደየአጎራባች ጳጳሳት ጉባኤ ጠራ። እነርሱን ግን ቀርበው እንዲከላከሉ ዕድል አልሰጣቸውም፤ ቃልም መተንፈስ አልቻሉም። በፊት በታላቅ መምህርነታቸውና በቅድስናቸው ያከብራቸው የነበሩትን አረጋውያን ሁሉ ኤስድሮስን እንደ እርሱ ባለማሳደዳቸውና ለእርሱ ባሳዩት ሐዘኔታ ምክንያት በአንዴ አወገዛቸው። በአንዴ ሁሉንም ማባረር ስለ ፈራ ተራ በተራ አንዴ ሁለቱን፣ ሌላ ጊዜ ሦስቱን እያደረገ አሳደዳቸው። ቴዎፍሎስ ለኃይል ርምጃና ለሁከት ወደ ኋላ አይልም ነበር፤ ራሱንም ዳግማዊ ሙሴ ይል ነበር ይባላል።[36]

[35] ከእነዚህ ሁለቱ በኒጥሪያ ገዳም በቅድስና ሕይወታቸውና በሃይማኖተኛነታቸው ይታወቁ የነበሩ አሞኒዮስና ዲዮስቆሮስ የሚባሉ መነኮሳት ነበሩ። ቴዎፍሎስም ለእነርሱ ከነበረው አክብሮት የተነሣ ዲዮስቆሮስን ጳጳስ ሲያደርገው አሞኒዮስን ደግሞ ከሌሎች ሁለት ጋር ወደ እስክንድርያ አስመጥቶ የቤተ ክርስቲያን ገቢና ንብረት ተቆጣጣሪዎች አደረጋቸው። ነገር ግን የቴዎፍሎስን ጠባይና በሕንፃ ላይ የሚያባክነውን ገንዘብ ሲያዩ ወደ ገዳማቸው ተመለሱ። ቴዎፍሎስ ወደ ገዳማቸው የተመለሱበትን እውነተኛ ምክንያት ሲያውቅ ሌሎች አጎው መነኮሳትን በእነርሱ ላይ በማስነሣት ሊበቀላቸው ቆርጦ ተነሣ። እነዚህ መነኮሳት ብዙም ትምህርት የሌላቸው ስለነበሩ ቴዎፍሎስ አንድ ጊዜ አንዳቸውን በሌላቸው ላይ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አጥቂ የነበረውን ተጠቂ እንዲሆን ያደረገ በዘዴ እንዲያጠቃቸው ተመቻችተው ተገኝተውለታል።

[36] ጳላድዮስ ምዕ. 7





ስለሆነም በመጀመሪያ በረ አሪገናዊ አመለካከትና አስተሳሰብ የነበራቸውን መነኮሳት ምንም እንኳ አስተሳሰባቸውን ይነቅፍ የነበረ ቢሆንም በእነ ኤስድሮስና የአሪገናዊ አስተሳሰብ ደጋፊዎች በነበሩት ላይ (የመለኮታዊ ባሕርይን ረቂቅነት የሚያምኑትን) በማስማራት ለዓላማው መጠቀሚያ አደረጋቸው። ከዚያም ከተጠቀመባቸው በኋላ እንደገና የጠላትነት ፊቱን ወደ እነርሱ መልሶ በ401 ዓ.ም. አሪገናዊነትን አወገዘ።

ከዚሁ በመቀጠል ወደ ገዳማቸው ወደ ኒጥሪያ በጦርኃይል ጅቦ በመሄድ ሊይዛቸው የሚፈልጋቸውን ሦስት ጳጳሳትና ሌሎች መነኮሳት ስላላገኛቸው በመነኮሳቱ በዓት የተገኘውን መናኛ ነገር ለተከተሉት ወጣቶች አከፋፍሎ፣ ገዳማቸውን ከነመጻሕፍቶቻቸውና ንዋያተ ቅድሳቶቻቸው አቃጥሎ ወደ እስክንድርያ ተመለሰ። በዚህ ቃጠሎ አንድ ሕፃንም አብሮ መቃጠሉ ይነገራል[37]። እነዚህ ሦስት መቶ የሚሆኑ መነኮሳትም አጽፋቸውን ጠቅልለው ወደ ፍልስጥኤም ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተሰደዱ። ሌሎቹም ወደ ሌሎች አገሮች ተበታተኑ። ቴዎፍሎስ ለፍልስጥኤም ጳጳስ እነዚህን ስደተኛ መነኮሳት በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በግል ማረፊያ እንዳይቀበላቸው መልእታክት ጻፈ።

## ስደተኞቹ መነኮሳቱ በቁስጥንጥንያ

እነዚህ ስደተኞች ከብዙ እንግልት በኋላ ቁስጥንጥንያ ደረሱ። ከዚያም ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከእግሩ ወድቀው በግፈኞች ይህን ያህል ግፍ የተፈጸመባቸውን ነፍሳት ይረዳቸው ዘንድ ተማጸኑት። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በመከራ የዛሉ አረጋውያን አባቶችን ከፊቱ አየ። በተለመደ ርኅራኄው ሁኔታቸው አሳዘነውና አለቀሰ፣ እንዲቀመጡም አላቸው። እነርሱም «ሌሎች ጳጳሳት ቴዎፍሎስን ከመፍራት የተነሣ እንዳደረጉት አንተም ምንም የማትለን ከሆነ የመጨረሻ አማራጫችን ወደ ሆነው ወደ ንጉሡ እንሄዳለን። ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን ክብር ስትል በግብጽ በገዳማችን እንኖር ዘንድ ቴዎፍሎስን ማልድልን» አሉት።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለዚህ ጉዳይ ከቴዎፍሎስ ጋር ተነጋግሮ ችግሩን መፍታት ቀላል እንደሆነ አሰበ። እነርሱንም ወደ ወንድሙ ወደ ቴዎፍሎስ ደብዳቤ ልኮ መልስ እስኪያገኝ ድረስ ለምን እንደ መጡ ለማንም እንዳይናገሩ አላቸው። ማረፊያ ቦታ ሰጣቸው፤ ሌላ አስፈላጊ ነገሮችን የሰጧቸው ግን ምዕመናን ናቸው (በተለይ ኦሊምፒያ ናት)። በዚያው ወቅት ከቴዎፍሎስ ቁስጥንጥንያ የተላኩ ካህናት ነበሩና

[37] ጳላድዮስ ምዕ. 7፤ ሶቅራጥስ 8፣7

እነዚህን ጠርቶ ተሰደው የመጡትን ገዳማውያን ያውቋቸው እንደሆነ ጠየቃቸው። እነርሱም እንደሚያውቋቸውና በገዳማዊ ሕይወታቸው የታወቁና የተመሰገኑ አባቶች መሆናቸውን፣ ነገር ግን በደል የደረሰባቸው መሆኑን በመግለጽ፣ «አባታችን ሆይ፣ በሚቻለው ነገር በርኅራኄ ተመልከታቸው» አሉት።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እነዚህን መነኮሳት በዕቅፉ ውስጥ እንዳሉ ትናንሽ ልጆቹ በመቁጠር ይቅር ይላቸውና ይቀበላቸው ዘንድ፣ እርሱም የቴዎፍሎስ ልጁና ወንድሙ መሆኑን በማውሳት ለቴዎፍሎስ በትሕትና ጻፈለት። ቴዎፍሎስ ግን አልተቀበለውም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሁኔታው ከሚያስከትለው ነገር አንፃር እነዚህን ገዳማውያን በቴዎፍሎስ ላይ ያሰቡትን ክስ እንዲተውትና እንዲታገሡ እርሱ ራሱም፣ በሌሎች ጳጳሳትም ለመናቸው። እነርሱ ግን ለዚህ ፈቃደኛ ባልሆኑ ጊዜ ወደ ቴዎፍሎስ «ግልጽ የሆነ ክስ ሊመሰርቱብህ እየተዘጋጁ ነው፣ ነገሩ በቀላሉ ማለቅ የሚችል ስለነበር አሁንም ወደ ተወሳሰበ ደረጃ ባይሄድ ጥሩ ነው። ከዚህ ውጭ ግን ጉዳዩን አንተ መልካም ነው ብለህ በምታስበው መንገድ ትይዘው ዘንድ ለአንተ እተዋለሁ፣ እኔ ከተማውን ለቀው እንዲሄዱ ላሳምናቸው አልችልምና» በማለት ላከበት። ከዚህ በኋላ እርሱ ማድረግ ያለበትን ስላደረገ ጉዳዩን ከሕሊናው አውጥቶታል።

## ቴዎፍሎስና ቅዱስ ኤጲፋንዮስ

ቴዎፍሎስ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ያሰበውን ሤራ በምሥጢር ይዞ በኦሪገናዊነት ሽፋንና ሰበብ ለመጠቀም አሰበ። ለዚህም በሕይወቱ ቅድስና የተመሰገነውንና የተከበረውን በቆጵሮስ ያለቺውን የሳላሚስን ጳጳስ ቅዱስ ኤጲፋንዮስን ከጎኑ ማሰለፍ እንደሚጠቅመው ተረዳ። በፊት አንትሮፖሞርፊስት ነው ብሎ ሲነቅፈው እንዳልነበር አሁን አስተሳሰቡ እንደ እርሱ መሆኑን የሚገልጽ የተነሳሒ ዓይነት የመግባቢያ መልእክትና የእነዚህ ስህተቶች ምንጭ የሆኑትን የኦሪገንን መጻሕፍት ላወግዝ ነው የሚል መልእክት ላከለት። ከእርሱም ጋር ወዳጅነት መሠረተ። ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የኦሪገንን መጻሕፍት ጥንቱንም በጥሩ ዓይን አያያቸውም ነበር። ስለሆነም አሁን የቴዎፍሎስን መልእክት በቀላሉና በፍጥነት ተቀበለው። ወዲያውኑ የቆጵሮስን ጳጳሳት ሰብስቦ የኦሪገንን መጻሕፍት ከማንበብ እንዲከለከሉ አለ። ለሌሎች ጳጳሳትና ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ሳይቀር የኦሪገንን መጻሕፍት እንዲያወግዙ ላከባቸው። እርሱ ቅንና ንጹሕ የቅድስና ሰው እንጂ የነገርና የሤራ ሰው





ስላልነበር ነገሮችን አቅልሎ በዚህ ዓይን አያቸው እንጂ የቴዎፍሎስ የረቀቀ ወጥመድ ውስጥ የገባና የሌሎች መሣሪያ የሆነ መሆኑን ገና አልተረዳም ነበር።

ቴዎፍሎስም አመለካከቱና ውሳኔው ምንም ይሁን በሕይወቱ ቅድስና የታወቀውንና የተከበረውን የቅዱስ ኤጲፋንዮስን ፈለግ በመከተል አደጋ እንደሌለው በማሰብ እርሱም በሥሩ ያሉ ጳጳሳትን ሰብስቦ የኦሪገንን መጻሕፍት አወገዘ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግን አሁን ጉዳዩን ያስነሣው ምንም ምክንያት ሳይኖር፣ እንዲሁም ብዙዎች የተገኙበት ታላቅ ጉባኤ ተደርጎ ሳይመከርበት በሩጫ ማንንም ማውገዝ አይገባም በማለ ጉዳዩን አዘገየው። ቴዎፍሎስም ቅዱስ ኤጲፋንዮስን ወደ ቁስጥንጥንያ ሄዶ የኦሪገንን መጻሕፍት እንዲያወግዝ ላከበት።

## ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በቁስጥንጥንያ

ቅዱስ ኤጲፋንዮስም በቴዎፍሎስ መል ክትና ጥያቄ መሠረት ከቆጵሮስ ተነሥቶ ወደ ቁስጥንጥንያ ሄደ። ቁስጥንጥንያ እንደደረሰም ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ አንድ ዲያቆን ሾመ፣ የቅዳሴ ሥርዓትም አከናወነ። ሆኖም በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት በሌላ ጳጳስ አገረ ስብከት ቄስም ሆነ ዲያቆን መሾም ሕገ ወጥ ነው።[38] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በአበው ሥርዓት መሠረት እንደሚገባው አክብሮ ይቀበለው ዘንድ ከካህናት ጋር ሆኖ ወደ እርሱ ሄደ። ኤጲፋንዮስ ግን ቴዎፍሎስን ለማስደሰት ሲል ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጋር አልሆንም፣ ከእርሱም ጋር አልገናኝም አለ።

ከዚያም ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሳያሳውቅ ወይም ሳያማክረው በቁስጥንጥንያ ያሉ ጳጳሳትን በስውር በግሉ ሰብስቦ ኦሪገንን ራሱን ሳይሆን መጻሕፍቱን ያወገዙ መሆቸውንና የውሳኔውን ግልባጭ በማሳየት እነርሱም ይህንን ውሳኔ እንዲደግፉ እንዲያጸድቁ አላቸው። አንዳንዶቹ ለቅዱስ ኤጲፋንዮስ ካላቸው አክብሮት የተነሣ ሲቀበሉት በስተቀር ብዙዎቹ ግን ከብዙ ጊዜ በፊት በሃይማኖት ያረፈውን አሁን መስደብና መርገም ተገቢ አይደለም አሉት። እንዲሁም ለቴዎፍሎስና ለአንተ ጉዳዩ ክስ አስኘቷችሁ ካልሆነ በስተቀር አሁን ይህን ውግዘትና ጉዳይ ምን አነሣው? አሉት።

[38] «ከአገረ ስብከቱ ውጭ በሆኑ ቦታዎች ክህነት ይሰጥ ዘንድ ማንም ጳጳስ አይድፈር። ነገር ግን በነዚያ ከተማዎችና ቦታዎች ላይ ሥልጣን ካለው ጳጳስ ሳያስፈቅዱ ወይም ከእርሱ ስምምነትና ዕውቅና ውጭ ክህነት ሲሰጥ ቢገኝ እርሱም፣ የሾማቸውም ይሻሩ» ይላል። ቀኖና ሐዋርያት ቁ. 35። የኒቅያ ጉባኤ ቀኖና ቁ. 16ም ተመሳሳይ አንቀጽ አለው።

እንዲህ ሆኖም እንኳ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አሁንም ለቅዱስ ኤጲፋንዮስ የነበረው አክብሮትና ፍቅር አልተለወጠም ነበር:: ስለሆነም በቤተ ክርስቲያን አብረው እንዲጸልዩና አገልግሎት እንዲፈጽሙ፣ በመንበረ ጵጵስናውም አብሮት እንዲሆን አሁንም ጋበዘው:: ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ግን የኦሪገንን መጻሕፍት ስካላወገዘና ቴዎፍሎስ ያሳደዳቸውን መነኮሳት አውግዞ ከቁስጥንጥንያ እስካላባረራቸው ድረስ ከእርሱ ጋር አብሬ አልሆንም፣ አብሬውም አልጸልይም ሲል አቋሙን ተናገረ:: በጉባኤ በአባቶች ተመክሮበት የተወሰነ ነገር በሌለበት እንዲሁ በቀረበ አሳብ ብቻ ተነሥቶ እርምጃ መውሰድ አግባብ ነው ብሎ ስላላመነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጉዳዩን ቀስ አድርጎ በትዕግሥትና በጥንቃቄ ለመያዝ ሞከረ::

በዚሁ ጉዳይ ላይ ጉባኤ ሊደረግ ሲልም የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጠላቶች ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ቀደም ብሎ ብቻውን የኦሪገንን መጻሕፍት እንዲያወግዝና ከግብጽ በቴዎፍሎስ የተሳደዱት መነኮሳትም ኦሪገናውያን በመሆናቸው የተወገዙ መሆናቸውን፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም እነርሱን ስላላሳደዳቸው እርሱን የሚነቅፍ ገለፃ ለሕዝቡ እንዲያደርግ ሁኔታዎችን አመቻቹ:: በዚህም ሁለቱን ደኅና አድርጎ ለማጣላትና በተለይም ሕዝቡ ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ያለውን ፍቅር ወደ ጥላቻ ለመቀየር ያስችለናል ብለው ስላሰቡ ነበር::

በሚቀጥለው ቀን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ይህንን ዕቅዱን በተግባር ለመፈጸም ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባ ሳለ ሤራውን የተረዳው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሊቀ ዲያቆኑን ሴራፒዮንን የሚከተለውን መልእክት አስይዞ ላከበት::

> *«ኤጲፋንዮስ ሆይ፣ ከቤተ ክርስቲያን ቀኖና ተቃራኒ የሆኑ ብዙ ነገሮችን አደረግህ፤ በመጀመሪያ በእኔ ስር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት እኔ ሳላውቅ ክህነት ሰጠህ፣ ገብተህም አገለገልህ፣ ጉባኤም አደረግህ:: በዚህም ላይ ልቀበልህ ስል እምቢ አልህ፣ ወደ እኛ ትመጣ ዘንድ ብትጋበዝም አልተቀበልህም:: ሁሉንም ነገር በራስህ ውሳኔ ታደርጋለህ:: አሁንም ያደረግከውና ልታደርገው ያሰብከው ነገር ሊያመጣ የሚችለው ሕዝባዊ ቁጣና ሁከት ሊያስከትል ለሚችለው ነገር ተጠያቂ እንዳትሆንና ራስህም አደጋ ላይ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ::»*

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ይህንን ወቀሳና ተግሣፅ ሲሰማ ወዲያውኑ ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ ወደ ቆጵሮስ ለመመለስ ጉዞ ጀመረ:: ቴዎፍሎስ ያሳደዳቸው መነኮሳትም ወደ እርሱ መጥተው *«አባት ሆይ፣ የእኛን ጽሑፎች ወይም የደቀ መዛሙርቶቻችንን አንብበህ ታውቅ ከሆነ*





*በአክብሮት ልንጠይቅህ መጣን»* አሉት:: እርሱም ይህን እንዳላደረገና እነርሱንም እንደማያውቃቸው በመለስ ጊዜ *«የእኛን አስተሳሰብ ሳታውቅ እንዴት መናፍቃን ናቸው ልትለን ቻልህ?»* አሉት:: እርሱም ስለ እነርሱ ከሌሎች በሰማው ነገር ላይ ተመሥርቶ እንደሆነ ሲነግራቸው እነርሱ ግን የእርሱን ጽሑፎች እንደሚያነቡና ትምህርቶቹን የሚነቅፉትን እንደሚቃወሙ ገልጸው፣ *«አንድን ሰው በሌለበት፣ ያውም ምንም እርግጠኛ ማስረጃ ሳይኖርህ ማውገዝ ይገባሃልን?»* አሉት:: እርሱም ነገሩ ስላሳመነው የድርጊቱን ምንነት ተረዳው::

አንዳንዶች ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ጉዞውን ሊጀምር ሲል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን «በመንበርህ እንዳለህ አትሞትም» እንዳለውና በዚህ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም «ካልክስ አንተም ከመንበረ ጵጵስናህ አትደርስም» እንዳለው ይናገራሉ:: በርግጥ ሁለቱም ያሉት ተፈጽሟል፤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ታሪኩን ወደፊት እንደምናገኘው ከመንበሩ ተሰዷል፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስም የተመለሰ ሳለ ሳይደርስ በመንገድ (በባሕር) ላይ ዐርፏል::[39]

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በሕይወቱ ቅድስና የተከበረ፣ በኦርቶዶክሳዊ ምንቱና ጠበቃነቱ የተመሰገነ ታላቅ አባት ነው:: ሆኖም ኑፋቄን ከመጸየፍና ለሃይማኖት ካለው ቅናት የተነሣ አልፎ አልፎ የነገረኞችና የመሠሪዎች መጠቀሚያ የመሆን አደጋም ገጥሞታል:: ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ወጣ ያለ ተግባርም ለመፈጸም ያነሣሳው የነበረው ይኸው ጠባዩ ነበር:: በኋላ ሁኔታውን ተገንዝቦ እውነትና ንጋት እየጠራ እስኪሄድለት ድረስ ቴዎፍሎስ የነገረውን እንዳለ በመቀበሉ ምክንያት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን በትክክል ሳይረዳው ቆይቷል:: ኋላ ግን ሁኔታዎችን ሲረዳ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ያደረጋቸውን ስህተቶች ዘርዝሮ ሲነግረው ቴዎፍሎስና አውዶክስያ መጠቀሚያ መሣሪያቸው ያደረጉት መሆኑ ገብቶታል:: በዚህም ወዲያውኑ ቁስጥንጥንያን ለቅቆ ለመመለስ ጉዞ ጀምሯል::

## 6. የመጀመሪያ ስደት (ግዞት):- ቴዎፍሎስ ዘ ስክንድርያ እና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስደተኞቹን መነኮሳት በርኅራኄና በአክብሮት ቢቀበላቸውም ከቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት እንዲሳተፉ ግን አልፈቀደላቸውም:: ምክንያቱም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት

[39] ሶዞ. 6፥12 ና 14 ፤ ሶቅ. 8፥11-15

በአንዱ ሀገረ ስብከት ጳጳስ የተሳደደና የተወነጀለ ሰው ጉዳዩ በሌላ ጉባኤ ታይቶ ሳይወሰን ከምሥጢራት እንዲካፈል ማድረግ አይገባም። ስለ እግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ ያላቸው እምነትና አስተሳሰብ፣ በአጠቃላይ እምነታቸው ኦርቶዶክሳዊ በመሆኑ ይቀበላቸው ዘንድ፤ ኦርቶዶክሳዊነታቸውን የማያምንበት ከሆነ ደግሞ በዚሁ ጉዳይ የሚከሣቸው ሰው ይልክ ዘንድ ላከበት። ቴዎፍሎስ ግን ሁሉንም ነገር አልቀበልም አለ።

ቴዎፍሎስ በመለዘብ ፋንታ የባሰበት እንደሄደ የተረዱት ስደተኞቹ መነኮሳት ግን የደረሰባቸውን በደል፣ እንዲሁም ቴዎፍሎስ ፈጽሟል ያሉትን በጣም ብዙና ከባድ ወንጀሎችን በመዘርዘር ከሰሱት። ከዚያም ወደ ንጉሡና ወደ ንግሥቲቱ ሄደው ክሳቸውን ለመንግሥት አቀረቡ። ለእውነትና ለፍትሕ ስለሚጠነቀቅና ማንንም ስለማይፈራ የእርሱ መኖር ፍትሐዊ ፍርድ ለማግኘት ይጠቅመናል ብለው ስላሰቡ ጉዳያቸው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ንጉሡ ባሉበት እንዲታይላቸው ጠየቁ። በዚህ ጊዜ ቴዎፍሎስ ፈቃደኛ ቢሆንም ባይሆንም ወደ ቁስጥንጥንያ እንዲመጣና ስለተከሠሠበት ጉዳይ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሚመራ ሲኖዶስ ፊት ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ የሚል ትእዛዝ ታዘዘ። ይህንም ለማስፈጸም አንድ የጦር ኃይል አዛዥ ቴዎፍሎስን ለማምጣት ወደ እስክንድርያ ተላከ።

በዚህ ጊዜ ከላይ እንደተገለጸው ቴዎፍሎስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለመበቀል ቆርጦ ተነሣ። ሆኖም ይህን አሳቡን በሚቻለው መጠን በስውር ደብቆ ያዘ። ለዚህ ዓላማው ማስፈጸሚያ ይሆነው ዘንድ በኦሪገናዊነት ሽፋን ለመጠቀም አሰበ። ለዚህም ለየጳጳሳቱ የኦሪገንን መጻሕፍት የሚያወግዝ መልእክት ላከ። በዚህ ሽፋንም የሚቻለውን ያህል ከጎኑ የሚሰለፍ ለማግኘት ደፋ ቀና ይል ጀመር። የቆጵሮሱን ቅዱስ ኤጲፋንዮስን በፊት አንትሮፖሞርፌስት ነው እያለ ሲነቅፈው እንዳልነበር አሁን እርሱን ወዳጁ አድርጎ ከጎኑ ለማሰለፍ ወሰነ።

ቴዎፍሎስም በወንጀል ተከሶ ብቻውን እንዲቀርብ የታዘዘ ቢሆንም እርሱ ግን ብቻውን ሳይሆን 29 የቅርብ ደጋፊዎቹ የሆኑ ግብጻውያን ጳጳሳትን አስከትሎ ከግብጽ ብዙ እጅ መንሻና የተለያዩ ስጦታዎችን በመያዝ ቁስጥንጥንያ ደረሰ። ቴዎፍሎስ በቁስጥንጥንያ በቤተ መንግሥትና በዙሪያው ያለውን ሁኔታ የሚነግሩት መገብተ ዜናና ተወካዮች በቋሚነት ነበሩት። ስለሆነም አሁን በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና በቤተ መንግሥት ሹማምንት በተለይም ከንግሥቲቱ አውዶክስያ ጋር ያለውን የሻከረ ግንኙነት ያውቅ ነበር። ስለዚህ ይህንን ሁኔታ ሊጠቀምበት ወሰነ።





ቁስጥንጥንያ ከደረሰ ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ሳምንታት ያህል በአባቶች ጳጳሳት መካከል እንዳለው ልማድ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ማረፊያና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ አዘጋጅቶ ሊቀበለው ቢፈልግም እርሱ ግን ከቤተ መንግሥት በተሰጠው ቤት ውስጥ ተቀመጠ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ደግሞ እንዲመጣ ቢማልደውም ግብዣውን አልተቀበለም፤ አላነጋገረውምም፤ ወደ ቤተ ክርስቲያንም ድርሽ አላለም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ከመንበሩ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ዓለም ሕይወትም የሚያሳድድበትን ነገር በመሥራት ቀንና ሌሊት ተጠምዶ ነበር። ለዚህ ዓላማው መሳካትም የገንዘብ ባሪያዎች የሆኑትን በገንዘብ፣ የውዳሴ ከንቱና የክብር ሱስ የያዛቸውን በቁልምጫና በውዳሴ፣ ሹመት ለሚፈልጉት የሹመት ተስፋ፣ ሆዳሞችን በጥሩ ምግብና መጠጥ፣ በአጠቃላይ ልዩ ልዩ ተስፋ በመስጠትና በደካማ ጎናቸው በመግባት ደጋፊዎችን መግዛት ጀመረ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከቤተ ክርስቲያን በታላቅ ወንጀል (በግድያና በዝሙት) ምክንያት ያባረራቸውን ሁለት ዲያቆናት በእርሱ ላይ ውንጀላ ካቀረቡ ወደ ቦታቸው እንደሚመልሳቸው ቃል ገባላቸው። እነርሱም ራሱ ቴዎፍሎስ ያስጠናቸውን ውንጀላ ስላቀረቡ ሤራው ሰምሮለት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከተሳደደ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሶ የቀደመ ሥራቸውንና ኃላፊነታቸውን በመስጠት ውለታቸውን መልሷል። ሌሎች ለሹመት፣ ለሥልጣንና ለውዳሴ ከንቱ ተገዢ የነበሩ ካህናትንም ጥቂቶችን በመረቡ ለማጥመድ ቻለ።

ቴዎፍሎስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለመበቀል የማይፈነቅለው ድንጋይ ባልነበረበት በዚህ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በአጠቃላይ ስለ ገንዘብ መውደድና የሴቶችን በአልባሳትና በጫማ ጌጥ ያላቸውን ሥርዓት ያጣና የተበላሸ ሁኔታ በተመለከተ ብዙ ጊዜም እንደሚያስተምረው በቤተ ክርስቲያን መድረክ አስተማረ። ጠላቶቹ በእርሱ ላይ ወንጀል በሚፈልጉበት ጊዜ ስለነበር ትምህርቱ እርሷን ለመስበክ የተነገረ እንደሆነ ያስመስሉ እነ ሴቬሪያንና መሰሎቹ ለአውዶክስያ ነገሯት። እንዲሁም የአንዲትን ባሏ የሞተባት ሴት የተክል ቦታ በመቀማቷ ምክንያት እስካልመለሰችላት ድረስ ከቤተ ክርስቲያን እንዳትገባ ያወገዛት በዚሁ ሰሞን ነው። በዚህ ሁሉ እርሷ ዋና ጠላቱ ሆና ተነሣች። የቴዎፍሎስ የበቀል ምኞት የአውዶክስያን ትልቅ እጅ አገኘ።

በብዙ ወንጀል ተከሶ በግዴታ ወደ ቁስጥንጥንያ የመጣው ቴዎፍሎስ በገንዘብና በልዩ ልዩ ማታለያ ሰዎችን በመግዛትና እንዲሁም በእነ አውዶክስያ ሞግዚትነት በአንድ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከሳሽ ሆኖ ተነሣ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ ተባረሩት መነኮሳት ሲማልደው በሌላው አገረ ስብከት ጉዳይ ገባህ ብሎ የተቆጣው ቴዎፍሎስ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አገረ ስብከት ብቻ ካይሆን መንበረ ጵጵስናው ባለበት ከተማ ዋና ከሳሽም ዳኛም ሆኖ ቀረበ። አውዶክስያ፣ ቴዎፍሎስና ሌሎች

ምግባረ ብልሹና የሹማምንትን እጅ መሳስ የሚወዱ፣ እንዲሁም ለሹመትና ለሥልጣን የሚቋምጡ ካህናት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ የጠላትነት ኅብረት ፈጠሩ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሃይማኖትና በምግባር ጉድለት ምክንያት የሻራቸው ጳጳሳት የነበሩም በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ላይ ሲሆን እንደሚታየው ዋና ከሳሾቹ ሆነው ተነሡ። እነዚህ የጠላትነት ምክንያታቸውና ዓላማቸው የተለያየ ቢሆንም ሁሉም ግን በእርሱ ላይ በነበራቸው ጠላትነት ለጊዜው አንድ ሆኑ።

ቴዎፍሎስ ከግብጽ አስከትሏቸው ከመጣቸው 29 ጳጳሳትና ከዚያው ከቁስጥንጥንያ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን መንበረ ጵጵስና ለመያዝ ከነገሩና ክፋት ከተጠናወታቸው ጳጳሳት ጋር በመሆን ውሳኔውና ዓላማው አስቀድሞ የማታወቅ የሤራና የሐሰት «ሲኖዶስ» ለመሰብሰብ ሽር ጉድ ማለት ጀመረ። በአንድ ጊዜ ራሱ ከሳሽ፣ ራሱ ዳኛ በመሆን በንግሥቲቱ በአውዶክስያ አስተባባሪነት እንዲሁም ከክርስትና መንገድ ባፈነገጠ ሕይወታቸው ምክንያት የእርሱ የቅድስና መንገድና ትምህርት ያልተመቻቸው ካህናት በአንድነት ተባብረው በኬልቄዶን ዳርቻ ባለ አክ በሚባል ቦታ ድብቅ ስብሰባ አደረጉ። ይህ ስብሰባ የአክ ጉባኤ[40] የተባለ ይጠራል።

በተለይም ደግሞ ሲሪኖስ የሚባለውና የኬልቄዶን ጳጳስ የነበረው፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን በሁሉም ነገር ጥፋተኛና የመጨረሻ ወንጀለኛ እንደሆነ እያስመሰለ ለዐመፀኛው ጉባኤ ይገልጽ ነበር። ሆኖም ከዚያው ከጉባኤው ሳይወጣ ከተሰብሳቢዎቹ አንዱ ባጋጣሚ ሳያየው እግሩን ስለረገጠው በመታመሙ ከሌሎቹ ከሳሾች ጋር ወደ ቁስጥንጥንያ መሄድ ስላልቻለ እዚያው ኬልቄዶን ቀርቷል።

እነዚህ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት የተውጣጡ የጽድቅ ጠላቶች ከእስክንድርያ ተነሥቶ ለማሳደድ በመጣው በቴዎፍሎስ መሪነት ሤራ ጎንጉነው ንግሥቲቱን ኤልዛቤል ብሎ ሰድቧታል፣ ካህናትን በድሏል ወዘተ የሚሉ የሐሰትና የፈጠራ ክሶችን መስርተው፣ ራሳቸው ከሳሽ፣ ራሳቸው ፈራጅ ሆነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን በሌለበት ከመንበሩ ወርዶ እንዲሰደድና ሕይወቱን ሙሉ በግዞት እንዲኖር ፈረዱበት። በተለይም «ክህደት ፈጽሟል» ያሉት ማለትም ንግሥቲቱን ሰድቧል ያሉት በሞት ሲቀጣ ለማየት ጓጉተው ስለነበር ነው።

በቀሪ የሕይወት ዘመኑ በግዞት እንዲኖር የመወሰኑ ጉዳይ እንደተሰማ የሕዝቡ ቁጣ ሊገለጽ በሚያስቸግር ሁኔታ ገነፈለ። ከእርሱ አንደበት አንድ

[40] (Synod of Oak)። በ451 ዓ.ም. ሁለት ባሕርይ ባዮችና የንጉሥ ፈቃድ ፈጻሚዎች ተሰብስበው በርጉም ልዮን መልእክት ተዋሕዶን የማይቀበሉ መሆናቸውን በማወጅ ከኦርቶዶክሳውያን የተለዩበትን ስብሰባ ያደረጉትም በዚሁ በኬልቄዶን ነው።





ቃል እንኳ ቢወጣ ኖሮ ሕዝቡ ከፍተኛ ብጥብጥና ሁከት ይፈጥር ነበር። እርሱ ግን ብጥብጥ እንዳይነሣ በማሰብ ራሱን በጸጥታ ለንጉሡ ወታደሮች አሳልፎ ሰጠ። እነርሱም በሌሊት ሰድሚ ልኩን በስደት እንዲኖር ወደ ተፈረደበት ግዞት ለመውሰድ በመርከብ አሳፈሩት። ቴዎፍሎስ ቁስጥንጥንያ ከተማ በድል አድራጊነት መንፈስ ገባ፤ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቅርብ ሰዎችና ረዳቶች በሆኑት ላይ የበቀል በትር ማሳረፍ ጀመረ።

ቁስጥንጥንያ ሲገባ በቤተ መንግሥት የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለመበቀል ከበቂ በላይ ሆኖ ስላገኘው ቀደም አድርጎ ለመበቀል ሰበብ ይሆነኛል ብሎ ሲዘጋጅበትና ሌሎችንም በወጥመዱ ሲያስገባበት የነበረውን የኦሪገናዊነት ጉዳይ አርግፎ ተወው። ዋናው ጉዳይ የበቀል ዓላማው መሳካቱ እንጂ ጥንቱንም ጉዳዩ ኦሪገናዊነት አልነበረምና። በኦሪገናዊነት ሰበብ ያባረራቸውን መነኮሳትም አጥፍታችኋል፣ ንስሐ ግቡ፣ ወይም አሳባችሁን ተው የሚል ምንም ነገር ሳይል እንዲሁ ታረቃቸው። የኦሪገንን መጽሐፍም ተቀብሎ ማንበብ ጀመረ። በኦሪገን ሰበብ ያን ሁሉ ሁከት ሲፈጥርና ብዙ ነገር ሲያደርግ የነበረው ሰው አሁን የእርሱን መጽሐፍ ተቀብሎ በማንበቡ ተገርመው «እንዴት የኦሪገን መጽሐፍ ታነባለህ?» ሲሉት «ጽጌረዳውን ከእሾሁ መሀል መምረጥ ችላለሁ» አላቸው።[41] ስለዚህ የመጀመሪያው ኦሪገናዊ ውዝግብ መነሻ ምክንያት የኦሪገን አስተሳሰብ ያለው ሃይማኖታዊ ስህተት ወይም ችግር ሳይሆን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለመበቀል ሲል ቴዎፍሎስ የፈጠረው ውዝግብ ነበር። ሆኖም ከላይ እንደተገለጸው ቴዎፍሎስ ያልጠበቀውን አቋራጭና የተሻለ መንገድ ሲያገኝ ይህንን ውጤታማነቱ አስተማማኝ ያልነበረ ዘዴ አርግፎ ትቶታል።

ሕዝቡ ግን ቤተ መንግሥቱን በቁጣ በመክበብ በንጉሡና በንግሥቲቱ ላይ እንዲሁም በአክ ጉባኤ ላይ የስድብና የቁጣ ቃላትን ይገልጽ ጀመር። በተለይም ደግሞ የሤራው ጠንሳሾች ተደርገው በተወሰዱት በቴዎፍሎስና በሴቬሪያን ላይ የሕዝቡ ቁጣ በጣም ገነፈለ። ሴቬሪያንም በዚህ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሊሳደድ የሚገባው መሆኑን ለሕዝቡ ለማሳመን በቤተ ክርስቲያን ማስተማር ጀመረ። ይህም የሕዝቡን ቁጣ ከቁጥጥር ውጭ ያደረገው ሄደ። የሚወዱት አባታቸው እንዲመለስላቸው አጥብቀው በኃይል መጠየቅ ቀጠሉ። ከዚህ የተነሣ የቁስጥንጥንያ ከተማ በከፍተኛ ሁከት ውስጥ ወደቀች።

በዚህ ከቁጥጥር የወጣ የሕዝብ ቁጣ የተነሣ ንጉሡ አርቃዴዎስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለመመለስ አሰበ። በሚቀጥለው ቀን ሌሊት ላይ ከተማዋን ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ ይንጣት ጀመር። በተለይም የመሬት መንቀጥቀጡ በአውዶክስያ ቤትና መኝታ ክፍል በተለየ ሁኔታ በጣም

[41] ሶቅ. 6፣17

ኃይለኛና እጅግ አስፈሪ ነበር:: አውዶክስያም ይህ መዓት በምን ምክንያት እንደመጣባት ሥራዋን ታውቃለችና ፈርታና ተደናግጣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን እንዲመለስ እንዲጠራውና በዚህም የእግዚአብሔርን ቁጣ ያርቅላት ዘንድ ንጉሡን ተማጸነች::[42]

እርሱን ለመመለስም በፍጹም ተዋርዶ ደጅ የሚጠይቁና እንዲመለስ የሚሽመግሉ መልእክተኞች ተላኩ:: እየተመለሰ ሳለም ከመንበሩ ወርዶ እንዲሳደድ የተወሰነበት ውሳኔ ሕገ ወጥነት በሌላ ብዙ ጳጳሳት በተገኙበት ትክክለኛ ሲኖዶስ እስካልተወሰነና ጥፋተኛ አለመሆኔ እስካልተገለጸ ድረስ ወደ ከተማውና ወደ መንበሬ አልመለስም አለ:: ሆኖም እርሱ በሚዘገይበት በእያንዳንዷ ቅጽበት ሕዝቡ በንጉሡንና በንግሥቲቱ ላይ የሚያሳየው ቁጣ እየተባባሰ ስለሄደ ንጉሡ ቶሎ እንዲመጣ ለመነው:: እርሱም የሕዝቡን ቁጣ ለማብረድ ሲል ለመግባት ተገደደ::

ብዙ መርከቦች ችቦ እያበሩ የደስታ ዝማሬ እያሰሙ ተቀበሉት:: ሕዝቡም የተፈጠረውን ክሥተት በቅመለከተ ያዘጋጁቻቸውን መዝሙሮች እየዘመሩ፣ መብራቶችን እያበሩ እጅግ ልዩ በሆነ ደስታ እና ሐሴት በዕልልታ እና በዝማሬ የሚወዱትን አባታቸውን ተቀበሉት:: በሩን ሲያልፍ ምዕመናን ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ከፍ አድርገው ተሸክመው ወስደው ከመንበረ ጵጵስናው ላይ አስቀመጡት:: ለተሰበሰበው ሁሉ ንግግር እንዲያደርግ ግድ ተባለ::[43] የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ድል አድራጊነት ሙሉና ፍጹም ነበር:: እርሱ በግፍ የተደረገበትን የስደት ውሳኔ በጸጋ ቢቀበልም እግዚአብሔር ግን በተአምራት ንጽሕናውንና ቅድስናውን በመግለጥ ጠላቶቹን አሳፈረለት:: የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መመለስ በራሱ ለአውዶክስያ ትልቅ ሽንፈትና ሀፍረት ነበር::

ይህን ሁኔታ ያየው ቴዎፍሎስ ሤራው እንደከሸፈበት ስለተረዳ በቁስጥንጥንያ መቆየት አደገኛ ሆኖ ስለተሰማው አብረውት ከመጡት ጋር ወደ እስክንድርያ በሌሊት ሾልኮ በመጥፋት ሕይወቱን አተረፈ:: በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ ባደረሰው ግፍ በተለይም ደግሞ ቴዎፍሎስ የፈጠራቸውን ክሶች ሕዝቡ ሲሰማ በጣም ከመበሳጨቱና ከመናደዱ የተነሣ ቢያገኙት በባሕር ሊያሰጥሙት እየፈለጉት ነበር::

[42] አውዶክስያ ራሷ እዲመለስ በመማፀን «ምን እየሆነ እንዳለ አላውቅም፤ ልጆቼን ማጥመቅህን ልረሳ አልችልም» ብላ ጽፋለች::

[43] በዚህ ጊዜ ባደረገው ንግግር ጻስ ቄሚል ሥዕላዊ አገላለጽ የግብጹ ንጉሥ የአብርሃምን ሚስት ሣራን ለመንጠቅ እንደሞከረው ቴዎፍሉስም በቤተ ክርስቲያን ላይ ችግር ለመፍጠር ሥራዬ ብሎ የተነሣ መሆኑን ገለጸ፤ ሕዝቡንም ስለ ሃይማኖታዊ ቅናታቸውና ላሳዩት መንፈስ ጠንካራነት አመሰገነ:: ንጉሡንና ንግሥቲቱንም እንዲመለስ ላሳዩት ቀናነት አመሰገነ:: በንግግሩና በመመለሱ ሕዝቡ በጣም ከመደሰቱ የተነሣ በተፈጠረው ከመጠን ያለፈ የደስታ ስሜት ንግግሩን ሳይጨርስ ለማቋረጥ ተገዷል::





የእርሱ ጠላቶች የሆኑት እነ ሴቬሪያንም ቁስጥንጥንያ ለሕይወታቸው አስጊ ሆና ስለታየቻቸው ከተማዋን ጥለው ጠፉ::

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ስደቱ የተሰማውን ሲሪያኮስ ለሚባል ጳጳስ በላከለት መልእክት ላይ እንዲህ ገልጾታል:-

> *«ከከተማው በተወሰድኩ ጊዜ ምንም አልተጨነኩም፤ ነገር ግን ለራሴ እንዲህ አልሁ:- ንግሥቲቱ ልታሳድደኝ ከፈለገች ምድርና ምላዋ ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፤ በመጋዝ ልትሰነጥቀኝ ብትፈልግ ከፊቴ ነቢዩ ኢሳይያስ አርአያ አለኝ፤ ወደ ውቅያኖስ ልታሰጥመኝ ብትፈልግ ዮናስን አስባለሁ፤ ወደ እሳት ብጣል ሦስቱ ወጣቶች ይህንኑ ተቀብለዋል፤ ለአራዊት ብሰጥ በአናብስት ጉድጓድ የተጣለ ዳንኤልን አስታውሳለሁ፤ በድንጋይ እንድወገር ከፈለገች በፊቴ ቀዳሜ ሰማዕት ስጢፋኖስን አያለሁ:: ራሴን ከፈለገች እንደ ፈለገች ታድርግ፤ ዮሐንስ መጥምቅ በፊቴ ያበራል:: ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጣሁ፤ ይህንን ዓለምም ራቁቴን እተወዋለሁ:: 'ሰዎችን ደስ የማሰኝ ከሆነ የክርስቶስ አገልጋይ አልሆንሁም' ሲል ቅዱስ ጳዉሎስ ያስታውሰኛል::»*

## 7. ሁለተኛ ግዞት፣ 404 ዓ. ም.

ከተቃጣበት ስደት ከተመለሰ በኋላ ጠፍቶ እንደተገኘ ዕንቁ በሕዝቡ ዘንድ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ተወዳጅና ተናፋቂ ሆነ:: በእግዚአብሔር ኃይል በልዩ ተአምር የተመለሰው ፓትርያርክ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና የተጸጸተችው ንግሥት ለጊዜው የታረቁ መሰሉ:: አውዶክስያም ጥፋቷን ለማካካስ ለሁለት ወራት ያህል ደፋ ቀና አለች:: ነገር ግን ክፋዎች ባሉበት ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ይህ ድል ዘላቂ ሊሆን አልቻለም:: ለሁለት ወራት ያህል በመንበረ ጵጵስናው በተለመደው ደገኛ ተግባሩ እንደቀየ የአውዶክስያና የአሽንጉሊቶቸዋ መሠሪነት እንደገና አገረሸበት:: ከስደቱ እንዲመለስ እንድትማጸነው ያስገደዳት ጭንቀትና ፍርሃት ሲለቃት እንደ ፈርዖን ጥላቻዋና የበቀል ስሜቷ እንደገና አገረሸባት:: አውዶክስያ መልከ መልካም፣ ነገር የማትረሳ፣ ገንዘብ ወዳጅ፣ በቀለኛ፣ ሤረኛ፣ ማዘዝና እስከ መመለክ የሚደርስ መከበር የምትወድ፣ ምኞቷ ሁሉ ሥጋዊ የሆነች ሴት ነበረች::

የሮም ግዛት ንግሥት መሆን አልበቃ ብሏት ቄሣሮቹ (ነገሥታቱ) ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት ለነበሩት ጣዖታውያን ቄሣሮችና ለቤተሰቦቻቸው ይደረግ እንደ ነበረው ልማድ የአማልክትነት ክብር ፈለገች:: ይህንን ፍላጎቷን እውን ለማድረግ ከብር የተሠራ የእርሷን ምስል የያዘ ትልቅ ሀውልት አሠር ሕዝቡ ያከብረው ዘንድ ጫጫ እና

ሁኑ በተምሳበት ዓይነት የጣዖት በዓል አከባበር ሥርዓት በመስከረም 403 ዓ.ም. በቅድስት ሶፍያ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ባለው አደባባይ እንዲቆም አደረገች:: በሀውልቱ ፊትም ሕዝባዊ ጨዋታዎችና ትርዒቶች ይደረጉ ነበር:: ይህ ድርጊት በቤተ ክርስቲያን ይደረግ የነበረውን አገልግሎት የሚያውክና የሚረብሽ ሆነ:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ይህ ድርጊት በቤተ ክርስቲያን ላይ ንቀትን ማሳየት ነው በማለት ለሕዝቡ ተናገረ::


ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መጥምቁ ዮሐንስ ሰማዕትነት በተቀበለበት ቀን መታሰቢያ በዓል ላይ በዚህ ከክርስትና እምነትም ሆነ ስነ ምግባር ጋር ተቃራኒ በሆነ የጣዖታዊ ድርጊት ላይ የተገኙትን ሁሉ:- ሕዝቡንም፣ ባለ ሥልጣናቱንም፣ እንዲሁም የድርጊቱን ዋና ባለቤት ራሷን ንግሥቲቱን - የድርጊቱን ተገቢ አለመሆን የሚገልጽ እውነተኛ ቁጣውንና ተግሣፁን ተናገረ::

በዚህ ስብከቱ መሀል ላይ ሁኔታው እጅግ ስላበሳጨው «አሁንም ሄሮድያዳ በቁጣ ላይ ናት፣ አሁንም እየዘፈነች ነው፣ አሁንም የዮሐንስን ራስ በወጭት ትፈልጋለች» አለ ይባላል:: ዕለቱ ዮሐንስ መጥምቅ በሄሮድያዳ ልጅ ዘፈን ምክንያት ሄሮድያዳ ልጇን መክራ የዮሐንስ መጥምቅ ራስ በወኅኒ ቤት ተቆርጦ በወጭት የተሰጠበት ቀን መሆኑን ልብ ይሏል:: በርግጥ እርሱ በቀጥታ ይህንን ይበል ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቃል ይናገር አጠራጣሪ ነው:: ብዙዎች የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምሁራን ግን ይህ ከአፈወርቅ ሰብእናና ማንነት ጋር የማይሄድ መሆኑን በማሳየት ጠላቶቹ እርሱን ለመወንጀል ይጠቀሙበት ብለው የፈጠሩት እንጂ እርሱ ቃል በቃል እንዲህ ያላለ መሆኑን ይገልፃሉ::

ሆኖም ነገር አቀብለው ለመወደድ ሲቋምጡ የነበሩ ሆድ አምላኩዎች መግቢያ አገኙና ነገሩን ያጋነኑና ያገዘፉ (በተለይም እነ ሴቬሪያን) ለአውዶክስያ እንዲህ አለሽ ብለው ነገሯት:: እርሷም ጥንቱንም በመጀመሪያ መመለሱ የተሰማትን ኀፍረትና ሽንፈት ለመበቀል የምትፈልገው ሰበብ ብቻ ስለነበር ይህን መግቢያ ስታገኝ ንጉሡን እንዲበቀልላት ጠየቀች:: በዚህ መንግሥታዊና ጳጳሳዊ ውዝግብ ቤተ መንግሥቱ ጊዜያዊ የግፍ ድል ሲያገኝ ጳጳሳዊው ደግሞ ሞራላዊና ዘለዓለማዊ ድል አገኘ:: አውዶክስያም የልብ አድራሿን ቴዎፍሎስንና እርሱን መሰሎችን እንደገና እንዲሰበሰቡና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን እንዲሽሩትና እንዲያሳድዱት ጠራቻቸው:: በዚህ ጊዜ የአፈወርቅ ጠላቶች ሥጋ እንዳየ ንስር ከየአቅጣጫው በፍጥነት ተሰባሰቡ::







የቅድስት ሶፍያ ቤተ ክርስቲያን[44]

ለደኅንነቱ ጠንቃቃ የሆነው ቴዎፍሎስ ግን በመጀመሪያው የማሳደድ ተግባሩ በቁስጥንጥንያ በአካል በመገኘቱ ከሕዝቡ ሊደርስበት የነበረውን ዓይነት አደጋ እንደገና እንዲደርስበት አልፈለገም:: ስለሆነም ከማያሰጋው ቦታ ከዚያው ከእስክንድርያ ሆኖ ክርቀት ሴራውን በማቀነባበር ይመራ ጀመር:: ቴዎፍሎስ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ የሠራው የመጀመሪያው ግፍ በእግዚአብሔር ኃይል ስለከሸፈበት፣ አሁን ሁለተኛ የሚከስበት ደግሞ ሌላ ምክንያት ስላጣ አሁን እዚያው እስክንድርያ ሆኖ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በ341 ዓ.ም. በአንጾኪያ ከተወሰነው ቀኖና ተቃራኒ በሆነ መልኩ ከመንበሩ እንዲሳደድ ከተፈረደበት በኋላ ወደ መንበሩ በመመለሱ ሊሳደድ ይገባዋል ብሎ ጻፈ::

[44] የቅድስት ሶፍያ ቤተ ክርስቲያን (Church of Eternal Wisdom - Hagia Sophia) ዛሬ በሚያሳዝን ሁኔታ በኢስታንቡል ከተማ (በቀድሞዋ ቁስጥንጥንያ) በእስላሞች ሚናሬት ተከቧል። ቤተ ክርስቲያኑ መጀመሪያ የተሠራው በ360 ዓ.ም. በቆስጠንጢኖስ 2ኛ (337-361) ነበር:: በ404 ዓ.ም. በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስደት ጊዜ ከተቃጠለ በኋላ እንደገና ቢሠራም አሁንም መልሶ በመቃጠሉ በ532 ዓ.ም ንጉሥ ጁስቲኒያን በብዙ ገንዘብ ድንቅ አድርጎ አሠራው:: በ1453 ዓ.ም. ቱርኮች ቁስጥንጥንያን ሲወሯት ይህ ቤተ ክርስቲያን መስጊድ ተደርጎ ለብዙ ጊዜ ከኖረ በኋላ በ1935 ዓ.ም መስጊድነቱ ቀርቶ ሙዚየም ሆኗል:: ይህም ቱርክ ከአውሮፓውያን ጋር ለመቀራረብና ለመግባባት እንዲረዳት የወሰደችው እርምጃ እንደሆነ ይነገራል:: አሁን ወደ ቤተ ክርስቲያንነቱ ለማስመለስ እንቅስቃሴዎች አሉ::

በጣም የሚገርመው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «አፍርሷል» ተብሎ በቴዎፍሎስ የተጠቀሰበት ቀኖናና ቀኖናውን የወሰነው የአንጾኪያ «ሲኖዶስ» አርዮሳውያንና መንፈቀ አርዮሳውያን «ጳጳሳት» ታላቁንና ደገኛውን የሃይማኖት አባት 20ኛውን የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስን ከመንበሩ ለማሳደድ ሲሉ የወሰኑት ቀኖና ነው::

ይህ የአንጾኪያ ቀኖና አንቀጽ 20 እንዲህ ይላል:- «በትክክለኛም ምክንያት ይሁን በግፍ ከመንበሩ እንዲወርድ ከተወሰነበት በኋላ ያው ያሳደደው ሲኖዶስ ሳይመልሰው ወደ መንበሩ የተመለሰ ማንኛውም ጳጳስ መጀመሪያ በተወሰነበት መሠረት ስደቱ የጸና ነው፣ አቤቱታ የማቅረብና ጉዳዩ እንዲታይለት የማድረግ መብትም አይኖረውም፣ እስከ መጨረሻው ስደቱ ይጸናበታል እንጂ» የሚል ነው:: ይህ «ቀኖና» አርዮሳውያን የንጉሡን ድጋፍ አግኝተው በነበረበት ጊዜ ቅዱስ አትናቴዎስን ለማሳደድ ይችሉ ዘንድ በልኩ የሰፉት የማሳደጃ «ቀኖና» ነበር:: ይህ ውሳኔ ሕገ ወጥ በመሆኑና በአርዮሳውያን የተደነገገ ስለሆነ ከመጀመሪያውም አይሠራም፣ ተፈጻሚነትም የለውም ነበር:: ይኸው የአርዮሳውያን ቀኖና ኦርቶዶክሳውያን አባቶች በሳርዴቅ (የዛሬዋ ሶፍያ፣ ቡልጋሪያ፣ በ343ዓ.ም) ባደገሩት ሲኖዶስ ተሽሯል:: ቴዎፍሎስ ጠላቱን ለማጥቃት የማይጠቀመው መንገድ አልነበረምና በሃይማኖቱ ኦርቶዶክሳዊ ሆኖ ሳለ ለማጥቃት ሲል ብቻ መንገድ ቢያጣ የአርዮሳውያንን ቀኖና ጠቀሰ::

በግርጥ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በመጀመሪያ ከተፈረደበት ስደት እንዲመለስ ሲጠራ ጠላቶቹ ወደፊት ይህንን ክፍተት ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ስለሚያውቅ ከመንበሩ እንዲሳደድ የወሰነበት የእነ ቴዎፍሎስ «ሲኖዶስ» አሁን መመለሱን ስካልወሰነለት ድረስ ወደ ቤተ ክርስቲያን አልገባም ብሎ ነበር:: ይኸም የሰይጣንን መግቢያ መንገድ ለመዝጋት ነበር:: ሆኖም ሕዝቡ በእርሱ ላይ በተደረገው ነገር በነበረው የቁጣ መንፈስ፣ በመመለሱ ደግሞ ሊገለጽ በሚያስቸግር የደስታ ስሜት ላይ ሆኖ የተለመደውን «ሰላም ለእናንተ ይሁን» የሚለውን አባታዊ ቡራኬውን እንዲሰጣቸው በአጽንኦት ከመናፈቃቸው የተነሣ ስላስቸኮሉት የሚያየው የሕዝቡ ሁኔታ ቃለ ምዕዳን እንዲሰጥ አስገደደው::

እንዲሁም ንግሥቲቱ ከደረሰባት መቅሠፍት የተነሣ ንጉሡም ወዲያውኑ እንዲመለስ አስቸኮሉት:: ባደረገው ቃለ ምዕዳንም እርሱ ተመልሶ የገባው ከንጉሡ በተሰጠው የመመለስና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገባ የሚያዝ ትእዛዝ መሠረት እንጂ በራሱ ፈቃድ ባለ መሆኑ





የሚያስጠይቀው ነገር የሌለ መሆኑን ገልጾአል:: ሕዝቡ እንደዚያ ባለ ሁኔታ ላይ ሆነው ሲያያቸው ለመንጋው ያለው ልባዊ ፍቅርና ሀዘኔታ ዝም ሊል አላስቻለውም:: ከዚያም በኋላ ስልሳ ጳጳሳት የተሰበሰቡበት ሲኖዶስ በዚያው በቁስጥንጥንያ ጉባኤ አድርጎ የእነ ቴዎፍሎስን የኦክ ሲኖዶስ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሠረዝና በመሻር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አሁንም በመንበሩ ላይ ያለ መሆኑን አውጇል::[45]

ከዚያው ከቁስጥንጥንያ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሳይሆን የአውዶክስያ ተላላኪዎችና ጉዳይ አስፈጻሚዎች እነ ሴቬሪያንና አካክዮስ[46] ንጉሡ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ስደት ያጸድቅ ዘንድ ይወተውቱ ጀመር:: በዚህ ጊዜ በሶርያ የሎዶቅያ ጳጳስ የነበረው ኤሊጽድዮስና ሌሎችም ንጉሡን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሚሳደድበት ምክንያት እንደሌለ አስረዱ፤ *«ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መጀመሪያም ቢሆን ከመንበሩ አልወረደም፣ በመንግሥት ኃይል እንዲሳደድ ተደረገ እንጂ፤ ሲመለስም ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ መንበሩ በራሱ ፈቃድ አልገባም፣ አንተ ይመለስ ዘንድ በአስቸኳይ ለጠራኸው ጥሪና ለፈቃድህ ታዘዘ እንጂ:: በተጨማሪም አሁን የሚጠቅሷቸው ቀኖናዎች በመናፍቃን የተወሰኑ ናቸው»* አሉ::

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጠላቶች በጩኸትና በልዩ ልዩ መንገድ አሳባቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ ይጥሩ ጀመር:: በዚህ ጊዜ ጳጳስ ኤሊጽድዮስ እንዲህ አለ:- *«ንጉሥ ሆይ፣ ከሳሾች የሆኑት ጳጳሳት ወንድሞቻችን አካክዮስና አንቶቂዮስ የስደት ውሳኔያቸው ማስረጃ አድርገው የሚጠቅሷቸው ቀኖናዎች ሃይማኖታቸው የቀና የኦርቶዶክሳውያን አባቶች ቀኖናዎች ናቸው ይበሉ፣ እነርሱም ቀኖናዎቹን ከሠሩቸው ሰዎች ጋር ሃይማኖታቸው አንድ መሆኑን ይናገሩ፤ ክርክሩ ሁሉ በዚህ ያልቃል[47]»* አለ:: ንጉሡም ይህ አሳብ ለውሳኔ ምቹና ቀላል በመሆኑ እነ አካክዮስን «ከዚህ የተሻለ መንገድ የለም» አላቸው:: በዚህ ጊዜ በጣም ተጨነቁ:: ሆኖም ማምለጫ ስላላገኙ ቀኖናዎቹን እንደሚቀበሏቸው ተናገሩ:: ሆኖም ቀኖናዎቹን ከተቀበሉ አርዮሳውያን ስለሚያስብላቸው ያለ ፈቃዳችን በሁኔታዎች አስገዳጅነት የተናገርነው ነው በማለት ቃላቸውን እንደገና አጠፉ:: ሆኖም ንጉሡን የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስደት ያጸድቅ ዘንድ በሚቻላቸው ሁሉ መወትወ ቻውን ቀጠሉ::

[45] ሶዞመን 8፣19

[46] ጳጳስ አካክዮስ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቁርጠኛ ጠላት የሆነው ወደ ቁስጥንጥንያ ሄጄ ሳለ በሚገባ አላስተናገደኝም በሚል ነበር፡፡

[47] ይህን ከተቀበሉ እነርሱም አርዮሳውያን ናችሁ ሊባሉ ሆነባቸው።

ምንም እንኳ ነገሩ እንዲህ ቢሆንም የነገሡና የንግሥቲቱ ፈቃድና ድርጊት ስለሆነ እንዲጋዝ ተፈረደበት:: እርሱ ግን እግዚአብሔር አደራ የሰጠውን ቤተ ክርስቲያን አልተውም በማለት ማስተማሩን ቀጠለ:: ይህን እንጂ ነገሩ በሕዝቡና በመንግሥት ወታደሮች መካከል ወደ ደም መፋሰስ ሊያመራ በመሆኑ በመንበረ ጵጵስናው ውስጥ ተወስኖ ተቀመጠ::

ጳጳሳትና ካህናት በ404 ዓ.ም. የትንሣኤ ዋዜማ ሌሊት ለብዙ ንዑስ ክርስቲያኖች የጥምቀት ምሥጢር ለመፈጸም በዝግጅት ላይ ሳሉ በጦር ኃይል አማካይነት ብዙ ግፍ ተፈጸመባቸው:: ተጠማቂዎች ተደበደቡ፣ ተንገላቱ፣ የምሥጢረ ቁርባን ንዋያተ ቅድሳት በአሕዛብ ወታደሮች ረከሱ:: ካህናቱ በአገልግሎት ላይ ሳሉ የለበሱትን ልብሰ ተክህኖ እንደ ለበሱ እያስወጡ በከተማው ውስጥ አሳደዷቸው:: የዚያ ሌሊት ሰቆቃ ሲያስታውሱት እጅግ ዘግናኝ ነው:: ጳላድዮስ ስለዚህ ሲናገር *«ንዑስ ክርስቲያኖች ሊጠመቁበት የተዘጋጀው የጥምቀት ውኃ በደም ተበከለ! ለኃጢአት ሥርየት ትሆን ዘንድ በተሰጠችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደም ማፍሰስ ተፈጸመባት»* ይላል:: የደስታና የሐሴት ጊዜያት የነበሩት የትንሣኤ ሳምንታት በክርስቲያኖች ዘንድ የሰቆቃና የመሪር ሐዘን ሳምንታት ሆኑ:: የግለሰብ መኖሪያ ቤቶች እየተወረሩ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቅርብ ረዳቶችና ጠንካራ ደጋፊዎች የሆኑት ብቻ ሳይሆኑ ይሆናሉ ተብለው የተጠረጠሩ ሁሉ የተገረፉ፣ እየተደበደቡና እየተሰቃዩ ወደ እስር ቤት ተጣሉ::

እርሱም በመንበረ ጵጵስናው ውስጥ ተወስኖ እያለ ሁለት ጊዜ ከተቃጣበት የመግደል ሙከራ ተረፈ:: በመጀመሪያ አንድ ርኩስ መንፈስ ያደረበትና አእምሮውን የሳተ የመሰለ ሰው የተሳለ ሳንጃ ይዞ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለመግደል ሲሮጥ ሳለ በሕዝቡ ተይዞ ለከተማው ሹም ተሰጠ:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግን ጳጳሳትን ልኮ በግርፋትና በስቃይ ከመመርመሩና ከመጠየቁ በፊት እንዲፈታ አደረገው:: ሌላም ሰው እንዲሁ ስለት በስውር ይዞ የሮጠ በመሄድ ሊይዘው ያለውን ሰው ሁሉ የወጋ የጣለ ወደ መንበረ ጵጵስናው በመሮጥ ሊገድለው ሲል ሕዝቡ በጭንቅ ይዞ አስቀረው::







የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የግሪክ ሥዕል

የእነ ቴዎፍሎስ የአምባ ገነንነት ውጤት በቤተ ክርስቲያን ላይ ይህን የመሰለ ደም መፍሰስና ስቃይ አመጣ:: የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ በዚህ ድርጊቱ ምናልባት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘ መስሎት ይሆን? *«የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል»* ብሎ ጌታችን በእውነት ተናገረ:: ዮሐ. 16፥2:: *መጀመሪያ* ባደረገው የሐሰት ውንጀላና ፍርድ እግዚአብሔር ነገሩን በተአምራት ሲያከሽፍበት እንዴት ጥፋቱን አውቆ ከእግዚአብሔር ሰው ጋር ሰላምን አይፈጥርም? ለካ የሥልጣን ፍቅር፣ አምባገነንነት፣ ዕብሪተኝነትና ቅንዓት አእምሮን ይህን ያህል ያሳውራሉ! *«ቅንአት ትበልዖሙ ለልበ ብዙኃን በመዓት፣ እስመ በቅንዓትሰ ኢይትረከብ ጸጋ እግዚአብሔር - ቅንዓት የብዙዎችን ልብ ያቃጥለዋል፣ በቅንዓትም የእግዚአብሔር ጸጋ አይገኝም»*[41] የተባለው ለዚህ ነው:: መ . 8፥6::

[41] የግእዙ መኃልየ መኃልይ ላይ

በመጨረሻም ሰኔ 5 ቀን 404 ዓ.ም. ብዙ ጊዜ ሲያመነ የቆየው ንጉ/ አርቃድዮስ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን የግዞት ውሳኔ በፊርማው አጸደቀ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ውሳኔውን በፍጹም ጸጥታ ተቀበለ። አብረው ከነበሩት ጳጳሳት ጋር በመንበረ ፓትርክናው ግቢ ውስጥ የመጨረሻ ጸሎ ካደረገ በኋላ ጳጳሳቱንና በዚያ የነበሩትን ካህናት «እኔ ሰረፋት ሳደርግ ል ነው፤ እናንተ ለጊዜው እዚሁ ቆዩ» አላቸው። እነርሱም በጥልቅ ሐዘ ተዋጡ። ከዚያም ድሆችንና ችግረኞችን በመርዳትና በአጠቃላ ሕይወታቸውን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሰጡትንና ሁል ጊ ከቤተ ክርስቲያን የማይለዩትን ኦሊምፒያንና ሌሎቹንም ጠርቶ እንዲ አላቸው፡-

> «የእኔ ጉዳይ ወደ ፍጻሜ እንደደረሰ ይታየኛል፤ መንገዴን ጨርሻለሁ፤ ከእሁ በኋላ ፊቴን የምታዩ አይመስለኝም። እናንተን የምጠይቃችሁ አንድ ነገር ቢኖር ለቤተ ክርስቲያን ያላችሁን ቅን አመለካከትና አገልግሎት ማንም አያስናክላችሁ ለቤተ ክርስቲያን የምታደርጉትንም አገልግሎት ቀጥሉ። በእኔ ቦታ የሚተካ ሰው እርሱ ሹመት ሳይፈልግና ያለ ፈቃዱ፤ እንዲሁም በሁሉም ስምምነ የሚሾም ከሆነ ልክ ዮሐንስ እንደሆን አድርጋችሁ ተቀበሉት፤ ለእ እንዳደረጋችሁት እርሱንም ታዘዙት፤ ቤተ ክርስቲያን ያለ ጳጳስ ልትሆ አይቻልምና። እንዲህ ብታደርጉ ምሕረትን ታገኛላችሁ። እኔንም በጸሎ ች አስቡኝ።»

በዚህ ጊዜ ጳጳሳቱም፣ ካህናቱም ዲያቆናዊቶቹም፣ ሁሉም የሚወዱ አባታቸው ሊለያቸው በመሆኑ በጥልቅ ሐዘን ላይ ወደቁ። ግማ ያለቅሳል፣ ሌላው የሐዘን ድባብ ውስጥ ሆኖ በአሳብ ባሕር ውስ ይመላለሳል፤ ብቻ ሁሉም በየራሱ መንገድ ሁኔታው የፈጠረበትን ሐዘ ይገልጽ ነበር። ኦሊምፒያና ሌሎቹም ዲያቆናዊያት በዕንባ እየታጠ በእግሩ ላይ ወደቁ። በዚህ ጊዜ ከካህናት አንዱን ጠርቶ በዙሪያው ያለው ዘብ ሆኖ እየጠበቀው ያለው ሕዝብ ሁኔታውን ሰምቶ ረብሻ እንዳይነ እነዚህን ወደዚያ ውሰዳቸው አለው። እነርሱም ራሳቸውን እንደምን አረጋጉ። መንበረ ጵጵስናውን ዙሪያውን ከቦ እርሱን በሚጠብቀው ሕዝብ በወታደሩ መካከል ግጭት ተፈጥሮ ደም እንዳይፈስ ለማድረግ ሕዝ በብዛት ተሰብስቦ ይጠብቀው ወደነበረበት በምዕራብ በኩል ወደነበረው ወ ቤተ ክርስቲያኑ በር የሚሄድ ከመሰለ በኋላ ወደ ምሥራቅ በር በኩ በመሄድ እርሱን ለማጋዝ ለተዘጋጁት ወታደሮች ራሱን ሰጠ። እነርሱ በሌሊት ወደ ባሕር ዳርቻ ወሰዱት።

ካህናት፣ ዲያቆናትና ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያንና ከየቤታቸው እየተያ ወደ እስር ቤት ተጣሉ። በየቦታው የነበሩ እስር ቤቶች በክርስቲያኖ ተሞሉ። እስር ቤቶች ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ተለወጡ። እርሱ ምት





እንዲሾሙ እነ አውዶክስያ ያዘጋጇቸውን እርሳኪዮስና አቲክስ[49] የተባሉትን የቤተ መንግሥት አሻንጉሊቶች ዕውቅና ስጥ ሲባል አልሰጥም አለ። ቤተ ክርስቲያን የራሷን መብት የሚያስጠብቅላት እውነተኛ አባት ማጣት የጀመረችው መሪዋን ነገሥታት እንደፈለጉ መሾምና መሻር ከጀመሩ ወዲህ ነው።

እንዲህ በወይዛዝርትና በመኳንንት ፈቃድ የሚሾሙ ሰዎች ቤተ መንግሥት ጢስ ሲጤስ የእነርሱ ዓይን ቀድሞ የሚያለቅስ፤ የቤተ ክርስቲያንን (የምዕመናንን) የልብ ትርታ ሳይሆን የሾሟቸውን የነገሥ ታትን ፍላጎት ሲያዳምጡ የሚኖሩ ናቸው። መሪዎች ሲያጠፉ ተው ብለው የሚቀጡበት ሞራሉም ሆነ ጥንካሬው ስለሌላቸው ባለ ሥልጣናት ያሻቸውን ቢያደርጉ የግፍ ጽዋቸውን ከመባረክ በቀር «ተው፣ አግባብ አይደለም» ለማለትም ሆነ ለመገሠጽ ሕሊናውም ሆነ ጥንካሬው የላቸውም። እንዲህ ያሉት እረኞች ሳይሆኑ ምንደኞች ናቸው። ዮሐ. 10፥11-13። ለዚህ ነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እነ አውዶክስያ ለራሳቸው ይመቹናል ብለው ለመሾም ላዘጋጇቸው ሰዎች ዕውቅና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ፈቃደኛ ያልሆነው። የቤተ ክርስቲያን አካሄድ እንዲህ ሲሆን አይገባምና። ይህም ተጨማሪ ከባድ ወንጀል ተደርጎ ተቆጠረበት።

እርሱን ከቤተ ክርስቲያን ይዘውት እንደወጡ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ ኃይለኛ እሳት ተነሥቶ ቤተ ክርስቲያኑንና መንበረ ጵጵስናውን፣ የመንግሥቱን የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት እና ሌሎች ሕንፃዎችን በሙሉ አመድ አደረጋቸው። እሳቱ የጀመረው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይቀመጥበትና ያስተምርበት ከነበረው ከመንበሩ ሥር ነው። ጳላድዮስ እንደሚገልጸው እሳቱ በቅዱሱ አባት መሰደድና ቤተ ክርስቲያን በደረሰባት ስብራት አዝነው የነበረውን ሕዝብ ሳይነካ እንደ ድልድይ በላያቸው ላይ ምንም ሳያደርጋቸው እያለፈ እየመረጠ የሚያቃጥልና ተአምራዊ እንደነበር ይገልጻል። በዚህም «ያቃጠልነው እኛ ነን» ብለው ያምኑላቸው

[49] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተሳደደ በመንበሩ ላይ የተተካው እርሳኪዮስ ነው። ሆኖም በሕይወትና በመንበሩ ላይ የቆየው ለአንድ ዓመት ከሁለት ወር ብቻ ነው። እርሳኪዮስ ከዚያ በፊት ጵጵስና እንዲሾም ሲጠየቅ «እኔ ሞቴን የጠበቅሁ ነው» በማለት ጵጵስና እንደማይሾም ምሎ ነበር። እርሳኪዮስ እንደሞተ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ በተፈጸመው ግፍ ብዙ ሥራ የሠራው አቲክስ ተተካ። አቲክስም በተፈጸመው የዓመጽና ሕገ ወጥ ድርጊት ምክንያት ከምሥራቃውያን ጳጳሳት እንዲሁም ከቁስጥንጥንያ ምዕመናን ማንም እንደማይቀበለው ስለተረዳ ዛቻና ማስፈራሪያ ዐወጀ። «ከቴዎፍሎስ፣ ከአርፈርዮስ (የእነርሱ የተሾሙ የእንጾኪያ ጳጳስ) እና አቲክስ ጋር ኅብረት የሌለው ጳጳስ ከቤተ ክርስቲያን ይባረራል፤ ንብረቱንም ይቀማል» የሚል ትእዛዝ አስተላለፈ። በጳጳሳትና በምዕመናን ላይ ብዙ መከራ አደረሰባቸው። ይህም ሆኖ ምዕመናኑም ሆኑ ብዙ ጳጳሳት ዕውቅና አልሰጡትም።

ዘንድ በእርሱ የቅርብ ሰዎች ላይ ልዩ ልዩ ስቃይና ዛቻ ቢያደርሱባቸውም ሊያምኑባቸው ግን አልቻሉም::

ለእርሱ በነበራቸው ታማኝነት የተጠሉ ካህናትና ጳጳሳት እነ አውዶክስያ በሾሟቸው የቤተ ክርስቲያንን ሳይሆን የሾሟቸውን ፈቃድ አስፈጻሚዎች በሆኑት «ጳጳሳት» ከየመንበራቸው እንዲሳደዱ እየተደረገ ተባረሩ:: የሮሙ ሊቀ ጳጳሳት ኢኖሰንት ጉባኤ አድርጎ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲሰደድ መደረጉ ሕገ ወጥ መሆኑን በመግለጽ ወደ መንበሩ እንዲመለስ ወሰነ:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን እንዲጋዝ የወሰነውን ሲኖዶስ ሕገ ወጥና የተሻረ ነው አለ:: ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በደረሰበት ነገር ሐዘኑ ውን በመግለጽ የሚያጽናና መልእክት ጻፈለት:: ንጉሥ አርቃዴዎስንም በዚህ ጉዳይ ላይ አጠቃላይ ጉባኤ እንዲጠራ አሳሰበ:: የምዕራቡ የሮማ ክፍል ንጉሥ የነበረው የአርቃዴዎስ ወንድም ንጉሥ አኖሬዎስም (395-423 ዓ.ም.) በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ የደረሰውን ነገር ሲሰማ በማዘን፣ በቴዎፍሎስ የተደረገው ነገር በጣም አሳዛኝ መሆኑን በመግለጽ የምሥራቅና የምዕራብ ክፍል ጳጳሳት የሚገኙበት አንድ አጠቃላይ ሲኖዶስ እንዲጠራ ለወንድሙ ለአርቃዴዎስ መልእክት ላከበት:: መልእክቱም እንዲህ ይላል:-

> *«በቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳት በዮሐንስ ላይ የተቀነባበረውን ሴራና የደረሰበትን ግፍ የሚያስተካክልና በቤተ ክርስቲያንም ፍትሕና ሰላም እንዲሰፍን የሚያደርግ ተገቢ የሆነ የማስተካከያ እርምጃ እንድትወስድ በመለመን ለክቡርነትህ ስጽፍልህ ይህ ሦስተኛ ጊዜዬ ነው፤ ሆኖም እስካሁን ምንም ነገር አልተደረገም:: ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና ደኅንነት ካለኝ መጨነቅ የተነሣ በአንተ ግዛት በምሥራቅ ያሉ ጳጳሳት በተሰሎንቄ እንዲሰበሰቡ ታደርግ ዘንድ አሁንም እንደገና ጻፍሁልህ፤ በምዕራብ በኩል እኛ ዝግጁዎች ነን:: ... በምዕራቡ ያሉት ጳጳሳት ለሊቀ ጳጳሳቱ ዮሐንስ ያላቸውን ስሜት ትረዳ ዘንድ እርሱን በተመለከተ በደረሰው ነገር በማዘንና አስቸኳይ የማስተካከያ ርምጃ ይወሰድ ዘንድ በመጠየቅ የላኩልኝን ደብዳቤ አብሬ ልኬልሃለሁ:: ክቡርነትህን በተለይ የማሳስበው ነገር ደግሞ የዚህ ሁሉ ችግር ምንጭ እንደሆነ የሚነገረውን የእስክንድርያውን ቴዎፍሎስን ፈቃደኛ ባይሆንም እንኳ በግድ እንዲገኝ እንድታደርግ ነው:: በዚህም ጳጳሳቱ በአንድነት ተሰብስበው የሆነውን ነገር ሁሉ መርምረው በቶሉ ተገቢውን ውሳኔ እንዲወስኑ ነው::»[50]*

ሆኖም ከንጉሥ አኖሬዎስና ከሮማው ፓትርያርክ ከኢኖሰንት (401-417 ዓ.ም.) ወደ ምሥራቁ ገዢ ወደ አርቃዴዎስ የተላኩት መልእክተኞች በምሥራቁ ክፍል የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ተይዘው ታስረው

---

[50] ጳላድዮስ፣ ምዕ. 3





ለወራት ከተንገላቱ በኋላ ተመለሱ:: የሮማው ፓትርያርክም ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ከቴዎፍሎስና[51] ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መሰደድ በኋላ በቁስጥንጥንያ መንበር ከተተካው ጋር፣ በአጠቃላይ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አሳዳጆችና ጠላቶች ከነበሩት ሁሉ ጋር ማንኛ ውንም ዓይነት ግንኙነት አቋረጠ::

## ፰. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በስደት ላይ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዚያ አካባቢ በጣም በሚያቃጥለው የሐምሌና የነሐሴ የሙቀት ወቅት በገላትያና በቀጳዶቅያ አድርገው በአርማንያ ወደሚገኘው የአውዶክስያ በቀለኛነት ወደመረጠለት እጅግ አስቸጋሪ ወደ ሆነው ካውካሰስ ወደሚባል ጠፍ ቦታ ተወሰደ:: የካውካሰስ ቦታ የአየሩ ጠባይ በጣም አስቸጋሪና ተለዋዋጭ፣ በክረምት ወራት ደግሞ ቅዝቃዜው እጅግ በጣም ከባድ ነው:: እንዲሁም ኢሱሪያንስ የተባሉ ዘላን ነገዶች ቦታውን በቀንና በሌሊት እየወረሩ አደጋ ያደርሱ ስለነበር በእነርሱ ይገደላል በሚል ተስፋ ወደዚያ እንዲጋዝ ተደረገ:: እርሱም በዚህ አስቸጋሪ በሆነ የስደት ቦታ በንዳድና በራስ ምታት በጣም ብዙ ተሰቃየ:: ከአንድ ጊዜ በላይ ለሞት እስኪደርስ ታመመ:: ወደዚያ እስኪደርስም ድረስ ለሰባ ሰባት ቀናት በተከታታይ በእግሩ ያለ ዕረፍት እንዲጓዝ ተደረገ::

የካውካሰስ ጳጳስ በርኅራኄና በሀዘኔታ ተቀበለው:: ከቅርብ ወዳጆቹና ከክርስቲያኖች ብዙ መልእክትና ስጦታ ይላክለት ነበር:: እንዲሁም ብዙዎች ከፍቅራቸው የተነሣ ያን ሁሉ አስቸጋሪ ቦታ ተጉዘው ካለበት

---

[51] በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይ፣ እንዲያውም በእርሱ ላይ ሳይሆን በክርስቶስሙሽራ በቤተ ክርስቲያን ላይ ይህን ያህል ወንጀል የፈጸመውን ፓትርያርክ ቴዎፍሎስን በተመለከተ ስንክሳርም ሆነ በድርሳነ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መቅድም ላይ ይህንን ድርጊቱን የሚያሳይ ምንም ነገር አልተባለም:: የድርሳኑ መቅድም እንዲህ ይላል:- «አውዶክስያ በድህይቱ መሬት ምክንያት ባወገዛት ጊዜ ወደ ቴዎፍሎስና ወደ ኤጲፋንዮስ ልካ በእርሱ ላይ ጉባኤ አድርጋችሁ የሚሻርበትን ምክንያት ፈልጋችሁ ከሹመቱ እንዲሻር አድርጉልኝ አለቻቸው:: እነርሱም እንዲህ አሏት:- ደግነቱ ባራቱ ማዕዘን የታወቀ ትምህርቱ ከሁሉ የደረሰ ዮሐንስ አፈወርቅን ምን ምክንያት ፈልገን እንሽረዋለን፣ አይሆንም አሏት::... እነርሱም ግዝቱን ፍታት ቢሉት የድሀይቱን መሬት ካልመለሰች አልፈታትም አይሆንም አላቸው:: ከዚህም በኋላ ተመልሰው በየቦታቸው ሄደዋል::» *ድርሳነ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መቅድም፣ አ/አበባ፣ ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ተሰፋ ገ/ሥላሴ ማ/ቤት*

እስካሁን በእስክንድርያ መንበር ላይ ከተሾሙት 117 ፓትርያርኮች ከዚህ በስተቀር በእርሱ ስም ቴዎፍሎስ ተብሎ የተጠራ ሌላ ፓትርያርክ የለም:: ግብጻውያን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን የሚወዱትና የሚያከብሩት ሲሆን (በስሙ የተሰየመ ገዳም አላቸው) የቴዎፍሎስን ጉዳይ ግን ብዙውን ጊዜ አለባብሰው ነው የሚያልፉት::

ድረስ እየሄዱ ይጠይቁት ነበር:: እርሱም በመልእክት ካለበት ቦታ ሆኖ የቁስጥንጥንያን ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ይመራ ነበር:: በመንበረ ጵጵስናው እያለ ያደርገው ከነበረው ቤተ ክርስቲያንን የመምራትና የመጠበቅ ሥራ ባላነሰ በስደቱ ጊዜም እንዲያውም በበለጠ ሁኔታ ተጽእኖው የጎላ ነበር:: በካውካሰስ ወደ አንድ ዓመት ያህል የአርማንያን ሕዝብ ጣፋጭ የሆነ ቃለ ወንጌልን የመገበ፣ ብዙ ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር እያቀረበ ኖረ:: ከቁስጥንጥንያ ደጋግ ምዕመናንና ከሌሎችም በተለይም ከኦሊምፒያስ ብዙ ገንዘብ የተላከለት በወራሪዎቹ በኢሱሪያንስ እስረኛ ተደርገው በምርኮ የተወሰዱትን ለማረኳቸው ብዙ ገንዘብ እየሰጠ ብዙዎቹን ነጻ እንዲለቀቁና ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲቀላቀሉ አደረጋቸው:: ብዙ ድሆችንም ይረዳቸው ነበር:: ብዙዎች ከአንጾኪያ፣ ከሶርያ፣ ከኪልቅያና ከሌሎችም ቦታዎች ወደ እርሱ ይሄዱ ነበር::

በሦስት ዓመት የስደቱ ወቅት ከላካቸው ብዙ መልእክታት ውስጥ 242 ያህሉ አሁን ድረስ ተጠብቀው ይገኛሉ:: እነዚህ መልእክታት ግልጽ፣ ድንቅና አሳማኝ በሆነ ዘይቤ የላቀና የመጠቀ የክርስትና መንፈስ ግልጽ ሆኖ የማታይባቸው ናቸው:: እነዚህ መልእክታቱ ለቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ጥቅምና ደኅንነት ያለውን እውነተኛ አሳብና ተቆርቋሪነት እንዲሁም እርሱ ከዚህ ዓለም ፈጽሞ የተለየና ከክርስቶስ ጋር መኖርንና ከእርሱ የሚገኘውን ሰማያዊ ክብር ብቻ እንጂ ከዚህ ዓለም ነገር ምንም እንደማይፈልግ አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው::

ለምሳሌ በፊንቄና በዐረብ ምድር ክርስትናን ለማስፋፋት አብሮ ብዙ ሲሠራ ለነበረው ኮንስታንቲየስ ለተባለ የአንጾኪያ ካህን ወደተፈረደበት የግዞት ቦታ እየሄደ በመንገድ ላይ ሳለ የላከለት መልእክት እንዲህ ይላል:-

*«ሐምሌ አራት ቀን ከኒቅያ እነሣለሁ:: ምንም እንኳ ማዕበሉ በየጊዜው የበረታ ቢሄድም የጀመርከውን ተግባር ማለትም የጣዖታትን አምልኮ ማጥፋትን! አብያተ ክርስቲያናትን ማነጽንና ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር የማቅረብን ነገር ችላ እንዳትል ለማሳሰብና ለማበረታት አደራ እልህ ዘንድ ይህንን ደብዳቤ ላኩልህ:: የዚህን ሥራ የራሴን ድርሻ ባልወጣና ግዴለሽ ብሆን አሁን የደረሰብኝ ባለው ነገር ምክንያት ከዚህ ኃላፊነት ራሴን ነጻ ማድረግ አልችልም:: ጳውሎስ በእስር ቤትና በመከራ ውስጥ እያለ የተሰጠውን ኃላፊነት ተወጥቷልና! ዮናስም በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ እንዲሁ! ሦስቱ ወጣቶችም በእሳት ውስጥ ሆነው እንዲሁ ተግባራቸውን አላቋረጡምና:: ስለዚህም የተከበርከ ጌታዬና ወንድሜ ሆይ፣ ይህንን አስበህ በፊንቄ፣ በዐረብና በምሥራቅ የተጀመረውን የስብከተ ወንጌል ተልእኮና*





*ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ችላ እንዳትል አደራ እልሃለሁ:: በዚህ ሁሉ ችግርና መከራ ውስጥ ለሥራው የሚቻልህን ብታርግ ዋጋህ ዕጥፍ ድርብ ይሆናልና::*

*«የሚወስዱኝ ወደ ሴባስቴ ሳይሆን ወደ ካውካሰስ እንደሆነ አሁን ተረድቻለሁ፣ ይህም ለአንተ ወደ እኔ መልእክት ለመላክ የተሻለ ቦታ ነው:: ስለሆነም ምን ያህል አብያተ ክርስቲያናት እንደታነጹ፣ ምን ያህል ሰዎች እንደተጠመቁና ምን ዓይነት የሕይወት ዕድገትና ለውጥ እንዳደረጉ በየጊዜው ጻፍልኝ:: በመርቅያን ኑፋቄ እየታመሰች ባለችው በቆጵሮስ ባለችው በሳላሚስ ተገቢ በሆኑት ሰዎች በኩል መደረግ የነበረበትን ነገር አደርግ ነበር፤ ነገሮችንም ሁሉ በቶሉ እንደሚገባ አስተካክል ነበር፤ ግን በስደት ላይ ሆንኩ:: ዓለሙን ሁሉ ያናወጠ ያለውን ኃይለኛ ማዕበል ጸጥ ያደርገው ዘንድ በትዕግሥት ሆነው ብዙ ጸሎትን ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርቡ ሁሉንም ክርስቲያኖች በተለይም ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸውን ተግተው እንዲጸልዩ አሳስባቸው::»[52]*

መልእክቶቹ ለምሥራቃውያንና ለምዕራባውያን ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ ዲያቆናዊያት፣ መነኰሳትና ሰባክያን የተላኩ ሲሆኑ በስደት ጉዞው ላይ የደረሰበትን እንግልትና ድካም የሚገልጹ፣ በተለያዩ ርእስ ጉዳዮች ላይ ምክርና ትምህርት የሚሰጡ፣ በአካል የተለያቸውን መንጋውን የሚያበረታቱና የሚያጽናኑ፣ በፋርስ (የዛሬዋ ኢራን)፣ ለጎቶች እና በሲጢያ ጀምሮት የነበረውን ስብከተ ወንጌል እንዲቀጥሉ የሚበረታቱ፣ እና ሌሎችንም ብዙ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው:: እውነተኛ አባት በአካል ቢሰደድም እርሱ ከምዕመናኑ፣ ምዕመናንም ከእርሱ አይለያዩም:: በእውነት ያልተመሠረተ ግን በአካል ቢቀርብም በመንፈስና በልብ ግን የራቀ ነው:: ሕዝቡ እነ አቲከስን አንቀበልም እያለ ብዙ መከራ ሲቀበል ከእውነተኛው አባቱ ጋር ግን በስደትም አልተለያዩም:: የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መልእክታት በቁስጥንጥንያና በየተገኙበት ቦታ ሁሉ በናፍቆትና በከፍተኛ ፍቅር ይነበቡ ነበር::

## ስደቱን ተከትሎ የተፈጠሩ ክስተቶች

ወደ ተመደበለት የስደት ቦታ ይወስዱት ዘንድ ከቁስጥንጥንያ ይዘውት እንደወጡ በቁስጥንጥንያ ከተማና በዙሪያዋ ባሉ ቦታዎች ላይ መጠኑ ታይቶ የማይታወቅ ታላላቅ የበረዶ ናዳ መዓት ወረደ:: ንግሥቲቱ አውዶክስያም በውርጃ ምክንያት ስትሰቃይ ቆይታ ከዚህ የበረዶ መዓት መውረድ በኋላ በዐራተኛው ቀን በጭንቅ ሞተች:: የተለያዩ ታሪክ ጸሐፊዎች አውዶክስያ ብዙ ዓይነት መከራና ችግር እንደደረሰባት

[52] መልእክት 221

ጽፈዋል። በቦታው የተተካው ሊቀ ጳጳሳት አቲከስም በተራው ሞተ። መንበረ ጵጵስናውና ቤተ ክርስቲያኑ፣ እንዲሁም ቤተ መንግሥቱ ከላይ እንደተገለጸው በእሳት ተቃጠለ።

እነ ቴዎፍሎስ በኬልቄዶን ባደረጉት የኦክ ጉባኤ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ዋና ከሳሽና ወንጀይ ሆኖ ለነ ቴዎፍሎስ ጥሩ መሣሪያ የነበረው የኬሎቄዶን ጳጳስ የነበረው ሲሪኖስ የተባለው ጳጳስ ወዲያውኑ ከዚያው ከውንጀላ ጉባኤያቸው ሲወጡ አንዱ ሳያየው ስለረገጠው እግሩ ታሞ ወደ ቁስጥንጥንያ መሄድ የማይቻለው ሆኖ በዚያው ቀረ። ከዚያም እግሩ ስለተመረዘ የተለያየ ቦታ ላይ ቢቆረጥም መዳን አልቻለም። ሁለት እግሮቹ ተቆርጠውም መዳን ስላልቻለ ተሰቃይቶ ሞተ።

በነገሥታት ጣልቃ ገብነት በቤተ ክርስቲያን ላይ የተፈጠረው ትርምስ መንግሥታዊ አስተዳደሩንም አልበጀውም። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሮም የምሥራቁ ግዛት በጦር መሪዎች ዐመፅና አድማ፣ በሕዝባዊ ዓመፅና በተለያዩ ሽፍታዎች ወረራ ይታመስ ነበር። በጦር መሪዎች ምክንያት የምሥራቁና የምዕራቡ የሮማ ግዛት እርስ በርሱ ሊዋጋና ሊጠፋፋ ደርሶ ነበር። ሮማውያን አረመኔዎች የሚሏቸው ኢሱሪያንስ ብዙ ከተማዎችን ወረሩ። ሌሎች ያመፁ ሰዎችም ብዙ አገር አጠፉ።

## 9. ዕረፍት

ሞቱን ለማየት ይናፍቁ ለነበሩት ጠላቶቹ ዕድሜው ረዘመባቸው። ስደተኛው ፓትርያርክ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለው ሚናና መልካም ተጽእኖ አሁንም አለመቋረጡም አናደዳቸው። አውዶክስያ ብትሞትም የግብር ልጆቿ የእርሷን የክፋት መሥፈሪያ ለመሙላት ደፋ ቀና ማለታቸውን ቀጠሉ። ስለዚህም የካውካሰስ መከራ ቶሎ ሊገድለው እንዳልቻለ ሲያዩ መጀመሪያ ከነበረበት ቦታ አራቢስከስ ወደሚባል ሌላ ቦታ፣ ከዚያም ጲጢየስ ወደሚባል በካውካሰስ አጠገብ ወደሚገኝ፣ በሮማ ግዛት ሥር ካሉት ቦታዎች ሁሉ ለመኖር እጅግ በጣም አስቸጋሪ ወደ ሆነው ቦታ ይወስዱት ዘንድ ከቤተ መንግሥት ወታደሮች መካከል በጣም ጨካኝ የሆኑ ሁለት ወታደሮች ተመርጠው ተላኩ። እነርሱም በእግሩ እያስቸኮሉና እያስጨነቁ ይወስዱት ጀመር። ወታደሮቹም ስለተሰጣቸው ትእዛዝ ሲናገሩ «በመንገድ ላይ ከሞተ የመዓርግ ዕድገትና ብዙ ሽልማት እንገኛላችሁ ተብለናል» አሉ።

ከሁለቱ አንዱ በማያስታውቅበት ሁኔታ ሰወር ያለ ርኅራኄ ሊያደርግለት ይሞክር ነበር። ሌላኛው ግን የመጨረሻ አረመኔ ጨካኝ ነበር። ኃይለኛ ዝናብ የጣለም፣ በጠራራ ፀሐይም፣ በሌሊትም ያለ ዕረፍት እንዲጓዝ በማድረግ በትኅርምት ሰውነቱ የደከመውን አባት ያለ ርኅራኄ አሰቃዩት።





የስደት ዘመኑ የደረሰበትን መከራ በቃላት አከናውኖ ለመግለጽ አይቻልም። ለሦስት ወራት ያህል በእግሩ በጨካኝ ወታደሮች እየተጎነጓተ ያደረገው የቅጣት ጉዞ ሰውነቱና ጤንነቱ ከትኅርምትና ከተጋድሎ ብዛት ለተጎዳውና ለተዳከመው አባት የቀስ በቀስ (አንድ ጊዜ በመግደል ያልተፈጸመ) ሰማዕትነት ነበር። በዚህ የስደት ዘመኑም ቢሆን በጣም ብዙ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ መልሷል።

በአርማንያ ሲያልፍ በሰማዕቱ በቅዱስ ባሲሊቆስ ቤተ ክርስቲያን ጸሎት አደረሰ። በዚያው ሌሊት ድል አድራጊው ታላቁ ሰማዕት ቅዱስ ባሲሊቆስ[53] በራእይ ተገለጠለትና *«ወንድሜ ዮሐንስ ሆይ፣ ነገ አብረን እንሆናለንና አይዞህ»* አለው። ይህ ሰማዕት አስቀድሞ ለቤተ ክርስቲያኑ ቄስ «እየመጣ ነውና ለወንድማችን ለዮሐንስ የሚሆን ቦታ አዘጋጅ» እንዳለው ይነገራል። እርሱም ይህንን ነገር ስለሰማ በማግስቱ ወታደሮቹን በዚያው በቅዱስ ባሲሊቆስ ቤተ ክርስቲያን ይቆይ ዘንድ ቢጠይቃቸውም ከለከሉት። እንደተለመደው ገና ሳይነጋ የስደቱን ጉዞ ጀመረ። ነገር ግን ብዙም ሳይሄዱ ስለታመመ ወደ ተነሱበት ቤተ ክርስቲያን መመለስ ግድ ሆነባቸው።

ካህናቱ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ነጭ ልብስ አለበሱት። እርሱም ነጭ መጎናጸፊያውን ለብሶ ከቅዱስ ምሥጢር (ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን) ተቀብሎ ወዲያው ነፍሱን በእግዚአብሔር እጅ ሰጠ። ከአንደበቱ ላይ የነበረው የመጨረሻ ቃል የሁል ጊዜ ምስጋናው *«ስለ ሁሉም ነገር ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን»*[54] የሚለው ነው። በርግጥም እርሱ በትምህርቱና በሕይወቱ በዘመናት ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ምክንያት ሆኗል። «ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁን ያከብሩ ዘንድ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» የተባለውን መዋቲ ሰው ሊያደርገው የሚችለው ድረስ ፈጽሟል። ይህም ዕረፍቱ ወደሚወስዱበት ቦታ ሳይደርስ በጳንተስ ባለች ኮማኒ[55] ከምትባል ቦታ ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው በሰማዕቱ በቅዱስ ባሲሊቆስ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ጊዜውም መስከረም 14[56] ቀን 407 ዓ.ም. በ60 ዓመቱ፣ በሊቀ ጵጵስናው ዐሥረኛ ዓመት ነው። በዚያም መነኰሳትና መነኰሳይያት ሌሎችም ብዙዎች ከተለያዩ ቦታዎች መጥተው በተገኙበት

[53] ሰማዕቱ ቅዱስ ባሲሊቆስ የኮማና ጳጳስ የነበረ ሲሆን ብዙ ክርስቲያኖችን በክርስትና ሃይማኖታቸው ምክንያት በጨፈጨፈው ንጉሥ በመክስምያኖስ ኒቆምድያ ላይ ሰማዕትነትን የተቀበለ ነው።

[54] (Glory be to God for all things, Amen.)

[55] ኮማኒ ዛሬ ጆርጂያ በምትባለው በጥቁር ባሕር አጠገብ በምትገኘው አገር ውስጥ የሚገኝ ቦታ ነው።

[56] ዕለተ ረፍቱንና ፍለስተ ዓፅሙን በተመለከተ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የቀናት ልዩነቶች አሉ። በእኛ ቤተ ክርስቲያን ዕለተ ዕረፍቱ የሚታሰበው ግቦትት 12 ቀን ነው። ይህንን በተመለከተ ስላሉት ልዩነቶች ኅዳር 17 ስንክሳር ተመልከት። ጥን ታዊያን የቤተ ክርስቲያን [illegible] ጸሐፊዎች እነ ሶቅራጥስ ዕረፍቱ መስከረም 14 መሆኑን ነው የጻፉት። ሶቅ. 6+21

በሰማዕቱ በቅዱስ ባሲሊቆስ ጎን ተቀበረ። የመቃብሩ ቦታም ተሳላሚዎች የሚሳለሙት የተከበረ ቦታ ነው።

## 10. የቅዱሱ ሰውነት ወደ ቁስጥንጥንያ መመለስ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሕይወቱ ቅድስና፣ የትምህርቱ ርቱዕነት፣ እንዲሁም በደረሰበት ግፍ በስደት ላይ በመከራ ሁኖ በ60 ዓመቱ የመሞቱ ነገር በክርስቲያኖች ልብ ውስጥ በማይረሳ ማኅተም የተቀረጸና ሁል ጊዜ ሲያስቡት የሚያሳዝንና ውስጥን የሚነካ ነው። የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ደቀ መዝሙር የነበረውና ከ434-447 ዓ.ም. ድረስ የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ የነበረው ቅዱስ ጵሮክለስ በቅድስት ሶፍያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ገናና መምህር ዓመታዊ የመታሰቢያ በዓል በቅዳሴ ላይ እያለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን በማስታወስ እንዲህ በማለት መስበክ ጀመረ፡-

> «ቅዱስ ዮሐንስ እንደሚገባው መጠን በትክክል ሊገለጽና ሊመሰገን የሚችለው እንደ እርሱ ያለ ሌላ ዮሐንስ ሲነሳ ብቻ ነው። ምዕመናን የእርሱን ድካሙን፣ ተጋድሎውን፣ ትምህርቱንና ጽናቱን ሲያስታውሱ ከጥሩ ምንጭ ጠጥቶ እንደረካ ሰው ጥማቸው ይቆረጣል። ከቅዱስ ዮሐንስ ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ፀሐይነት በግልጥ የሚያይበት የእግዚአብሔር የጸጋ ነጸብራቅ ወጣ፣ በዚህ አምሳካዊ የጸጋ የብርሃን ነጸብራቅም አንዱ ኦርቶዶክሳዊት እምነትን ከኑፋቄ ማጽዳትን አየበት፣ ሌላው እውነትን ከሐሰት ለይቶ አየበት፣ ሌላው ደግሞ በሃይማኖትና በምግባር ጸናበት፣ ሌላው የሚያበራ ሰማያዊ ክብርን ተመለከተበት። ስም አጠራርህ መዓዛው ከሚጣፍጥ ነገር ሁሉ በላይ የሆነ ቅዱስ አባት ሆይ! ግብርህ ሰማያዊ የሆነ አባት ሆይ! የእግዚአብሔርን ቃል ሳትታክት ያስተማርክ አፈወርቅ! ከሰማያት ይልቅ ከፍ ከፍ ያሉ ምሥጢራትን የተናገረ አንደበት ሆይ! ከነጎድጓድ ይልቅ ጮኸህ ወንጌልን ያስተማርህ መምህር ሆይ!

ይህ ዮሐንስ በትክክል በዘመን ከሚቀድመውና ሰባኬ ንስሐ ከነበረው ከዮሐንስ መጥምቅ ጋር አንድ ነው። ያ ዐዋጅ ነጋሪ ነበር፤ ይህ ደግሞ የወንጌል ቀርን ነው። ያ የማይናወጽ ነበር፤ ይህ ደግሞ የማይሸነፍ ነው። ያ ድንግል ነበር፤ ይህም የንጽሀና ድል አድራጊ ነው። ያ በምድረ በዳ አጠመቀ፣ ይህ ደግሞ መረቡን በከተሞች ላይ ጣለ። ያ ዝሙትንና አመንዝራነትን ገሠፀ፣ ይህ ደግሞ የስግብግብነትንና ለገንዘብ ሟችነትን ስህተትነት አጥብቆ አስተማረ። ያ ወደ እስር ቤት ተጣለ፣ ይህ ደግሞ ተሳደደ። ያ ራሱን ተቆረጠ፤ ይህ ደግሞ ስለ እውነት አንገቱን አስጣለሁ አለ። በዚህ ምድር ላይ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መከራዎችና ትግሎች በጣም ብዙ ነበሩ፤ በሰማያትም ክብሩ የብዙ ብዙ ነው።





> አሁን ከሐዋርያው ጋር እንዲህ ያለ ይመሻል፡- «የክርስቶስ መልካም መዓዛ ነኝ፣ ዓለሙን ከስህተት መጥፎ ሽታ አንጽቼአለሁ። በኤፌሶን ጣዖታትን አጥፍቻለሁ፣ በፍርግያ ሐሰተኞች አማልክትን ልጅ አልባ አድርጌአቸዋለሁ፣ በቂሣርያ አስነዋሪ ድርጊት መፈጸሚያ ቦታዎችንና ቤቶችን አስወግጃለሁ፣ በሶርያ የአሕዛብን መሰባሰብና ከንቱ ልማድ አስቀርቻለሁ፣ በፋርስ የእግዚአብሔርን ቃል ዘር ዘርቻለሁ። በየቦታው ኦርቶዶክሳዊት እምነትን ተክያለሁ።» ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ፣ ሕይወትህ በፈተና የተመላና በጣም አሳዛኝ ነበር፤ ሞትህ ግን የከበረ ነው። የከበረ ሥጋህ ያረፈበት መቃብርህም የተባረከ ነው፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነት የተዘጋጀልህን አክሊል አገኘ ዘንድ ከድካምህ በርፈሃል፤ ዋጋህም እጅግ የበዛ ነው። የከበርክ አባት ሆይ፣ የጊዜንና የቦታን ወሰን አልፈህ ጠፈርንና ወሰናቸውን አቋርጠህ የዚህን ዓለም ድካምና ውሱንነት ድል አድርገሃል። የቅዱሱን ሥራና ተአምር የማድረግ ኃይል ቦታ አይወስነውምና በዚህ የፈተና ዓለም ያለን እኛን ልጆችህን አትርሳን።»

በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበሩና ይህን ስብከት ይሰሙ የነበሩ ክርስቲያኖች ቅዱስ ጵሮክለስ በተናገረው ልባቸው በጣም ስለተነካ ስብከቱን እንኳ እስኪጨርስ መታገሥ አልቻሉም። ሁሉም በአንድ ቃል የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የከበረ ሰውነት ከኮማኒ ወደ ቁስጥንጥንያ ይመጣ ዘንድ ንጉሡን እንዲማልድላቸው አጥብቀው ለመኑት። ፓትርያርክ ጵሮክለስም የበዓሉ ፍፃሜ እንደሆነ ወዲያውኑ ወደ ንጉሡ ወደ ቴዎዶስዮስ 2ኛ (የንጉሥ የአርቃዴዎስ ልጅ 408-450 ዓ.ም.) በመሄድ የቅዱሱን ዐፅም እንዲመጣ ይፈቅድ ዘንድ ለመነው። እርሱም ንጉሡን እንዲህ አለው፡-

> «ንጉሥ ሆይ በጥምቀት ምሥጢር ልጅነት የሰጠህን፣ ስምዖን አረጋዊ ጌታችንን በቤተ መቅደስ እንደተቀበለው አንተንም በቤተ ክርስቲያን የተቀበለህን ይመለስ ዘንድ አድርግ። ቤተ ክርስቲያን ወደ አንተ እንዲህ እያለች ታለቅሳለች፡- <ውበቴ ደብዝዟል፣ አንደበቴ ተዘግቷል፣ ደም ግባቴ ጨፍግጓል፣ በአፈወርቅ እረኝነት ሲጠበቁ የነበሩትን በጎች ክፉ አውሬ በትኗቸዋል፣ የእኔ አንደበት ሆኖ ያገለግለኝ የነበረውን የእርሱን መንፈሳውያን ልጆች ጨካኝ አውሬዎች ነጣጥቀዋቸዋል። የአገልጋዬ ጠላቶች በቅንዓት ተነሳሥተው የእርሱን የቅድስና መንበር አርክሰውታል። በጫካ ባሉ ዛፎች እንደሚደረግ በመጥረቢያ ቅዱሱን ከእኔ ቆርጠው በመቃብር ዝም እንዲል አድርገውታል። መናፍቃን በሁሉም ነገር ልንቋቋመው አንችል የነበረውን እርሱን አሁን ትምህርቶቹን ከንቱ እናደርጋቸዋለን፣ አሁን የእኛን ትምህርት ይቃወም ዘንድ እርሱ በሕይወት የለምና ይላሉ።

ግርማዊ ሆይ፣ በአፈወርቅ ላይ ስለ ሆነው ነገር ጠላቶቹ እስከ መቼ ድረስ በእኔ ላይ ይሳለቁብኛ? የእኔን ሙሽራ ክርስቶስን በትክክል የሰበከውንና ያንጸባረቀውን እርሱን ወደ እኔ መልስልኝ። መንፈሳዊ አባትህን ለመንፈሳዊ እናትህ ለእኔ መልስልኝ። በሥጋ የወለደችህን እርሷን አትምሰላት፤ ልቧ ምሕረትን የማያውቅና ፈቃዷም ወደ ክፋት ያዘነበለ ነበርና። ነገር ግን ማንም እርሱን ገንዘብ ካላደረገ እግዚአብሔርን ሊያይ የማይችለውን ቅድስናን ተከተል። አውዶክስያ አሁን የለችም፣ ቤተ ክርስቲያን ግን ለዘለዓለም ትኖራለች። እኔ ዘላለማዊት እናትህ ነኝ። አፈወርቅን መልሰውና ደስ እንዲለኝ አድርግ፤ በዚህም እኔ በእግዚአብሔር ፊት አስታራቂ እሆንሃለሁ። አፈወርቅን አማላጅህ እንዲሆን አድርግ፣ ራስህንም የእውነት ልጅ መሆንህን በሥራህ አሳይ፣ በአባትህ ጸሎት የጸናህ ትሆን ዘንድ።>»

ንጉሡም የቅዱስ ጵርክሎስን ልመና በመቀበል ለሕዝቡ ጥያቄ ስምምነቱን ገለጸ። ከዚያም ላቅ ባለ ሥልጣናትና መኳንንት የቅዱስ የሐንስ አፈወርቅን የከበረ ዐፅም ያመጡበት ዘንድ ከብር የተሠራ ሳጥን ይዘው ወደ ኮማኒ ሄዱ። እዚያ እንደደረሱ ለአካባቢው ጳጳስና ለሕዝበ ክርስቲያኑ የከበረውን የቅዱሱን ሰውነት እንዲያስረክቧቸው የሚያዘውን የንጉሡን ደብዳቤ ሰጧቸው። በዚህ ነገር ጳጳሱና ሕዝቡ እጅግ በጣም አምርረው አለቀሱ።

ሆኖም እርሱ የቅዱሱን ዐፅም ያመጡ ዘንድ የላካቸው ሰዎች የከበረ ዐፅሙን ከመቃብሩ ማንቀሳቀስ አልተቻላቸውም፤ ከቋጥኝ ዓለት ይልቅ ከበዳቸው። ምንም ዓይነት ሙከራ ቢያደርጉ ሊያወጡት አልቻሉም። ቅዱሱ በዚያው መቅረት ፈልጎ ይሆናል ብለው በማሰብ መኳንንቱ ለቴዎዶስዮስ የሆነውን ነገር የሚገልፅ ደብዳቤ ጻፉለት። ንጉሡም ከፓትርያርክ ጵርክሎስና ከሌሎች ደጋግ ሰዎች ጋር ከተመካከረ በኋላ ያለ ጸሎት እንዲሁ ዝም ብሎ የቅዱሱን ዐፅም እንዲመጣ ማዘዙ ስህተት መሆኑን ተረዳ። ከዚያም ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ ድፍረቱና ስህተቱ ይቅርታ የሚጠይቅና ወደ መንበሩ በመመለስ መንጋውን ደስ ያሰኝ ዘንድ፣ ልክ በሕይወተ ሥጋ እንዳለ የተማጽኖ ደብዳቤ ለመጻፍ ወሰነ። ንጉሡ በእጁ የጻፈው ይህ ደብዳቤ እንዲህ ይላል:-

«ከንጉሥ ቴዎዶስዮስ፣ የዓለሙ ሁሉ መምህር ለሆንህ፣ ለመንፈሳዊ አባቴ ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እጅግ የከበርክ አባት ሆይ፣ የከበረ ሰውነትህን ሕይወት እንደሌለው እንደ ሌሎች ሰዎች ሰውነት ቆጥሬ በቶሎ ወደዚህ ይመጣ ዘንድ አዘዝሁ። ነገር ግን እኔ ለዚህ የበቃሁ ካለመሆኔ የተነሣ እንዳሰብኩት አልሆነም። ስለዚህ የእኔንና የሕዝቡን ልመና ትቀበል ዘንድ በእውነት ሕያው ለሆንህ ለአንተ ይህንን እኔ ራሴ በእጄ የጻፍኩትን ደብዳቤ





ላክሁ። ንስሐን የሰበክ ክቡር አባት ሆይ፣ ለቅድስናህ በማይገባ ሁኔታ የፈጸምኩትን በደል ሁሉ በይቅርታህ ጥልቅ ውስጥ ጣልልኝ፣ ተነሳሒውን እኔን ይቅር በለኝ። ወደሚወዱህ ልጆችህ ተመለስ፣ ወደ እኛ በመምጣትህም ደስ ይበለን። ትመጣ ዘንድ አላዝህም፣ ሁለተኛ እንዳላፍር ትመጣ ዘንድ በትሕትና እማጸንሃለሁ እንጂ። እጅግ የተወደድክና የተከበርክ አባት ሆይ፣ እባክህ በፈቃድህ ወደ እኛ ና፣ በፍጹም ደስታና ፍቅር እንቀበልህ ዘንድ።»

ንጉሡ ጽፎ እንደ ጨረሰ ለመልእክተኞቹ ሰጣቸውና ደብዳቤውን ወስደው በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መቃብር ላይ እንዲያስቀምጡትና ሌሊቱን ሙሉ በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ሲደርስ እንዲያድር አዘዘ። ይህ አገልግሎት ከደረሰ በኋላ ደብዳቤው በቅዱሱ ሰውነት ላይ ሲደረግ የከበረውን ዐፅም ከመቃብሩ በቀላሉ ማውጣት ቻሉ። ከዚያም በታላቅ ደስታ ሆነው ከንጉሡ በተላከው ሳጥን ውስጥ አደረጉት። ከመቃብሩ ላይ የወደቀ የጨርቅ እላቂ ነበር። ያን እላቂ ጨርቅ አንድ እግሩ የሰለለ የአካባቢው ድሀ በሽተኛ ወስዶ በሰለለው እግሩ ዙሪያ ጠመጠመው። ወዲያው እንደ ጤነኛው እግሩ ሆነ፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገነ በደስታ ዘለለ።

በእጃቸው መብራቶችን ይዘው የአካባቢው ሕዝብ የቅዱሱን ሰውነት ለመጨረሻ ለማክበር ተሰበሰቡ። የዚህ የከበረ አባት ሰውነት ስለተወሰደባቸው ያዘኑና ያለቀሱ ተከትለው ብዙ ሸኟቸው። የከበረ ዐጽሙን የያዙት ከኬልቄዶን ወደቦች ሲደርሱ ንጉሡ ቴዎዶስዮስ ከመንግሥት ሹማምንት ጋር፣ ከፓትርያርኩ ከካህናቱ ጋር፣ ስፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ በጀልባ ሆኖ ተቀበላቸው። የቅዱሱን ዐፅም የያዘው ሳጥን በንጉሡ መርከብ ላይ ተደረገ። ነገር ግን መርከቦቹ ወደ መናገሻ ከተማዋ ወደ ቁስጥንጥንያ ሲጓዙ ኃይለኛ ማዕበል ተነሣ። የቅዱሱን ሰውነት ከያዘችው መርከብ በስተቀር ሌሎቹ ሁሉም በማዕበሉ ተበታተኑ። ይህቺ መርከብ አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያዋ (ኮምፓስ) ቢጠፋባትም ወዲህና ወዲያ ሳትል በቀጥታ ወደ ባሕሩ ዳርቻ መዳረሻ ተጓዘች። መርከቧም በሕይወተ ሥጋ ሳለ በተከራከረላትና የስደቱ አንድ ምክንያት በሆነችው ባሏ በሞተባት ሴት የተክል ቦታ ላይ ደረሰች። በዚህም ከሞቱም በኋላ ይህ አባት ለጽድቅ ያለውን ቀናዒነት አረጋገጠ፣ ግፍንም አወገዘ።

የቅዱሱን ሰውነት የያዘችው ይህቺው መርከብ ወደ ዳር ስትደርስ ማዕበሉ ጸጥ እያለ ሄደ። ከዚያም ሁሉም ጀልባዎች ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስባቸው በሰላም ወደ ወደቡ ደረሱ። የቅዱሱ ዓፅም ከመርከቡ ወረደ። የቁስጥንጥንያ ከተማ ሕዝብ በሙሉ ወጥቶ መብራት ይዘው መዝሙር እየዘመሩ በደስታና በሐሴት ተቀበሉት። ይህም

የሆነው በ438 ዓ.ም. ከረፈ ከ30 ዓመት በኋላ ሲሆን የቅዱሱን ዐፅም የያዘው ሳጥን በሰማዕቱ በቅዱስ ኢሬን ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ተደረገ።

ንጉሡና ፓትርያርኩ ሳጥኑን ሲከፍቱት የቅዱሱን ሰውነት ምንም ሳይለወጥ እንዳለ አገኙት። ልዩ የሆነና የሚመስጥ መልካም መዓዛ ከሰውነቱ ይሸት ነበር። ቴዎዶስዮስም ልብሰ መንግሥቱን አውልቆ በቅዱሱ ሰውነት ላይ ጣለና ራሱን በቅዱሱ ደረት ላይ አድርጎ ዓይኑ በዕንባ እየታጠበ በሲቃ እንዲህ አለ:-

«ቅዱስ አባት ሆይ፣ እባክህ በአንተ ላይ የተደረገውን ኃጢአት ይቅር በል፣ ስለ እናቴ በደልና በአንተ ላይ ስለነበራት ጥላቻ እኔ እቀጣ ዘንድ አትተወኝ። የአንተ አሳዳጅ ልጅ ብሆንም እኔ ግን ምንም አልበደልኩህም። የእርሷ ልጅ በመሆኔ እንዳልቀጣ እባክህ በደሏን ሁሉ ይቅር በላት። የመንግሥቱን ክብር ከእግርህ ላይ ጥዬ የአንተን ምልጃና ይቅርታ ብቻ ደጅ እየጸናሁ ዓቅመ ቢስ ሆኜ ከእግርህ ስር ወድቄአለሁ። አንተን የበደለችህን የእርሷን ግፍ ይቅር በል፣ እርሷ በእኔ አንደበት እንዲህ እያለች ትማጸንሃለችና:- <አባት ሆይ፣ በደልን ይቅር ስለማለት ያስተማርከውን ትምህርት አስብ፣ በደሌን ሁሉ ተውልኝ፣ ከውድቀቴ ልነሳ እመኛለሁና የዕርዳታ እጅህን ዘርጋልኝ፤ አንተ የወደቀ ማንም ቢኖር ይነሣና ይዳን ብለሃልና። አሁን ያንተን መከፋትና ማዘን መሸከም አልችልም፣ መቃብሬ እንኳ ለአጥንቶቼ ዕረፍትን አልሰጣቸውምና።

በፍርድ ቀን በክርስቶስ ግራ እንደምቆምና ዘላለማዊ ቅጣት እንደሚጠብቀኝ ስለማውቅ በጣም በጭንቀት ላይ ነኝ። በትምህርትህ ብዙዎችን አድነሃል፤ እኔን ብቻ ከድኅነት ውጭ አታድርገኝ። ወደ አንተ የምጮኸውን እኔን አትተወኝ፣ ሔዋንን በእግዚአብሔር ላይ እንዳነሣሳት እኔንም አንተን በድል ዘንድ ያነሳሳኝን ዲያብሎስን ተበቀለው እንጂ። ርኅሩኅ ሆይ፣ በእኔ ላይ አትዘንብኝ፣ አትጨክንብኝም። በሕይወት ዘመንህ በአንተ ላይ የሚያደርሱብህን በደል አታስብም ነበር፣ አሁን በሰማያት ስትሆን ደግሞ የበለጠ የተበደልኸውን አታስብ። እኔ በጊዜያዊ መንግሥት በደልሁህ፣ አንተ ግን በዘላለማዊ መንግሥት ይቅር በለኝ፣ በደሌን ከመቃብር ባሻገር ማረኝ። ክብሬ ሁሉ አልፏል፣ አሁን ምንም የሚጠቅመኝ ነገር የለም፤ ስለዚህም፣ አባት ሆይ፣ በሰማያዊ ብርሃን ያለህ አንተን ርዳታህን እማጸናለሁ። ምንም መልስ የሌለኝ እኔ በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት ሳይፈረድብኝ እባክህ ይቅር በለኝ።>»

ይህንን ነገር ስለ እናቱ ስለ አውዶክስያ ሲናገር የቅዱሱን አካል በዕንባ አጠበው፤ በታላቅ አክብሮትና ፍቅር ሳማቸው። ፓትርያርኩ ጵሮክለስም የቅዱሱን አካል በታላቅ ትሕትናና ክብር ሳመ፤ እንዲህ አለ:- «ክርስቶስን





የምትወድ በጣም የተወደድክ መምህር ሆይ፣ ደስ ይበልህ። እኔ የአንተ መንፈሳዊ ወተት እየጠጣሁ ያደግሁ ልጅህ ነኝ። እኔ የአንተ ወራሴ መንበር እንደ መሆኔ የእኔ በጎች የአንተ ናቸው። ዛሬም ድረስ አንተ ትተኸው በሄድከው መኖ እየተመገቡ ነው። እባክህ መኖርህን ግለጥ፣ እኛንም ተናገረን።»

የተሰበሰበው ሕዝብ የቅዱሱ ሰውነት ያለበትን ሳጥን ለመንካት በጣም ጓጓ። በቤተ ክርስቲያንም ጸሎት ሲደረግ፣ ሕዝቡም ቀኑና ሌሊቱን ሙሉ የቅዱሱን ሥጋ ከያዘው ሳጥን ሳይለይ አደረ። በሚቀጥለው ቀን ጧት የቅዱሱ ሰውነት በንጉሡ ሠረገላ ላይ ተደርጎ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ወደ ቅዱሳን ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ተወሰደ። የቅዱሱን ሰውነት የያዘው ሳጥን በመንበረ ፓትርክናው ላይ በተቀመጠ ጊዜ ሕዝቡ በአንድ ቃል ሆኖ «አባት ሆይ! መንበርህን ተረከብ!» እያሉ በዕንባና በሲቃ ይጮኹ ጀመር። ፓትርያርክ ጵሮክለስና በዚያ በቅዱሱ ሰውነት አጠገብ የነበሩ ካህናት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አፉን ከፍቶ አድርጎ የተለመደውን የጳጳሳት ቡራኬ «ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» ሲል አዩት፣ ሰሙትም።

በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ ብዙ በሽተኞች በቅዱሱ ሰውነት በተአምራት ተፈወሱ። የአውዶክስያ መቃብር ግን ከተንቀጠቀጠ በኋላ በዚያው ሰጠመ። በመጨረሻም የቅዱሱ ሰውነት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ውስጥ ከቀደሙ ፓትርያርኮችና ነገሥታት ጋር በክብር ዐረፈ። በረከቱና ጸሎቱ፣ ጣዕሙና ፍቅሩ በእውነት ይደርብን፣ ለዘለዓለምም አይለየን፤ አሜን።



ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የተቀበረበት ሣጥን፤ በኮማኒ፣ ጆርጂያ የሚገኝ

በ1204 ዓ.ም. ( .ኤ.አ.) ዐፅሙ በመስቀል ጦረኞች ከቁስጥንጥንያ ወደ ሮም ተወሰደ። በሮም ቫቲካን ከቆየ በኋላ በሮሙ ሊቀ ጳጳሳት በዮሐንስ ጳውሎስ 2ኛ ኅዳር 27 ቀን 2004 ዓ.ም. ( .ኤ.አ) ወደ ቁስጥንጥንያ ተመለሰ።

## 11. አጠቃላይ ሰብእናውና ጠባዩ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ታላቅነትንና ደግነትን፣ ልዩ ተሰጥኦንና ፍጹም ሃይማኖተኛነትን በአንድ ላይ አዋሕደው ከያዙት፣ ትተዋቸው በሄዱት በድርሳናቶቻቸው (በጽሑፎቻቸው) እና በአርአያነታቸው በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በዘመናት ሁሉ አስደሳች የሆነ ግንቢና አዎንታዊ ተጽእኖ ካሳደሩት ጥቂት ቅዱሳን አባቶች አንዱ ነው:: እርሱ ለዘመኑም ትክክለኛ ሰው ነበር፣ ለሁሉም ዘመንም ትክክለኛ ሰው ነው::[57] ጎልቶ የማታየው ሰብእናው ባሕታዊነቱና ገዳማዊ ሕይወቱ ነበር::

በብሕትውናው ሳለ የተጎዳው ጤንነቱ በቀሪ የሕይወት ዘመኑም በቋሚነት ያስቸግረው ነበር:: በተለይም ከትኅርምት ብዛት የተነሣ በተፈጠረበት ከባድ የውስጥ ደዌና በኃይለኛ የራስ ሕመም ይሰቃይ ነበር:: በዚህም ምክንያት ምንም እንኳ በአጠቃላይ ሰብእናው ግብዣዎችንና ሌሎች ግርግሮችን የማይወድና የማይካፈል የነበረ ቢሆንም ሲገኙባቸው በሚያስፈልጉ በአንዳንድ ማኅበራዊና ሥርዓታዊ ጉዳዮችና ሁኔታዎች ላይ ለመገኘትና ለመካፈል ይቸገር ነበር:: ጠላቶቹ በእርሱ ላይ ማግኘት የቻሉት፣ እነርሱ ጥፋት ነው ያሉት ነገር ቢኖር ይህ ነበር፣ «ከሰው ጋር አይደባለቅም፣ ሰው አይወድም» የሚል::

ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች:- ከወጣቱም፣ ከአዛውንቱም፣ ከወንዶችም፣ ከሴቶችም፣ ከድሀውም ከሀብታሙም - ጋር ራሱን ዝቅ በማድረግ በነጻነት ይቀላቀል ነበር:: ከሁሉም ወገን በጣም የሚወዱት ብዙ ወዳጆች ነበሩት:: ጠላቶችም እንዲሁ ነበሩት:: ነገር ግን የሚወዱት ለእርሱ የነበራቸው ፍቅር ከሞት የጠነከረ፣ ከሲኦልም ይልቅ የሚያቃጥል ነበር:: በርግጥ በሚያፈቅሩት ሰዎች ያን ያህል የሚወደድ ከሆነ የሚወዱትን እንዲህ አጽንተው እንዲወዱት ያደረጓቸው እነዚያው ምክንያቶች የሚጠሉትን ደግሞ እንዲጠሉት ቢያደርጓቸው ተምክንያታዊ ነው:: ይህ የሚወዱት ሰዎች ሁኔታ በዘመኑ የነበሩት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከዚያ በኋላ በየዘመኑ የሚነሡና የእርሱን ሕይወትና ማንነት ያወቁ ሰዎች ሁሉ ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሚኖራቸው ፍቅርም እንዲሁ በጣም የጸናና ከመገለጽ በላይ የሆነ ነው:: በቅድስና ሕይወት፣ በእውነተኛነት፣ ከእግዚአብሔር በቀር ማንንም ባለመፍራት፣ በቅንና በንጹሕ ሕሊና፣ በርኅራኄ፣ ክርስቶስን

[57] (He was a man for his time and for all times)





በማፍቀርና ለክርስቶስ ክብር ብቻ በመኖር፣ ... በሁሉም ነገር ፍጹም አርአያ ነው:: እርሱን ማሰብም ልዩ ስሜትን ይፈጥራል::

ከላይ እንደተገለጸው ዋና አብነት አድርጎ የሚወስደው ቅዱስ ጳውሎስን ነበር:: እንዲሁም የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ፍቅርና ተወዳጅነት ነበረው:: ቅዱሳት መጻሕፍት የዕለት ምግቡ ነበሩ:: ለምዕመናንም ሆነ ለካህናት ደግሞ ደጋግሞ በአጽንኦት መጽሐፍ ቅዱስን እንዲማሩና እንዲያጠኑ ይመክር ነበር:: የብዙ ስህተቶች ምንጭ ቅዱሳት መጻሕፍትን አለመማርና አለማወቅ ነው ይላል:: ንጹሕ ሰው፣ የተግባር ክርስቲያን፣ የሰባክያን ንጉሥ ነበር:: አንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አዋቂ እንዲህ አለ:- «አንድ ካህን ሊሆን ስለሚገባው ነገር በወጣትነት ጊዜው በጋለ መንፈስ በጻፈው መጽሐፍ ላይ (በእንተ ክህነት) የገለጸውን፣ ሥጋ የለበሰ ሰው ሊያደርገው እስከሚችለው የመጨረሻ ደረጃ ድረስ በራሱ ሕይወት ላይ በተግባር ፈጸመው::» የሌላውን ወንድሙን መንፈሳዊ ሕይወት እንዲጸናና እንዲያድግ ማድረግ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ተግባር እንደሆነ ያስገነዝብ ነበር:: «ሌሎችን ለማዳን ምንም ጥረት እንደማያደርግ ክርስቲያን የሚያሳዝን ነገር የለም:: ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን ድህነትም ይሁን ዝቅተኝነት፣ ወይም ሌላ ነገር ከዚህ ታላቅ ኃላፊነት ነጻ ሊያደርጋቸው አይችልም» ይላል::

የዚህን አባት ዜና ሕይወት በተመለከተ ወጥ አድርገው ከጻፉት ብዙ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍያን መካከል አንዱ እርሱ በጻፈው ላይ አንድ አስተያየት ሰጪ የሆነ ሌላ ሰው የእርሱ ጉድለት ነው ያለውን ሲናገር እንዲህ እንዳለው ይገልጻል:-

> «የማይዘለቅ ነገር ጀመረ፣ ማለትም ካህናትን ለማስተካከልና የቤተ መንግሥት ሹማምትን በእውነትና ያለ አድልዎ እንዲሠሩ፣ ሁሉም ለእውነትና በእውነት ብቻ እንዲኖሩ ለማድረግ ተነሣ፤ ከተለያየ አቅጣጫ ጠላቶቹ በእርሱ ላይ አንድ ሆነው እንዲሰባሰቡበትና እንዲተባበሩበት ዕድል ሰጣቸው:: ይህም የሆነው ጠላቶቹን አንዱን በአንዱ ላይ የማስነሣትና የመለያየት የዲፕሎማሲ ሥራ ስለማያውቅ ነው::»

ጸሐፊው ይህን አስተያየት ለሰጠው ሰው ሲመልስ ደግሞ እንዲህ አለ:-

> «ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቢዛንታይን «ዲፕሎማት» ቢሆን ኖሮ አንዱን ከአንዱ እያጋጨና ሌሎች ዘዴዎችን የተጠቀመ ጠላቶችን የማዳከም ዘዴ ሊኖረውና ይህንንም ሊጠቀም ይችል ይሆን ነበር፤ ነገር ግን እንዲህ አድርጎ ቢሆን ኖሮ እርሱ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አይሆንም ነበር::

በእርሱ ዘመን የነበረውም፣ ከዚያ በኋላ በየዘመኑ የሚነሣው ትውልድም የእርሱን ጫፍ የደረሰ ከክፋትና ከተንኮል የጸዳ ነቁጥ የለሽ ፍጹምነትና እውነተኛነቱን እጅግ በጣም በታላቅ አክብሮትና ፍቅር ሊያየውና ሊያፈቅረው አይችልም ነበር። እርሱ እንዲህ ከነበረበት ዘመን እንሥቶ ታላቅና ተወዳጅ የሆነው በዘመኑ ከነበሩ አድመኞችና ዲፕሎማቶች ፈጽሞ የተለየ ስለነበረ ነውና። አዎ፣ በአፍአዊ ሁኔታ ለጊዜው ተሸንፏል፣ ነገር ግን በዓለሙ ሁሉ የሕሊና ፍርድ ዘለዓለማዊ የሞራል አሸናፊ ነው።»

*ኃጢአትንና ግፍን ፈጽሞ ይጸየፋል፤ ኃጥአንን ግን ወደ አምላካቸው በንስሐ ይመለሱ ዘንድ በማጽናናት ያበረታቸዋል። ሰዎችን ማስተማርና ማሳመን እንጂ ማስገደድ አግባብ አለመሆኑን ያስረዳ ነበር። ስለዚህም እንዲህ ብሏል፦ «ከማንም ሰው በላይ ክርስቲያኖች የኃጢአተኞችን ስህተቶች በኃይል እናስተካክላለን እንዳይሉ ተከልክለዋል። ... ሰውን በኃይል ሳይሆን በማሳመን የተሻለ ሰው ማድረግ ተገቢ ነው። ኃጢአተኞችን ከኃጢአታቸው ለማስቆም በሕግ የተሰጠ ሥልጣን የለንም፤ ቢኖረንም እንኳ እንዴት እንደምንጠቀምበት አናውቅም፤ እግዚአብሔር አክሊል የሚሠጠው ከክፋት በግድ ሳይሆን በፈቃድ ለተጠበቁት ነውና።» ስለዚህ ሁሉም ሰው በራሱ ፈቃድ ከኃጢአት ይለይ ዘንድና ወደ እግዚአብሔር በእውነተኛ ልብ ይቀርብ ዘንድ ባለጸጎችና ባለ ሥልጣናት ግፍ እንዳይሠሩና ከጽድቅ እንዳይርቁ ማንንም ሳይፈራና ለሰው ፊት ሳያደላ የወንጌልን እውነት በቀጥታ አስተማረ። ድሆችን ደግሞ አጽናና። ስለዚህም አንድ ጸሐፊ ሲናገር «የተደላደሉትን ያስደነግጣል፣ የተጨነቁትን ደግሞ ያጽናናል»[58] አለ።*

ሀብትን በተመለከተ ኃጢአት የሚሆነው ባለ ጸጋ መሆን ሳይሆን ገንዘብን ለጽድቅ አለማዋልና ከዚያም አልፎ ለኃጢአት መሣሪያ ማድረግ እንደሆነ ያስተምራል። «ሀብትን አናወግዝም፣ ከሀብት በስተጀርባ ያለውን ትዕቢት ግን እናወግዛለን» ይላል። ድሆችንም ድሀ ስለሆኑ ብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ አስተያየት እንደማይደረግላቸውና ማስተዋል ያለባቸው መሆኑን ያስገነዝባል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቀጥተኛ ነበር። በቤተ መንግሥት ቅምጥሎችና ባልሹዎች ጠላትነት ከዓላማው አንድ ስንዝር ፈቀቅ አላለም። ከመጀመሪያ ስደቱ ከተመለሰ በኋላም ከዚያ በፊት ያደርግና ያስተምር እንደነበረው አሁንም ክፋትን፣ ኃጢአትንና ግፍን መቃወምን ወደ ኋላ አላለም። ቤተ ክርስቲያንን ለሹማምንትና ለባለ ሥልጣናት እንድታገበድድ አላደረገም፣ የቤተ ክርስቲያንን ሉዐላዊነት ለማንም አሳልፎ አልሰጠም። በዚህም ስለ እውነት የመጨረሻውን ዋጋ ከፈለ። ተጋድሎውና ሕይወቱ በአንጾኪያና

[58] (He teriffied the comforted and comforted the terrified)





በቁስጥንጥንያ ሳለ ከነበረው በበለጠ በስደቱ በተቀበለው መከራ በሰማዕትነት ታተመ። የሦስቱ ዓመታት የስደትና የመከራ ጊዜያት የሕይወቱና የተጋድሎው የክብር አክሊላት ናቸው። ምንም እንኳ በቀጥታ አንገቱ ተሰይፎና ደሙ ፈሶ ባይሞትም ለክርስትና ሃይማኖትና ለእውነት ሲሉ ማንኛውንም መከራ ለመቀበል ዝግጁ ከሆኑት ከእውነተኛ ሰማዕታት ወገን (ሰማዕት ዘእንበለ ክዕወተ ደም[59]) ደገኛው መስካሪ ሰማዕት ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሕይወቱ፣ ከዚህም በላይ በአሳዛኝ አሟሟቱ በምዕመናን ልቡና ውስጥ በጥልቁ ታትሟል። ይህም ሕይወቱና ሥራዎቹ ትተውት በሄዱት ጥልቅና ሰፊ የሆነ አሻራ ግልጽ ሆኖ ይታያል። ተወዳጅነቱና ታላቅነቱም በአጠቃላይ በታሪክ ሰምኝም ሳይቀር ነው። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ የሆነው አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ስድስተኛ መጽሐፉን ሙሉውን ማለት በሚቻል መልኩ ስለ እርሱ ከጻፈለት ከኦሪገን በስተቀር የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ያህል ስለ ሕይወቱና ስለ ቅድስናው የተጻፈለት የቤተ ክርስቲያን አባት የለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ነክም ሆነ ተዛማጅ ድርሳናት በዓይነትና በብዛት የእርሱን ያህል የተጻፈለት የቤተ ክርስቲያን አባት የለም። ስለ እርሱ በየዘመኑ በጣም ብዙ ተጽፏል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች ምስክርና ዋቢ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን በተካሄደው 3ኛው ዓለም ዓቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ላይ ቅዱስ ቄርሎስና ጉባኤው ዋቢ አድርጎ ካቀረባቸውና ካደመጣቸው የአባቶች ትምህርቶች አንዱ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው። እንዲሁም በ8ኛው መቶ ዓመት ለቅዱሳት ሥዕላት ሊሰጣቸው ስለሚገባው ክብርና በክርስትና ውስጥ ሥዕላትን መጠቀም ይገባል አይገባም በሚለው ወዝግብ ምክንያት በተጠራ አንድ ጉባኤ ላይም ለሥዕላት ተገቢ የሆነ አክብሮት እንደሚገባቸው የሚገልጽ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት የተገኘ ምንባብ በተነበበ ጊዜ ከተሰብሳቢዎቹ አንዱ ጳጳስ «ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሥዕላትን በተመለከተ እንዲህ ከተናገረ ከእርሱ በተቃራኒ ይናገር ዘንድ ማን ይችላል?» ብሎ አሰምቶ ተናገረ። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ተቀባይነቱ ምን ያህል ደረጃ መድረሱን ነው። በ407 ዓ.ም. የተፈጸመው የዚሁ ዓለም ድካሙና ሥራው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የክርስቲያኖችን ሕይወት ሲያግዝና ሲያበራ ይኖራል። ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አባት በላይ በቤተ ክርስቲያን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴና ሕይወት ላይ የተቀደሰ ተጽእኖውና አሻራው ጎልቶ ይታያል።

[59] (Confessors)



ሞስኮ (ሩሲያ) የሚገኝ የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ገዳም (1882)

አንድ ስለ እርሱ ዜና ሕይወት የጻፈ ከእርሱ ጋር ዘመን ገጠም የነበረ ጸሐፊ እንዲህ አለ፦ *«ለሰው ልጅ ትምህርትና ጥቅም ይሆን ዘንድ፣ እንዲሁም ታላቅ በሆነው የኤጲስ ቆጶስነት ተግባር የሚሰማሩ ሁሉ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን አርአያቸው ያደርጉት ዘንድ ስለ እርሱ የሰማሁትን ግማሽ ብራና ላይ በብዕር እጽፋለሁ።»* አንድ ሌላም የእርሱን ትምህርቶች ደህና አድርጎ ያነበበ ሰው፣ በዚህም ያገኘውን ጠቀሜ እና ያሳደረበትን መልካም ተጽእኖ ሲገልጽ፦ *«ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ የእርሱን ትምህርቶች አንብቤአለሁ፣ ከእነዚህም ከውስጣቸው ሊገለጽ የማይቻል ልዩ ጣዕም ይፈልቃል። ከሕፃንነቴ ጀምሮ እርሱን በማወቄ በጣም ደስ ይለኛል። ድምፁን የምሰማውም እንደ እግዚአብሔር ድምፅ አድርጌ ነው። እኔ ላወቅሁትና ለሆንሁት ሁሉ አመሰግነዋለሁ»* ብሏል።[60]

በስደት ጊዜው የተቀበለው አደልፊዮስ የተባለ ጳጳስ ቅዱስ የሐንስ አፈወርቅን አሳየኝ ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀው። እግዚአብሔርም በራእይ የቤተ ክርስቲያንን ቅዱሳን ሊቃውንትና[61] ሁሉንም ቅዱሳን አሳየው፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ግን አላሳየውም። ከዚያም እያዘነ ሲወጣ የእግዚአብሔር መልአክ አየውና «ይህን ክብር አይተህ እንዴት ታዝናለህ?» ቢለው «እይ አባቴን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ስላላየሁት ነው» ቢለው መልአኩም «እርሱን ገና በምድር ላይ ያለ መዋቲ ሰው አያየውም፤ ከሁሉም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በላይ ነው፣ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ» እያሉ ከሚያመሰግኑ መላእክት ከሱራፌልና ከኪሩቤል ጋር ከመንበሩ ሥር ነው» እንዳለው ይነገራል።

[60] (Nicephorus Callistus, Hist. Eccl. 13-2, Migne 146, 933 C.)
[61] (Doctors of the Church)





## 12. የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሥራዎች

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ያስተማረው ትምህርትና የጻፈው እጅግ በጣም ብዙ ነው። ከኦሪገን በስተቀር የእርሱን ያህል የጻፈና የሥራው ተጽእኖ ጎልቶ የወጣ የለም። የጽሑፍ ሥራው በጣም ብዙ ነው። ሥራዎቹን እንደሚከተለው ከፋፍለን እናያለን።

### 12.1 ከመጀመሪያው በመጽሐፍ መልክ የተዘጋጁ ሥራዎች[62]

እነዚህ ሥራዎቹ በቀጥ ከመጀመሪያው በመጽሐፍ መልክ ጽፎ ያዘጋጃቸው ናቸው። እነዚህም እንደየ ርእሰ ጉዳያቸው በተለያዩ ርእሶች ሊመደቡ ይችላሉ።

1. ገዳማዊ ሕይወትን በተመለከተ -

   እነዚህ ብዙዎቹ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በወጣትነት ጊዜው የጻፋቸው ሲሆኑ ለዚህ ሕይወት ምን ያህል ምክንያታዊ የሆነ አድናቆት እንደነበረው የሚያሳዩ ናቸው።

- የትምህርት ቤት ጓደኛው ለነበረውና በኋላም እንደ እርሱ ገዳማዊ ሕይወትን ከጀመረ በኋላ በአንዲት ሴት ምክንያት ከዓላማው በማፈግፈግ ወደ ዓለም ተመልሶ ለነበረው ለቴዎድሮስ የላከለት ሁለት መልእክታት (በ371 እና በ378 ዓ.ም. መካከል የተጻፉ)፦ በመጀመሪያው መልእክቱ ሄርሞን በምትባል ወጣት ሴት ውበት በመማረኩ በመውቀስ ወደ ቀደመ ሕይወቱና ዓላማው ይመለስ ዘንድ በሲያል መከራና በመንግሥተ ሰማይ ተድላ ደስ ይመክረዋል። እንዲሁም ቢመለስ ይቅር እንደየሚያገኝ ብቻ ሳይሆን ቀድሞ አግኝቶትና ደርሶበት ከነበረው የቅድስና ክብር የበለጠ የሚያገኝ መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ማስረጃ ያጽናናዋል። በሁለተኛው መልእክት ደግሞ የጋብቻን ሕጋዊነት ምክንያት አድርጎ ለጠቀሰበት ለቴዎድሮስ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ለማግኘት ከሚከብደው ከክርስቲያናዊ ነጻነት አንጻር የዚህ ዓለም ተድላና ደስታ ምን ያህል ጊዜያዊና አስተማማኝ ያልሆነ እንደሆነ ያስረዳዋል። ይህም ድካሙ ሠምሮ ቴዎድሮስ የማግባት አሳቡን ትቶ ወደ ገዳማዊ ሕይወቱ ተመልሷል። በኋላም የሞፕሶስቲያ ጳጳስ ሆኗል።

[62] (Non Oratorical Works)

- ❖ ስለ ንስሐ - (375-376 ዓ.ም የተጻፉ) ለሁለት የተለያዩ ሰዎች የተጻፉ ሁለት መጻሕፍት ሲሆኑ ስለ ንስሐ አስፈላጊነትና ጠቀሜ የሚገልጹ ናቸው። ንስሐ ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስን ያፈቀረውን ያህል ወደ ማፍቀር ደረጃ እንደርስ ዘንድ የምንበርበት ክንፍ ይሰጠናል ይላል። ዳዊትና ቅዱስ ጳውሎስ በንስሐ እንዴት እንደከበሩ በማሳየት የንስሐን ጠቀሜታ በሚገባ ፍንትው አድርጎ ያሳያል።

- ❖ በገዳማዊ ሕይወት ተቃዋሚዎች ላይ የተጻፉ ሦስት መጻሕፍት (375-376 ዓ.ም. የተጻፉ)፡- እነዚህ መጻሕፍት የገዳማዊ ሕይወት ጠላቶች የክርስቶስ እና የሐዋርያት ጠላቶች እንደነበሩት እንደ አይሁድ መሆናቸውንና እነርሱ ያገኙት ቅጣት የሚገባቸው መሆኑን ያሳያል። በሁለተኛው መጽሐፍ ደግሞ በመንፈሳዊ ጥበብ፣ በምግባርና በሃይማኖት የከበረ ክርስቲያናዊ ሕይወት በምቾትና በቅምጥ እንዲሁም በከፍተኛ ክብርና ሥልጣን ከኖረ ሕይወት በጣም የሚበልጥ መሆኑን ያስረዳል። በሦስተኛው መጽሐፍ ደግሞ ለአንድ ክርስቲያናዊ አባት ልጁን ወደ ገዳም ለመግባት ለምን ሊፈቅድለት እንደሚገባ ያስረዳል።
- ❖ የመነኩሴና የንጉሥ ንጽጽር (መጠኑ አነስ ያለ መጽሐፍ)፡- የንጉሥን ሥልጣን፣ ሀብትና ክብር በእውነተኛ ፍልስፍና (በገዳማዊ ሕይወት) ከሚኖር የመነኩሴ ሕይወት ጋር ያነጻጽራል።

## 2. ስለ ክህነት

የክህነትን ኃላፊነት፣ ታላቅነትና ከባድነት፣ እንዲሁም አንድ ካህን እንዴት ሊሆንና ሊያደርግ እንደሚገባው የሚያስረዱ ስድስት ተከታታይ መጻሕፍትንም ጽፏል።

## 3. ስለ ድንግልናዊ ሕይወትና ስለ ንጽሕናና ራስን ስለመግዛት፣ እንዲሁም ስለ ትምህርት የተጻፉ የተለያዩ ድርሰቶች

- ❖ ስለ ትዕቢትና የልጆች ትምህርት በተመለከተ የተጻፈ መጽሐፍ
- ❖ ስለ ድንግልናዊ ሕይወት የተጻፈ መጽሐፍ - ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጋብቻና ድንግልናዊ ሕይወት ያስተማረውን (1ቆሮ. ምዕ. 7) የሚተረጉምና የሚያብራራ ነው። ጋብቻ ክቡርና ጥሩ ነው፤ ሆኖም ድንግልና የበለጠ ጥሩ ነው።
- ❖ ለአንዲት ባሏ ለሞተባት ወጣት ሴት ማጽናኛ





- ❖ ባላቸው የሞተባቸው ሴቶች ከሁለተኛ ጋብቻ ይልቅ ተጠብቀው ቢኖሩ የሚሻል መሆኑን ዘርዘር አድርጎ የሚያስረዳ መጽሐፍ
- ❖ ሁለት አጠር ያሉ ጽሑፎች - መጀመሪያ ደናግሎችን፣ ሁለተኛ ዲያቆናዊቶችን ይህ ድርጊት በሚያስከትለው ጥፋት ምክንያት ከካህናት ጋር በአንድ ቤት መኖርን ይከለክላል።

## 4. ስለ ሃይማኖትና ስለ እግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ የተጻፉ

እነዚህ ሁሉም የጥብቅና ሥራዎች[63] ናቸው ማለት ይቻላል።

- ❖ በከሃዲው ንጉሥ በጁሊያንና በመመልከያን ጣዖት ላይ የተጻፈ ድርሰት - ሃይማኖቱን ከዶ ለአሕዛብ እምነት ጠበቃ ለነበረውና ክርስትናን ለማጥቃት መጽሐፍ ለጻፈው ንጉሥ ለጁሊያን የተጻፈ የጥብቅና መጽሐፍ
- ❖ ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን የሚያስረዳና ሚያስረግጥ፣ በነቢያት ትንቢት መሠረት የመጣና ኢየሱስ እውነተኛውና ይጠበቅ የነበረው መሲሕ (ክርስቶስ) መሆኑን ለአይሁድና ለአሕዛብ የሚያስረዳ መጽሐፍ
- ❖ በሕሊና ስቃይና በጭንቀት ሲቸገር ለነበረ አንድ መነኩሴ የተጻፉ ሦስት መጻሕፍት - በመከራ ውስጥ ያለውን የአምላካዊ መግቦት ሥራና ፈተና ለመለኮታዊ አስተዳደር ያለውን ሚና ያሳያል። በመጽሐፉ ውስጥ ውጤታማ የሆነ የሐዘን መድኃኒትን አስቀምጧል።

## 5. መልእክታት

ሁሉም በስደት ዘመኑ (404-407) የተላኩ ሲሆኑ ሁለት መቶ ዓርባ ሁለት (242) የሚሆኑት ዛሬም ድረስ ተጠብቀው ይገኛሉ። እነዚህም፡-

- ❖ ለጳጳሳትና ለሌሎች ወዳጆቹ እርሱንና ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ የተላኩ፣
- ❖ የማጽናኛ መልእክታት፡- በጣም የሚበዙት እነዚህ ሲሆኑ በተለይ 17ቱ ለኦሎምፒያ የተላኩት መልእክታት ብዙ ትምህርቶችን በውስጣቸው የያዙ ናቸው።
- ❖ እንዲሁም በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የተላኩ ሌሎች መልእክታት ናቸው።

[63] (Apologetic)

በመከራው የበለጠ ፀሩህና ንጹሕ የሆነችው የታላቁ አባት ንጽሕት ነፍስ በመልእክቶቹ ሁሉ ያበለጠ ግልፅ ሆና ትታያለች::

፩. ቅዳሴ፦ አንድ የቅዳሴ መጽሐፍ አለው::

## 12.2 መጀመሪያ በቃል ተሰብከው የተጻፉ ሥራዎች[64]

ከእነዚህ ውስጥ በተለያየ ርእሰ ጉዳይ ላይ ያስተማራቸውና[65] በመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ላይ ያስተማራቸው የትርጓሜ ትምህርቶች[66] ዋናዎቹ ናቸው::

### ፩. በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የሰበካቸው ስብከቶች እንደሚከተለው ሊከፈሉ ይችላሉ::

**ሀ. ክሥተት ነክ የሆኑ**

- በመንበሩ ላይ ሲሾም ያስተማረው ትምህርት
- በንጉሡ ሀውልቶች መሰባበር ምክንያት የሰበካቸው ስብከቶች (21)
- በዩትሮጲየስ መውደቅ ምክንያት የሰበከው ስብከት (2)
- ከመጀመሪያው ስደቱ በፊትና በኋላ የሰበካቸው ሁለት ስብከቶች

**ለ. በአጽራረ ቤተ ክርስቲያንና በአጽራረ ሃይማኖት ላይ ያስተማራቸው ትምህርቶች**

- «ስለ መለኮታዊ ባሕርይ አይመረመሬነት» - በአርዮሳውያንና በመንፈቀ አርዮሳውያን ላይ የተሰጡ 12 ትምህርቶች - ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ራሳችንን ወደ መለኮታዊ ምሥጢር ከፍ ከፍ ማድረግና ባሕርዩን መረዳት እንችላለን የሚል እብደት የተጠናወታቸውንና በባዶው ሲኩራሩ የነበሩትን አርዮሳውያንን ከንቱነታቸውንና ባዶነታቸውን በማሳየት አነርሱን ያሳፈረበትና ድል ያደረገበት ድንቅ ሥራ ነው::
- በአይሁዳውያንና አይሁድ ዘመም በሆኑ ክርስቲያኖች ላይ የተሰጡ 8 ስብከቶች - የአይሁዳውያንን በዓል የሚያከብሩትንና በበዓላቸው የሚሳተፉትን፣ እንዲሁም ትንሣኤን ከአይሁድ ፋሲካ ጋር አንድ ቀን የሚያከብሩትን ስህተትነት ይገልጻል::

**ሐ. የግብረ ገብነት (ሞራል) ስብከቶች**

- ለንዑሰ ክርስቲያኖች ከመጠመቃቸው በፊት የተሰጠ ትምህርት
- በአዲስ ዓመት በዓል ላይ ስለሚታዩ ከግረ ገብነት የወጡ ድርጊቶች ላይ ያስተማረው ትምህርት
- ስለ ምጽዋት
- ስለ ንስሐ
- በቲያትር ቤቶችና በትርዒት ቦታዎች በሚካሄዱ ጨዋታዎችና ውድድሮች ላይ ያስተማረው ትምህርት
- ፈተናን በተመለከተ የተሰበኩ ስብከቶች ናቸው::

**መ. በምሥጢራት ላይ የተሰበኩ ስብከቶች**

እነዚህ ብዙዎቹ በጌታችን ዐበይት በዓላት ዕለት የተሰበኩ ናቸው:: ከእነዚህም፦

- በልደት
- በጥምቀት
- በጸሎተ ሐሙስ ስለ ይሁዳ መካድ 3 ስብከቶች
- በስቅለት -2 (አንደኛው የእርሱ መሆኑ አጠራጣሪ ነው)
- በዕርገት
- በበዓለ ሃምሳ የሰበካቸው ስብከቶች ናቸው::

**ሠ. ስለ ቅዱሳንና ሰማዕታት የሰበካቸው**

እነዚህ ብዙ ናቸው:: ከእነዚህም በጣም የሚደነቁት እንጸኪያ ሳለ ስለ ቅዱስ ጳውሎስ የሰበካቸው ሰባቱ ስብከቶች ናቸው:: ከሌሎቹም ውስጥ ስለ ሦስቱ የብሉይ ኪዳን አርአያነት ያላቸው ሰዎች- ኢዮብ፣ አልዓዛርና መቃቢስ የሰበካቸው፣ ስለ ሰማዕታቱ ቅዱስ ባቢላስና ቅዱስ አግናጥዮስ፣ ስለ ቅዱስ ኤዎስጣቴዎስ ዘአንጾኪያ፣ ስለ ቅዱስ መላጥዮስ፣ ስለ ሮማኖስና ስለ በረላም የሰበካቸውን መጥቀስ ይቻላል::

**ረ. በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ክፍሎችና ርእሰ ጉዳዮች ላይ የሰበካቸው በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው ስብከቶች**

እነዚህም በአልዓዛርና በባለጸጋው ላይ የሰበካቸውን ስብከቶች ጨምሮ በጣም ብዙዎች ናቸው::

### 2. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች

መጽሐፍ ቅዱስን የተረጎመባቸው እነዚህ ተከታታይ ሥራዎች ዋናዎቹ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሥራዎች ናቸው::

---

[64] (Oratorical Works)
[65] (Sermons)
[66] (Homilies)

### ሀ. ዛሬም ድረስ ያሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ትርጓሜዎች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል

- በኦሪት ዘፍጥረት ላይ - 67 ሆሚሊ [67]
- ስለ ሐና እመ ሳሙኤል - 5 ሆሚሊ
- ስለ ዳዊትና ሳዖል - 3 ሆሚሊ
- በዖዝያስ ላይ - 6 ሆሚሊ
- በመዝሙረ ዳዊት ላይ - 59 ሆሚሊ
- በትንቢተ ኢሳይያስ ከምዕ. 1-6 - 6 ሆሚሊ

### ለ. ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ትርጓሜዎቹ ደግሞ

- የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜ - 90 ሆሚሊ
- የዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ - 88 ሆሚሊ
- የሐዋርያት ሥራ ትርጓሜ - 55 አምስት ሆሚሊ
- የሁሉም የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ትርጓሜዎች - 250 ሆሚሊ

ሁሉም ትርጓሜዎቹ በጣም ደስ የሚሉና የመጽሐፉንና የኃይለ ቃሉን ውስጣዊ ትክክለኛ መልእክት ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው:: በተለይ ደግሞ የጳውሎስ መልእክታት ትርጓሜዎቹ ራሱን በቅዱስ ጳውሎስ ቦታ አድርጎ እያሰበ ጸሐፊው ሊለው የፈለገው ምን እንደነበረ በትክክል ተረድቶ የቅዱስ ጳውሎስን የውስጥ አሳብ አብራርቶ የገለጠባቸው ድንቅ ትርጓሜዎች ናቸው:: የፔሉዚየሙ ቅዱስ ኢስድሮስ ስለዚህ ሲናገር እንዲህ አለ:- *«ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአቴናውያን የአጻጻፍና የማብራራት ስልት ጽፎ ቢሆን ኖሮ መልእክቱን ይጽፍና ይገልጽ የነበረው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በተጠቀመባቸው ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ነበር::»* ብሏል:: የትርጓሜ ስልቱም እንደ እስክንድርያ ትምህርት ቤት የትርጓሜ ስልትም ከገጸ ንባቡ የራቀና በጣም ምሳሌያዊ የትርጓሜ ስልትን[68] የማይከተል፣ እንደ አንጾኪያ ትምህርት ቤት የትርጓሜ ስልትም እስከ ጽንፍ የደረሰ ንባብና ቁጥር ተኮር ያልሆነ ነው:: በርግጥ በጣም የሚያደላውና የሚከተለው የአንጾኪያን ትምህርት ቤት የትርጓሜ ስልት ነው:: የትርጓሜ ስልቱ የአንጾኪያ ትምህርት ቤት የትርጓሜ

[67] (Homily ) ሆሚሊ - (homilia) ሆሚሊያ ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ቃል ነው:: ይህ ቃል ከኦሪገን ጊዜ ጀምሮ በአንድ የተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ የሚደረግ ወይም የሚሰጥ የማብራሪያ፣ የሐተታ፣ የትንታኔና የትርጓሜ ትምህርት ማለት ሆኗል:: ጌታችንም ይህንን በሚመስል መንገድ አስተምሯል (ሉቃ. 4፥16-20):: ቅዱሳን ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይጠቀሙበት የነበረ የስብከት (የትምህርት) ዓይነት ነው:: ሆሚሊ በአንድ ጊዜ በአንድ ርእስ ጉዳይ ላይ ወይም በተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምንባብ መሠረት የሚሰጠውን ክፍለ ትምህርት የሚገልጽ ጥንታዊ ስያሜ ነው:: ይህ ዓይነት የትርጓሜና የስነ ጽሑፍ ስልት ስለ ጥንቷ ቤ/ክ. ባህል፣ አሠራር፣ ሥርዓት፣ ምሥጢራት አፈጻጸምና ትምህርት ጠቃሚ መረጃዎችና ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች ተገልጸው ለትውልድ የተገኙበት መንገድ ሲሆን ለዚህ ስልትም የመጀመሪያውን ከፍተኛ አስተዋጽ ያደረገው ኦሪገን ነው:: ከታላላቆቹ ሆሚሊስቶች ቅ.አትናቴዎስ፣ ቅ. ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅ.አውግስቲን፣ ጀሮም፣ ኢስድሮስ ናቸው:: በዚህ መጽሐፍ ሆሚሊ የሚለው ክፍለ ትምህርት በሚል ተወራራሽ ቃል ተመልክቷል::

[68] (Allegoric)





ስልት መሠረት የሆነው የዲያድርስ የትርጓሜ ስልት ጥሩ ወካይና መገለጫ ነው:: ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ምሳሌያዊና ዘይቤያዊ የትርጓሜ ስልትንም አልፎ አልፎ ይከተላል:: አተረጓጎሙም በገጸ ንባቡ ዙሪያ ያለውን የአሳቡን መሠረታዊ ጭብጥ ፈልፍሎ በማውጣት ውስጠ ነገሩን እንደ መስታወት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው:: በአጠቃላይ የትርጓሜ ሥራዎቹና ጽሑፎቹ ቢቀዱ የማይነጥፉ የዶግማ፣ የሥነ ምግባርና የልዩ ልዩ ተዛማጅ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ምንጮች ናቸው:: በርግጥም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜና አተረጓጎም ትክክለኛ ግንዛቤና ውቀት ለማግኘት የእርሱን የትርጓሜ ሥራዎች ማንበብ የግድ ይላል::[69] በእውነትም እግዚአብሔር ሐዋርያትን ወንጌል እንዳጻፈ የመተርጎም ሀብትን ደግሞ ለዚህ አባት ሰጥቶታል::

ከእነዚህም ሌላ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጾችና ኃይለ ቃሎች ላይ፣ በቤተ ክርስቲያን የበዓል ቀናት፣ በሐዋርያትና በሰማዕታት የዕረፍት ቀናት ተጋድሎአቸውንና ክብራቸውን የሚመለከት ትምህርት፣ በጣዖት አምላኪዎች ላይ፣ በአይሁዳውያን ላይ፣ አይሁዳዊና አሪታዊ ልማዳቸውን ወደ ክርስትና ይዘው በሚመጡ ክርስቲያኖች ላይ፣ በአርዮሳውዊያን ላይ፣ ሌላም ብዙ ጽሑፎችን ጽፏል፤ ትምህርቶቹ ተጽፈዋል፤ ከዛሬም ደርሰዋል::

የትርጓሜም ሆኑ በተለያዩ ርእስ ጉዳዮች ላይ የተሰጡት ትምህርቶቹ በጥንቱ ግሪክ የተጻፉ ስለሆነ፣ ከዚህም ጋር ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ሲገላበጡ የቋንቋና የአገላለጽ ይላቸው[70] እንዲሁም የአሳብ ፍሰታቸው ብዙ ሳይጎዳ አልቀረም:: ሆኖም ግን ትምህርቶቹና ስብከቶቹ ትውልድን ሁሉ ሲያስተምሩና ሲመክሩ ኖረው ዛሬም ድረስ ሕያው ናቸው:: በውስጣቸው ብዙ ጣዕምና ጠቃሚነት ያላቸው፣ በተነበቡ መጠን እየተወደዱ የሚሄዱ ናቸው:: የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ትክክለኛ ማንነት ማወቅ የሚቻለውም ሥራዎቹን በሚገባ በማንበብ ነው::

ማንኛውንም ሰው በሚገባ ማወቅ የሚቻለው ስለ እርሱ የሚገልጹ ነገሮችን በማንበብና በመስማት በተለይም ደግሞ አስተምህሮዎቹን፣ አስተሳሰቦቹንና በአጠቃላይ እርሱነቱን የሚገልጹ የጽሑፍ ሥራዎቹን፣ ትምህርቶቹንና መልእክታቱን በማንበብ ነው:: ስለሆነም የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ማንነት በመጠኑ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ፣ ከዚህም በላይ ደግሞ ትምህርቶቹ በያዙት ቁም ነገር እንጠቀም ዘንድ ከብዙ ትምህርቹ መካከል የሚከተሉትን ሦስት ትምህርቶቹን እንደሚከተለው ተርጉመን አቅርበናል::

[69] የቤተ ክርስቲያንን ታሪካዊ አመጣጥና ትክክለኛ ሥዕሏንና ገጽታዋን ለማወቅና ለመረዳት፣ እንዲሁም የቀደሙ አባቶቻችን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የነበራቸውን አመለካከቶችና አሳቦች ለማወቅ ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ እስከ 5ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ድረስ የነበሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የጻፏቸውን ጽሑፎችና ያስተማሯቸውን ትምህርቶች በሚገባ ማንበብና መረዳት የግድ ይላል::

[70] (Rhetorical power)

# ክፍል ሁለት

# የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርቶች





## ትምህርት አንድ

### *ወደ ቤተ ክርስቲያን ስላልመጡ ምዕመናን ያስተማረው ትምህርት*

1. ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥታችሁ የቃለ እግዚአብሔርና የቅዱስ ምሥጢር ተካፋዮች ትሆኑ ዘንድ ልባችሁን ለማነሳሣት ብዬ በቅርብ ቀን ተሰፋ አድርጌ ባስተማርኳችሁ ትምህርት ውጤት ያገኘሁ አይመስለኝም፡፡ አሁንም ቤተ ክርስቲያናችን ልጆቿ ቀርተውባታልና፡፡ የመጣችሁትን ደጋግሜ ስለዚህ ነገር በመናገሬ ላበሳጫችሁና ደስ ላላሰኛችሁ ብችልም እኔ ግን አሁንም ስለዚህ ነገር ከመናገር ወደ ኋላ አልልም፤ እነርሱን የምናገራቸው ከስንፍናቸው ያልተላቀቁ በመሆናቸው ሲሆን እናንተን ደግሞ ለወንድሞቻችሁ ድኅነት የእርዳታ እጃችሁን ለእነርሱ ባለ መዘርጋታችሁ ነው፡፡

ስለ ራሴ ወይም ስለ ሌላ ጉዳይ ሳይሆን ከምንም በላይ ለእኔ ውድና ክቡር ስለ ሆነው የእናንተ ድኅነት ስል የማልመችና የማስለች መስዬ መታየት ግድ ሆነብኝ፡፡ ማንም ይህን በክፋም ቢሆን ይውሰደው፤ እኔንም ስለ አንድ ነገር መደጋገም የሚወድ ይበለኝ፤ ሁል ጊዜ ስለ አንድ ነገር በተደጋጋሚ ላለመስማት ስትሉ ለወገኖቻችሁ ታስቡ ይሆናልና፤ ለእነርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣትና የጸጋው ተካፋይ መሆን የሚቻላችሁን ሁሉ ታደርጉ ይሆናልና፡፡

የእናንተን በሃይማኖትና በምግባር ማደግና መበልጸግ ካላየሁ ስለ ትምህርቱ ብታመሰግኑኝ ምን ይጠቅመኛል? እናንተ በሃይማኖት ስታድጉ ካየሁ ከሰማዕያኑ ምስጋና አለመስማትስ ምን ይጎዳኛል? የሰባኪ ክብሩና ምስጋናው ከጭብጨባና[71] ከሙገሣ ሳይሆን ሰማዕያኑ ለጽድቅ ሥራ ከሚያሳዩት መንፈሳዊ ቅናትና የሕይወት ለውጥ ነው፤ በመስማት ጊዜ ከሚደረግ የደስታና የአድናቆት መግለጫ ሳይሆን ዘላቂነት ባለው መልካም ሕይወት ነው፡፡ የቃላት ሙገሳ ከከንፈር እንደ ወጣ ወዲያውኑ በአየር ተበትኖ ይጠፋል፤ የሰማዕያን የሥነ ምግባር መሻሻልና ዕድገት ግን ለሁለቱም፦ ቃሉን ለሚናገረውም፤ ሰምተው ለሚታዘዙትም የማይጠፋና የማያልፍ ዘላለማዊ ዋጋ ያስገኛል፡፡

[71] ሲያስተምር ሰማዕያኑ ከመደሰታቸው የተነሣ ያጨበጭቡ ነበር፤ እርሱ ግን ይህን ልማድ ፈጽሞ ይከለክልና እግባብ አለመሆኑን ይገልጽ ነበር፤ «ትምህርቱን መቀበላችሁን በጭብጨባ ሳይሆን በሕይወታችሁ በተግባር አሳዩኝ» ይላቸው ነበር፡፡

የደስታችሁ ጨዋታና የምትገልጹለት አድናቆት ሰባኪውን በዚህ ዓለም ጥሩ ሰባኪ ሊያሰኘው ይችል ይሆናል፤ የነፍሳችሁ በእምነት መጠንከር ግን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ለመቆም የተሻለ ይረዳዋል። ስለዚህ ማንም የሚያስተምረውን ሰው ቢወደው ማመስገንና ማድነቅን ሳይሆን የሰማዕያኑን ጥቅም ይፈልግ።

ወንድማችንን መርሳት ቀላልና ተራ በደል አይደለም፤ ከባድ ቅጣትን የሚያስከትል ነው እንጂ። መክሊቱን የቀበረው ሰው ሁኔታ ይህን ያረጋግጥልናልና። ይህ ሰው በራሱ ሕይወት አልተነቀፈም፣ ምክንያቱም ስለ ተቀበለው አንድ መክሊት አልተወቀሰም፣ የተሰጠውን መክሊት እንዳለ ሳያበላሽ አስረክቧልና። ነገር ግን የተሰጠውን በአግባቡ ተጠቅሞ ሥራ ላይ ባለ ማዋሉና ባለ ማትረፉ በጌታው ተቀጣ።

ከዚህ የምንረዳው ምንም እንኳ ራሳችን ቅኖችና እንደሚገባ በአግባቡ የምንኖር ብንሆንና ቅዱስ ቃሉን ለመስማት ጥልቅ ፍቅር ቢኖረን እንኳ ለመዳናችን ይህ ብቻ አይበቃንም። የተሰጠን መክሊት ሊበረክት ይገባዋልና፣ መክሊታችን የሚበዛውም ከራሳችን ድኅነት ጋር ለሌሎች ድኅነት የሚሆን የሚቻለንን ነገር ስናደርግ ነው። በምሳሌ የተነገረው ሰው «እነሆ መክሊትህ አለልህ» ማለቱ ራሱን ከጌታው ቁጣና ቅጣት ሊያድነው አልቻለምና፤ «ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው ይገባህ ነበር» ተባለ እንጂ። ማቴ. 25÷27።

የጌታ ትእዛዝ እንዴት ቀላል እንደ ሆነ ትመለከቱ እንድ እለምናችኋለሁ፤ ገንዘብ የሚያበድሩ ሰዎች ተበዳሪው ለማንም ያበድረው፣ ምንም ይሥራበት፣ የሚፈልጉት የተዋዋሉትን ወለድ ማግኘታቸውን ብቻ ነው። ተበዳሪው እንዳሰበው ማትረፍ ባይችል ይህ ለአበዳሪዎቹ ጉዳያቸው አይደለም፤ ያስያዘውን ሀብት ንብረትም ቢሆን ሸጦ እንዲከፍል ያደርጉታል እንጂ። እግዚአብሔር ግን እንዲህ አያደርግም። ከእኛ የሚፈልገው ለለዋጮች አደራ እንድንሰጥ ብቻ ነው፤ ከዚያ በኋላ ለሚከሠተው - ለትርፉ መጠን፣ ገንዘቡ አደራ የተሰጣቸው ሰዎች ስለ መመለስ አለመመለሳቸው ጉዳይ የእኛ ኃላፊነት አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገረው ሰው መምከር እንጂ ማሳመን አይችልምና። ስለዚህም «እናንተን የምጠይቃችሁ አደራ ስለ መስጠት እንጂ ስለ ትርፉ መጠን አይደለም» አለን። ከዚህ የቀለለ ኃላፊነት ምን አለ? ሆኖም ያ አገልጋይ ጌታውን «ጽኑና ጨካኝ» አለው። ሰነፎችና ውለታ ቢሶች እንዲህ ናቸውና፤ ሁል ጊዜ የራሳቸውን ስህተትና ድካም በጌታቸው ማሳበብ ይወዳሉ። ስለዚህም ይህ ሰው ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት በውጭ ወዳለው ጨለማ ተጣለ።





እኛም ይህ ቅጣት እንዳያገኘን ቢቀበሉትም ባይቀበሉትም በወንድሞቻችን ልቡና የምንችለውን ያህል ምክርና የእግዚአብሔር ቃል እናስቀምጥ። ቢቀበሉት ራሳቸውንም እኛንም ይጠቅማሉ፤ ባይቀበሉት ግን ራሳቸው የማይቀርላቸውን ቅጣት ይቀበላሉ፤ የእነርሱ አለማመን ግን በእኛ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ሊያደርስብን አይችልም። ምክር በመስጠት የራሳችንን ድርሻ ተወጥተናልና፤ ባይሰሙ ግን በመናገራችን የምንጎዳው አንዳች ነገር የለም። ባለ መምከራችንና ባለ መናገራችን እንጂ ባለ መሰማታችንና ማሳመን ባለ መቻላችን የሚያሳፍር ነገር የለምና።

ስለዚህ ምናልባት ወንድሞቻችሁ ወደ ቤተ ክርስቲያን የማይመጡትና ሕይወታቸው ያልተስተካከለው እናንተ እንደሚገባ ደጋግማችሁ በቃለ እግዚአብሔር ስላልመከራችኋቸው እንዳይሆን እሰጋለሁ። በተደጋጋሚ በእግዚአብሔር ቃል የሚመከርና የሚገሠጽ ሰው አንድ ቀን ሕይወቱ መለወጡ አይቀርምና። «የማያቋርጥ የውኃ ጠብታ ዐለት ያጎድጉዳል» የሚለው የተለመደ አባባል ይህን ያሳያልና። ከውኃ የለሰለሰ ምን አለ? ከዐለትስ የጠነከረ ምን አለ? ሆኖም ግን የማያቋርጥ ድርጊት ተፈጥሮን ያሸንፋል። ተፈጥሮን ካሸነፈ ደግሞ አእምሮታዊ የሆነ የሰውን ነጻ ፈቃድ በበለጠ ይለውጣል። የምወዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ክርስትና የሕፃናት ጨዋታ አይደለም፣ ምትክና ሁለተኛ ያለው ጉዳይም አይደለም።

2. በበዓላት ቀን የባሕር ስፋት እስኪመስሉ ድረስ ብዙዎች ሲመጡ ዛሬ ግን የዚያ ትንሽ መጠን እንኳ አለመምጣታቸውን ሳስብ ውስጤ ያዝናል። በበዓላት ቀናት ቤተ ክርስቲያን እስክትጠብ ድረስ የሚሞሉት ሰዎች አሁን የታሉ? አሁንም እንደዚያን ጊዜው በቤተ ክርስቲያን ይገኙ ዘንድ ስፈልጋቸው አላገኘኋቸውምና። ምጻኅነት መንገድ መግዝ ከጀመሩት መካከል ብዙዎቹ ጠፍተውኛልና ስለ እነርሱ ተክዤአለሁ። እንዴት ይህን ያህል ወንድሞችን አጣሁ! ስለ ድኅነት በሚያስፈልገው ነገር ልናገኛቸው የምንችለው በጣም ጥቂቶች ናቸው። የቤተ ክርስቲያን ሰውነት ብዙው የሞተና የማይንቀሳቀስ በድን ሆኗልና። «ይህ ለእኛ ምን ጉዳያችን ነው?» ትሉ ይሆናል። ዋና ጉዳያችሁ ነው እንጂ።

ወንድሞቻችሁን መምከር፣ መምራት፤ ከድካማቸው እንዲበረቱ፣ ከጥፋታቸው እንዲመለሱ ልታደርጉ የምትችሉትን የመጨረሻ ደረጃ ድረስ የማድረግና ወደዚህ ይዛችሁ የመምጣት ኃላፊነት አለባችሁ። አንድ ክርስቲያን ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌላውም ጠቃሚ መሆን እንዳለበት ክርስቶስ በግልጽ አስተምሯልና፡ «እናንተ የዓለም ጨው፣ እርሾ እንዲሁም ብርሃን ናችሁ በማለት። ማቴ. 5+13-14 ፤ 13+33። እነዚህ

ነገሮች ጠቃሚነታቸው ለሌሎች ነውና:: መብራት በጨለማ ሳለ እንጂ ለራሱ አያበራም:: አንተንም ክርስቶስ ብርሃን ያደረገህ ለራስህ ብቻ በብርሃኑ ደስ እየተሰኘህ በጨለማ ያሉትን እንድትረሳቸው አይደለም፤ በጨለማና በሞት ጥላ ሥር ያሉትን ፈልገህ እንድታመጣቸው እንጂ:: በጨለማ ሳለው የማያበራ «ብርሃን» ብርሃንነቱ ምኑ ላይ ነው? ብርሃን መባሉስ ምን ጥቅም አለው? ማንንም የማይጠቅምና ደጠፉትና ወደ ሕይወት የማያመጣ ክርስቲያንስ ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው

ጨውም የሚያጣፍጠው ለራሱ አይደለም፤ አልጫ የሆነውን የሌሎችን ምግብ ጭምር ሟሙቶ ያጣፍጣል እንጂ:: እንዲሁም የራሱን ሳይሆን የሰዎችን ቁስል በማድረቅና በማጋጠም ከመበላሸትና ከማመርቀዝ ይከላከላል:: አንተንም እግዚአብሔር መንፈሳዊ ጨው አድርጎሃልና የቆሰሉትንና የታመሙትን የክርስቶስ አካላት ማለትም ከቤተ ክርስቲያን የራቁትን ወንድሞች ከቁስልና ከመበስበስ እንደ ማውጣት ቁስንፍናቸውና ክርስቶስን ከመዘንጋታቸው ደዌ አውጥተህ ከሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን አካላት ጋር አንድ አድርጋቸው:: አንተን «እርሾ» ያለህም ለዚህ ነው:: እርሾ ራሱን አያቦካምና:: ነገር ግን ምንም መጠኑ ትንሽ ቢሆን ብዙ የሆነውን ዱቄት ያቦካዋል:: እናንተም በቁጥር ትንሽ ብትሆኑም በእምነታችሁ ጥንካሬና ለእግዚአብሔር ባላችሁ ቅናት ኃይለኞችና ብዙዎች ሁኑ:: እርሾው መጠኑ ጥቂት መሆኑ ብዙዉን ዱቄት ከማቡካት እንደማያግደው፤ ነገር ግን በተፈጥሮው እርሾ ከመሆኑ የተነሣ የእርሾነቱን ሥራ እንደሚሠራ ሁሉ እናንተም እንደ እምነታችሁ ጥንካሬና ለእግዚአብሔር እንዳላችሁ ቅናት መጠን የቁጥራችሁ ትንሽነት ሳያግዳችሁ ብዙዎችን መመለስ ትችላላችሁ::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕዝቡ ሲበዛ የሚፈጠረውን ሙቀት እንዲሁም ኃይለኛ ቃጠሎ ያለውን የበጋ ወቅት እንደ ምክንያት ያቀርቡላችሁ ይሆናል:: እንዲህ ሲሉ እሰማለሁና:- «ሙቀቱ የሚያፍን ኃይለኛ ነው፣ ፀሐይዋ ታቃጥላለች፤ በዚያ ሕዝብ በበዛበት ተጨናንቀን መታፈንና በላብና በሙቀት መጨነቅ አንችልም::» እንዲህ ያለው ምክንያት ራስን በጣም ከማለስለስና መንፈስን ከማድከም የሚመነጭ ስለሆነ፤ እመኑኝ፤ እኔን በጣም ያሳፍረኛል:: ለእንዲህ ዓይነቱ ደካማ ምክንያት መልስ የማያስፈልገው ቢሆንም ለእነርሱ ጥቅም ስንል መመለስ አስፈላጊ ነው:: በእሳት መሀል ሆነው ዙሪያቸውን በእሳት ነበልባል ተከበው ወላፈኑና ነዲዱ አፋቸውን፣ ዓይናቸውን፣ እስትንፋሳቸውን ሳይቀር ከብቦት እያለ





እንኳ ከሥነ ፍጥረቱ ጋር በአንድነት በደስታና በምስጋና ዝማሬያቸውን ለልዑል እግዚአብሔር ያቀረቡትን ሦስቱን ወጣቶች አስታውሳቸዋለሁ::

ከእነዚህ ከሦስቱ ወጣቶች ጋርም በአናብስት ጉድጓድ የተጣለውን ነቢዩ ዳንኤልን አስታውሳቸዋለሁ:: ዳን. 6፥24:: እርሱንም ብቻ ሳይሆን በገመድ አድርገው ጭቃ በሞላበት ጉድጓድ ውስጥ የጣሉትን ነቢዩን ኤርምያስንም አስታውሳቸዋለሁ:: ኤር. 38፥5-6:: ከጉድጓድ ስንወጣ ደግሞ እነዚህን ሙቀትንና መጨናነቅን እንደ ምክንያት የሚያቀርቡትን ሰዎች ጳውሎስና ሲላስ እጃቸውና እግራቸው በጥብቅ ታስሮ በሌሊት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ወዳደሩበት ወደ እስር ቤት በሕሊና ልውሰዳቸው:: የሐዋ. 16፥19-34::

በእሳት ውስጥና በአናብስት ጉድጓድ ውስጥ፣ በአራዊትና በጭቃ ጉድጓድ የተጣሉት፣ በእስር ቤት እግር ከእጅ በጭንቅ የታሰሩትና ብዙ መከራ የተቀበሉት ቅዱሳን ስለ ደረሰባቸው ነገር ምንም አላጉረመረሙም፣ ሁል ጊዜ ምስጋናና ዝማሬ ከማቅረብ በስተቀር፣ እግዚአብሔርን ከማመስገን በስተቀር ፈጽሞ አላማረሩም:: ከእነዚህ መከራዎች አንዱ ያልደረሰብን እኛ ግን ቤተ ክርስቲያን ተገኝተን ለሕይወታችን የሚጠቅመንን ቅዱስ ቃሉን ሰምተን ከምሥጢራት ተካፍለን ለመሄድ ለትንሽ ጊዜ ያውም መጠነኛ የሆነን ሙቀትና ድካም እንደ ምክንያት እያቀረብን ወደ ገበያዎችና ሌሎች ቦታዎች በከንቱ እንባዝናለን:: ውስጣችንን የሚያረካና የሚያድስ መለኮታዊ ጸጋ በገፍ ባለበት ሙቀትን ምክንያት ታደርጋለህን? ክርስቶስ *«እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል»* ብሏልና:: ዮሐ. 4፥14:: እንዲሁም *«በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል»* ብሏል:: ዮሐ. 7፥38:: እንዲህ ያለ የሚያረካ መንፈሳዊ ጉድጓድና ወንዝ ከውስጥህ እያለህ አፍአዊ ሙቀትን በመፍራትና በመሳቀቅ ከቤተ ክርስቲያን ትቀራለህ?

ብዙ ሁካታ፣ ግፊያና መጨናነቅ ካለበት ከገበያ ቦታ ስለ እነዚህ ምክንያቶች ትቀራለህን? ወደ ገበያ ለመሄድ ስታስብ የፀሐዩ ማቃጠል፣ የሰው ብዛት፣ ግፊያውና መጨናነቁ ለምን አላስቀረህም? ከገበያ ቦታ ይልቅ ቤተ ክርስቲያን ያለው ሁኔታ በቁሳዊ ምቾትና ፀጥታ አይሻልምን? የተከለለ ቦታ ውስጥ ስለ ሆንህ አየሩ ቀዝቀዝ ያለ፣ የፀሐዩም ቃጠሎ በቀጥታ የማያገኝህ፣ ሙቀቱም መጠነኛ ነውና:: እዚያ ግን ፀሐይዋ በሁሉም አቅጣጫ ጠንካራ ናት፣ ብዙ መጨናነቅ

አለ፤ አቧራና ተቢያ ሞልቷል፤ በአጠቃላይ ከዚህ ይልቅ የማይመቹ ብዙ ነገሮች አሉ።

3. እነዚህ አሁን እያልኳቸው ያሉትን ነገሮች የምናገረው ከእነርሱ ይልቅ ከነዋመ ሀኬት ሳልቀሰቀሳችኋቸውና ወደዚህ የድኅነት መካን ላላመጣችኋቸው ለእናንተ ነው:: በአንድ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች አንድ የጋራ ሥራ ሲሠሩ ሲሉ አብረዋቸው የሚሠሩትን ባልደረቦቻቸውን ሁሉ ይጠራሉ፤ እናንተ ግን ወደዚህ መንፈሳዊ አገልግሎት ስትቀርቡ በስንፍናችሁና በቸልተኝነታችሁ ምክንያት ከዚህ በረከትና ጸጋ እንዳይሳተፉ ወንድሞቻችሁን ትተዋቸዋላችሁ:: «እነርሱ ካልፈለጉ ምን ማድረግ እንችላለን?» ትላላችሁ::

እናንተ በተደጋጋሚ ሳታቋርጡ በመወትወት እንዲፈልጉ አድርጓቸው:: እናንተ ሙጭጭ ብላችሁ ለራሳቸው ጥቅም ስትወተውቷቸው ሲያዩ በእርግጥ ይፈልጉታል:: ልጆቻቸው አብረዋቸው ያልመጡ ስንት አባቶች እዚህ አሉ? ከልጆቻችሁ ቢያንስ የተወሰኑትን እንኳ ማምጣት ያን ያህል አስቸጋሪ ነውን? በውጭ ለቀሩት አለመምጣት ምክንያቱ የራሳቸው ስንፍና ብቻ ሳይሆን የእናንተም ግዴለሽነት መሆኑ በዚህ ይታወቃል::

ስለዚህ ከአሁን በኋላ እያንዳንዱ ሰው ቢያንስ ከቤተሰቡ አባላት ጋር እየሆነ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይምጣ:: አባት ልጁን፤ ልጅ አባቱን፤ ባሎች ሚስቶቻቸውን፤ ሚስቶችም ባሎቻቸውን፤ አሠሪ ሠራተኛውን፤ ወንድም ወንድሙን፤ ጓደኛ ጓደኛውን፤ ጓደኞቻችንን ብቻም ሳይሆን ጠላት የምንላቸው ቢኖሩ እንኳ ወደዚህ ለሁላችን ወደ ተዘጋጀ የሕይወት መዝገብ እንዲመጡ እንቀስቅሳቸው፤ እንገፋፋቸው:: ጠላትህ እንኳ ቢሆን ለእርሱ ድኅነት ስታስብና ስትጨነቅለት ሲያይህ ጥላቻውን እርግፍ አድርጎ ይተዋል::

«ሰንበታቸውን በፍጹም ጥንቃቄ በሚያከብሩና ከጧት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ከማንኛውም ዓይነት ሥራ ከሚታቀቡ ከአይሁድ እንኳ ታንሳለህን?» በለው:: በማዘጋጀት ቀን (ዓርብ) ፀሐይ ልትገባ ስታቆለቁል ካዩዋት ማንኛውንም ዓይነት ሥራ ያቆማሉ፤ ንግዳቸውን ይዘጋሉ:: ከምሽት በፊት ዕቃ የገዛቸው ሰው ኖሮ ዋጋውን ማታ ቢያመጣላቸው አይቀበሉትም:: ሕጋቸውን ከሚያፈርሱ ምንም ዓይነት ገበያና ትርፍ ቢያመልጣቸው ይመርጣሉ::

ታዲያ አይሁድ ጊዜው ያለፈበትንና መጠበቁ ምንም ዋጋ የሌለውን ይልቁንም የሚያስጎዳቸውን ሕግና ሥርዓት እንዲህ አጽንተው ሲጠብቁ





ለእነርሱ የተሰጠው ምሳሌና ጥላ ሳይሆን እማናዊውን ክብርና ጸጋ ያገኘህ፤ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን ታይ ዘንድ የተመረጥክ፤ ለሰማያዊ መንግሥት ዜግነት የተሰጠህ አንተ ጊዜው ያለፈበትን ነገር የሙጥኝ ብለው አጥብቀው ከያዙት ጋር እንኳ የሚስተካከል ቅንዓትና ትጋት አይኖርህምን? እውነቱን የያዝህ አንተ ስህተቱን ከያዙት በጽናትና በቅንዓት አንሰህ ትገኛለህን? ያውም እዚህ የምትቆየው ለተወሰነ ሰዓታት ነው::

ታዲያ የተወሰኑ ሰዓቶችን መለኮታዊ ቃልን ለመስማት ማዋል ሊከብድህና ሊበዛብህ ይገባልን? ይህን ላለማድረግህ ከተጠያቂነት ነጻ ሊያደርግህ የሚችል ምን ዓይነት ነገር ይኖራል? ተቀባይነት ያለው ምን ዓይነት ምክንያት ማቅረብ ትችላለህ? ሕይወቱን ለሰጠው ለፈጣሪው እርሱ ከሰጠው ብዙ ሰዓት ውስጥ የተወሰነውን ለመስጠት ያልፈለገን ሰው ምን ዓይነት ምክንያት ይቅርታ ሊያስገኝለት ይችላል? የዓለማዊ ጉዳዮችንና ሥራዎችን መብዛትና አስቸኳይነት ሽህ ጊዜ እንደ ምክንያት ቢያቀርብ ይህን ያህል ግድ የለሽና ሰነፍ የሆነ ሰው ይቅርታ ያገኝ ዘንድ አይችልም::

እዚህ መጥተህ እግዚአብሔርን ለአምላክነቱ እንደሚገባ አምልከህ ከዚያ በኋላ ወደ ሥራህ ብትሄድ የምትሠራው ሥራ የተባረከና የሠመረ እንደሚሆንልህ አታውቅምን? የሚያስጨንቅህ የዚህ ዓለም ጉዳይ አለብህ? እዚህ በምታሳልፈው ጊዜ የእግዚአብሔርን ርዳታና ምሕረት ታገኝ ዘንድ፤ በመረጋጋትና በመጽናናት መንፈስ ሆነህ ትሄድ ዘንድ ስለዚህ ምክንያት ወደዚህና:: እርሱ ኃይልህና ጋሻህ ይሆን ዘንድ፤ በሰማያዊ ሥልጣን በመጠበቅ ለጠላቶችህ ለአጋንንት የማትሸነፍ ትሆን ዘንድ ወደዚህ ወደ ጸጋው ዙፋንና:: በአባቶች ከሚደርሰው ጸሎት ሱታፌ ካለህ፤ በማኅበር ጸሎት ከተሳተፍክ፤ ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ከሰማህ፤ የእግዚአብሔርን ርዳታ ካገኘህ፤ እነዚህን መሣሪያዎች ከታጠቅህ የትም ብትሄድ እንዳንተ ያሉ ሥጋ የለበሱ ጠላቶችህ ክፉዎች ሰዎች ይቅርና ዲያብሎስ ራሱ ፊትህን ማየት አይችልም:: ነገር ግን ከቤትህ እንደ ተነሣህ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሳትመጣ ወደ ገበያ፤ ወደ ሥራ፤ ወዘተ ብትሄድ ብቻህን ያለ ምንም መንፈሳዊ ትጥቅና ጸጋ እግዚአብሔር ስለምትሆን ሁሉም ነገር በአንተ ላይ ይበረታብሃል፤ ጠላቶችህም በቀላሉ ያጠቁሃል:: በቤታችን ውስጥም ሆነ በውጭ ብዙ ነገሮች እንደ ጠበቅነው ሳይሆን በተቃራኒው የሚሆኑብን አስቀድመን ለመንፈሳዊው ነገር ቅድሚያ ስላልሰጠንና ሌላውን የዚህ ዓለም ነገር ከዚያ በኋላ ማድፈግ ሲገባን እኛ ግን ቅደም ተከተሉን ስላገላበጥነው ነው:: ስለዚህ ምክንያት የነገሮች ትክክለኛ

ቅደም ተከተልና አቀማመጥ ተዛብቷል፤ ጉዳዮቻችን ዝብርቅርቃቸው ወጥቷል።

ክብረ በዓል ሲሆን የከተማው ሰው ሁሉ ማንም የሚጠራውና የሚቀሰቅሰው ሳይኖር ይመጣል፤ ሆኖም ክብረ በዓሉ እንዳለፈ ቀኑን ሙሉ ልሳናችን እስኪታክት ድረስ ትመጡ ዘንደ ብንጠራ እንኳ ጉዳዩ ብሎ የሚሰማን የለም። ይህን ሳስተውለው የሚሰማኝን ሐዘን ምን ያህል እንደ ሆነ ትገነዘቡልኛላችሁ? ይህን ነገር በሕሊናዬ ሳመላልሰው በጣም እያዘንሁ ለራሴ እንዲህ አልሁ፦ ሁሉንም ነገር የምታደርጉት በልማድ ብቻ ከሆነና ከማስተምራችሁ ትምህርት የተነሣ ትንሽ እንኳ የተሻላችሁ ካልሆናችሁ የትምህርተና የምክር ጥቅሙ ምንድን ነው? በበዓላት ጊዜ ለመምጣት ከእኔ ምክርና ጥሪ አትፈልጉም፤ እነዚያ የበዓላት ቀናት ሲያልፉና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድትመጡ ስጠራችሁ ደግሞ አትመጡም። ታዲያ በልማድ እንጂ በተማራችሁት ትምህርት መሠረት ማድረጋችሁ የታለ?

4. ምናልባት እነዚህን ነገሮች ከሚሰሙት ብዙዎቹ ሊያዝኑና ደስ ሳይላቸው ይችላል። የሰነፉ ሰው ስሜት ግን እንዲህ አይደለም። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ ለራሳቸው ድንነት ግዴለሽነታቸውን እርግፍ አድርገው ይተው ነበር። ከቤተ ክርስቲያን ቀርታችሁ ካጣችሁት አንፃር በምትሠሩት ሥራ ምን አተረፋችሁ? እዚህ በምታጠፉት ጊዜ የምታተርፉትን ያህል ምንም በፍርድ ቤትም ሆነ በገበያ ቦታ፣ በስብሰባም ሆነ በሥራ ቦታ፣ በቤተ መንግሥት እንኳ ቢሆን ልታገኙ አትችሉም። እዚህ ለሚመጡ የምናደርግላቸው በማንኛውም ሥራም ሆነ በየትኛውም ቦታ ሊገኝ የማይችል ሰማያዊ ነገር ነውና። ምሥጢራቱን የምንፈጽመውም እኛ በራሳችን ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው።

እዚህ የሚመጡ ከዚህ ዓለም ሥልጣንና ግዛት የበለጠ የሚያገኙት ነገር ምንድን ነው? ውሳጣዊ ስሜቶቻቸውን እንዲገዙ፣ ክፉ ምኞትን እንዲቆጣጠሩ፣ የቁጣ መንፈስ ድል እንዳያደርጋቸው፣ ክፉ ፈቃድ እንዳይሰለጥንባቸው፣ የውዳሴ ከንቱን አሳብ እንዲያሸንፉ ይማራሉ፣ ይሰለጥናሉና። ግምጃ ለብሶ ዘውዱን ደፍቶ በመንበሩ ላይ የተቀመጠ ንጉሥ፣ በክፉ ምኞትና በርኩሰት አሳቦች ላይ ይገዛ ዘንድ ርቱዕ የሆነ የሕሊናውን ሚዛን በእነዚህ ላይ ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሰውን ያህል አይከብርም። በዚህ ዓለም ሌሎችን ሰዎች የገዙ ብዙዎች አልፈዋል፤ የራሳቸውን ክፉ ፈቃድ ድል አድርገው የገዙ ግን ጥቂቶች ናቸው። *«ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይሻላል፤ በመንፈሱ ላይ የሚገዛ ከተማን ከሚወስድ ይበልጣል»* እንደ ተባለ። ምሳ. 16+32።





ነፍስ በሥጋ ምኞትና በኃጢአት ተማርካ እያለ ሰውነት በወርቅ የተለበጠ ልብስ ቢለብስና አክሊል ቢደፋ ጥቅሙ ምን ላይ ነው? ሰውነትን የምትመራውና የምታስተዳድረው ነፍስ አሳዛኝ በሆነ የኃጢአት የባርነት ቀንበር ሥር ወድቃ ሳለ ውጫዊ ነጻነት ብቻ ምን ይጠቅማል? ኃይለኛ የሆነ ሕመም ወደ ውስጥ ገብቶ ከተሰራጨና ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎችን ካጠቃቸው የውጭው የሰውነት ክፍል ጉዳቱ ለጊዜው ያን ያህል ጎልቶ ባይታይበትና እንደ ውስጠኞቹ ተጠቅቶና ተጎድቶ አለመታየቱ ምን ጥቅም አለው?

ነፍሳችንም ከውስጥ በሚመነጩ ክፉ ምኞቶችና ራስን አለመግዛት ምክንያት ከታመመች ውጫዊ ገገርነትና ሀብት፣ ራሱ የንጉሥነት መንበረ ሥልጣን ቢሆን እንኳ ምንም ጥቅም የለውም። የሕሊና የማሰብ ኃይልና ራስን የመግዛት ሚዛን በውሳጣዊ ምኞቶች ድል ሆኖ ከመንበሩ ተፈናቅሎ እነርሱ ለሚያመጡበት ነገር ሁሉ የታዘዘ ደጅ ሲጸናቸውና ሲታዘዛቸው ይኖራልና። ይህ እንዳይሆንብን የሥጋ መሻትን እንድንቆጣጠርና ለኃጢአት ተገዢዎች እንዳንሆን፣ ምክንያታዊ ያልሆነውን ከውስጥ የሚመነጭ ኃይልና ግፊት እንድናስወግድ፣ ከዚህ ዓለም ገዢዎች ግዛት የበለጠ ግዛት ገንዘብ እንድናደርግ ነቢያትና ሐዋርያት በሁሉም አቅጣጫ ተባብረው ይመክሩናል።

ስለዚህም ራሳቸውን ለወንድሞቻቸው ከማሰብና የሚጠቅማቸውን ከማድረግ ውጭ ያደረጉ ሰዎች ራሳቸውን ጎድተዋል። በሕግ *«በእግዚአብሔር ፊት ባዶ እጃችሁን አትታዩ»* ተብሏልና። ዘጸ. 23+15። ይህም ማለት ወደ ቤተ መቅደስ ስትገቡ መሥዋዕት ሳትይዙ አትግቡ ማለት ነው። ወደ እግዚአብሔር ቤት መሥዋዕት ሣይዙ መግባት ተገቢ ካልሆነ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ከወንድሞቻችን ጋር ልንመጣ የበለጠ ይገባናል። ነፍሳትን ይዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመምጣት መሥዋዕትና መባዐ ከዚያ እጅግ የበለጠ ነውና። ሰዎች ያሰለጠኗቸው ርግቦች በተላኩ ጊዜ የጠፉትን እንዴት እንደሚፈልጉ አላየህምን? እኛም እንዲሁ እናድርግ። አእምሮ የሌላቸው እንስሳት የራሳቸውን ወገን ሲፈልጉ እውቀትና ጥበብ የተሰጠን እኛ የጠፉ ወገኖቻችንን ባንፈልግ ምን ምክንያት ይኖረናል?

ቀደም ብዬ እንደ ነገርኳችሁ እያንዳንዳችሁ ወደ ጎረቤቶቻሁ ቤት ሂዳችሁ እስኪወጡ ጠብቃችሁ ወደ እናታቸው ይዛችኋቸው ኑ፣ ረብ ጥቅም ወደ ሌላቸው ወደ ቴአትርና ልዩ ልዩ ትርዒቶች የሚሄዱ ሰዎች ቀጠሯቸውን ጠብቁጡ በጧት እየተጠራሩ ተሰባስበው

የሚሄዱትን ምስሏቸው:: እነርሱ ለማይረባ ነገር ቀጠሯቸውን ጠብቀው እየተጠሩ ከሄዱ ወደ ሰማያዊ ጸጋ የተጠራን እኛማ እንዴት ተጠራርተንና ተሰባስበን ልንመጣ ይገባን ይሆን? ሆኖም ይህን ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ብናገርም ምንም ሰውጥ ማምጣት አልቻልኩም:: ስለዚህም እናንተን በዚህ ጉዳይ ላይ ማሳመን እስክችል ድረስ አሁንም ቢሆን ደጋግሜ ከመናገር ወደ ኋላ አልልም:: ወደ ተግባር ካልተለወጠ መስማት ብቻ ምንም አይጠቅምምና::

ስለ አንድ ነገር ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ እየተነገረን ነገር ግን ያን ነገር የማናደርገው ከሆነ አይጠቅመንም ብቻ ሳይሆን ቅጣታችንን ያከብደዋል:: ቅጣቱ ከባድ እንደሚሆንም መድኃኒታችን ስለዚህ ጉዳይ የተናገረውን እንስማ፣ *«እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸው ነበር፤ አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም::»* ዮሐ. 15፥22:: ሐዋርያውም *«ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና»* ይላል:: ሮሜ 2፥13::

እነዚህን ሰማዕያኑን በተመለከተ ተናገረ:: ተናጋሪውን በተመለከተ ደግሞ እርሱም ሕይወቱና ድርጊቱ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር የሚሄድ፣ ተግባሩ ከንግግሩ ጋር የተስማማ ካልሆነ በስተቀር በማስተማሩ ብቻ ምንም ነገር እንደማያገኝ ሲገልጽ ነቢዩ *«ኃጢአተኛውን እግዚአብሔር አለው፣ ለምን አንተ ሕጌን ትናገራለህ? ኪዳኔንም በአፍህ ለምን ትወስዳለህ? አንተ ተግሣጼን ጠልተህ፣ ቃሎቼንም ወደ ኋላ ጥለህ ሳለ»* ይለዋል:: መዝ. 49፥17-18::

በማስተማራቸው ብቻ ትልቅ *ሥራ* የሠሩ ለሚመስላቸው ሰዎች ስለዚሁ ጉዳይ ሐዋርያው ሲናገር እንዲህ ይላል:- *«የዕውሮች መሪ፣ በጨለማ ላሉ ብርሃን፣ የሰነፎችም አስተማሪ፣ የሕፃናትም መምህር እንደ ሆንህ ለራስህ ብትታመን፤ እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን?»* ሮሜ 2፥19-21:: የተነገረውን ስምተን እስካልተገበርነው ድረስ እኔን መናገሬ፣ እናንተንም መስማታችሁ በራሱ ምንም አይጠቅመንም፤ እንዲያውም ፍርዳችንን ያከብድብናል:: ስለዚህ የልቡናችንንና የመንፈሳችንን ቀራጥነት በመስማት ብቻ አንገድበው:: የተነገረውን በሥራችን እንግለጠው እንጂ:: ቅዱስ ቃሉን ለመስማት ጊዜ መስጠት ትልቅ ነገር ነው፤ ሆኖም ከመስማት የሚገኘው ጥቅም አብሮት ከሌለ ይህ መልካም የሆነ ነገር ዋጋ ቢስ ይሆናል::

ስለዚህ መሰብሰባችን በከንቱ እንዳይሆን አስቀድሜ «ወንድሞቻችሁን ወደ እኛ ይዛችኋቸው ኑ፣ ከቤተ ክርስቲያን ቀርተው በየጎዳናው





የሚዞሩትን ምከሯቸው፣ በቃል ብቻ ሳይሆን በሕይወታችሁም ምከሯቸው» እንደምላችሁ አሁንም በፍጹም ትጋት ይህን ታደርጉ ዘንድ እናንተን ከመማፀን ወደ ኋላ አልልም:: በሕይወታችንና በድርጊታችን የሚደረግ ትምህርትና ምክር የበለጠ ኃይል ያለው አስተማሪ ነውና:: ቃል እንኳ ባትናገሩ ከዚህ ከቤተ ክርስቲያን ስትመለሱ በገጽታችሁ፣ በአነጋገራችሁ እና በአጠቃላይ ሁኔታችሁ ምን ያህል እንደ ተጠቀማችሁና ጸጋና በረከት ይዛችሁ እንደ መጣችሁ ለቀሩት ሰዎች ለማሳየትና እነርሱን ለመምከር በቂ ነው::

ከቤተ ክርስቲያን ስንመለስ በአስተሳሰባቸው ሰማያዊነትና ምጥቀት፣ በአነጋገራቸው ልዝብነት፣ ሁሉንም ነገር እንደሚገባና በአግባቡ በማድረግ ልክ ከሰማይ እንደ ወረዱ ሰዎች ሆኖ መመለስ ይገባናልና:: ሚስት ባሏን፣ አባት ልጁን፣ ጠላት ጠላቱን ከጉባኤ ሲመለስ ሲያዩ የእናንተን ሁኔታ በማየት እዚህ በመምጣታችሁ ያገኛችሁትን ጸጋና ጥቅም ከፊጽታችሁና ከሁኔታችሁ ማንበብ እንዲችሉ መሆን ይጠበቅባችኋል:: እናንተ ከፊት ይልቅ ገራሞች፣ ደጋጎች፣ አስተሳሰባችሁ የበሰለ እና ሃይማኖተኛነታችሁ የጨመረ ሆናችሁ ሲያዩ ነው ይህን ሊገነዘቡ የሚችሉት:: ወደ ቅዱስ ምሥጢር (ቅዱስ ቁርባን) የቀረባችሁ ምን ያህል ጸጋና ክብር እንዳገኛችሁ አስተውሉ:: ከእነ ማን ጋር ሆናችሁ ምሥጢራዊና ረቂቅ ምስጋና እንደምታቀርቡ፣ ከእነ ማን ጋር ሆናችሁ እንደምትዘምሩ ልብ አድርጉ::

ከነገደ ሱራፌል ጋር ኅብረት ያገኛችሁ መሆናችሁን፣ የሰማያዊ አገር ዜግነት ያገኛችሁ መሆናችሁን፣ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ» እያሉ ከሚዘምሩ ከመላእክት ማኅበር አባልነት ማግኘታችሁን፣ ከጌታ ጋር ቀርባችሁ መነጋገራችሁንና ከንጉሠ ሰማይ ወምድር ከክርስቶስ ጋር መሆናችሁን በሕይወታችሁ አስተምሯቸው:: ራሳችንን እንዲህ ከገዛንና ሕይወታችንን እንደሚገባ ከመራን ወደ ቀሩት ወንድሞቻችን ስንሄድ ብዙ ቃላት መናገር አያስፈልገንም:: እኛ ካገኘነው ጥቅም እነርሱ ምን ያህል እንደ ቀረባቸውና እንደ ተጎዱ ራሳቸው ያውቁታል፣ እነዚህን በአንተ የሚያዩዋቸውን መልካም ነገሮች ለራሳቸው ለማግኘት ሲሉ ፈጥነው ወደዚህ ይመጣሉ:: የአንተ የነፍስ ንጽሕና ከውስጥህ ሲያበራ ሲያዩ ምንም ያህል ሰነፎች ቢሆኑ እንኳ ልባቸው መነካቱ አይቀርም:: አፍአዊና ሥጋዊ ውበት እንኳ የሚያዩትን የሚያስደስት ከሆነ የነፍስ ውበት በበለጠ ሁኔታ ተመልካቹን መማረኩና እርሱን ለመምሰል ማነሳሳቱ አይቀርም:: ስለዚህ ውስጣችንን በቅድስና ለማስዋብ እንነሳ፣ እዚህ የሚነገረውንም እናስተውል::

ከዚህ ስንወጣ እዚህ የተማርነውን የምናስታውስበትና በተግባር ላይ የምናውልበት የሥራ መስክ ነውና:: እንደ ተወዳዳሪ በውድድር በታ ድል ለማስመዝገብና ውጤት ለማግኘት አስቀድሞ በልምምድና በሥልጠና ጊዜ ያጠናቸውን ስልቶችና ትምህርቶች በተግባር እንደሚያሳይ እኛም እዚህ የሰማናቸውን ነገሮች በሥራችን በማሳየት ከእኛ ውጭ ላሉት የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃድ ልናሳያቸው ይገባል:: ከዚህ በወጣችሁ ጊዜና ዲያብሎስ በቁጣ ወይንም በውዳሴ ከንቱ ወይንም በአመንዝራነት ወይንም በትዕቢት ወይም በሌላ በማንኛውም ነገር ሊያጠምዳችሁ ቢሞክር እዚህ የተማራችሁትን ቃል በማስታወስ የእርሱን ወጥመድ በቀላሉ ስብራችሁ ታልፉ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን የምትማሩትን ነገር ልብ ብላችሁ ያዙ::





# ትምህርት ሁለት

## አጋንንት በሰው ሕይወት ላይ ሥልጣን እላቸው ስለሚሉ ያስተማረው ትምህርት

### መግቢያ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሦስት ክፍል ያስተማራቸው እነዚህ ተከታታይ ትምህርቶች በሕይወት ዘመኑ ከብዙ ሰዎች ይሰማቸው የነበሩና እርሱ ግን አጥብቆ ስህተትነታቸውን ይናገርባቸው በነበሩ የተለመዱ አስተሳሰቦች ላይ ነው:: የሞራል ውድቀትና ሕገ ወጥነት ተንሰራፍቶ በነበረበት በዚያ ዘመን (ዛሬም ቢብስበት እንጂ አልተሻለውም) በራሳቸውም ሆነ በሌሎች የሚታየውን ክፋትን[72] ለመቋቋም አለመቻል፣ «ይህ ዓለም ለአጋንንት ግዛት ተሰጥቷል፣ አለዚያም ማንም ምንም ሊያደርገው በማይችለው በዕድሉ (የአርባ ቀን ዕድል) ላይ ተወስኗል» በሚል አስተሳሰብ ለጥፋታቸው ራሳቸውን ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ ይሞክሩ ነበር:: ሰውን «እኔ የአርባ ቀን ዕድሌ ነው፣ ምንም ማድረግ አልችልም፣ አጋንንትን መቋቋም አልችልም» እያለ ራሱን ለሰሜቱ ኃይል አሳልፎ የሚሰጠውን ይህን አደገኛ አስተሳሰብ ለመቃወም የሰውን የፈቃድ ነጻነት፣ የሕሊና ተጠያቂነትንና ፈተናን ለቋቋም እንደሚቻልና ለዚህም ምን ማድረግ እንደሚገባ ለማሳየት ይህንን ትምህርት አስተማረ::

በዚህና በሌሎቹም ትምህርቶቹ አበክሮ የሚቃወመው ነገር "ክፋት (ኃጢአት) የሰው የተፈጥሮው (የባሕርዩ) ነው" የሚለውን የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው:: ክፋት የተፈጥሮ ባሕርያችን ቢሆን ኖሮ፣ ይላል፣ እንደ ተፈጥሮ ፍላጎቶቻችንና ዝንባሌዎቻችን ይሆን ነበር እንጂ ሊሻሻልና ሊስተካከል፣ እንዲሁም ሊቀርና ሊወገድ አይችልም ነበር:: በተፈጥሮ ያለን ነገር መለወጥ አይቻልም፤ ኃጢአትን ግን በምክር፣ በትምህርትና በቅጣት መለወጥና ማስቀረት ይቻላል፤ ስለዚህ ኃጢአት ባሕርያዊ አይደለም:: ኃጢአት የሚመጣው በሞራል ግድፈትና በሕሊና ዝገት ነው:: የመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን የወደቁት በስንፍናቸውና ባለመጠንቀቃቸው ነው:: ዛሬም የኃጢአት ዋናው ምክንያት ይኸው ነው:: በእነርሱ ውድቀት ምክንያት የሰው ልጅ ሕሊናዊ ነጻ ፈቃድ

[72] (Evil)

የደከመና ወደ ኃጢአት እያዘነበለ መጣ። ስለዚህ ኃጢአት የሰው የባሕርዩ ባይሆንም ከነጻ ፈቃዱ መድከም የተነሣ ግን ወደ ኃጢአት ያዘነበለ ሆነ። ስለሆነም ይህን መጥፎ ዝንባሌ ከእግዚአብሔር ርዳታና ቸርነት ጋር ሕሊናን በማንቃት፣ ራስን በመግዛትና ጠንክሮ በመጋደል በማያቋርጥ ሁኔታ መቋቋምና ማስተካከል ይገባል።

በአንድ በኩል ለኃጢአት ያለውን ዝንባሌ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሰውን ነጻ ፈቃድ በመገንዘብ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ማስጠንቀቂያዎችንና ማጽናኛዎችን እንዳስፈላጊነታቸው በተገቢው ሁኔታ እያስማማ ያቀርባል። ውድቀትን ከሚያመጣ ስንፍና፣ ግዴለሽነት፣ የሞራል መላሸቅና ደካማነት ያስጠነቅቃል። በእግዚአብሔር ቸርነት የተሰጠውን ኃይል በመጠቀምና በእርሱ ላይ የሚታመኑትን የማይተው ሰውን ወዳጅ አምላክ መሆኑን በመገንዘብ ሰው የተሰጠውን ኃይልና ሥልጣን በአግባቡ እንዲጠቀምበት ያበረታታል። ተስፋ መቁረጥ ዲያብሎስ የሰውን ውድቀት እውን የሚያደርግበት ዋናውና ታላቁ መሣሪያው ነው፤ ከወደቀ በኋላ እንዳይነሣ የሚያደርገው ይህ ነውና። ቅዱስ ጳውሎስ ተጸጸተ፣ ንስሐ ገባ፣ ተስፋ ባለመቁረጡ ከመላእክት ወገን ተቆጠረ። ይሁዳ ተጸጸተ፣ ነገር ግን ተስፋ በመቁረጡ ራሱን ወደ ጥፋት ጣለ። ስለዚህ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «መውደቅ አዳማዊ ነው፤ ወድቆ አለመነሣት ግን ዲያብሎሳዊ ነው» ይለናል።





# ክፍለ ትምህርት - አንድ[73]

አጋንንት በሰዎች ሕይወት ላይ ሥልጣን እላቸው ስለሚሉና በእግዚአብሔር ተግሣጽ ስለማይደሰቱ፣ ኃጢአተኞች ለጊዜውም ቢሆን በልጽገው፣ እውነተኞች ጻድቃን ደግሞ ችግርና መከራ ሲያገኛቸው ሲያዩ በመለኮታዊ ጥበቃ (በአምላካዊ መግቦት)[74] ላይ ግራ ለሚጋቡ ሰዎች የተሰጠ ትምህርት

ባለፈው ትምህርት ራሳችንን ስለ ኃጢአታችን መውቀስና በራሳችን ላይ መፍረድ እንጂ ሌላ ሰውን በተመለከተ በእርሱ ላይ መፍረድም ሆነ ስለ እርሱ ክፉ መናገር እንደማይገባ ተምረናል። ለዚህም ራሳቸውን ሲወቅሱና ሲከሱ ሌሎችን ግን በትዕግሥት የሚያልፉ ቅዱሳንን አስታውሻችኋለሁ። ቅዱስ ጳውሎስ *«የኃጢአተኞች ዋና እኔ ነኝ፣ ተሳዳቢ፣ አሳዳጅና አንገላች በነበርኩት በእኔ ላይ ምሕረቱን አሳየ»* አለ። 1 ጢሞ. 1፥13፥15። ራሱን ሐዋርያ ተብሎ ለመጠራት እንኳ የሚገባኝ አይደለሁም በማለት ያለጊዜው እንደ ተወለደ ጭንጋፍ ነኝ አለ። 1 ቆሮ. 15፥8-9። ቅዱስ ጴጥሮስም *«ጌታ ሆይ፣ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ራቅ»* አለ። ሉቃ. 5፥8። ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ሐዋርያ ከሆነ በኋላ እንኳ ራሱን «ቀራጭ» ብሎ ጻፈ። ማቴ. 10፡ 3። ዳዊትም *«ኃጢአቴ በራሴ ላይ ከፍ ከፍ ብሏልና፣ እንደ ከባድ ሸክምም በላዬ ከብዷልና»* አለ። መዝ. 37፥5። ነቢዩ ኢሳይያስም *«እኔ የረከስኩና ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ»* አለ። ኢሳ. 6፥5። ሦስቱ ወጣቶች በእቶን እሳት ውስጥ ተጥለው ሳሉ *«የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አልጠበቅንም፣ በድለናል፣ ሕግህንም ተላልፈናል»* አሉ። ነቢዩ ዳንኤልም ተመሳሳይ ቃልን ተናገረ።

እነዚህን ቅዱሳን ከዘረዘርኩ በኋላ በሰው ላይ የሚፈርዱትን ደግሞ ዝንቦች እንዳልኋቸውና ይህንንም ያልኩት በተገቢ ሁኔታ መሆኑን አስታውሳላችሁ። ዝንቦች ማንዣበባቸውና ውሏቸው በሌሎች ቁስል ላይ እንደ ሆነ ሁሉ ከሳሾች የሆኑ ሰዎችም የሌሎችን በኃጢአት የቆሰለ አካል ይነክሳሉ። በዚህም የኃጢአትን በሽታ ቀስመው ወደ ጤነኛው ሰው ያስተላልፋሉ። ከዚህ በተቃራኒው የሚያደርጉትን ደግሞ ንቦች ብዬ ሰይሜያቸዋለሁ። በሽታን ሳይሆን ማር የሚሠሩበትን አበባ

[73] (Homily I)
[74] (Providence)

ይቀስሙ ዘንድ በታላቅ ትጋት ሆነው ወደ ቅዱሳን የሕይወትና የተጋድሎ የአበባ መስክ ይበራሉና፡፡

አሁን መግቢያው ይብቃንና ካለፈው ቀን ወደ ቀረን ትምህርት በቀጥታ እንሂድ፡፡ ያን ጊዜ ያላየነው እርሱ ምን ነበር? ሰዎች ሁሉ አንድ ተፈጥሮ እንዳላቸው ሁሉ አንድ ቋንቋ የነበራቸው መሆኑን ነው፡፡ በቋንቋም ሆነ በልሳን የተለየ ማንም አልነበረም፡፡ ታዲያ ዛሬ የምናየው ይህ ሁሉ የቋንቋ መለያየት ከየት መጣ? ሥጦታውን ከተቀበሉት ሰዎች ግዴለሽነትና ስንፍና ነዋ! ለሁሉም አንድ ቋንቋ በመስጠቱ የእግዚአብሔርን ቸርነት በአንድ በኩል፣ በቋንቋ መደበላለቅ ደግሞ የተቀባዮቹን ከንቱነት በማሳየት ተነጋግረናል፡፡ ሥጦታውን እንደምናበላሸው አስቀድሞ እያወቀ ከመስጠት አልከለከለንምና፡፡ ሥጦታውን እግዚአብሔር የነጠቀን ሳይሆን እኛው ራሳችን የተሰጠንን አበላሸነው፡፡ ተሰጥቶን ሲያበቃ ራሳችን ባጠፋነው ሥጦታ ምትክ ደግሞ ከእነዚያ ካበላሸናቸው የበለጠ ሰጠን፡፡ በጊዜያዊ ድካም ምትክ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ሰጠን፡፡ በእሾህና አሜኬላ ምትክ የመንፈስ ፍሬዎች ከውስጣችን እንዲያፈሩ አደረገ፡፡

እንደ ሰው የተሰጠውን ያበላሸና ርባና ቢስ የሆነ አልነበረም፤ እንደ ሰውም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደና የከበረ የለም፡፡ የሥነ ፍጥረቱ መጨረሻ ነበር፤ ነገር ግን እግር የነበረው ራስ ሆነ፤ ወደ መለኮታዊ ዙፋን ከፍ ተደረገ፡፡ ቸርና በጣም ሀብታም የሆነ አንድ ሰው ሌላን ሰው ከመርከብ አደጋ ያለውን ሁሉ ትቶ ነፍሱን ብቻ ለማትረፍ ራቁቱን ሲወጣ ቢያገኘውና ያንን ሰው በእጁ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ወስዶ ደማቅና ብሩህ የሆነ አዲስ ልብስ ቢያጎናጽፈውና ታላቅ ክብርን ቢያከብረው አስደናቂ ነገር እንደ ሆነ ሁሉ እኛንም በተመለከተ እግዚአብሔር ያደረገው እንደዚያ ዓይነት ነገር ነው፡፡

ሰው ያለውን ሁሉ አሽቀንጥሮ ጣለ፤ የተሰጠውን በነጻነት የመኖር ጸጋ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን አንድነት፣ በገነት መመላለስን፣ መከራና ድካም የሌለበትን ሕይወት ሁሉ፣ ልክ ያለውን ሁሉ ጭኖ በመርከብ ሲጓዝ ማዕበል እንዳጠፋበትና ራቁቱን ብቻ እንደ ወጣ ሰው የተሰጠውን ሁሉ አጥፍቶ ራቁቱን ቀረ፡፡ ሀብታም የነበረው ድሀ፣ ነጻ የነበረው የኃጢአትና የሞት ባሪያ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር ግን ወዲያውኑ በምሕረቱ ተቀብሎ በመስቀል ላይ ስለ ሰው ራቁትነት እርሱ ተራቁቶ በመካስ ጸጋውን አለበሰው፣ በእጁ ተቀብሎ ቀስ በቀስም ወደ ሰማያዊ አገሩና ክብሩ መለሰው፡፡ ይህም ሆኖ ግን የሰው በማዕበል መናወጥና





ያለውን ሁሉ ማጣት ይቅርታ የሚያሰጥ አልነበረም፡፡ ይህ በሰው ላይ የደረሰው መከራና መራቆት ፈተናው ስለከበደውና የማይቋቋመው ስለ ነበረ ሳይሆን ከመርከቡ መሪ (ከሰው) ስንፍናና ጥንቃቄ ጉድለት የመጣ ነውና፡፡

ሰው በስንፍናው ምክንያት ቢወድቅም እግዚአብሔር ግን ይህን ሳይመለከት ምሕረትን አደረገለት፡፡ በወደብ ላይ ሳለ በማዕበል የተወሰደውን ይህ ፈተና ልክ በጥልቁ ባሕር ላይ ሳለ እንደ ደረሰበት አድርጎ ተቀበለው፡፡ በገነት እያሉ መውደቅ በወደብ እያሉ በማዕበል እንደ መጨነቅ ነውና፡፡ ምክንያቱም ባሕርያችንን የሚፈታተን ምንም ዓይነት ሐዘን፣ ድካም፣ ጭንቀትና ሌላም ነገር ሳይኖር ነው ተንኮታኩተን የወደቅነው፡፡ አንዳንድ ክፉ ባሕረተኞች መርከቡን በብረት ነድለው የባሕሩ ውኃ እንዲገባበትና መርከቡ እንዲሰጥም እንደሚያደርጉት ዲያብሎስም የአዳምን መርከብ፣ ማለትም ነፍሱን፣ በመልካም ነገሮች ሁሉ ተመልታ፣ ከብራና አሸብርቃ ባያት ጊዜ መጣና እንደ ትንሽ ብረት በሆነ በቃል በመናገር ብቻ ቦርቡሮ ያለውን ሁሉ አራቆተው፣ መርከቡን ራሱንም አሰጠመው፡፡ እግዚአብሔር ግን በቸርነቱ ካጣነው እጅግ የበለጠ ነገር እንደገና ሰጠን፤ የእኛንም ባሕርይ በተዋሕዶ በመለኮታዊ ዙፋኑ ላይ አስቀመጠው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ነገር በማድነቅ እንዲህ እንዳለ፡- *«በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ለሚመጡ ዘመናት ሁሉ ያሳይ ዘንድ፣ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡»* ኤፌ. 2፥6-7፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ሆይ፣ ነገሩ አንድ ጊዜ ሆኗል፣ አንተ ግን *«ለሚመጡ ዘመናት ሁሉ ያሳይ ዘንድ»* እንዴት ትላለህ? የጸጋውን እጅግ ባለጠጋነት አሳይቶ የለምን? አዎ አሳይቷል፣ ነገር ግን ለሁሉ አይደለም፤ ለሚያምኑ ነው እንጂ፡፡ የማያምኑት ግን ይህን አስደናቂ ነገር ገና አላዩም፡፡

በዚያን ቀን ግን የሰው ልጅ በሙሉ ይሰበሰብና እግዚአብሔር ለሰው ባደረገው ነገር ይገረማል፣ ይደነቃል፤ ለእኛም የበለጠ ግልጥ ይሆናል፡፡ እኛ አሁንም እናምናለን፣ ሆኖም ግን መስማትና ማየት አንድን ነገር የማስረዳትና ምንነቱን የመግለጥ ችሎታቸው እኩል አይደለም፡፡ የሰማይት መጋረጃዎች ሲከፈቱ ስናይ፣ የነገሥታት ንጉሥ በእእላፋት መላእክት ታጅቦ ሲወርድ ስናይ አድናቆታችንና አግራሞታችን አሁን ካለን እጅግ በጣም የበለጠ ይሆናል፡፡ ከእኛ የነሣውን ሥጋና ባሕርይ

ከራሱ ጋር አንድ ከማድረጉ የተነሣ ይህን የእኛን ባሕርይ ኪሩቤል በሚሸከሙት ዙፋን ላይ ተቀምጦ መላእክት ዙሪያውን ከበውት ሱራፌል እያመሰገኑት ማየት ምን ያህል እንደ ሆነ እስኪ ልብ ብለህ ተመልከት።

3. የእግዚአብሔርን ቸርነትና ሰውን መውደድ ለእኛ ያስረዳን ዘንድ ስንት ዓይነት ዘይቤና አገላለጽ ለመጠቀም ሲሞክር የቅዱስ ጳውሎስን ጥበብ ተመልከት። *ጸጋ ወይም ሀብት* ብቻ አላለምና፤ *«ለእኛ ባለው ቸርነትና ርኅራኄ ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት»* አለ እንጂ። ኤፌ 2፥7። ሆኖም አሁንም ቢሆን መግለጽ የፈለገውን ያህል መግለጽ አልቻለም። የእግዚአብሔርን ፍቅርና ቸርነት ምንም ዓይነት አገላለጽ ብንጠቀም እንደሚገባ አከናውነን መግለጽ አይቻለንምና። ጥልቅነቱና ምጡቅነቱ የእኛን የዐረፍተ ነገር አሰካክና የቋንቋችንን የመግለጽ ዐቅም ዱዳ ያደርገዋል። ቅዱስ ጳውሎስም ሊገልጸው ያሰበውን ነገር በቃላት መናገር በሞከረ መጠን የሚጠቀማቸው ቃላት ሊገልጸው ያሰበውን ምሥጢር ሊሸከሙለት እንዳልቻሉ ስለ ተረዳ አንድ ነገር ብቻ ተናግሮ ነገሩን በዚያ ዘጋ። እርሱ ምንድን ነው? *«ስለማይነገር ሥጦታው እግዚአብሔር ይመስገን»* የሚል ነው። 2 ቆሮ. 9፥15። የእግዚአብሔርን ጥበቃና አድራጎት ምንም ዓይነት ንግግርም ሆነ ሕሊና ሊገልጸውና ሊደርስበት አይችልምና። ስለዚህም በሌላ ቦታ *«አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን ይጠብቃል»* አለ። ፊል. 4፥7።

ቀደም ብዬ እንዳልኳችሁ ተሰጥቶን ሳለ ያጣነውን ሥጦታ እግዚአብሔር ያልነጠቀን መሆኑ፤ እንዲሁም የጣነው ፋንታ የተሰጡን መልካም ነገሮች ያጣነውን የሚተኩ ብቻ ሳይሆኑ ካጣናቸው የሚበልጡና የከበሩ መሆናቸውን ማስታወስ እፈልጋለሁ። ከእነዚህም በተጨማሪ ሦስተኛ ነገር መጥቀስ እወዳለሁ። ይህ ሦስተኛው ምንድን ነው? ካጣናቸው ይልቅ እጅግ የተሻሉና የከበሩ የሆኑትን ነገሮች ባይሰጥ፤ ነገር ግን ተሰጥቶን የነበረውን ቢወስድ እንኳ ይህ ብቻ በራሱ ለእኛ ያለውን ቸር ጠባቂነት ያስረዳል። መስጠት ብቻ ሳይሆን የሰጠውን መልሶ መውሰድም የታላቅ ፍቅርና ጥበቃ መግለጫ ነውና። ይህ እንዴት ይሆናል ብትለኝ እስኪ ገነትን በተመለከተ ያለውን ነገር በጥሞና ለማየት እንሞክር። ገነትን ለሰው ልጅ ሰጠ። ይህንም ያደረገልን ማንም አሳስቦት ሳይሆን ከራሱ አባታዊ ባሕርያዊ ቸርነት የተነሣ ነው። ነገር ግን ለዚህ ሥጦታው ያልተገባን ሆነን ተገኘን።





ይህም ከራሳችን ጅልነት የተነሣ ነው። በዚህ ጊዜ ለቸርነቱ ሥጦታ የማይገባቸው ሆነው ከተገኙት ሰዎች የሰጠውን ወሰደ። ይህም እንደ መስጠቱ ሁሉ ከቸርነቱ የተገኘ ነው። የሰጠውን መልሶ መውሰድ ምን ዓይነት ደግነት ነው? የሚል ይኖራል። ይህ እንዴት እንዲህ እንደሚሆን ትንሽ ታገሥና በሚገባ ታያለህ።

ቃየን የወንድሙን ደም ካፈሰሰና ነፍሰ ገዳይ ከሆነ በኋላ በገነት ቢኖር ምን ይሆን እንደ ነበር እስኪ አስብ። ከገነት ከተባረረ በኋላ፤ በላቡ ወዝ ጥሮ ግሮ እንዲኖር ከተፈረደበት በኋላ፤ የሞት ፍርሃት በላዩ ላይ እያንዣበበበት፤ የአባቱ ሐዘን በፊቱ እየታየውና የእግዚአብሔር የቁጣ መዓት ቅሬት በፊቱ በሁሉ ነገር ግልጥ ብሎ እየታየውና ዙሪያው በብዙ አስጨናቂ ነገሮች ተከቦ እያለ እንኳ ከአንድ ማኅፀን የተወለደውንና ምንም ያልበደለውን ወንድሙን ለመግደል እንዲህ ወዳለ ወደር የሌለው ወንጀል የሚሄድ ከሆነ ይህ ሁሉ አጥርና ቅጥር በሌለበት በነጻነት ቦታ (በገነት) ቢኖር ኖሮ ይህ ሰው ወደ ምን ዓይነት ከባድ ክፋት ይሄድ ኖሯል?[75]

በገነት ኃጢአት መሥራት አይቻልም እንዳይባል አባቱና እናቱ የበደሉት በገነት ነው። እግዚአብሔር ራሱ *«ኃጢአት በደጅህ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፣ አንተ ግን በእርሷ ላይ ንገሥባት»* እያለ የመከረውና ያስጠነቀቀው ፈጣሪውን አልሰማም ብሎ በወንድሙ ደም እጁን የሚያጥብ ቃየን በገነት ቢኖር ምን ሊያደርግ ኖሯል? ዘፍ. 4፥7። ይህ ሁሉ ክልከላና ጥበቃ እያለ ያልተጠበቀ ሰው ልቅ በሆነ በነፃነት ቦታ ቢሆን ምን የማያደርገው ነገር ይኖር ኖሯል?

ከእርሱ ብቻ ሳይሆን የማይገባት በሆነች ጊዜ ከገነት መባረሯ ምን ያህል እንደ ጠቀማት ከእናቱ ከሔዋንም፤ በፊት ምን እንደ ነበረችና ከተባረረች በኋላ ደግሞ ምን እንደ ሆነች በማነጻጸርም መማር እንችላለን። በገነት ሳለች ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ የተረገመ ዲያብሎስ የሰጣትን ከንቱ ተስፋ ወዳና ፈቅዳ ተቀብላለች። የበለስን ዛፍ በማየት ብቻ በሕያው እግዚአብሔር የተሠራውን ሕግ ተረማምዳበታለች። ከገነት ከተባረረች በኋላ ግን ምን ያህል እንደ ተሻሻለች ተመልከት። ልጅ ስትወልድ *«ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘሁ»* አለች። ዘፍ. 4፥1። በገነት ሳለች ፈጣሪዋን የነቀፈችው አሁን

[75] በከባድ ወንጀል ምክንያት ተፈርዶበት እስር ቤት ያለ ሰው በዚያ እያለ እንኳ ከባድ ወንጀል ከመፈጸም የማያርፍ ከሆነ በነጻነት እንዲኖር ቢለቀቅ የማይፈጽመው ምን ወንጀል ይኖራል?

ግን በቀጥታ ወደ ፈጣሪዋ በእምነት ተጓዘች፤ የተደረገላትንም የተፈጥሮ ሂደት ነው ወይንም የጋብቻ ውጤት ነው አላለችም፤ *ገሥን ፍጥረትን* ጌታ እርሱ ሰጠኝ አለች፣ ልጅ ስለሰጣት ለእርሱ ምስጋና አቀረበች።

ከዚህ በፊት ባሏን ወደ ስህተት የመራች እርሷ ኋላ ግን ትንሹን ሕፃን እንኳ ሳይቀር ከስም አወጣጥ ጀምራ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ መኮትኮት ጀመረች፤ የእግዚአብሔርን ሥጦታ ሁል ጊዜ የሚያስታውሳት ስም ሰጠችው። ሌላ ልጅ በወለደች ጊዜም *«ቃየን በገደለው በአቤል ፋንታ እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው።»* ዘፍ. 4፥25። በአቤል ሞት የደረሰባትን መከራ አስታውሳ በማዘን ፈጣሪዋን ከማመስገን ወደ ኋላ አላለችም፤ በሞተው ምትክ ልጅ ስለ ሰጣት ምስጋና አቀረበች እንጂ። እንዲሁም የተወለደውን ልጅ በስጦታነቱ «ሴት» ብላ ሰየመችው። እርሱን ስታይ ስጪዋን እንድታዘክር በፊቷ ቋሚ ምስክር ይሆንላት ዘንድ። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠውን በመውሰድ ባዶ ባደረገ ጊዜም እንኳ የበለጠ ነገር ሰጠ። ሔዋን ከገነት ተባረረች፣ ነገር ግን በመባረሯ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ተመራች፤ ስለሆነም ካጣችው ገነት ይልቅ የሚበልጥ - እግዚአብሔርን ማወቅንና ስለ ሥጦታው ሁሉ ማመስገንን አገኘች።

ከገነት መባረራቸው እንደማይቀርና ይህም እንደሚጠቅማቸው እያወቀ ከመጀመሪያው ለምን ገነትን ሰጣቸው? ብሎ የሚጠይቅ ይኖራል። ከገነት መባረር ለእኛ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘው በስንፍናችንና በግዴለሽነታችን ከወደቅን በኋላ ነው። ነገር ግን ከመጀመሪያው ፈጣሪያቸውን ያስታውሱ፣ ትእዛዙን እየጠበቁ፣ ራሳቸውን ገዝተው በተሰጣቸው መጠን ኖረው ቢሆን ኖሮ በክብር እንደ ነበሩ ይኖሩ ነበርና። የተሰጣቸውን ታላቅ ስጦታ በናቁና በረገጡ ጊዜ ግን የተሰጣቸውን ተቀምተው መባረራቸው ጠቃሚያቸው ሆነ።

ታዲያ እግዚአብሔር ከጥንቱ ለምን ሰጠ? የሰጣቸው፣ እርሱ ለሰው ያለውን ፍጹም መውደድና ጥልቅ ፍቅር መልካም ነገር በመስጠት ያሳይ ዘንድ፣ እንዲሁም ከዚህም ወደሚበልጥ ታላቅ ክብር ሊያሸጋግረን አስቦልን ስለ ነበር ነው። እኛ ግን የተሰጠንን መልካም ነገር አክብረንና ተጠንቅቀን ባለመያዛችንና ከቦታችን ራሳችንን በማባረራችን በሁሉም አቅጣጫ የቅጣታችን ምክንያቶች እኛው ራሳችን ነን። የተሰጡትን ነገር ማበላሸት ያበላሸውን ተቀባዩን እንጂ ሰጪውን አያስነቅፍም። በዚህ





የሰጪው ቸርነት፣ የተቀባዩ ደግሞ ስንፍናና አለማስተዋል ግልጥ ሆኖ ይታያል።

ደግ አባት በመጀመሪያ ልጁ በቤቱ እንዲኖርና በቤቱ ያለውን መልካም ነገር ሁሉ እንዲያገኝ ያደርገዋል። ነገር ግን ልጁ ለዚህ መዓርግና ክብር የሚበቃ ሆኖ ካላገኘው ከማዕዱ ይለየዋል፣ ከዕይታው ያርቀዋል፣ እንክብካቤውን ያስቀርበታል። ይህም የአባቱን ማዕድ፣ ፍቅሩን፣ እንክብካቤውንና በአባቱ ቤት ያለውን መልካም ነገር ሁሉ እንዳጣ ሲገነዘብ ያጣውን ነገር ዋጋውን አውቆ ወደ ቀድሞ ሁኔታው ይመለስና አባቱ ያሰበለትን መልካም ነገር ያገኝ ዘንድ ለማድረግ ነው። እግዚአብሔርም ያደረገው እንዲህ ነው፤ ገነትን ለሰው ሰጠ፣ የማይገባው ሆኖ በተገኘ ጊዜ አስወጣው፣ ተባርሮ በውጭ በመኖሩና ክብሩን በማጣቱ የተሻለና ራሱን የሚገዛ ሆኖ ለመመለስ የሚበቃ ይሆን ዘንድ ነው። ከእነዚህ ነገሮች በኋላ ሲስተካከል *«ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ»* ብሎ መልሶታልና። ሉቃ. 23፥43። ስለዚህ ገነትን መስጠቱ ብቻ ሳይሆን ከገነት ማባረሩም የታላቅ አባታዊ ርህራኄውና ፍቅሩ መገለጫ እንደ ሆነ አየህን? ከገነት ባይባረር ኖሮ ለገነት የተገባ ሆኖ አይገኝም ነበር።

4. ስለዚህ ይህን ነገር ሁል ጊዜ እናስበው፣ ከፊታችን ላለውም ጉዳይ እንተግብረው። ይህ ጉዳይ ምንድነው? እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ቋንቋ መስጠቱ ነው። ይህም ለሰው ያለው ፍቅር መገለጫ ነው። ነገር ግን ሰዎች ይህን ስጦታ በአግባቡ አልተጠቀሙበትም። አንድ ቋንቋ ስላላቸው ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ ወደሚል የሞኝ ሥራ ከሄዱ በቶሎ ባይገሠፁ ኖሮ ራሱን ሰማይን እንያዝ ባላሉ ነበርን? የማይሆንላቸው ቢሆንም እንኳ ከከንቱ አሳባቸው የተነሣ ወደዚህ ዓይነት ነገር መሄዳቸው አይቀርም ነበር። ይህን ሁሉ አስቀድሞ የሚያውቅ እግዚአብሔር በቋንቋ አንድ መሆናቸውን በአግባቡ ለጥሩ ነገር ስላልተጠቀሙበት ቋንቋቸውን በመደባለቅ ከፋፈላቸው። በዚህም ከእኔ ጋር አብረህ ቸርነቱንና ለሰው ያለውን ፍቅሩን ተመልከት፤ ቋንቋቸውን ከመደባለቁ በፊት *«እነሆ፣ እነርሱ አንድ ቋንቋ አላቸው፣ ይህንም ለማድረግ ጀመሩ»* አለ። ዘፍ. 11፥6።

እግዚአብሔር ለምን ይህን አለ? በአንድ ጊዜ በቀጥታ ቋንቋቸውን ወደ መለያየት ያልሄደው ለምንድን ነው? በቅድሚያ ልክ በፍርድ ቤት ለፍርድ እንደ ቀረበ ሰው የራሱን መከላከያ አሳብ ተናገረ። እርሱን ማንም «ለምን ይህን አደረግህ?» ብሎ ሊጠይቀው አይችልም። እርሱ

የወደደውን እንደ ፈቀደ ማድረግ ይችላልና:: እንዲያም ሆኖ ግን ስለ ድርጊቱ ራሱን መከላከል እንዳለበት ሰው መከላከያ አቀረበ::[76] ይህም እኛን ትሑታንና ሰውን ወዳጆች እንድንሆን ሲያስተምረን ነው:: ጌታ የሆነ እርሱ ለባሪያዎቹ ራሱን ከተከላከለና የሚያደርግበትን ምክንያት ካስረዳ፣ ያውም በድለውት ሳለ፣ እኛ ደግሞ የበለጠ ከበደሉን ጋር እንኳ ቢሆን እርስ በርሳችን ልንወቃቀስ፣ ልንመካከርና አሳባችንን በመግለጽ ልንረዳዳና ልንተማመን ይገባናል::

ሲያደርገው ያሰበውን ድርጊት ትክክለኛነት ከነምክንያቱ ሲያስረዳ *«ሁሉም አንድ ቋንቋና አንድ ንግግር አላቸው:: አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም»* አለ:: ይህም የሰዎች ቋንቋ ተለያይቶ ሲያይ በዚህ ማንም የሚወቅሰኝ አይኑር ብሎ ራሱን እንደሚከላከል ሰው ነው:: ይህ ቋንቋ መለያየት ከመጀመሪያ ጀምሮ የነበረ ነው ብሎ ማንም አያስብ:: *«እነሆ፣ ሁሉም አንድ ቋንቋና ንግግር አላቸው::»* ነገር ግን ስጦታቸውን ለጥሩ ነገር አላዋሉትም:: ስለዚህ ቋንቋቸውን ደባለቀባቸው::

እግዚአብሔር የሚቀጣውና የሚገሥፀው፣ እንዲሁም የሰጠውን የሚነሣው ባለፈው ስለ ተደረገው ጥፋት ከሚያደርገው ይልቅ በበለጠ ወደፊት ከሚመጣው ለማረምና ለማስተካከል መሆኑን ለመረዳት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ስማ፡ - *«ይህንም ለማድረግ ጀመሩ፣ አሁንም ያሰቡትን ከማድረግ አይከለከሉም»* አለ:: ዘፍ. 11፥6:: ይህ እንዲህ እንደ ማለት ነው፤ በጥፋታቸው አሁን ካልተቀጡና ክፋታቸው ከሥሩ ካልተቆረጠ ከክፋት አያርፉም:: «የጀመሩትን ነገር ከመሥራት አይከለከሉም» የሚለው አባባል እንዲህ ማለት ነውና፤ ከዚህ የባሰ ሌላ ከባድ ነገር ይፈጽማሉ ማለት ነው:: ኃጢአት እንዲህ ነውና፤ ገና ሲጀምር በእጭሩ እንዲቀር ካልተደረገ በስተቀር የሚቃጠል ነገር እንዳገኘ እሳት ወደ ሰማይ መውጣቱ አይቀርም:: ስለዚህ የቋንቋና የንግግር አንድነትን ማስቀረቱና ቋንቋን መደባለቁ የቸርነቱ ደገኛ *ሥራ* እንደ ሆነ አየህን?

[76] እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ሲያጠፋ ሲል በዚያ ሁሉ አገርና ከተማ ራሳቸውን በመግዛትና በእግባቡ የሚኖሩ ዐሥር ሰዎች እንኳ የሌሉ መሆናቸውንና ሁሉም ከልክ ባለፈ ኃጢአት ውስጥ የተዘፈቁ መሆናቸውን በማሳየት እነርሱን የማጥፋቱ ነገር አግባብ ያልሆነ አለመሆኑን አስቀድሞ ለአብርሃም አስረዳ:: ዘፍ. 18፥22-33:: ሎጥንም እንዲሁ የሰዎቹን እንግዳ የማይቀበሉ መሆንና አስጸያፊ ፍትወታዊ መቃጠል ካሳየው በኋላ የፍርዱን እሳት አመጣ:: ዘፍ. 19:: ለሕዝቅኤልም እንዲሁ ከተማረኩት እስራኤላውያን ጋር በባቢሎን እንዲኖር ሲያደርገው በኢየሩሳሌም ያሉትን ሰዎች ክፉ *ሥራ* እንዲያይ አደረገው:: ሕዝ. 8፥5:: ለኤርምያስም «አትጸልይላቸው፣ የሚያደርጉትን አታይምን?» አለው:: ኤር. 7፥16-17





ወደ ባሰ ኃጢአት እንዳይሄዱ የቋንቋን ልዩነት እንደ አጥርና ቅጥር አደረገላቸው::

ስለዚህ ይህን ነገር ማለትም ሲሰጥ ብቻ ሳይሆን ሲገሥጽና ሲቀጣም ቢሆን እግዚአብሔር ቸርና ሰውን ወዳጅ መሆኑን በሕሊናህ ቅረጸው:: ቅጣቶቹና ተግሣጾቹም ቢሆኑ የቸርነታውና የመለኮታዊ ጥበቃው ዋና መንገዶች ናቸው:: የሚቀጣው ቸር ስለ ሆነ ለጥቅማችን እንጂ በክፋት አለመሆኑን ልብ ብለህ አስተውለው:: ስለዚህ ረሃብ፣ በሽታ፣ ድርቅ፣ ጎርፍና ከባድ ዝናብ፣ በአየር ጠባይ ላይ ያልተለመደ ነገር፣ ወይም ሰውን ከሚቀጡት ነገሮች አንዱን ወይም ሌላውን ብታይ አትበሳጭ፣ ተስፋም አትቁረጥ፣ ነገር ግን ያመጣቸውን እርሱን አምልከው፣ መግቦቱንና ርህራኄውንም አድንቅ::

እነዚህን ነገሮች የሚያደርገው ነፍስ ጤናማ ትሆን ዘንድ *ሥጋን*ም ሳይቀር የሚቀጣው እርሱ እግዚአብሔር ነው:: እነዚህን ነገሮች የሚያመጣቸው እግዚአብሔር ነውን? የሚል ይኖራል:: አዎ፣ እግዚአብሔር ይህን ያደርጋል፤ የከተማው ሰው ሁሉ፣ እረ እንዲያውም ዓለሙ ሁሉ በፊቴ ቢሆን እንኳ እግዚአብሔር ይህን አደረገ ከማለት ወደ ኋላ አልልም:: ይህን የምለው ከራሴ አይደለምና፣ ነቢዩ እንዲህ ያለ ሲጮህ እሰማዋለሁና:- *«ክፉ ነገር በከተማው ውስጥ የመጣ እንደ ሆነ ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን?»* አሞ. 3፥6:: «ክፉ ነገር»[77] ቃሉ አሻሚ ነው:: ከቃሉ አሻሚነትና ግልፅ አለመሆን የተነሣ ሳትረዱት እንዳትቀሩና ወደ ነቀፌታ እንዳትሄዱ የእያንዳንዱን ነገር ትክክለኛ አሳብ ትረዱ ዘንድ እወዳለሁ::

5. በራሱ ክፉ የሆነ ክፉ ነገር አለ፤ እነዚህም አመንዝራነት፣ ዝሙት፣ ስስታምነትና ፍቅረ ነዋይና ስፍር ቁጥር የሌላቸው የመጨረሻ ውግዘትና ቅጣት የሚገባቸው አስፈሪና አሳፋሪ የሆኑት ተመሳሳይ ነገሮች ሁሉ ናቸው:: በሌላም በኩል ረሃብ፣ በሽታ፣ ሞት፣ ሕመምና እነዚህን የመሰሉ ሌሎችም «ክፉ» ተብለው ይጠራሉ:: እነዚህ እንደ መጀመሪያዎቹ ክፉዎች አይደሉምና ለዚህ ነው «ክፉ» ይባላሉ ያልኩት:: ምክንያቱም በራሳቸው ክፉዎች ቢሆኑ ኖሮ ትዕቢታችንን በመገሠፅ፣ ክስንፍናችንን በማንቃት፣ ጥንካሬያችንን በመጨመርና የበለጠ ትጉሃን እንድንሆን በማድረግ የመልካም ነገር ምንጭ ሊሆኑ አይችሉም ነበር:: *«በገደላቸው ጊዜ»*፣ ይላል ነቢዩ፣ *«ወዲያው ፈለጉት፣ ተመለሱ፣*

[77] (Ev'.)

*ወደ እግዚአብሔርም ገሥጸሱ»* መዝ. 77፥34:: ስለዚህ ይህን የበለጠ የሚያነጻቸውን፣ ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ከጽርእት የሚያነቃቃቸውን፣ ለመንፈሳዊ ነገር ያላቸውን ቅንዓትና ጥንካሬያቸውን የሚጨምረውንና ጥበብን ወደ ማፍቀር የሚመራቸውን «ክፉ» አለው፤ ነውርና አስጸያፊ የሆነውን ኃጢአትን አይደለም::

በራሱ ክፉ የሆነ ኃጢአት ግን የእግዚአብሔር ሥራ አይደለም፤ እግዚአብሔር ኃጢአትን ፈጽሞ አልፈጠረም:: ኃጢአት የእኛ ነፃ ፈቃድ የፈጠራ ውጤት ነው:: ያ ግን ይህን ለማስታገሥና ለማጥፋት ከእግዚአብሔር የሚመጣ ነው:: በኃጢአታችን ምክንያት ለቅጣት የሚመጡትን ነገሮች ክፉ አላቸው፤ እንዲህ ብሎ መጥራቱም ነገሩን ከራሱ ተፈጥሮ የተነሣ ሳይሆን ሰዎች በልማድ የሰጡትን ስያሜ ወስዶ ነው:: ስርቆትንና ዝሙትን ብቻ ሳይሆን መቅሰፍቶችንም ክፉ እያልን መጥራት ስለ ለመደብን ነቢዩም ከሰዎች አሰያየም አንፃር ጠርቶታል:: ነቢዩ ያለው *«በከተማው ውስጥ እግዚአብሔር ያላደረገው ክፉ ነገር የለም»* ነው::

ይህን እግዚአብሔር በኢሳይያስ አማካይነት ከላይ እንዳየነው መቅሠፍቶችን ክፉ ብሎ በመሰየም እንዲህ በማለት የበለጠ ግልፅ አድርጎታል:- *«ሰላምን የማደርግ፣ ክፋትንም የምፈጥር አምላክ እኔ ነኝ»* አለ:: ኢሳ. 45፥7:: ይህን ክፋት ክርስቶስም ለደቀ መዛሙርቱ አመልክቷቸዋል፤ *«ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋልና»* በማለት:: ማቴ 6፥34:: «የቀኑ ክፋት» የተባለም በዚያ ቀን የሚገጥመውን መከራና ጭንቀት ነው:: ስለዚህ ቅጣትን ክፉ ይለዋል፣ እነዚህኑ ደግሞ በእኛው ላይ ያመጣቸዋል፣ በዚህም መለኮታዊ ጥበቃውን በሁሉም መንገድ ያሳይ ዘንድ ነው::

ሐኪም የሚመሰገነው በሽተኛውን ወደ መስክና ደስ ወደሚሉ የአትክልት ቦታዎች ሲወስደውና ጥሩ ምግብ ሲያቀርብለት ብቻ ሳይሆን ያለ ምግብ እንዲቆይ ሲያዘውም፣ እንዲህ ያለውን አትብላ፣ እንዲህ ያለውን አትጠጣ ብሎ ሲከለክለውም፣ ከአልጋው እንዳይነሣ ሲያዘውና አልጋውን እንደ እስር ቤት ሲያደርግበትና ፀሐይን እንኳ እንዳያያት ሲከለክለውም፣ ቤቱን በሁሉም አቅጣጫ በመጋረጃ ሲጋርደውም፣ የሚቆረጥ አካል ካለ ያንን ጨክኖ ሲቆርጥና ስለት ሰውነቱ ላይ ሲያሳርፍበትም፣ የሚመሩ መድኃኒቶችንም ሲያመጣና በሽተኛውን እንዲወስድ ሲያዘውም፣ በእነዚህ ሁሉ አሁንም እንደዚያኛው እኩል ሐኪም ነው:: ይህን ያህል ከባድና አስጨናቂ ነገር የሚያደርገውን ሐኪም እያሉ እየጠሩና ድርጊቱንም ለሰውዬው ጤንነት ከማሰብ እንደ





ሆነ በመረዳት እያመሰገኑና እያወደሱ፣ እግዚአብሔር ግን ከእነዚህ ነገሮች- ረሃብ ወይም ሞት አንዱን እንኳ ቢያደርግ ማማረርና መግቦቱን እስከ መካድ ደርሶ በእርሱ ላይ የማይገባ ነገር መናገር ምን ያህል የሚያበሳጭና የሚያሳዝን ነገር ነው?

እንዲህ ሆኖም የነፍስና የሥጋ እውነተኛ ሐኪም እርሱ ነው:: ከዚህም የተነሣ ይህን ምቾትና ሀብት ሲበዛበት ለመውደቅ የሚንገዳገደውንና በኃጢአት ትኩሳት የሚጨነቀውን ሰውነታችንን በረሃብ፣ በእጦት፣ በሞትና በሌሎች እርሱ በሚያውቃቸው በልዩ ልዩ መድኃኒቶች ያዝ በማድረግ ከኃጢአት በሽታ ነፃ ያደርገናል:: ነገር ግን በረሃብ የሚቀጣው ድሀው ብቻ ነው የሚል ይኖራል:: እርሱ እኮ በረሃብ ብቻ አይቀጣም፤ ስፍር ቁጥር በሌላቸው በሌሎች ነገሮችም ነው እንጂ:: በድህነት የሚኖረውን ብዙ ጊዜ በረሃብ ገሥጾታል፣ ባለ ጸጋውንና በምቾት የሚኖረውን ደግሞ በሥጋት፣ በበሽታ፣ በመቅሠፍት ይቀጣል:: ሁሉም ዓይነት ሀብት ያለው ሙሉ ባለ ጸጋ ነውና፤ እንዲሁም ለእኛ ድህነት ያሉት መድኃኒቶች በጣም ብዙ ዓይነቶች ናቸው::

እውነተኛ ዳኞችም የሚያደርጉት እንዲሁ ነው:: መልካም ያደረጉትን መሸለምና ማክበር ብቻ ሳይሆን ያጠፉትንም ያርማሉና:: ስለዚህም ሰይፋቸውን ይስላሉ፣ የቅጣት አንቀጽ ያዘጋጃሉ፤ ጅራፍ፣ እስር ቤት፣ የገንዘብ ቅጣት፣ ሌላም ብዙ ዓይነት የሆነ የቅጣት ዝርዝርና ዓይነት ያዘጋጃሉ:: እነዚህ መቅጫዎች ለዳኞች እንደ ሆኑት ረሃብና ልዩ ልዩ መቅሰፍቶችም ለእግዚአብሔር እንዲሁ ናቸው:: እንደ ሕግ አስፈጻሚዎች እነዚህም ከስህተታችን በማረም ከኃጢአት እንድንርቅ ያደርጉናልና:: ይህን በገበሬም ማየት ይቻላል:: ወይን ተካይ የሆነ ገበሬ ሥሩን ብቻ የሚጠብቅ አይደለም፣ ቅርንጫፉንም ሁሉ እየተንከባከበ የሚጠብቀው አይደለም፤ ከቅርንጫፉ የማይረባውን ይቆርጠዋል፣ ይገርዘዋል እንጂ:: ስለዚህም ምክንያት ገበሬዎች መኮትኮቻ ብቻ ሳይሆን ማጨጃና መቁረጫ የሚሆን ማጭድም ይይዛሉ:: ሆኖም ግን እንዲህ በማድረጋቸው ለምን እንዲህ አደረጉ? ብለን ድርጊታቸውን ጥፋት ነው አንልም:: ይልቁንም ብዙ ፍሬ ማፍራት የሚችለው ግንድ ይመቸውና ብዙ ፍሬ ያፈራ ዘንድ የማይረባውን ሲቆርጡ እንዲህ በማድረጋቸው እናደንቃቸዋለን እንጂ አጠፉ፣ ተሳስተዋል አንላቸውም::

ታዲያ ወላጅ አባቶችን፣ ሐኪሞችን፣ ዳኞችን፣ ገበሬዎችን እንዲህ በማድረጋቸው ድርጊታቸውን እያወደስን፤ ይመከር ዘንድ ልጁን ከቤት የሚያስወጣ አባት፣ በጽኑ የታመመ በሽተኛን ሐኪሙ ሰውነቱን እስከ መቅደድ ድረስ ቢያደርግበት፣ ጥፋተኛውን የሚያርመው ዳኛ፣ ወይኑን

የሚገርመው ነገሩ፣ እነዚህ ሁሉ ሳይነቀፉ በኃጢአት ስካር ስንደነዝዝ እግዚአብሔር ቢገሥጽ መጠን በሌለው ሁኔታ ለምን እንወቅሰዋለን? እንደ እኛ ላሉ ሰዎች የምንሰጠውን የመቅጣትና የማረም ተገቢነትና ትክክለኛነት ያህል እንኳ ለእግዚአብሔር ትንሽ ድርሻ ለመስጠት አለመቻል ምን ያህል ታላቅ እብደት አይሆን ይሆን?

6. ድንጋይ ወደ ሰማይ እንዳይወረውሩና መልሰው አናታቸውን እንዳይመቱ፣ ደማቸውም በራሳቸው እጅ እንዳይፈስ እግዚአብሔርን ለሚነቅፉ ሰዎች ስለ እነርሱ ይህን እናገራለሁ:: እግዚአብሔር የሰጠንን ለራሳችን ጥቅም ብሎ እንኳ ባይሆን እንዲሁ የሰጠውን መልሶ ቢወስድ በዚህ እንኳ ማንም ሊነቅፈው አይችልም:: የእርሱ የሆነው ጌታ (ባለቤት) ነውና:: ሰዎች እንኳ ያበደሩንን ገንዘብ መልሰው ሲወስዱ እስከዛ ጊዜ ድረስ እንድንጠቀምበት ስለ ሰጡን እናመሰግናቸዋለን እንጂ የራሳቸውን ገንዘብ መልሰው ስለ ወሰዱ አንቆጣም:: ታዲያ እግዚአብሔር የራሱ የሆነውን ቢወስድ ልንቆጣ ይገባልን? ይህ ወደር የሌለው ሞኝነት አይደለምን?

ምስጉንና ታላቅ የሆነው ኢዮብ እንዲህ አላደረገም:: ሲቀበል ብቻ ሳይሆን ሲወሰድበትም ለእግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ምስጋናን አቅርቧልና፣ እንዲህ በማለት፡- *«እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔር ነሣ፣ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን»* ኢዮ. 1፥21:: ስሁሉም እንደሚገባ ምስጋና ማቅረብ የሚገባ ከሆነ፣ መውሰድም ከመስጠት ያላነሰ የሚጠቅመን ከሆነ፣ ከማንኛውም ሐኪም በላይ አዋቂ የሆነውን፣ ከማንኛውም አባት በላይ የሚወደንን፣ ከማንኛውም ዳኛ ይልቅ እውነተኛ የሆነውን፣ ከማንኛውም ገበሬ በበለጠ ፍሬ እናፈራ ዘንድ የሚያስፈልገንን ሁሉ በየጊዜው ለማድረግ የሚተጋውን እርሱን ልናመልከውና ልናመሰግነው ሲገባ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መንፈስና ስሜት ሆነን ቁጣዉን መታገሥ አቅቶን ልንነቅፈውና መለኮታዊ ጥበቃውንና መግቦቱን ስንጠራጠር ብንገኝ ለይቅርታ የሚያበቃ ምን ምክንያት ይኖረን ይሆን? እንዲህ ባለ ደገኛ እንክብካቤና ጥበቃ መሀል እየኖሩ መለኮታዊ ጥበቃ የለም ከሚሉ ሰዎች የባሰ አእምሮውን ያጣና ሕሊናውን የሳተ ምን ነገር ይኖራል?

የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ ግልፅ ሆኖ የሚታየውን ያህል ፀሐይ እንኳ ደምቃ አትታይም:: ሆኖም ግን አንዳንዶች አጋንንት የእኛን ጉዳይ ይወስናሉ እስከ ማለት ደርሰው ይናገራሉ:: እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ? የሚወዳችሁ አፍቃሪ ጌታ አላችሁ፤ እንደምትሉት





ለአጋንንት አሳልፎ ስጥቷችሁ እነርሱ እንዴት አድርገው እንደሚያስተዳድሩ በተጨባጭ ከሚያሳያችሁ ይልቅ የእናንተን ስድብና የማይገባ ንግግር ቢታገሥ ይመርጣልና::

የምትሉትን በተግባር ታዩት ዘንድ ቢተዋችሁ ኖሮ ምን ያህል ክፉዎች እንደ ሆኑ ከምታዩትና ከሚገጥማችሁ ታውቁ ነበር:: አዎ፣ አሁን እንደ ምሳሌ በፊታችሁ ይህን ተመልከቱ:: አጋንንት ያደሩባቸው ሰዎች ከመቃብር ወጥተው ክርስቶስን ተገናኙት፤ አጋንንቱም ወደ እሪያ መንጋ ይገቡ ዘንድ እንዲፈቅድላቸው ለመኑት:: መድኃኒታችንም ፈቀደላቸው፤ እነርሱም ወጥተው ወደ እሪያዎቹ ሄዱና ገቡ:: ማቴ. 8፥28-32:: ከዚያስ አጋንንቱ እሪያዎቹን ምን አደረጓቸው? በእሪያዎቹ እንደ ገቡባቸው ወዲያውኑ በቅጽበት የእሪያዎቹ መንጋ ከአፋፉ እየተጣደፉ ወደ ባሕር ውስጥ በመስጠም ሞቱ::

አጋንንት የሚያስተዳድሩት እንዲህ ነው:: ያውም ከእሪያዎች ጋር የተለየ ጠላትነት የላቸውም፣ ከአንተ ጋር ግን የማያቋርጥና የማይበርድ፣ ዕርቅና የሰላም ውል የሌለው ጦርነት ላይ ናቸው፣ ለአንተ ያላቸው ጥላቻም ቋሚና የማይሞት ነው:: የተለየ ጠላትነት በሌላቸው በእሪያዎች ላይ ሳይቀር እንዲህ ትንሽ እንኳ በሕይወት እንዲኖሩ ጊዜ ሳይሰጡ በቅጽበት እያጣደፉ ወደ ባሕር አስጥመው ካጠፏቸው፣ በእኛ ላይ ሥልጣን ቢኖራቸው ኖሮ ሁል ጊዜ ጥፋታችንን የሚመኙልንን እኛን ምን የማያደርጉን ነገር ይኖር ነበር? ምንስ የማያደርሱብን ውጥንቅጥና ዝብርቅርቅ ይኖር ነበር? አእምሮ በሌላቸው ፍጥረታት ላይ በሚያደርሱት ጥፋት የአጋንንትን ክፋት ምን ያህል እንደ ሆነ ትረዳ ዘንድ ነው ወደ እሪያዎቹ ይገቡ ዘንድ ሲለምኑት የፈቀደላቸው:: [78]

እንዲሁም አጋንንቱ ያደሩባቸው ሰዎች ባሉበት ሁኔታም ሆነው የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ ባይጠብቃቸው ኖሮ ልክ ሲፈቀድላቸው በእሪያዎቹ ላይ እንዳደረጉት እነርሱንም ወዲያውኑ

[78] ጌታችን አጋንንቱ በእሪያዎቹ እንዲያድሩባቸው የፈቀደበት ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሌላው ምክንያት ከሚታየው ነገር ውጭ ሌላ መንፈስ የሚባል ነገር የለም የሚሉ ሰዱቃውያን የሚባሉ ቁስ አካላውያን (Materialists) በእስራኤል ዘንድ ስለነበሩ እነርሱን ለማሳመን ነው:: ስለማያዩአቸው የመናፍስትን መኖር አያምኑም ነበር:: በእሪያዎቹ ሲያድሩ፤ ከዚያም ወደ ባሕር እያጣደፉ ሲያሰጥሟቸው አይተው የአጋንንትን መኖር፣ ብዛታቸውንና ክፋታቸውን ከሥራቸው እንዲረዱ ለመርዳት ነው:: ርኩሳን መናፍስት ካሉ ቅዱስ መንፈስም የማይኖርበት ምክንያት የለም:: ነፋስን በዓይናችን አናየውም፣ ነገር ግን ዛፎችን ሲያንቀሳቅስ እያየን የለም ብንል ጤነኛ አስተሳሰብ አይሆንም:: ስለዚህ ጌታችን ይህን አድርጎላቸው ካላመኑ ላለማመናቸው ምክንያት የላቸውም::

እንዳደሩባቸው ባጠፏቸው ነበር። ሰዎቹን ግን ቢያድሩባቸውም የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ ስላልተለያቸው ሊያጠፏቸው አልቻሉም። ዛሬም ቢሆን አጋንንት ያደሩበት ሰው ብታይ እግዚአብሔርን አምልክ፣ የአጋንንትንም ክፋት ተመልከትበት። በአጋንንት ድርጊት የእነርሱንም ክፋት፣ የእግዚአብሔርንም ቸርነት ሁለቱንም ማየት ይቻላልና። የአጋንንትን ክፋት ያደሩባቸውን በማስጨነቃቸውና በማሰቃየታቸው እናያለን፤ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጥበቃ ደግሞ በሰው ሲያድሩ ሰውዬውን በእሪያዎቹ እንዳደረጉት አጣድፈው ወደ ባሕርና ገደል ከተው ሊገድሉት ሲፈልጉ ክፋታቸውን ለመግለጥ ያህል በመጠኑ እንጂ ሙሉ ኃይላቸውን እንዲጠቀሙና ሰውዬውን እንዲያጠፉት አይፈቅድላቸውምና ጥበቃውን በዚህ እናያለን።

እግዚአብሔር ኃይሉን እንዲጠቀም ሲፈቅድለት ጋኔን ነገሮችን እንዴት እንደሚያደርግ ለማየት ሌላ ምሳሌ ትፈልጋለህ? የኢዮብን የበግና የከብት መንጋዎች ሁሉንም በአንድ ጊዜ እንደ ደመሰሳቸው አስታውስ፤ አሳዛኝ የሆነ የልጆቹን ሞት አስብ፤ በሰውነቱ ላይ የወረደበትን ቁስልና ደዌ ልብ አድርግ። በዚህም የአጋንንትን ፍጹምና ይህን ያህል ተብሎ ሊገለጽ የማይችል ጭካኔና ክፋት በግልጽ ታይበታለህ። ከእነዚህም ነገሮች እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ነገር ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮና እንደ ፈለጉ ማድረግ ቢችሉ ኖሮ ማንኛውንም ነገር ምስቅልቅሉን ባወጡትና በእኛም ላይ ልክ በእሪያዎቹ ላይ እንዳደረጉት ባደረጉብን ነበር። ሌላው ቀርቶ ለአንዲት ቅጽበት ያህል እንኳ እንድንኖር አይፈቅዱልንም ነበር።

አጋንንት በዚህ ዓለም ባሉ ነገሮች ላይ ሥልጣን ቢኖራቸው ኖሮ ካደሩባቸው ከእነዚያ ሰዎች የተሻለ ሕይወትና አኗኗር አይኖረንም ነበር። እንዲያውም ከእነርሱም የባሰን እንሆን ነበር። ያደሩባቸውን ሰዎች ሙሉ በሙሉ ለአጋንንት ሥልጣን አሳልፎ አልሰጣቸውምና። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ እንደ እሪያዎቹ ሰጥመው ይሞቱ ነበር። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ስላልተዋቸው ያደሩባቸውን ሰዎች እንኳ አጋንንቱ እንደ ፈለጉት ማጥፋት አልቻሉም።

እንዲህ የሚሉትን እኔ ይህን ልጠይቃቸው እፈልጋለሁ፤ ሕይወታችንን ሁሉ እንዲህ ለአጋንንት ሥልጣንና ግዛት አሳልፈው የሚሰጡት እነዚህ ሰዎች ምን ዓይነት የተመሰቃቀለ ነገር አይተው ነው? ፀሐይ ይኸው ከተፈጠረች ጀምሮ ዕለት በዕለት ትወጣለች፤ ትገባለች፤ የሰማይ ፈርጥ





የሆኑ የከዋክብት ስብስቦች ሥርዓታቸውን ጠብቀው ይኖራሉ፤ የጨረቃ መንገድ አይደናቀፍም፤ ቀንና ሌሊት እንደሚገባ ይፈራረቃሉ፤ ክረምትና በጋ ጊዜያቸውን ጠብቀው ይመግባሉ፤ በአጠቃላይ በሰማይም ሆነ በምድር ያሉት ሥነ ፍጥረቶች በተቀመረና በተቀናጀ ስምምነት ሁሉም ቦታቸውን ጠብቀው ሳይፋለሱ የፈጠራቸው እግዚአብሔር ከመጀመሪያ የወሰነላቸውን አክብረውና ይዘው ይጓዛሉ።

7. የእኛ ሕይወትና በዚህ ዓለም የምናየው ነገር ዝብርቅርቅ ብሎ ሳለ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብትና ሌሎችም ሥነ ፍጥረቶች ሥርዓታቸውን ይዘው ቢገኙ ይህ ሁሉ ምን ጥቅም አለው? የሚል ይኖራል። ወንድሜ ሆይ፣ የምትለኝ ምን ዓይነት መዘበራረቅና ቅጥ ማጣት ነው? አንዱ ሀብታምና ሌሎችን በማዘዝ፣ በምቾትና በድሎት ብቻ የሚኖር ነው፣ እንዲሁም ስስታምና የሰዎችን ሳይቀር የሚቀማ ነው፣ ድሆችን ቀን በቀን ያላቸውን ይቀማቸዋል፣ ይገፋቸዋል፤ ነገር ግን ምንም ክፉ ነገር አያገኘውም። ሌላው ደግሞ በትዕግሥት፣ ራስን በመግዛት፣ በእውነተኛ ነገር በመጽናትና በመልካም ሥነ ምግባር ያጌጠ ነው፣ ነገር ግን በድህነትና በበሽታ ይማቅቃል፣ በልዩ ልዩ መከራ ይሰቃያል። ታዲያ አንተን ያበሳጨህ እነዚህ ነገሮች ናቸው? አዎ፣ እነዚህ ናቸው ይላል። ከክፉዎች ብዙዎቹ ሲቀጡ፣ በቅድስና ከሚኖሩት ደግሞ ብዙ መልካም ነገር ሲያገኙ ስታይስ ይህን አስተሳስበህን ትተህ ለምን ፈጣሪህን አታመሰግንም? አይ፣ እኔን የበለጠ የሚያሳዝነኝ ይህ ነው ይላል። ሁለት ክፉ ሰዎች ቢኖሩ አንዱ የሚገባውን ቅጣት ሲቀበል ሌላው ለምን ሳይቀጣ ይቀያል? ሁለት ደጋግ ሰዎች ቢኖሩ አንዱ መልካም ሲያገኝ ሌላው ለምን በመከራ ይጨነቃል?

ይህም ነገር ቢሆን ታላቅ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ ሥራ ነው።[79] ሁሉንም ክፉዎች በዚህ ዓለም ቢቀጣ፣ እንዲሁም ደጋግ ሰዎችን ሁሉንም እዚህ ክብራቸውን ቢገልጥ የፍርድ ቀን አላስፈለገ ይሆን ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ እንደ ሥራው የሚከፈልበት የፍርድ ቀን ስላለ እስከዚያ ድረስ አሁን በዚህ ዓለም ከክፉዎች ማንንም ባይቀጣና ከደጋጎቹም ማንንም ስለ ጽድቁና ደግነቱ

[79] «... ይህ ዓለም የዋጋ መቀበያ ቦታ አይደለምና በቅድስና የኖረ መከራ የሚቀበል ቢኖር እግዚአብሔር የበለጠ ክብር እያዘጋጀለት ነውና ደስ ይበለው። ስለዚህ የክብር አክሊል በሚሰጥበት ጊዜ ዋጋችን እንዳይቀነስብን አሁን በዚህ ዓለም ዋጋ እንድናገኝ አንጠይቅ። ራሳቸውን በመርዳት የሚሠሩ ሠራተኞች በክፍያ ቀን ከፍ ያለ ክፍያ ሲቀበሉ ምግባቸውን ከአሠሪዎቻቸው የሚቀበሉ ሠራተኞች ግን ትንሽ የማይባል መጠን ከክፍያቸው ይቀነስባቸዋልና። በቅዱሳንም እንዲህ ነው፤ ብዙ መልካም ሥራ እየሠራ ብዙ መከራ የሚቀበል ስላደረገው መልካም ሥራ ብቻ ሳይሆን ስለተቀበለው መከራም ብዙ ክብርና ዋጋ ያገኛል። በዚህ ዓለም በዕረፍትና በሰላም የኖረ ግን በዚያ እንደዚያኛው ያለ ታላቅ አክሊል አያገኝም።...» 1ቆሮ. ምዕ.16 ትርጓሜ፣ Homily 43።

ክብሩን ባይገልጥ እግዚአብሔርን ለመንቀፍና ለመውቀስ ሰበብ የሚፈልጉ ሰነፎች የበለጠ ለስንፍና አስተሳሰባቸው መግቢያ ቀዳዳ ያገኙ ነበር። ከክፉዎችም፣ ከደጋጎችም አንዳንዶቹ ሲቀጡ በማየታቸው የሰው ሕይወት በመለኮታዊ ጥበቃ ሥር አይደለም ካሉ ይህ ባይኖር ምን የማይሉት ነገር ይኖር ነበር? ምን ነቀፋስ ይበቃቸው ኖሯል? ስለዚህም ምክንያት ከክፉዎች አንዳንዶቹን ይቀጣቸዋል፤ አንዳንዶቹን ደግሞ ዝም ይላቸዋል። ከደጋጎችም አንዳንዶቹን ክብራቸውን ይገልጣል፤ ሌሎቹን ደጋጎች ደግሞ ክብር የሌላቸው ይመስል ዝም ይላቸዋል፤ በመከራም ውስጥ ወድቀው ይታያሉ።

ሁሉም እንደ ሥራው ዋጋውንም ሆነ ፍዳውን የሚቀበልበት ትንሣኤ እንዳለ እንድታምን አሁን ሁሉንም ክፉዎች አይቀጣም። ሆኖም በሌሎቹ መቀጣት በጣም ሰነፎች የሆኑትን ያስፈራራቸውና ያስተምራቸው ዘንድ አንዳንዶችን ይቀጣል። ሌሎች እነርሱን አይተው ለሃይማኖትና ለምግባር ይነሣሡ ዘንድና መልካም ሕይወታቸውን አርአያ ያደርጓቸው ዘንድ ከደጋጎች አንዳንዶችን አሁን (በዚህ ዓለም) ያከብራል። ነገር ግን ለእያንዳንዱ እንደየ ጽድቁ ዋጋውን የሚያገኝበት የፍርድ ቀን እንዳለ ታውቅ ዘንድ ሁሉንም በዚህ ዓለም ክብራቸውን አይገልጥም። ሁሉም የድካማቸውንና የተጋድሏቸውን ዋጋ በዚህ ዓለም ቢቀበሉ የትንሣኤን መኖርና አስፈላጊነት ይጠራጠሩ ነበር።

ሆኖም ግን እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ለማንም ሰው ምንም ዓይነት እንደ ሥራው ባያደርግ (ሁሉንም ክፉዎች ባይቀጣና ሁሉንም ደጋጎች ክብራቸውን ባይገልጥ) ብዙዎች ግዴለሽ ይሆኑ ነበር። ኃጢአት ቅጣት የሌለው፣ ጽድቅም ዋጋ ቢስ የሚመስላቸው ሰነፎች አሳባቸው ትክክል ሊመስላቸው ይችል ነበር። ስለዚህ ምክንያት አንዳንዶችን አሁን ይቀጣል፣ ሌሎቹን ደግሞ ዝም ይላቸዋል፤ በዚህ አድራጎቱም የተቀጡትንም፣ ያልተቀጡትንም ሁለቱንም ወገን ይጠቅማቸዋል። የተቀጡትን በተግሣጽ እንዲታረሙ ሲያደርጋቸው እነዚህን ደግሞ ከእነዚያ ቅጣት እንዲማሩ ዕድል ይሰጣቸዋል። ይህም ራሱ ክርስቶስ ከተናገረው ግልፅ ሆኖ እናገኘዋለን። ግንብ ወድቆ ስለ ገደላቸው ሰዎች ባወሩለት ጊዜ እንዲህ አላቸው፦ *«እነዚህ ሰዎች ብቻ ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስላችኋልን? አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁም እንዲሁ ትጠፋላችሁ።»* ሉቃ. 13፥4።

የጠፉት በኃጢአታቸው ምክንያት እንደ ጠፉ፣ የተረፉት ሌሎቹ ግን ያልጠፉት ስለ ጽድቃቸው እንዳልሆነ፣ ነገር ግን በሌሎች ቅጣት ተምረው ንስሐ ይገቡና የተሻሉ ይሆኑ ዘንድ እንደ ሆነ አስተዋልህ? እንዲህ ከሆነ የተቀጡት ያገኛቸው ነገር ኢፍትሐዊ አይሆንምን (የበለጠ አልተጎዱምን)? የሚል ይኖራል። እነርሱም እንዳልተቀጡት ሰዎች ከሌሎች ቅጣት ተምረው የተሻሉ ሊሆኑ ይችሉ ነበርና። ነገር ግን በንስሐ ተመልሰው ጥሩ ሰዎች የሚሆኑ ቢሆኑ ኖሮ ይህን የሚያውቅ እግዚአብሔር አይቀጣቸውም ነበር። ብዙዎች በተለያየ ኃጢአት እያሳበኑትና እንደማይመለሱ እያወቀ እንኳ የራሱን ድርሻ ለማድረግ ሲል ቶሎ ሳይቀስፋቸው ዕድሜ እየሰጠ አንድ ቀን ልብ አድርገው ወደርሱ ይመጡ ዘንድ የሚታገሣቸው ከሆነ ከሌሎች ቅጣት ተምረው በንስሐ የሚመለሱትንማ እንዴት የንስሐ ዕድል ይነሳቸዋል? ዕድሜ ቢሰጣቸው ሕይወታቸው የሚለወጥ ቢሆን ኖሮ የንስሐ ዕድሜ ባልከለከላቸው ነበር። ነገር ግን ዕድሜም ቢሰጣቸው የባሰ በኃጢአት ላይ ኃጢአት የሚጨምሩ መሆናቸውን እርሱ በአምላክነቱ ሁሉንም ስለሚያውቅ መቀጣታቸው እንደሚሻላቸው አውቆ ይህንኑ አደረገ። በመቀጣታቸው ከክፉ ግብራቸው ስለተለዩና ነጻ ስለ ወጡ ይጠቀማሉ።[80] እንዲሁም እዚህ ስለ ተቀጡ በዚያ የሚያገኛቸው ቅጣት ስለሚቀልላቸው በመቀጣታቸው ይጠቀማሉ እንጂ ያለ አግባብ የተደረገባቸው ምንም ዓይነት ኢፍትሐዊ ነገር የለም።

ያልተቀጡትም እንዲሁ የተደረገባቸው ኢፍትሐዊ ነገር የለም፤ ፈቃደኞች ካላቸው የእግዚአብሔርን ትዕግሥት በማድነቅና የተሰጣቸውን የንስሐ ዕድል በመጠቀም በተቀጡት ላይ የደረሰውን አይተው አንድ ቀን ከክፉ ግብራቸው ወጥተው ራሳቸውን በጽድቅ ጎዳና ለማስማራት ይችላሉና። በክፋታቸው ቢቀጥሉ ግን ይመለሱና ይድኑ ዘንድ ዕድል የሰጠ እግዚአብሔር በዚህ ምክንያት ተወቃሽ አይደለም፤ እነርሱ ግን የእግዚአብሔርን ሰፊ ትዕግሥት አልተጠቀሙበትምና ይቅርታ የማይገባቸው ናቸው። ይህንንም አሳብ ኃጢአተኞች ሁሉ ለምን በዚህ ዓለም እንደማይቀጡ ለማሳየት ብቻ ሳይሆን ስለሌላም ከዚህ ሳላነሰ ነገር ማስረጃ አድርጎ መጠቀም ይቻላል። ይህ ሌላ ነገር ምንድነው?

እግዚአብሔር በሁሉም ሰው ላይ እንደየ ኃጢአቱ የሚገባውን ቅጣት ቢያመጣ ኖሮ የሰው ልጅ ዘር ከብዙ ዘመን በፊት ጠፍቶ ነበር፤ የሰው ልጅ ከትውልድ ወደ ትውልድ የመተላለፉ ነገር ያከትም ነበር። ይህ እውነት መሆኑን ትረዳ ዘንድ ነቢዩ እንዲህ ሲል ስማው፣ *«እመሰ ኃጢአተኑ ትትዐቀብ እግዚኦ እግዚኦ መኑ ይቀውም - አቤቱ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ፤ በፊትህ ማን ይቆማል?»* መዝ. 129፥3። ይህንን ቃል ትንሽ ገባ ብሎ ማየት ጥሩ መስሎ ከታየህ ትክክለኛውን ራስን የመመርመር ጉዳይ ለእያንዳንዱ ለራሱ ትተን ሁሉም ተስማምቶና ተያይቶ የሚሠራውን ኃጢአት እንኳ እስኪ እንመልከት።

[80] ቅዱስ ጳውሎስ «እስመ ዘሞተሰ ድኅነ እምገቢረ ኃጢአት - የሞተስ ከኃጢአት ነፃ ወጥቷል» ይላል። የሞተ ሰው ያልሞተውን የሚበልጠው በዚህ ነው፤ ማለትም ተጨማሪ ኃጢአት የመሥራት እድል የለበትም፤ በኃጢአት ከመገዛት ነፃ ወጥቷል። ሮሜ 6፥7

ከዚህም ስለ እያንዳንዱ ኃጢአታችን ብንቀጣ ኖሮ ከስንት ዘመን በፊት እንጠፋ እንደ ነበር ግልጽ ሆኖ እናየዋለን::

ጌታችን *«ወንድሙን ደንቆሮ የሚለው የገሃነም ፍርድ ይገባዋል»* ብሏል:: ማቴ. 5፥22:: ከእኛ መካከል በዚህ ኃጢአት በድሎ የማያውቅ ይኖራል? ስለዚህ ከብዙ ጊዜ በፊት፣ በጣም ከብዙ ዘመን በፊት ጠፍተን፣ ወደ ገሃነም ተጥለን ነበር:: እንደ ገናም መሐላ የሚምል ከክፉው (ከዲያብሎስ) ነው ይላል:: ማቴ. 5፥ 37:: እስኪ መሐላ ምሎ የማያውቅ ማነው? አለመማል ቀርቶ በሐሰት ምሎ የማያውቅ አለ? *«ወደ ሴት ያዩ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል»* ይላል:: ማቴ. 5፥28:: ከዚህ ኃጢአትም ብዙዎች ንጹሐን አይደሉም:: እንግዲህ እነዚህ የታወቁ ኃጢአቶች እንዲህ ከባዶችና እያንዳንዳቸውም ከባድ ቅጣትን የሚያስከትሉ ሲሆን፣ በእነዚህ ላይ እያንዳንዳችን በስውር የምንሠራውን ኃጢአት ምን ያህል እንደ ሆነ ደኅና አድርገን ብናስበው የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃና መግቦት በእያንዳንዱ ኃጢአታችን እንዳልቀጣን እናያለን::

ስለዚህ ገንዘብ አሳዳጅ፣ ዘራፊ፣ አመንዝራ፣ ሰውን የሚገፋና የሚበድል፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ወዘተ የሆነ ማንንም ሰው ሳይቀጣና ሳይቀሰፍ ዝም ተብሎ ብታይ ሕሊናህን በራስህ ላይ እውነተኛ ፈራጅ አድርገህ ሰይምና እስከ ዛሬ ያደረግኸውን ኃጢአት ሁሉ አንድ በአንድ ለቋስታወስ ሞክር::[81] በዚህም ስለ እያንዳንዱ ኃጢአት ወዲያውኑ ቅጣት መቀበል እንዴት ከባድና የሚያስቸግር እንደ ሆነ በራስህ ላይ ቢሆን በሚሰማህ ስሜት ትረዳዋለህ::

ነገር ግን ስለ ሌሎች እንደሚያወሩትና በሌሎች የሚሆነውን አጥብቀው እንደሚመረምሩት ያህል አስቀድመው የራሳቸውን ኃጢአት ስለማያዩ ስለዚህ ምክንያት ብዙ ሰዎች ፍሬ ቢስና ትርጉም የለሽ ንግግር ለመናገር እንደበታቸው ይፈጥናል፤ እያንዳንዱ የራሱን በራሱ ደብቆ የሌላውን ጉዳይ ጥብቅ መርማሪ ይሆናል:: እኛ ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንዲህ አናድርግ፣ በተቃራኒው እንጂ:: እንዲሁም ማንኛውንም ጻድቅ ሰው ሲቀጣና በመከራ ሲፈተን ብታይ ኢዮብን አስታውሰው፣ ማንም ጻድቅ ቢሆን ከኢዮብ የበለጠ ጻድቅ አይሆንምና:: ብዙ መከራ የሚቀበል እንኳ ቢኖር ያ ታላቅ ጻድቅ ኢዮብ የተቀበለውን ያህል አልተቀበለምና::

8. ይህን በሕሊናህ ይዘህ ጌታህን መውቀስ አቁም:: እግዚአብሔር ይህን ሰው መከራ ይቀበል ዘንድ የተወው ረስቶት ወይም ትቶት ሳይሆን

[81] «ክፉና ኃጥእ የሆነ ሰው በልጽግና ደስ ብሎት በጥሩ ሁኔታ ሲኖር ብታይ በአንድ ወቅት የሠራው ጥቂት መልካም ነገር እንዳለና የዚያንም ዋጋ እዚህ እየተቀበለ መሆኑንና በሚመጣው ዓለም ግን የሚቀበለው ነገር እንደ ሌለው እወቅ» ይላል:: *(Or.* lxv.)





የድል አክሊል ይሰጠውና የከበረና የተለየ ያደርገው ዘንድ ፈልጎ ነውና:: ኃጥእ ሰው ሲቀጣ ብታይ፣ በአልጋው ላይ 38 ዓመት ያሳለፈውን መጻጉእን አስታውሰው:: ያ ሰው ደዌው የመጣበት በኃጢአቱ ምክንያት ነውና፣ ጌታችን *«እነሆ ድነሃል፣ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ»* ያለው ለዚህ ነው:: ዮሐ. 5፥5 ፣14:: ስንቀጣ ወይም የኃጢአታችንን ፍዳ እንከፍላለን፣ በጽድቅ ሕይወት እየኖርን መከራ ከደረሰብን ደግሞ የክብር ምክንያት ይሆንልናል::

ስለዚህ በኃጢአትም ኖርን በጽድቅ ቅጣትና ተግሣጽ ጠቃሚያችን ነው፤ አንዳንድ ጊዜ የከበርንና ከሌሎች የተለየን እንድንሆን ያደርገናል፣ ራሳችንን የምንገዛ እንድንሆን ይረዳናል፣ የሚመጣውንም የኃጢአታችንን ፍዳ ያቀልልናል:: እዚህ የሚቀጣና ይህንንም በትዕግሥትና በአኰቴት የሚቀበል እዚያ የሚያገኘው ቅጣት ቀላል እንደሚሆንለት ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል:- *«ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፤ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል:: ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብን ነበር፤ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኰነን በጌታ እንገሠጻለን::»* 1 ቆሮ. 11፥32:: ስለዚህ እነዚህን ነገሮች አውቀንና ተረድተን በእግዚአብሔር ጥበቃና መግቦት ላይ ያለንን አስተሳሰብ በዚህ መልኩ እናስተካክል፣ የነቃፊዎችንም አንደበት ዝም እናሰኝ::

እየሆኑ የምናያቸው ነገሮች የእኛን የመረዳትና የማወቅ ወሰን ያለፉ ቢሆኑ ከዚህ የተነሣ የእኛ ሕይወትና ጉዳይ በእግዚአብሔር መግቦት ሥር እንዳልሆነ አናስብ፤ ነገር ግን አምላካዊ መግቦቱን መረዳትና ማወቅ በምንችለው መጠን ተገንዝበን ከዐቅማችን በላይ የሆነውን ደግሞ ለጥበቡና ለእውቀቱ አይመረመሬነትና አይደረሴነት እጅ እንስጥ:: ከእርሱ ጋር በሚገባ ቀርቦ ሳልተነጋገረ ሰው የሌላውን ሰው የጥበብ ሥራ እንኳ አንድ በአንድ በቀላሉ አጣርቶ ማወቅ የማይቻለው ከሆነ ከዚህ ይልቅ እጅግ በጣም ረቂቅና ምጡቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ወሰን የለሽ መለኮታዊ ጥበቃ ለመረዳት ለሰው ሕሊና እንዴት ይቻላል?

ሐዋርያው ይህን እንዲህ እያለ ያደንቃልና እኛም አብረን ከእርሱ ጋር እናድንቅ:- *«ባለ ጠጋነቱና ጥበቡ እውቀቱም እጅግ ጥልቅ ነውና፣ ፍርዱም የማይመረመር ነው፣ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም::»* ሮሜ 11፥33 :: ሆኖም ግን ስለ አንድ ነገር ትንሽ ክፍል በምናገኘው እውቀት ስለ ሙሉው ነገር ለማወቅና ለመረዳት እንደምንችለው ሁሉ በዓቅማችን ልንረዳቸው በምንችላቸው ነገሮች መሠረት የማንረዳውንም ቢሆን በረቂቅ ጥበቡ እርሱ ባወቀ እንደሚያደርግ ተረድተን ስለሚሆነው ሁሉ እናመስግነው::

የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ጥበቃ በተመለከተ ይህን ለማያምኑ ለሌሎች ሊገልፁ ለሚፈልጉ ሰዎች ሌላም የማይናቅ ነገር አለ:: ከሃዲዎችን እግዚአብሔር አለ ወይ? ብለን ስንጠይቃቸው «የለም» የሚሉ ከሆነ ምንም አንመልስላቸው:: አእምሮው ለታመመ ለእብድ መመለስ ጥቅም እንደ ሌለው ሁሉ እግዚአብሔር የለም ለሚሉም እንዲሁ ነው:: ሰዎችንና ብዙ ዕቃ የጫነች፣ ነገር ግን ነጂና መሪ የሌላት መርከብ አቅጣጫዋን ጠብቃ አንድ ማይል እንኳ በባሕር ላይ በጥሩ ሁኔታ መሄድ የማትችል ከሆነ ብዙ ሰዎችን በውስጡ የያዘ፣ ከብዙ የተለያዬ ነገር የተሠራና የተገኘ ይህ ዓለምም የሚመራው፣ የሚቆጣጠረውና ህልውናውን የሚጠብቅ አምላክ ባይኖር ኖሮ ይህን ለሚያህል ብዙ ዘመን እንዲህ ሥርዓትን ጠብቆ ሊጓዝና ሊኖር አይችልም ነበር::[82]

ነገር ግን በብዙዎች እምነት መሠረት እንዲሁም በሁኔታዎች ከሚታየውና ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው አምላክ አለ ካሉ እንዲህ እንበላቸው:: አምላክ ካለ፣ በርግጥም አዎ አምላክ አለ፣ ይህ አምላክ ቅንና ርቱዕ[83] ነው:: ርቱዕ ካልሆነ አምላክ አይደለምና:: ርቱዕ ከሆነም ለእያንዳንዱ እንደየሥራው የሚገባውን ይሰጣል:: ስለዚህ እያንዳንዱ እንደየሥራው በመቀበሉ የእግዚአብሔር ርቱዕነት ይገለጥ ዘንድ ሌላ የፍርድ ቀን (የዋጋ መቀበያ ቀን) ያለ መሆኑን ተስፋ ማድረግ ይገባል:: ይህን ማስተዋል መለከአታዊ ጥበቃን በተመለከተ ስላለን ግንዛቤ ብቻ ሳይሆን ስለ ትንሣኤም ለመረዳት ይጠቅመናል:: እኛም ሌሎችን እናስተምር፣ በፈጣሪያቸው ላይ አፋቸውን የሚከፍቱትን አንደበታቸውን ዝም እናሰኝ፣ እኛ ራሳችንም በሁሉም ነገር እናከብረው:: የእርሱን ርዳታና ጥበቃ የበለጠ የምናገኘው፣ በእውነት ክፉ ከሆነው የምናመልጠውና በማያልፈው ዓለም መልካሙን ሁሉ የምናገኘው በዚህ ነውና፣ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን መውደድና ቸርነት፣ በእርሱና ከእርሱ ጋር ምስጋና ለባሕርይ አባቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዛሬም ዘወትርም እስከ ዘለዓለሙ አሜን::

[82] ቅዱስ አትናቴዎስ ይህ ዓለም ያለ ፈጣሪ እንዲሁ በራሱ ተገኘ ለሚሉ ኤፒኩሪያንስ ሲመልስ - ይህ ዓለም እንዲህ ከራሱ ቢገኝ ኖሮ ሁሉም አንድ ዓይነት - ወይ ፀሐይ፣ ወይ ጨረቃ፣ ወይም ሌላ አንድ ዓይነት ነገር ብቻ በሆነ ነበር፤ በሰውም ሁሉም ነገሩ ወይ እጅ ብቻ፣ ወይም እግር ብቻ፣ ወይም ዓይን ብቻ፣ ወዘተ ይሆን ነበር:: ነገር ግን እንደምናየው እንዲህ አይደለም:: በሥነ ሥርዓት ተስማምተው የሚታዩ የተለያዩ ሥነ ፍጥረቶች - ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣... አሉ:: በሰው አካልም እጅ፣ እግር፣ ዓይን ወዘተ አሉ:: ይህ ዓይነት የተለያዩ ሥነ ፍጥረታት መኖር፣ እንዲሁም በአንድ ሰው ያሉ የተለያዩ ግን ሁሉም የተስማሙና የተቀናበሩ አካላት መኖራቸው የሚያሳየው ከራሳቸው መገኘታቸውን ሳይሆን እንዲህ አስማምቶ የፈጠራቸው አስገኚ መኖሩን ነው:: ከእነዚህ ከሥነ ፍጥረቶችም ሁሉንም በሥነ ሥርዓትና በስምምነት እንዲኖር በልዩ ጥበቡ ያዘጋጃቸውን እግዚአብሔርን ማወቅ ይቻላል:: *በእንተ ሥጋዌ፣ ምዕ. 2 ቁ. 1-2::*

[83] (Just)





# ክፍለ ትምህርት ሁለት[84]

## <u>እግዚአብሔር ሰይጣንን ለምን ፈጠረው? ለምንስ አላጠፋውም? ከዚህ ዓለምስ ለምን አላስወገደውም? ስለሚሉ ሰዎች የተሰጠ ትምህርት</u>

በቀድሞ ዘመን ይስሐቅ በልጁ እጅ ምግብ ይበላ ዘንድ በወደደ ጊዜ ልጁን ከቤት ወደ ዱር ወደ አደን ስፍራ ላከው:: ይህ ይስሐቅ ከእኔ እጅ ምግብ ይቀበል ዘንድ በወደደ ጊዜ ግን እኔን ከቤት ወደ ዱር የላከኝ ሳይሆን እርሱ ራሱ ወደ እኛ ማዕድ መጣ:: ከእርሱ የበለጠ ለእኛ ያለውን ጥልቅና እውነተኛ ፍቅር ያሳይ ዘንድ የፈቀደ ማን አለ? ከእርሱስ የበለጠ ትሑት ወዳጅ ይገኝ ይሆን? ከዚህም የተነሣ ያለ ኃይላችንን በጧቱ ትምህርት ጨርሰን የነበረ ቢሆንም የአባትነት ፊቱን ባየን ጊዜ ድካማችንን ረሳነው፣[85] የኃይላችንን ማለቅ ዘነጋነው፣ በደስታ ከፍ ከፍ አልን፣ ብሉየ መዋዕል የሆነ አስደናቂ ራሱን ባየን ጊዜ ነፍሳችን በብርሃን ተዋጠች::

በልቶ ይባርከን ዘንድ ስለዚህም ምክንያት ማዕዳችንን አዘጋጅተን አቀረብን:: በዚያ እንደ ነበረው ያለ ማታለል በዚህ የለም:: ምግብ እንዲያመጣ የታዘዘው አንዱ ነበር፣ ያመጣው ግን ሌላው ነው::[86] እዚህ ግን እኔው እንዳመጣ ታዘዝሁ፣ እኔው ራሴ አመጣሁ:: አባቴ ሆይ፣ ስለዚህ እኔን ልጅህን በመንፈሳዊ በረከት ባርከኝ፣ ይህም ሁላችንም እናገኘው ዘንድ ሁል ጊዜ የምንፈልገውና ስለርሱም የምንጸልይለት በረከት ሲሆን ለእናንተ ብቻ ሳይሆን ለእኔም፣ እዚህ ላለነውም ሁሉ የሚጠቅመን ነው:: የሁላችንንም የጋራ አባት ዕድሜያችሁን እስከ ይስሐቅ ዕድሜ ድረስ እንዲያረዝምላችሁ ለምኑት:: ይህ ከሰማይ ጠልና ከምድር ስብ የበለጠ ጠቃሚና አስፈላጊ ነውና::

ነገር ግን ማዕዳችንን የማዘጋጀት ጊዜ ደርሷል:: ይህ ምንድን ነው? ለእናንተ ካለን ፍቅር የተነሣ ቅርብ ጊዜ ካልነው የተረፈው ትምህርት ነው:: ዛሬ ጧትም ተዘጋጅተው ለቀረቡ ቃል ኪዳንና ሰይጣንን መካድን በተመለከተ እንደ ተናገርናቸው፣ ከሁለት ቀን በፊት ዲያብሎስን

[84] (Homily II)

[85] እንዲህ የሚለው ሊቀ ጳጳሱን ነው፣ ይህን ትምህርት ያስተማረው ሊቀ ጳጳሱ በተገኙበት ስለ ነበር ነው::

[86] ይስሐቅ አደን አድኖ ምግብ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብለትና በዚህም እንዲመርቀው ያዘዘው ዔሳውን ነበር:: ነገር ግን ዔሳው ገና ከአደን ሳይመለስ ወንድሙ ያዕቆብ "እኔ ዔሳው ነኝ" ብሎ ምግብ አቅርቦ አባቱን ይስሐቅን አብልቶ የዔሳውን ምርቃት በተንኮል ወሰደበት:: ዘፍ. 27

የሚለን ስለሆነ ሳይሆን እርሱን በተመለከተ የምትማሩት ትምህርት ለመጠንቀቅና ለመጠበቅ በጣም የሚጠቅማችሁ ስለሆነ ነው::

እርሱ ጠላትና ባላጋራ ነው፤ ስለሆነም የጠላታችሁን ዘዴና ተንኮል ማወቅ ጠቃሜታው ታላቅ ነው:: እርሱ በኃይል ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ነገር ወይም በማስገደድ ማሸነፍ እንደማይችል በቅርቡ ተነጋግረናል:: እንዲህ ቢሆን ኖሮ ሰውን ሁሉ አንድ ሳያስቀር ባጠፋ ነበር:: ለዚህም ምስክር እርሱ (ጌታችን) እስኪፈቅድላቸው ድረስ ምንም ሊያደርጓቸው ያልቻሉትን እሪያዎችን አይተናል:: ማቴ. 8፥31:: የኢዮብን የበግና የከብት መንጋም ከላይ ፈቃድ ጠይቆ እስኪሰጠው ድረስ ሊያጠፋ አልደፈረም:: ስለዚህ በመጀመሪያ በኃይልም ይሁን በማስገደድ ምንም ማድረግ እንደማይችል ይህን አንድ ነገር ተምረናል፤ ከዚህም ቀጥሎ በማታለልና በተንኮል እጅ ሲያደርግ እንኳ ሁሉንም ድል እያደርግም፤ ሁል ጊዜም ድል አይቀናውም:: ለዚህም አሁንም ታላቁን አትሌት ኢዮብን እንስተናል፤ ዲያብሎስ ራሱ ዋና ተዋናይ ሆኖ፤ ያለ የሌለ ኃይሉን ሁሉ አሰልፎ ተዋግቶት እንኳ ድል ሊያደርገው አልቻለም፤ ተሸንፎ አፍሮ ከጦርነቱ ተባረረ እንጂ::

አሁንም አንድ ጥያቄ ይቀራል:: እርሱ ምንድን ነው? በኃይል ድል ማድረግ ባይችልም በማታለልና በተንኮል ያስታል:: ስለዚህም ምክንያት ቢጠፋ ይሻል ነበር:: ኢዮብ ቢያሸንፈውና ቢከብርበትም አዳም ግን ተታልሎ ወድቆበታል:: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከዚህ ዓለም ተወግዶ ቢሆን ኖሮ አዳም ፈጽሞ አይስትም ነበር:: አሁን ግን ዲያብሎስ በዚህ ዓለም ስላለ አንዱ ቢያሸንፈው እንኳ ብዙዎችን ድል ያደረጋል:: አሥር ቢያሸንፉት እልፍ አእላፋትን ድል አድርጎ ይማርካል፤ እግዚአብሔር አጥፍቶት ቢሆን ኖሮ ግን እነዚህ እልፍ አእላፋት ባልጠፉ ነበር ይላሉ::

ስለዚህ ምን እንላለን? በመጀመሪያ ደረጃ ድል ከሚሆኑት ይልቅ ድል የሚያደርጉት ቁጥራቸው ከነዚያ ያነሰ ቢሆንም እንኳ በጣም ከፍ ያለ ዋጋ አላቸው:: *«ትእዛዙን ከማይጠብቁ ከሺህ ሰዎች ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ አንድ ይበልጣል»* ይላልና:: ሢራ. 16፥3:: ቀጥሎም፤ ተቃዋሚው ቢወገድ ኖሮ ድል የሚያደርጉ ይጎዱ ነበር:: ዲያብሎስን እንዳለ ብትተወው ሰነፎች የሚጎዱት ከጥንቁቆቹ የተነሣ አይደለም፤ በራሳቸው ስንፍና እንጂ:: ስለ ሰነፎቹ ስትል ጠላትን እንዳይኖር ብታደርገው ግን ትጉሃኑ ስለ ሰነፎቹ የመንፈሳቸውን ጥንካሬ በእግዚአብሔር ርዳታ የሚያሳዩበትን ዕድል አሳጣሃቸው፤ የክብር አክሊልም እንዳያገኙ መንገዱን ዘጋህባቸው ማለት ነው::



እንደገና የበለጠ ግልጽ አድርጌ እናገረው ዘንድ አስፈላጊ ነው:: ምንም ተቃዋሚ (ሰይጣን)[87] የለም እንበል:: ከእርሱ ጋር የሚወዳደሩ ሁለት አትሌቶች አሉ እንበል:: ከእነዚህ አንዱ አብዝቶ የሚበላ፤ ያልተዘጋጀ፤ ጥንካሬ የሌለው ደካማ ነው እንበል፤ ሌላው ግን ትጉህ፤ ብዙ ጊዜውን በልምምድና በሥልጠና ላይ ያጠፋና ለውድድሩ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሁሉ በማድረግ ሲዘጋጅ የቆየ ነው እንበል:: ከዚያም ተቃዋሚውን ብታጠፋው (ውድድሩን ብትሰርዘው) ከእነዚህ ከሁለቱ የጎዳኸው የትኛውን ነው? ያልተዘጋጀውን ሰነፉን ነው? ወይስ በመዘጋጀት ያን ያህል የደከመውን? የተዘጋጀውን እንደሆነ ግልጽ ነው:: ተቃዋሚው ቢወገድ ጠንካራው በሰነፉ ተጎድቷልና:: ሰነፉ ግን ከጎበዙ የተነሣ ምንም አይጎዳም:: የሰነፉ አለመዘጋጀትና ስንፍና እንዳይገለጥ ሲባል ብቻ ተቃዋሚው እንዳይኖር ቢደረግ ጠንካራው ስለ ሰነፉ ሲባል በሚደረገው ነገር ተጎዳ ማለት ነው:: ምክንያቱም እርሱ ያን ያህል ተዘጋጅቶ ለውድድር ቀርቦ የሰነፉ ስንፍና እንዳይገለጥ ስትል ብቻ ውድድሩን በማስቀረትህ የድካሙን ፍሬ ሊያይ የሚችልበትን ዕድል አሳጣኸው ማለት ነው:: ስለዚህ ይህ አካሄድ ስንፍናን የሚያበረታታ፤ ጥንካሬንና ራስን መግዛትን ግን የሚያዳክም ነው:: ሰነፉ ውድድር ኖረም አልኖረም ጥንቱኑ በራሱ ስንፍና ወድቋልና:: የተዘጋጀው ግን ተወዳድሮ በማሸነፍ ዝግጅቱንና ድካሙን የሚያካክስበት ሽልማትና ክብር ያገኝ ነበር::

የማይጠነቀቁትን የሚጎዳቸው ዲያብሎስ ሳይሆን የራሳቸው ስንፍና መሆኑን የበለጠ ትረዳ ዘንድ ለዚህ ጉዳይ ሌላ አስረጅ አመጣለሁ:: ዲያብሎስ በተፈጥሮው ሳይሆን በራሱ ምርጫና ድርጊት በጣም ክፉ ነው:: ዲያብሎስ በተፈጥሮው ክፉ እንዳልሆነ ከስሙ እንኳ ማወቅ ትችላለህ[88]:: ዲያብሎስ ሐሰተኛና ሐሜተኛ ነው፤ ሰውን ለእግዚአብሔር እንዲህ ብሎ አምቷልና፡- *«በውኑ ኢዮብ አንተን የሚያመልክህ በከንቱ ነውን? ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ዳብስ፤ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል::»* ኢዮ. 1፥9፥ 11:: እንደ ገናም እግዚአብሔርን ለሰው አምቷል፤ እንዲህ በማለት፡- *«የእግዚአብሔር እሳት ከሰማይ ወደቀች፤ በጎቹንም አቃጠለች»* ኢዮ. 1፥16:: ይህ መከራ የመጣበት ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሆነ ለማሳመንና አገልጋዩን ከጌታው፤ ጌታውን ከአገልጋዩ ጋር ለማጣላትና ለማለያየት ሞከረ:: ነገር ግን አዳም ከእግዚአብሔር ጋር እንዳደረገው ሌላ አገልጋይ ከጌታው

[87] ሰይጣን የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን መስተጻርር፤ መስተቃርን - ተቃዋሚ፤ ተቃራኒ ማለት ነው::

[88] የመጀመሪያ ስሙ ሳጥናኤል እንደ ነበር ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይናገራሉ:: ሳጥናኤል ማለትም ቅሩብ እግዚአብሔር ማለት ነበር:: ግብሩ ሲለወጥ ስሙም አብሮ ተለወጠና ሰይጣን (ተቃራኒ፤ ተቃዋሚ)፤ ዲያብሎስ (የግሪክ ቃል - የወደቀ፤ ውዱቅ)፤ ጋኔን (የከፋ የከረፋ) የሚሉ የክፉ ሥራው ገላጭ የሆኑ ስያሜዎች ተሰጡት::

ኃይል ሳይሆን ከሰውዬው የግል ስንፍናና አለማስተዋል እንደ ሆነ ታውቅ ዘንድ፤ እዚህ ላይ ምክረ እንጂ አልቻለም። ስለሆነም ዲያብሎስ የተባለው ስለዚህ ምክንያት እንጂ በተፈጥሮው አይደለም። ለማጣላት ሲሉ በሐሰት ማውራትም ሆነ ከዚህ መራቅ ተፈጥሮአዊ (ባሕርያዊ) ሳይሆን በራስ ምርጫና ውሳኔ ሊደረግም ሆነ ሊቀር፣ ሊቋረጥም ሆነ ሊቀጥል የሚችል ድርጊት ነው። ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ወደ ነገሩ መሠረታዊና ይዘታዊ ባሕርይ የሚደርሱ አይደሉም።

እንዲሁም ክፉ ይባላል። ነገር ግን ክፋቱ ከተፈጥሮው አይደለም። በተፈጥሮው ክፉ ሆኖ ስለተፈጠረ ሳይሆን ከራሱ ምርጫ የመጣ ነው። ስለዚህ ባሕርያዊ ስላልሆነ ክፋቱ ከመጀመሪያ ሲፈጠር ጀምሮ የነበረበት ሳይሆን በኋላ በድርጊቱ የተሰጠው ስያሜ ነው። ስለዚህም ነው ከሃዲ የሚባለው። ብዙ ክፉ ሰዎች ቢኖሩም ክፉ የሚለው ቅጽል ለእርሱ የተሰጠው ከክፋቱ ወደር የለሽነት የተነሣ ነው። ለምን እንዲህ ተባለ? ምክንያቱም እኛ ምንም ያደረግነው ነገር ሳይኖር ነገር ግን የሰውን ልጅ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብሮ ባየው ጊዜ ባገኘው መልካም ነገር በመቅናት ወዲውያኑ ጠላቱ ሆነ። ምንም ተገቢ ምክንያት ሳይኖር እንዲህ ዋና ጠላት ከመሆን የበለጠ ምን ክፋት አለ?

ከተጠነቀቅን ዲያብሎስ በእኛ ላይ ጉዳት የማያደርስብን መሆኑን፣ በመሪጡት ሕይወት ደካሞች፣ ያልተዘጋጁና ሰነፎች ለሆኑ ደግሞ ዲያብሎስ ባይኖር እንኳ ራሳቸውን በብዙ ኃጢአትና ውድቀት እንደሚጥሉ ትረዳ ዘንድ እስኪ እርሱን እዚያው እንተወውና ሥነ ፍጥረትን እንመልከት። ዲያብሎስ ክፉ መሆኑን እኔም ራሴ ደጋግሜ አድርጌ አውቀዋለሁ፣ ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይም ነው። ሆኖም አሁን ልንነጋገራቸው ያላቸውን ነገሮች ልብ ብለህ ተከታተል። ተራ ነገሮች ሳይሆኑ ስለ እነርሱ በየቦታው ብዙ ጊዜ ተዘውትሮ ብዙ ቃላት የሚነገርላቸው፣ ስለ እነርሱም ምክንያት አማንያን ከኢ-ማንያን ጋር ብቻ ሳይሆን የሚያምኑት ከሚያምኑት ጋር ሳይቀር ብዙ ጦርነትና ክርክር የሚደረግባቸው ናቸው። በጣም የሚያሳዝነውም ይህ ነው።

3. ከላይ እንዳልሁ ዲያብሎስ ክፉ መሆኑ በሁሉም ዘንድ የታወቀና የታመነ ነገር ነው። ስለዚህ ውብና ድንቅ ፍጥረት ምን እንላለን? ሥነ ፍጥረትን እንደሚነቅፍ ያለ አእምሮውን ያጣና አላዋቂ ማን አለ? በተፈጥሮው ክፉ ሳይሆን ውብ ፍጥረት እንዲሁም የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል እና የፍቅሩ ማሳያና መግለጫ ነበርና። ነቢዩ እያደነቀ እንዲህ ሲል ሰማው፡- *«ጥቀ ዐቢይ ግብርከ እግዚኦ ወኩሎ በጥበብ ገበርከ - አቤቱ ሥራህ እንዴት ድንቅ ነው፣ ሁሉንም በጥበብ አደረግህ»*



ሊረዱት ከማይቻለው የእግዚአብሔር
ዘወር አለ።

እርሱንም እንዲህ ውብና ታላቅ አድርጎ እንደ ፈጠረው ሲገልፅ ሌላው እንዲህ ይላል፡- *«ከሥነ ፍጥረት ታላቅነትና ውበት የተነሣ ፈጣሪያቸው ግልጽ ሆኖ ይታያል»* ጥበብ 13፥5። ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ይላል፡- *«የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና»* ሮሜ 1፥20። እያንዳንዱን ሥነ ፍጥረት ስናየው ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ይመራናል።

ታዲያ ይህን ውብና ድንቅ ፍጥረት በራሱ ለብዙዎች ፈተናና ህፀፅ ምክንያት ሲሆን ብናይ ከዚህ የተነሣ ፈጣሪውን ልንነቅፍ ይቻለናልን? በምንም መንገድ መንቀፍ አይቻለንም፤ መድኃኒቱን በአግባቡ መጠቀም ያልቻሉትን እንጂ። ይህ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ይመራሉ ከተባሉት ድንቅ ፍጥረቶች አንዱ የነበረ እርሱ እንዴት የክህደትና የህፀፅ ምክንያት ሆነ? *«ጥበበኞች»* ይላል፣ *«አሳባቸው ከንቱ ሆነ፤ የሚያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፤ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መሰለው ለወጡ። በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን አመለኩ፤ አገለገሉም»* ሮሜ 1፥21፥25። እዚህ ላይ ዲያብሎስ የለም፤ እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምረን ዘንድ መምህር ሆኖ በፊታችን ያለው ሥነ ፍጥረት ብቻ ነው። ታዲያ ይህ ሥነ ፍጥረት እንዴት የስህተትና የክህደት ምክንያት ሆነ? ሥነ ፍጥረት በራሱ ተፈጥሮ እንዲህ ያደረገ ሳይሆን ሥነ ፍጥረትን ተጠቅመው ፈጣሪያቸውን ሊያውቁ ሲገባቸው ራሱን ሥነ ፍጥረትን ያመለኩት ሰዎች የልቡና ድንዛዜ ውጤት ነው። ታድያ ከዚህ የተነሣ ሥነ ፍጥረትንም እንዲሁ ሊጠፋ ይገባል እንበልን?

ስለ ሥነ ፍጥረት ለምን እናገራለሁ? ወደ ራሳችን የሰውነት ክፍሎች እንምጣ። እነዚህም በተፈጥሯቸው ሳይሆን ከእኛ ስንፍና የተነሣ እስካልተጠነቀቅንና በአግባቡ እስካልያዝናቸው ድረስ የጥፋት ምክንያቶች ሆነው እናገኛቸዋለንና። ዓይን የተሰጠህ ሥነ ፍጥረትን ተመልክተህ ፈጣሪያቸውን እንድታደንቅና እንድታመሰግን ነበር። ነገር ግን ይህን ዓይንህን በአግባቡ ካልተጠቀምህበት የዝሙት መሣሪያ ይሆንብሃል። አንደበት የተሰጠህ መልካምና ጠቃሚ የሆነ ነገር እንድትናገር፣ ፈጣሪህን እንድታመሰግን ነው። ነገር ግን አንደበትህን ካልገዛህ የስድብና የነቀፋ

መሣሪያ ይሆንብሃል:: እጆች የተሰጡህ ለጸሎት ትዘረጋቸው ዘንድ፣ መልካም ሥራም ትሠራባቸው ዘንድ ነው:: እስተዋይ ካልሆንክ ግን የሰው ገንዘብ ለመቋማት ልትዘረጋቸው ትችላለህ::

ወደ መልካም ሥራ ትገሰግስ ዘንድ እግሮች ተሰጡህ፣ ግዴለሽና ጥንቃቄ የሌለህ ከሆንህ ግን በእነርሱ ተጉዘህ ክፉ ሥራዎችን ልትሠራ ትችላለህ:: ደካማውን ሰው ሁሉም ነገር እንደሚጎዳው አየህን? ከራሳቸው ተፈጥሮ የተነሣ ሳይሆን በራሱ ድክመት ምክንያት በሰነፍ ሰው ላይ የድኅነት መድኃኒቶች ራሳቸው ሳይቀሩ ለሞት እንደሚያበቁት ተመለከትህን? እግዚአብሔር ሰማይን የፈጠረው በሥራው ተደንቀህ ሠሪውን እርሱን ታመልከው ዘንድ ነው:: ሌሎች ግን የሰማይን ፈጣሪ ትተው በራሳቸው የአእምሮ ድንዛዜ ምክንያት ራሱን ፍጥረቱን ሰማይን አመለኩ::

ስለ ሥነ ፍጥረት ለምን እናገራለሁ? ከመስቀል የበለጠ ለድኅነት የተመቸ ምን ነገር አለ? ነገር ግን ይህ መስቀል እንኳ ለሰነፍ ሰው ዕንቅፋት ሆኖበት እናያለን:: *«የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፤ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና::»* 1 ቆሮ 1፥18:: እንደ ገናም *«እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ፣ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው::»* 1 ቆሮ. 1፥13:: ለማስተማርስ ከቅዱስ ጳውሎስና ከሐዋርያት የበለጠ ማን ይገኛል? ነገር ግን ሐዋርያት ለብዙዎች የሞት ሽታ ሆነውባቸዋል:: እንዲህ ይላልና:- *«በሚድኑትና በሚጠፉት ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና፤ ለእነዚህ ልሞት የሚሆን የሞት ሽታ፣ ለእነዚያ ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን::»* 2 ቆሮ 2፥16:: ለሃይማኖትና ለምግባር ግድ የለሽ የሆነው ደካማው ሰው በቅዱስ ጳውሎስ እንኳ ሳይቀር ሲጎዳ መንፈሰ ጠንካራው ግን በዲያብሎስም እንኳ እንደማይጎዳ አየህን?

4. ይህን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የቸርነት የማዳን አገልግሎት ማየት ትወዳለህ? እርሱ በቸርነቱ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ፣ ክቡር ደሙን አፍስሶ ሳደረገልን ለዚያ ቸርነት ምን መግለጫ ቃላትና ቋንቋ ይኖረናል? ከዚህስ የቸርነት የማዳን ሥጦታ የበለጠ ለሰው ድኅነት ጠቃሚ የሆነ ምን ነገር ይገኛል? ነገር ግን እምላካችን ባሕርያችንን ተዋሕዶ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ተመላልሶ በመጨረሻም በቀራንዮ አደባባይ የፈጸመው የማዳን ሥጦታ ለብዙዎች የዕዳና የቅጣት ማክበጃ ሆኖባቸዋል:: እንዲህ ይላልና:- *«የማያዩ እንዲያዩ፣ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ»* ዮሐ. 9፥39:: ነገሩ እንዴት ነው? ብርሃን እርሱ ለመታወር ምክንያት ሆነን? አይደለም፣ ብርሃን የመታወር ምክንያት አልሆነም፣ ነገር ግን የነፍስ





ዓይን ደካማና በሽተኛ መሆን ብርሃኑን ለማየትና በብርሃኑ ለመመላለስ አላስቻለም::

መንፈሰ ደካማ ሰው በሁሉም አቅጣጫ እንደሚጎዳ፣ እግዚአብሔርን በማመን በእርሱ ኃይልና ርዳታ ላይ በመታመን የተመሠረተ ጠንካራ ሰው ግን እግዚአብሔር በሰጠው በሁሉም ነገር ተጠቃሚ እንደሚሆን አይተናል:: በማንኛውም ነገር ዋናው መሠረታዊ ነገር ዓላማ ነው፣ ወሳኙና ገዢውም ዝንባሌና ውሳኔ ነው::

ዲያብሎስ የማይጎዳን ብቻ ሳይሆን ነገሩን በደንብ ከተረዳኸው፣ ካወቅንበትና በአግባቡ ከተጠቀምንበት ልናተርፍበት እንችላለን፣ በጣምም ይጠቅመናል:: ይህን ከኢዮብ በመጠኑ አይተናል:: ይህን ከቅዱስ ጳውሎስም መማር እንችላለን:: ስለ አመንዝራው ሲጽፍ እንዲህ ይላልና:- *«መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው::»* 1 ቆሮ 5፥5:: ልብ በል፣ ለሰይጣን መሰጠት እንኳ ለመዳን ምክንያት ሆነ! ነገር ግን ይህ የሆነው ከሰይጣን የሚገኝ ደግ ነገር ኖሮ ሳይሆን ከሐዋርያው ጥበብ የተነሣ ነው:: ሐኪሞች እባቦችን ወስደው መርዘኛ አካላቸውን በመቁረጥ የመርዝ ማርከሻ መድኃኒቶችን ለማዘጋጀት ይጠቀሙባቸዋልና:: ቅዱስ ጳውሎስም ያደረገው እንዲሁ ነው:: ተነሳሕያን ኃጥአንን በቀኖና ለመቅጣት የሚያስፈልገውን ከዲያብሎስ ክፋት የሚገኘውን ወስዶ የቀኖና መድኃኒት አዘጋጀበት:: ዲያብሎስ ሊያጠፋና ሊውጥ የሚፈልግ እንጂ የድህነት ምክንያት እንዳልሆነ ትረዳ ዘንድ ከዚያ ውጭ ያለውን የዲያብሎስን ነገር ግን የማይጠቅም ስለሆነ ከዚያው ጣለው::

ቅዱስ ጳውሎስ በተሰጠው ጥበብ የዲያብሎስን ጉሮሮውን የቆረጠው ስለ መሆኑ በሁለተኛ የቆሮንቶስ መልእክቱ ስለዚህ አመንዝራ ሰው የሚለውን ስማ:- *«እንደዚህ ያለው ከልክ በሚበዛ ሐዘን እንዳይዋጥ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት ይገባችኋል:: ስለዚህ ከእርሱ ጋር ፍቅርን እንድታጸኑ እለምናችኋለሁ::»*፣ *«በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና::»* 2 ቆሮ. 2፥7-8፥11:: ይህን ሰው አስቀድሞ ከአውሬ መንጋጋ (ከአመንዝራነት ኃጢአት) ነጥቀነዋል፣ ይላል ሐዋርያው:: ይህ ሐዋርያ ሰይጣንን በሕግ የታዘዘን ቅጣት እንደሚፈጽም ቅጥረኛና ሕግ አስከባሪ ይፎቀምበታልና:: ሕግ አስፈጻሚዎች የሚቀጡት የፈቀዱትን ሳይሆን ዳኞች ያዘዟቸውን ነው::

ሕግ አስፈጻሚ ሲበቀልና ሲቀጣ የዳኛውን ትእዛዝ በጠበቀ መልኩ ነው:: ሐዋርያው እስከ የት ደረጃ እንደ ደረሰ ታያለህን? ሥጋ የለበሰው እርሱ መንፈስ የሆነውን ሰይጣንን እንደ መሣሪያ ተጠቀመበት::

የሁለቱም የጋራ ጌታ እግዚአብሔር ዲያብሎስን ኢዮብን በተመለከተ፤ *«ሕይወቱን ግን እንዳትነካ»* በማለት ይህ ክፉ አውሬ ያለ መጠን እንዳያስቃየውና ከመጠን እንዳያልፍ በኢዮብ ላይ ማድረግ የሚችለውን ነገር መጠኑን ለክቶ እንደ ሰጠው ቅዱስ ጳውሎስም እንዲሁ አደረገ:: ኢዮ. 2፥5-6:: አመንዝራውን ለእርሱ አሳልፎ ስለ መስጠት ሲናገር «ለሥጋው ጥፋት» አለ፤ ማለትም «ሕይወቱን እንዳትነካ» ማለት ነው:: ለአገልጋዩ የተሰጠው ሥልጣን እስከ ምን ድረስ እንደ ሆነ ተረዳህ? ስለሆነም ምንም እንኳ እርሱ ሥጋ ያለበሰ ረቂቅ መንፈስ ቢሆንም ዲያብሎስን አትፍራው:: ዲያብሎስ ሥጋ ባይለብስም እንኳ በክርስቶስ በሚያምኑ ዘንድ ደካማ ነውና:: እንደ ገናም መዋቲ ሥጋ ቢለብስም እንዲህ ዲያብሎስን እንደ መሣሪያ እንዳስፈላጊነቱ እንደሚጠቀም የክርስቶስ አገልጋይ ያለ ጠንካራ የለም::

5. ይህን ሁሉ ያልሁት ሰይጣንን ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ ሳይሆን እናንተ ከስንፍናና ከሐኬት ነጻ ትሆኑ ዘንድ ነው:: ራሳችንን በዚህ ከንቱ ተስፋ እያታለልን ወደ ሁሉም የኃጢአት ዓይነት ወድቀን ፍዳችን ጽኑ እንዲሆንና በጥፋታችን ራሳችንን ወቅሰን ንስሐ በመግባት ይቅርታ እንዳናገኝ ለማድረግ የኃጢአታችንን ምክንያት እርሱ ነው እንድንልና በርሱ እንድናመካኝ በጣም ይፈልጋልና:: ሔዋን በእርሱ በማመካኘቷ ምንም ነገር እንዳልተጠቀመች እኛም በእርሱ እያመካኘን በኋላ እንድንቀጣ ይፈልጋልና:: እኛ ግን ይህን አናድርግ፤ ራሳችንን እንወቅ እንጂ::

እንዲህ በማድረግ በሽታችንን ማከም እንችል ዘንድ:: በሽታውን ያላወቀ ለድካሙ ትኩረት አይሰጠውም:: ሁላችንም ብዙ ኃጢአት ሠርተናል፤ ሁላችንም ቅጣት የሚገባን ነን:: ይቅርታን ማግኘት ግን እንችላለን፤ የንስሐን መንገድ መጠቀም የምንችልበት ጊዜም አልተቆረጠብንምና ተጸጽተን የመመለስ ዕድል አለን:: ወደ ሕይወትህ ፍጻሜ የተቃረብህ ዕድሜህ የገፋ ሽማግሌ ነህን? ንስሐ መግባት የማትችል መስሎህ ስለ ድኅነትህ ተስፋ አትቁረጥ፤ በመስቀል ላይ ነጻ የወጣውን ወንበዴ አስበው:: ይህ ወንበዴ ቀድሞ ገነት የመግባትን እክሊል ከተቀዳጀበት ከዚያ ጊዜ ያነሰ[89] ምን ጊዜ አለ? ሆኖም ለመዳን ያቺ አጭር ጊዜ በቅታዋለች::

ወጣት ነህን? ወጣት በመሆንህ ገና ብዙ ዘመን አለኝ፤ ዕድሜዬ ገና ነው፤ ብለህ አትተማመን፤ ተለክቶ የታወቀ ቀሪ ጊዜ ያለህም አድርገህ

[89] ይህ ሽፍታ ከጌታችን ጋር በመስቀል ላይ የቆየው ከ6 እስከ 9 ሰዓት ብቻ ነበር:: ከዚህም ጊዜ ውስጥ ኋላ ተጸጽቶ «አቤቱ በመንግሥትህ ስትመጣ ጊዜ አስበኝ» በማለት እስኪመለስ ድረስ እየነቀፈ ብዙ ጊዜ በከንቱ አጥፍቷል:: ሉቃ. 23፥43፤ ማር. 15፥32::





አታስብ፤ *«የጌታ ቀን ድንገት እንደ ሌባ በሌሊት ይመጣልና»* 1 ተሰ. 5፥2:: ስለዚህ ምክንያት የዕድሜያችንን መጨረሻ አስቀድመን እንዳናውቀው አደረገ፤ ከዛሬ ዕለት ጀምሮ በትጋት ዝግጅታችንን እንጀምር ዘንድ:: በለጋ ዕድሜያቸው ሲቀጩ በየቀኑ አታይምን? ስለዚህም አንዱ ሲመክር እንዲህ ብሏል:- *«ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ አትዘግይ፤ ከዛሬ ነገ እመለሳለሁ እያልህ አትቅጠር»* ሲራ. 5፥8:: ዛሬ ነገ እመለሳለሁ ስትል አንድ ቀን ባቋራጭ እንዳትወሰድ::

ስለዚህ ሽማግሌውም ይህን ምክር ልብ ይበል፤ ወጣቱም ይህን ነገር ተረድቶ ተግባራዊ ያድርግ ዘንድ ይሁን:: ወይስ በምቾትና ሁሉ ነገር ተሟልቶልህ የምትኖር፤ እስካሁን ችግር የሚባል ደርሶብህ የማታውቅ ባለጸጋ ነህን? እንዲህም ቢሆን ቅዱስ ጳውሎስ የሚለውን ስማው:- *«ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል::»* 1 ተሰ. 5፥3 :: የዚህ ዓለም ነገሮች ሁሉ ተለዋዋጮች ናቸው:: እኛ በራሳችን የወደፊት ሕይወትና ሁኔታ ላይ ማዘዝ የምንችልና የሰለጠን አይደለንም:: ነገር ግን በጽድቅ ሥራ ላይ የሰለጠንን እንሁን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቸርና ሰውን ወዳጅ ነውና::

ስለ ንስሐ መንገዶች እናገር ዘንድ ትወዳለህን? ሁሉም ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡን የተለያዩና ብዙ የንስሐ መንገዶች አሉ:: የመጀመሪያው የንስሐ መንገድ ኃጢአተኝነትን ማመንና ኃጢአትን ማውገዝና መጥላት ነው:: *«እንድትጸድቅ መጀመሪያ ኃጢአትህን ተናገር»* ይላልና:: ኢሳ. 43፥26:: ነቢዩም *«በደሌን አልሸፈንኩም፤ ለእግዚአብሔር መተላለፌን እነግራለሁ አልሁ፤ አንተም የልቤን ኃጢአት ተውህልኝ»* አለ:: መዝ. 31፥5:: ስለዚህ ራስህን ስለ ኃጢአትህ ውቀስ:: ይህ ጌታህ አንተን ይቅር ይልህ ዘንድ ታላቅ ነገር ነው:: ራሱን ስለ ኃጢአቱ የሚወቅስና ኃጢአቱን የሚኮንን ሰው በቶሎና በቀላሉ ተመልሶ አይያዝባቸውምና:: በጌታ የፍርድ ዙፋን ፊት የሚወቅስህ እንዳይኖር ዛሬ እውነተኛ ወቃሽ የሆነውን ሕሊናህን አንቅተህ በራስህ ላይ ወቃሽና ከሳሽ አድርገው:: ይህ አንዱና ደገኛው የንስሐ መንገድ ነው:: እርሱ ብቻ ግን አይደለም:: ከዚህ ያላነሰ ሌላም መልካም መንገድ አለ፤ እርሱም የወገኖቻችንን በደል ይቅር ማለትና በበደሉህ ላይ ቅሬታና ቂም አለመያዝ ነው:: እንዲህ ካደረግን እኛ በጌታችን ላይ ያደረግነውን በደል ይቅር እንባላለንና:: *«ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፤ የሰማዩ አባታችሁ እናንተንም ደግሞ ይቅር ይላችኋል»* ብሎናልና:: ማቴ. 6፥14::

ሦስተኛ የንስሐ መንገድን ማወቅ ትፈልጋለህን? መንበረ ፀባዖት የሚደርስ በትጋትና በጥልቅ ስሜት የሚደረግ ከልብ የመነጨ ጸሎት

ነው:: ጨካኙ ዳኛ እንዲፈርድላት ያደረገቿው ያቺ መበለት እንዴት እንዲፈርድላት እንዳደረገችው አታያትምን? ሉቃ. 18፥3:: አንተ ግን ርህሩኅና መሐሪ የሆነ ጌታ ነው ያለህ:: እርሷ በጠላቶቿ ላይ እንዲፈርድላት ነው የጠየቀችው፤ አንተ ግን የምትለምነው ስለ ራስህ ድኅነት ነው::

አሁንም ሌላ መንገድ ከፈለግህ አራተኛ መንገድም አለ፤ እርሱም ምጽዋት መስጠት ነው:: ይህም እጅግ በጣም ታላቅ የሆነ ኃጢአትን የማሥተሰረይ ኃይል አለውና:: ናቡከደነፆር ኃጢአትን ንቅስ ጥቅስ አድርጎ በሠራና ወደ ክህደት ዓይነት ሁሉ በገባ ጊዜ እንዲህ ብሏልና:- *«ንጉሥ ሆይ፣ ምክሬ ደስ ያሰኝህ፣ ኃጢአትህንም በጽድቅ፣ በደልህንም ለድሆች በመመጽወት አስቀር::»* ዳን. 4፥27:: እንዲህ ዓይነት ቸርነትና ሰውን መውደድ ምን ወደር ይኖረዋል? ስፍር ቁጥር የሌለው ኃጢአት ከሠራ በኋላ፣ ከዚያ ሁሉ በደል በኋላ እንደ እርሱ ለሆኑ ሰዎች ርህራኄን ቢያደርግ ከተገዳደረውና ከተጣላው አምላክ ጋር መታረቅ እንደሚችል ቃል ተገባለት:: እንዲሁም ትሕትናና ራስን ማዋረድ ኃጢአትን ያደክማል:: ይህንም ቀራጩ ያረጋግጥልናል፤ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ማንሣት እንኳ እስኪፈራ ደርሶ በታላቅ ትሕትና ራሱን ባዋረደ ጊዜ *«ጻድቅ ሆኖ ሄደ»* ተባለለት::ሉቃ. 18፥13::

አምስት ያህል ወደ እግዚአብሔር መመለሻ የሚሆኑ የንስሐ መንገዶችን አይተናል:: እነዚህም አንደኛ ኃጢአትን መውቀስና መጥላት፣ ሁለተኛ የወገኖቻችን ኃጢአትና በደል ይቅር ማለት፣ ሦስተኛ ከጸሎት የሚገኝ ይቅርታ፣ አራተኛ ምጽዋት፣ አምስተኛ ትሕትና ናቸው:: ስለዚህ በእነዚህ በየቀኑ ተመላለስባቸው እንጂ ሰነፍ አትሁን:: ምናልባት ድሀ ብትሆን ቁጣህን መተው፣ ትሑት መሆን፣ እንደሚገባ መጸለይ፣ ኃጢአትን መኰነን ትችላለህ:: ድህነትህ ከጽድቅ ሥራ አይከለክልህም:: ድህነትህ ምጽዋት ከመስጠትም እንኳ ቢሆን አያግድህም:: ሁለት ሳንቲም የሰጠቿው መበለት ጥሩ ማስረጃ ናት:: ማር. 12፥42::

የቁስላችንን መድኃኒቶች በሚገባ ዐውቀን እነዚህን መድኃኒቶች ሁል ጊዜ በቁስላችን ላይ እናድርጋቸው፤ ከደዌአችን ተፈውሰን ወደ ጤንነታችን እንመለስ ዘንድና ከቅዱስ ምሥጢር (ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ) [illegible]ርሱ ቸርነት እንደሚገባ እንቀበል ዘንድ፣ በታላቅ ክብርና በሐሤት ወደ ክብር ባለቤት ዘለዓለማዊ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ እንቀርብ ዘንድ፣ እርሱ በቸርነቱ፣ በጸጋው፣ ሰውን በመውደዱና በርህራኄው የሚያወርሰውን ዘለዓለማዊ ሕይወት እናገኝ ዘንድ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱና ከእርሱ ጋር ክብር፣ ኃይልና ምስጋና ለባሕርይ አባቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ይሁን:: አሜን::





# ክፍለ ትምህርት ሦስት[90]

## ሰው የሰይጣንን ፈተና ለመቋቋም ስለ ተሰጠው ኃይልና ሥልጣን

ክፋት ከስንፍና፣ መልካም ምግባር[91] ደግሞ ከትጋትና ሕሊናን ከማቅናት እንደሚመጡ፣ በሃይማኖት የሚኖርንና አስተዋይ የሆነን ሰው ክፉ ሰዎችም ሆኑ ራሱ ዲያብሎስ ምንም ጉዳት የማያደርሱበት ስለ መሆኑ፣ የዚህ ማስረጃና ማረጋገጫ ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ በተለይም አዳምንና ኢዮብን በተመለከተ ከተጻፉት፤

1. ከትናንትና በፊት ለእናንተ ካለን ፍቅር የተነሣ ዲያብሎስን በተመለከተ የነበረውን ትምህርት ሰፋ አድርገን ተምረናል:: ይህ ትምህርት ሲሰጥ በነበረበት በዛው ቀን ሌሎቹ አልነበሩም፤ በቴአትር ቤት ተቀምጠው የዲያብሎስን ትርዒት ሲመለከቱ ነበር:: እናንተ ከቅዳሴውና ከመንፈሳዊው ዝማሬ ስታፈ ስታደርጉ እነርሱ ግን በዘፈንና በጭፈራ መሀል ተገኝተው የድርሻቸውን እየወሰዱ ነበር:: እናንተ የአባታችሁን ማዕድ ስትመገቡ እነርሱ ደግሞ የዲያብሎስን ፍርፋሪ ሲለቃቅሙ ነበር:: ማን አታሎ ወደዚያ ወሰዳቸው? ከተቀደሰው የክርስቶስ መንጋ ማን ለያቸው? ዲያብሎስ አታለላቸውን? እናንተን ለምን አላተለላችሁም? ተፈጥሯችሁን በተመለከተ እናንተም እነርሱም ሁላችሁም ያው ሰዎች ናችሁ:: እናንተም እነርሱም አንድ ዓይነት ነፍስ ነው ያላችሁ፣ ተፈጥሮን በተመለከተ መሠረታዊ ፍላጎታችሁ አንድ ዓይነት ነው:: ታዲያ ለምን እናንተና እነርሱ በአንድ ዓይነት ቦታ አልነበራችሁም? የዚህ ምክንያት እናንተና እነርሱ አንድ ዓይነት ዓላማ ስለሌላችሁ ነው::

ስለዚህም ምክንያት እነርሱ ሲታለሉ እናንተ ግን አልተታለላችሁም:: አሁንም እንዲህ የምለው ዲያብሎስን ከተጠያቂነት ነጻ ለማውጣት አይደለም፣ እናንተን ከኃጢአት ነጻ ለማውጣት በጣም ከመፈለግ እንጂ:: ዲያብሎስ ክፉ ነው፣ ይህ የታወቀና ደጋግመን ያልነው ነገር ነው፤ ነገር ግን ከተጠነቀቅን ክፋቱ ለራሱ እንጂ ለእኛ አይደለም:: የክፋት ጠባይ እንዲህ ነውና፣ ጎጂነቱ ለእነዚያው ሥራዬ ብለው ለያዙቱ ብቻ ነው:: መልካም ምግባር ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው:: ጠቃሚነቱ ገንዘብ ላደረጉት ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ለተጠጉትም ይተርፋል:: ክፉ ክፋቱ ለራሱ ሲሆን መልካም ነገር ግን ለሌሎችም መልካም እንደሚሆን ትረዳ

[90] (Homily III)
[91] (Virtue)

ዘንድ በምሳሌ ከተነገረው ማስረጃ እሰጥሃለሁ፣ *«ክፉ ብትሆን ክፉትህን ለራስህ ትሸከማለህ፤ አዋቂ ብትሆን ግን ለራስህም ለባልንጀራህም አዋቂ ትሆናለህ።»* ምሳ. 9፥12።

እነርሱ ወደ ቴአትር ቤትና ወደ ልዩ ልዩ አልባሌ ቦታዎች በመሄድ ሲታለሉ እናንተ ግን አልተታለላችሁም። ይህ በሁሉም ነገር ወሳኙ ዓላማ ስለ መሆኑ ግልፅ ማስረጃና ዋና ማረጋገጫ ነው። እናንተም እንዲሁ ይህን የማረጋገጫ መንገድ ተጠቀሙ። በክፋት የሚኖርና ኃጢአትን ሁሉ የሚሠራ፤ እንዲህም እየኖረ ደግሞ በዚያ ላይ የእግዚአብሔርን አጠራቅሞ የሚያማርር፣ በአርባ ቀን ዕድሉ ምክንያት ዕጣው እንደ መለከአታዊ ጥበቃ የሆነበት፣ እንዲሁም በአጋንንት ጭካኔና ኃይል ምክንያት ይህ እንደ ደረሰበት አድርጎ በማቅረብ በሁሉም አቅጣጫ ተጠያቂነቱን ከራሱ ለማራቅ የሚጣጣርንና ለሁሉም ቸርነቱን ወደሚያደርገው ቸር ፈጣሪ ኃጢአቱን የሚያላክክ ሰው ብታዩ አንደበቱን በቃል ሳይሆን በተግባር ዝም አሰኙት።

ለዚህም በመልካም ሕይወትና በትዕግሥት የሚኖር ሌላ ወንድም አሳዩት። ብዙ ንግግር ማድረግ፤ የረቀቀ የንግግር ችሎታና ስልት ወይም የአመክንዮ ድርደራ አያስፈልግም። በተግባራዊ ሕይወት ጉዳዩ ይረጋገጣል። አንተም ፍጡርና አገልጋይ ነህ፣ እርሱም እንደ አንተ እንዲሁ ፍጡርና አገልጋይ ነው፤ አንተም ሰው ነህ፣ እርሱም ሰው ነው፤ ሁላችሁም የምትኖሩት በአንድ ዓለም ውስጥ ነው፤ ሁላችሁም ካአንድ ሰማይ በታች ባለ አንድ ዓይነት የእግዚአብሔር ምግብና የምትመገቡ ናችሁ። ታዲያ አንተ በኃጢአት ስትኖር እርሱ እንዴት በመልካም ሕይወት መኖር ቻለ? በሉት።

ስለዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ኃጥአንን ከደጋጎች ጋር ተቀላቅለው በአንድ ላይ እንዲኖሩ አደረገ። ለክፉዎች የተለየ ዓለምና ሌላ ሕግ አልሰጠም፤ ደጋጎችንም ለይቶ ለብቻቸው በሌላ ዓለም እንዲኖሩ አላደረገም፤ ሁለቱም ይጠቀሙ ዘንድ ተቀላቅለው በአንድ ላይ እንዲኖሩ አደረገ እንጂ። ደጋጎቹ ደግነታቸውና ጽድቃቸው የበለጠ የሚታወቀውና የሚረጋገጠው በቅድስና እንዳይኖሩ ወደ ኋላ በሚጎትቷቸውና ወደ ኃጢአት በሚገፋፏቸው መካከል ኖረው እነርሱ ግን ፈተናውን ተቋቁመው መልካም ነገርን ይዘው ሲገኙ ነውና። *«ከእናንተ መካከል የተፈተኑት እንዲገለጡ በእናንተ ዘንድ ኑፋቄ ሊኖር ግድ ነውና።»* 1 ቆሮ. 11፥19።

ስለዚህም ከዚህ ምክንያት የተነሣ ደጋጎች የበለጠ ያበሩና ደምቀው ይታዩ ዘንድ ክፉዎቹን በዚህ ዓለም እንዲኖሩ ትቷቸዋል። ጥቅሙ ምን ያህል እንደ ሆነ አየህን? ነገር ግን ጥቅሙ ስለ ክፉዎቹ ሳይሆን ከደጋጎቹ ጥንካሬና ጽናት የተነሣ ነው። ከዚህም የተነሣ ኖኅን የምናደንቀው ጻድቅ ስለ ነበረ ብቻ ወይም ፍጹም ስለ ነበረ ብቻ አይደለም፣ በዚያ ክፉና





የተበላሸ ትውልድ መሀል እየኖረ የጽድቅ ሕይወቱን አልለወጠም፣ በዘመኑ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ወደ ኃጢአት የሚነጉዱና የሚሽቀዳደሙ የነበሩ ሲሆን እርሱ ግን ልክ ብዙዎች ወዲህና ወዲያ ሲዋዥቁ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ሳይል መንገዱን ብቻ ይዞ ቀጥ ብሎ እንደሚሄድ መንገደኛ በጽድቅ ጎዳና ብቻ ተጓዘ። ስለዚህም ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ *«ኖኅ ጻድቅ፣ ፍጹም ነበረ»* ብቻ አላለም፤ *«በትውልዱ»* የሚል ጨመረ እንጂ። ዘፍ. 6፥9። በዚያ የተበላሸና ክፉ ትውልድ መካከል ጻድቅ ሆኖ ተገኘ። ደጋጎቹ ከክፉዎቹ ጋር በመኖራቸው ያገኙት ጥቅም ይህ ነው፤ ማለትም ከክፉዎች መሀል ጻድቃን ሆነው በመገኘት በሌሊት በሰማይ እንደሚያበሩ ከዋክብት ሆኑ። ዛፍ እንኳ በነፋስ ወዲህና ወዲያ ሲወዛወዝ ይጠነክራል።

ክፉዎቹም ከደጋጎቹ ጋር ተቀላቅለው በመኖራቸው ይጠቀማሉ። ደጋጎችን ሲያዩ በኃጢአታቸው ያፍራሉ፣ ይሳቀቃሉ፣ የመዋረድ ስሜት ይሰማቸዋል፤ ከኃጢአት ባይታቀቡም እንኳ በስውር የሚያደርጉትን በአደባባይ ለማድረግ አይደፍሩም። ኃጢአትና ነውረኛ ነገር በአደባባይ በግልጥ አለመደረጉም ቀላል ነገር አይደለም። የሌሎቹ መልካም ሕይወት የእነዚህን ክፋት ወቃሽ ምስክርና ዳኛ ይሆንባቸዋልና። በደጋግ ሰዎች መኖር ምክንያት በኃጢአት መሳቀቅና ራስን መውቀስ ቀላል የማይባል ራስን የመለወጥ የመጀመሪያ ደረጃ ነው። በእነርሱ መኖር በሕሊና መሳቀቅ በኃጢአት ከመደሰትና ከመኩራራት፣ ኃጢአታዊ ምኞትን ሁሉ በዘፈቀደ ከመከተል እንደ ልጓም ያዝ ያደርጋል። በአንድ ላይ ተቀላቅለው በመኖራቸው ደጋጎቹ ከክፉዎቹ የሚያገኙት፣ ክፉዎቹም ከደጋጎቹ የሚያገኙት ጥቅም ታላቅ እንደ ሆነ አስተዋልህን? ስለዚህ ምክንያት እግዚአብሔር በዚህ ዓለም አንዱን ከሌላው አልለያቸውም፤ በአንድ ላይ ተቀላቅለው እንዲኖሩ አደረገ እንጂ።

2. ዲያብሎስን በተመለከተ ያለን አስተሳሰብም እንዲሁ ይሁን። ስለዚህ ምክንያት በዚህ ዓለም ትቶታልና፣ አንተን የበለጠ ጠንካራ ያደርግህ ዘንድ፣ አትሌቱን ታዋቂና ዝነኛ ያደርገው ዘንድ፣ ውድድሩ ታላቅ ይሆን ዘንድ። ስለዚህ ማንም እግዚአብሔር ዲያብሎስን ለምን በዚህ ዓለም ተወው? ቢል እንዲህ በለው፡- ዲያብሎስ አስተዋዩንና ጠንቃቃውን ሰው አይጎዳውም ብቻ ሳይሆን ካለመጉዳት አልፎ ምንም እርሱ ክፉ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም እነርሱ ግን በጥበብ መንፈሳዊና በረድኤተ እግዚአብሔር የክፋቱን መርዝ በማክሸፍ መሰናክሉን በማለፍ የበለጠ ይጠቀሙበታል።

በኢዮብ ላይም ሰይጣን ያን ሁሉ ፈተና ያመጣበት ኢዮብ እንዲከብር ፈልጎ ሳይሆን እርሱን ለመጣልና ለማዋረድ ነበር። ስለዚህ እርሱ በዓላማውም በፍላጎቱም ሁሉ ክፋትን የሚመኝ ክፉ ነው። ሆኖም ግን ያን ጻድቅ ሰው

(ኢዮብን) አልጎዳውም። ዲያብሎስም ክፋቱን ገለጠ፣ ኢዮብም ጽናቱንና ትዕግሥቱን ገለጠ። እንዲያ ባይፈተን ኖሮ የኢዮብን ታላቅነት ከፈጣሪው በቀር ማን ማወቅ ይችል ነበር? ነገር ግን በራሱ ኃይልና ሥልጣን ባይሆንም ብዙዎችን ያሸንፋል የሚል ይኖራል። ይህም ራሱ በብዙ ምሳሌዎች ተረጋግጧል። ሕሊናህንና ዓላማህን ቀጥተኛ አድርገህ ረድኤተ እግዚአብሔርን ኃይልህ አድርገህ ተነሥ፣ ከማንም ጉዳት አይደርስብህም፣ መልካም ከሆነው ነገር ብቻ ሳይሆን ከክፋውም ታላቅ ጥቅም ታገኝበታለህ።

ስለዚህም ምክንያት አስቀድሜ እንዳልሁ እግዚአብሔር አንዱ ከሌላው ጋር እንዲኖር ፈቅዷልና፣ በተለይም ክፋዎች ከደጋጎች ጋር። ይህም ደጋጎች ክፋዎችን ወደ እነርሱ መልካም ሕይወት ይመልሷቸውና ያመጧቸው ዘንድ ነው። ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያላቸውን አድምጥ፦ *«መንግሥተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች።»* ማቴ. 13፥33። ይህም ማለት ጻድቃን ክፋዎችን ወደ እነርሱ ዓይነት ሕይወት ይመልሷቸው ዘንድ የእርሾ ኃይል አላቸው ማለት ነው። ነገር ግን እርሾው ትንሽ እንደ ሆነ ጻድቃንም ጥቂቶች ናቸው። ሆኖም የመጠን ወይም የቁጥር ትንሽነት ሥራን ከመሥራት ዕንቅፋት አይሆንም። እርሾ ትንሽ ቢሆንም ከእርሾነቱ ጠባይ የተነሣ ብዙውን ዱቄት እንዲቦካ በማድረግ ወደርሱ ጠባይ ይለውጠዋል።

እንዲሁም የጻድቃን ኃይል ከቁጥራቸው ብዛት ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነሣ ነው። ሐዋርያት አሥራ ሁለት ነበሩ። እርሾው ምን ያህል ጥቂት እንደ ሆነ አየህን? ዓለሙ በሙሉ በአለማመን ጥላ ሥር ነበር። ዱቄቱ ደግሞ ምን ያህል ብዙ እንደ ሆነ ተመልከት? ነገር ግን እነዚያ አሥራ ሁለቱ ዓለሙን ሁሉ ወደ ራሳቸው መለሱት። እርሾውና ዱቄቱ አንድ ዓይነት ተፈጥሮ አላቸው፣ ግብራቸው ግን የተለያየ ነው። ስለዚህም ምክንያት ክፋዎችን በደጋጎች መሀል ተዋቸው፣ በተፈጥሮአቸው ከጻድቃን ጋር አንድ እንደ ሆኑ ሁሉ ዓላማቸውና ሕይወታቸውም አንድ ይሆን ዘንድ።

እነዚህን ነገሮች አስታውስ። በእነዚህም የሰነፎችን፣ የጽሩዓንን፣ የመልካም ሕይወት ምግባርን ገንዘብ ለማድረግ ሕሊናቸውን ሳጸንኑና ፈጣሪያቸውን የሚከሱትን አፋቸውን እንዲዘጉ አድርጋቸው። በድለሃል፣ ነገር ግን «ኃለተኛ ታላቅ በደል አትጨምር» ሢራ. 21፥1። ኃጢአት ከሠሩ በኋላ በፈጣሪው ማመካኘትና እርሱን መውቀስ ኃጢአት ከመሥራቱ የባሰ በደል ነው። የኃጢአትን ምንጭ በሚገባ ካስተዋልህ ከበደልከው ካንተው ከራስህ ሌላ ማንም ተጠያቂ እንዳልሆነ ትረዳለህ። በሁሉም ቦታ ቅን ሕሊና አስፈላጊ ነው። ይህን ከቀላል አመክንዮ ብቻ ሳይሆን እንደ እኛ ካሉ በዚህ ዓለም ከሚኖሩ አገልጋዮችም አሳይቼሃለሁ። አንተስ ይህንን ማረጋገጫ ትጠቀማለህን? የሁላችንም ጌታ የሚፈርድብን እንዲህ ነውና። ይህን





የማስረጃ ዘዴ ልብ አድርግና ከዚያ ማንም ከአንተ ጋር መከራከር አይችልም። አመንዝራ የሆነ አለ? ራሱን የገዛ ሌላ ሰው አሳየው። ስስታምና ቀማኛ የሆነ አለ? ምጽዋት የሚሰጥና ከፍቅረ ንዋይ ነጻ የሆነ ሌላ ሰው አሳየው። በቅንዓትና በምቀኝነት የተቃጠለ ይኖራል? ከዚህ ሁከት ነጻ የሆነውን አሳየው። በቁጣ ድል ይሆናል? በትዕግሥትና በጥበብ የሚኖረውን አሳየው።

የቀደሙትን ብቻ ሳይሆን በዘመናችን ያሉትንም አብነት ማድረግ ይገባናልና። ዛሬም ቢሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ከቀድሞው ያላነሱ ደጋግ ሥራዎች ይሠራሉና። የማያምንና ተጠራጣሪ ሰው አለ? ቅዱሳት መጻሕፍት ውሸት ናቸው ብሎ ያስባል? ኢዮብ እንደሚባለው የነበረ መሆኑን አያምንም? የኢዮብን ሕይወት አርአያ ያደረገ በእርሱ ዘመን የሚኖር ሌላ ሰው ከዘመኑ አሳዩት። ጌታችንም የሚፈርድብን እንዲህ ነውና። አገልጋዮችን ከአገልጋዮች ጋር በአንድነት አኑሯቸዋልና። አንድ መክሊት የተሰጠው፣ ነገር ግን በተሰጠው መክሊት ሌላ መክሊት አትርፎ በማምጣት ፋንታ «አንተ ጨካኝ ሰው ነህ» በማለት ክስና ወቀሳ ይዞ እንደ መጣው እንደዚያ ክፉ ባሪያ የሚናገር እንዳይኖር ፍርድንም እንደ አምላክነቱ እንደሚገባው ከራሱ ብይን አይሰጥም። ማቴ. 25፥24። ያ ክፉ ባሪያ ምን አለ? «አንተ ክፉ መሆንህን አውቃለሁ» አለ። አንተ ክፉና ኀስቋላ፣ ውሉታ ቢስና ሰነፍ ሰው! የራስህን ስንፍና ልትወቅስ ይገባህ ነበር፣ በዚህም ከኃጢአትህ ትንሽ እንኳ ሊቀልልህ ይችል ነበር። አንተ ግን ስንፍናህን በጌታህ ላይ በማሳበብ መክሊትህን እጥፍ በማድረግ ፋንታ ኃጢአትህን እጥፍ አደረግህ።

3. ስለዚህ ምክንያት እግዚአብሔር አንዱ በአንዱ ይፈርድበት ዘንድ፣ እንደ እነርሱ ባሉ በሌሎች የተፈረደባቸውም ወደ ፊት ጌታቸውን ማማረርና መውቀስ እንዳይችሉ አገልጋዮችንና አገልጋዮችን በአንድ ላይ አስቀመጣቸው። ስለዚህም *«የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ይመጣል»* አለ። ማቴ. 16፥27። ከአባቱ ጋር በክብር አንድ መሆኑን ተመልከት። የአባቱን ክብር በሚመስል ክብር አላለም፣ «በአባቱ ክብር» አለ እንጂ። እንዲሁም በየቦታውና በየዘመኑ የኖረውን የሰው ልጅ ሁሉ ይሰበስባል። ይህ ችሎት በጣም አስፈሪ ነው፤ ለኃጥአን በጣም አስጨናቂ ነው። በእርሱ ቸርነት ታምነው በመልካም ሕይወት ለኖሩ ደግሞ የሚፈለግና አስደሳች ነው። በዚህ የፍርድ ቀንም «በጎቹን በቀኙ፣ ፍየሎቹንም በግራው ያቆማቸዋል።» ማቴ. 25፥33። እነዚህም እነዚያም ሁለቱም ሰዎች ናቸው። በምን ምክንያት እነዚያ በጎች፣ እነዚህ ደግሞ ፍየሎች ሆኑ? በተፈጥሮ የተለያዩ ሆነው ሳይሆን በአኗኗራቸውና በግብራቸው ልዩነት የመጣ መሆኑን ታውቅ ዘንድ ነው።

በጎች ለተባሉት ምን ይላቸዋል? *«ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛ*

*ልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና»* ይላቸዋል። ለእነዚያ ግን የዚህን ተቃራኒ ይላቸዋል። ነገር ግን እነዚህም እነዚያም ሁለቱም ከአንድ አባት የተገኙ፣ አንድ ዓይነት ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ነበሩ። እነዚህም እነዚያም የተሰጣቸው ተስፋና ቃል ኪዳን አንድ ዓይነት ነበር፤ ለሁለቱም መልካም ቢያደርጉ ይሰጣቸው ዘንድ የተዘጋጀላቸው ዋጋ አንድ ነበር። ወደ እነዚህም፣ ወደ እነዚያም የሄዱት ርኁባን፣ ዕሩቃን፣ ጽሙዓን፣ እንግዶች አንድ ዓይነት ሰዎች ነበሩ። ለእነዚያም ለእነዚህም የተሰጣቸውና የነበረው ሁሉም ነገር አንድ ነበር።

እንዲህ ከሆነ ፍጻሜያቸው ለምን አንድ ዓይነት ሳይሆን ቀረ? ምክንያቱም ዓላማቸው ይህን አልፈቀደም።

የልዩነቱ መሠረታዊ ምክንያት ይህ ብቻ ነው። ስለዚህም ምክንያት አንዱ ወገን ወደ ገሃነም ሲሄድ ሌላው ግን ወደ መንግሥተ ሰማያት ሄደ። የኃጢአታቸው ምክንያት ዲያብሎስ ቢሆን ኖሮ ግን የበደለውና ወደ ኃጢአት የጣላቸው ሌላ (ዲያብሎስ) ሆኖ ሳለ እነርሱ አይቀጡም ነበር። መልካም ያደረጉትንና የበደሉትን ሁለቱንም ታያቸዋለህ? ኃጥኣን እንደ እነርሱ ያሉትን ሰዎች በማየታቸው አፋቸው እንደ ተዘጋ አየህ? እንደ እነርሱ የነበሩ ሰዎች መልካም ሠርተው ሲመሰገኑና ወደ ሕይወት ሲወሰዱ እነዚያ ይህን ክብር ላለማግኘታቸው ከራሳቸው ስንፍናና ግዴለሽነት ውጭ ምን ምክንያት አላቸው? «ሰዎች ሆነን አንተን ማብላት፣ ማልበስ፣ መጠየቅ፣ ... እንዴት ይቻለናል? አንተ ከሰው የምትፈልገው ከዓቅሙ በላይ ነው» የሚል ምክንያት እንዳያቀርቡ በጎች የተባሉት፣ «ተርቤ አብልታችሁኛል፣ ታርዤ አልብሳችሁኛል፣ ...» ተብለው በመልካም ሥራቸው የተመሰገኑትም እንደ እነርሱ ሰዎች የሆኑ፣ በአንድ ዓለም ውስጥ የኖሩ፣ አንድ ዓይነት ሕግና ተስፋ የተሰጣቸው መሆናቸውን ሲያዩ ምንም ማመካኘት አልቻሉም። ስለዚህ ዝም አሉ።

ሌላ ምሳሌ እንጨምርና እንመልከት። አሥር ደናግል ነበሩ ይላል። ማቴ. 25። እዚህም ላይ ርቱዕ የሆኑ ዓላማ ያላቸው አሉ፣ ዓላማቸው ያልቀናም አሉ። የአንደኛውን ወገን ኃጢአት (የሰነፎቹን ደናግል)፣ የሌላውን ወገን (የልባሞቹን ደናግል) መልካም ሥራ ታይ ዘንድ ንጽጽሩ የበለጠ ግልፅ ያደርገዋልና። እነዚህም እነዚያም ደናግል ነበሩ። ሰነፎቹም አምስት ናቸው፣ ልባሞቹም እንዲሁ። ሁሉም ሙሽራውን ይጠብቃሉ። አንዳንዶቹ ከሙሽራው ጋር አብረው ወደ ሰርጉ ቤት ሲገቡ ሌሎቹ እንዴት ሳይገቡ ቀሩ? ምክንያቱም ያልገቡት ሰነፎች ስለ ነበሩ ሲሆን፣ የገቡት ደግሞ ፍቅር ያላቸው ትጉሃን ስለ ነበሩ ነው። ዲያብሎስ ሳይሆን ዓላማቸውና ሕይወታቸው የሰዎቹን ፍጻሜ እንደ ወሰነ አስተዋልህ?





ፍርዱ ትይዩ እንደ ሆነና ብይኑም አንድ ዓይነት ከሆኑ እርስ በርሳቸው እንደ ተሰጠ አየህ? ኅደኛ ኅደኛውን ይፈርድበታል። ሰነፎቹ ደናግል ከሙሽራው ጋር ወደ ውስጥ ላለመግባታቸው ከራሳቸው ውጭ የሚወቅሱት ሌላ ማንም የለም። እነዚያን አብረውት እንዲገቡ የተቀበለ ክርስቶስ እነርሱንም ይቀበላቸው ነበር። ነገር ግን ዝግጅታውን ጨርሰው በመጠበቅ ሙሽራው ክርስቶስ ሲመጣ አብሮ እንደ መግባት ገና የመብራት ዘይት ሲገዙ ወደ ውጭ ወጡ። በዚህም አለመዘጋጀታቸው ተገለጠ። ስለሆነም በራሳቸው ስንፍና በውጭ ቀሩ። ስለዚህ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤ የበደላቸው ምንም ነገር የለም።

ፍርዱ የከበደ እንዲሆን ሌላ ምሳሌ እንይ? *«የነነዌ ሰዎች ተነሥተው በፍርድ ቀን ይህን ትውልድ ይፈርዱበታል።»* ይላልና። ማቴ. 12፥41። በፍርድ አንጻር ያሉት የተለያዩ ናቸው፤ አንደኛው ወገን አረማውያን ሲሆኑ ሌላኛው ደግሞ አይሁድ ናቸውና። እነዚህ (አይሁድ) የነቢያትን ትምህርት ሲያገኙ የኖሩ ሲሆኑ እነዚያ (የነነዌ ሰዎች) ግን የመለኮታዊ ቃልና ትእዛዝ ሱታፌ ደርሷቸው አያውቅም። ልዩነቱ ይህ ብቻ አይደለም፤ ወደ ነነዌ የተላከው አገልጋይ (ዮናስ) ሲሆን ወደ አይሁድ ግን የፍጥረታት ጌታ ራሱ ሄደ። ዮናስ ሄዶ «ነነዌ በሦስት ቀን ወስጥ ትጠፋለች» የሚል አስፈሪ የጥፋትን ነገር ሰበከ፤ ጌታችን ግን የመንግሥተ ሰማይን መልካም ዜና የምሥራች (ወንጌል) ሰበከ።

ከእነዚህ ከሁለቱ ከተደረገላቸው ነገር አንጻር የትኛው የበለጠ ሊያምን ይገባ ነበር? የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የማያውቁት አረመኔ የነበሩት አሕዛብ ወይስ ከመጀመሪያው ጀምሮ በእግዚአብሔር ሕግ ሲኮተኮቱ ያደጉት አይሁድ? በበለጠ ሁኔታ የማመን ዕድል ያላቸውና ማመን የሚጠበቅባቸውም አይሁድ መሆናቸው ለማንም ግልጥ ነው። ነገር ግን ተቃራኒው ሆነ። እነዚህ ራሱ ባለቤቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥተ ሰማያትን ሲሰብክላቸው ሳያምኑትና ሳይቀበሉት ቀሩ፤ እነዚያ (የነነዌ ሰዎች) ግን እንደ እነርሱ ፍጡር ከሆነው ከአገልጋዩ (ከዮናስ) እንደበት ጥፋትንና ድምሳሴን በሰሙ ጊዜ ትምህርቱን ተቀበሉት። ይህም የነነዌ ሰዎች ደግነታቸው፣ የአይሁድ ደግሞ ቂልነታቸውና ክፋታቸው የበለጠ ይገለጥ ዘንድ ነው።

ታዲያ በዚህ ላይ ዲያብሎስ የሁለቱንም ሁኔታ በመወሰን ላይ የታለ? ዕጣ ፋንታ ወይም የአርባ ቀን ዕድል የሚባል ነገርስ የታለ? ለክፋቱም ሆነ ለመልካም የቅድስና ሕይወቱ እያንዳንዱ ለራሱ ምክንያትና ተጠያቂ አይደለምን? እያንዳንዳቸው ለራሳቸው ድርጊት ተጠያቂ ባይሆኑ ኖሮ በዚህ ትውልድ ላይ ይፈርዱባቸዋል ባሏለ ነበር። ንግሥተ አዜብም በአይሁድ ላይ ትፈርድባቸዋለች ባላለ ነበር። ወደ ስህተት ለመሄድ የበለጠ ተጋላጭ

ድጋፍና ርዳታ የነበራቸው በተቃራኒው ከፍተውና ተበሳሽተው ሲገኙ አንድ ሕዝብ በሌላው ሕዝብ ላይ (የነነዌ ሕዝብ በሕዝበ አይሁድ ላይ) የሚፈርድ ብቻ ሳይሆን አንድ ግለሰብም ብቻውን በሌላው ሕዝብ ላይ ይፈርዳል:: እንዲቷ ንግሥተ አዜብ በአይሁድ ሕዝብ ላይ ትፈርድባቸዋለች ያለው ለዚህ ነው:: ማቴ. 12፥42:: እርሷ እንደ እርሷ ፍጡር የሆነውን የሰሎሞን ጥበብ ስትሰማ እርሱን ለማየት አገር አቋርጣ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛለች:: አይሁድ ግን ለሰሎሞን ጥበብን የሰጠው የሰሎሞ ፈጣሪ ኢየሱስ ክርስቶስ አገር አቋርጦ መሄድ ሳያስፈልጋቸው እነርሱ ካሉበት ከቦታቸው ተገኝቶ ቢያስተምራቸው ነገሩን አልተቀበሉትም:: ስለዚህ በአይሁድ ላይ ለመፍረድ ንግሥተ አዜብ ትበቃቸዋለች::

ስለዚህም ምክንያት አዳምንና ኢዮብን አንሥተን ነበር:: የጀመርነውን ይህን ትምህርታችንን ለመፈጸም ወደዚያ መመለስ ያስፈልገናልና:: ሰይጣን አዳምን የፈተነው በቃላት ብቻ ነው፤ ኢዮብን ግን በተግባር ነው:: ኢዮብን የነበረውን ነገር ሁሉ አንዳች ሳያስቀር አጠፋበት፣ ልጅ አልባ አደረገው:: ከአዳም ግን ካለው ነገር ቅንጣት ታክል እንኳ አልወሰደበትም:: ሰይጣን አዳምን የተናገረውንና እርሱን ለማሳት የተጠቀመበትን ዘዴ እስኪ በደንብ እንመርምረው:: እባብ ወደ ሔዋን ቀረበና *«በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዟልን?»* አላት:: ዘፍ. 3፥1::

ልብ አድርግ፣ እዚህ የሚናገረው እባብ ነው፣ ኢዮብን ግን የተናገረው በሚስቱ አድሮ ነው:: የመሣሪያዎቹን የጎላ ልዩነት ተመልከት:: ኢዮብን የሕይወቱ ረዳት በሆነች በሚስቱ ሲፈትነው አዳምን የፈተነው ግን ለሰው ተገዢ ሆነው ከፈተጠሩት ሥነ ፍጥረታት አንዱ በሆነው በእባብ ነው:: ሰው የሥነ ፍጥረት ገዢ ነውና:: ነገር ግን ተገዢው የሆነው እባብ ገዢውን አዳምን አታለለው፤ ኢዮብን ግን የሕይወቱ አጋርም ልታናውጸው አልቻለችም::

እባብ የተናገረውን እንመልከት፡- «በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዟልን?» አለ:: እግዚአብሔር ያለው ይህን ሳይሆን የዚህን ተቃራኒ ነው:: የሰይጣንን ተንኰል ተመልከት፣ የተባለውን ያውቅ ዘንድ ያልተባለውን ተናገረ:: ከዚያስ ሔዋን ምን አደረገች? ከእርሱ ጋር ምንም ቃል መለዋወጥና መነጋገር አይገባትም ነበር፣ ቢያንስ ዝም ልትለው ይገባ ነበር:: ነገር ግን በሞኝነት የጌታዋን ምሥጢር አወጣች፣ በዚህም ለሰይጣን ጥሩ የሆነ መግቢያ ከፈተችለት፣ ራሷን የምታስደበድብበትን በትር ከነመያዣው እጇታ አቀበለችው::

4. በራሳችን ላይ ለሚያሤሩና ወጥመድ ለሚያዘጋጁ ለጠላቶቻችን ራስን በችኮላ አሳልፎ መስጠትና ቀዳዳ መክፈት እንዴት አደገኛ እንደ ሆነ



*ተመልሰውም እንዳይነክሷችሁ»* አለ:: ማቴ. 7፥6:: ይህ በሔዋን ደረሰባት:: የተቀደሰውን የእግዚአብሔር ምሥጢር ለውሻ ሰጠች፣ በእሪያ ፊት አስቀመጠች:: እርሱም የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል በእግሩ ረገጠው፣ ተመልሶም እርሷን ነከሳት:: እንዴት ተንኰለኛና ክፉ እንደ ሆነ ተመልከት፣ እንዲህ አለ፡- «ሞትን አትሞቱም» ዘፍ. 3፥4::

ሔዋን ይህን ተንኰሉን በሚገባ ማወቅ ትችል እንደ ነበረ ለማየት በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረትህን ስጠኝ:: ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ተቃውሞ በቀጥታ በመግለጽ በእርሱ ላይ ያለውን ጠላትነትና ተቃዋሚነት አሳይቷል:: እሺ ያለፈው መናገሯ ይሁን፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተናገረችው ማወቅ ስለ ፈለገና ስለ ጠየቀ ነው እንበል:: ከዚህ በኋላ የዚያን ተቃራኒውን የተናገረውን ለምን ተከተለችው? እግዚአብሔር ያለው «ከእርሱ በበላችሁ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ» ነው:: ዲያብሎስ ለዚህ ሲመልስ እንዲህ አለ፡- «ሞትን አትሞቱም» ከዚህ የበለጠ ጠላትነት ምን አለ? በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንዲህ በተቃራኒው ሲመልስ ከማየት የበለጠ የጠላትነት መለያ መታወቂያ ምን አለ? በዚህ ጊዜ ከዚህ የተንኰል ወጥመድ ቶሎ ብላ ልታመልጥ ይገባት ነበር:: *«ሞትን አትሞቱም፤ ከእርሷ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ፣ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንደምትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ::»* አላት::

አምላክ የመሆንን ባዶ ተስፋ ሲነግራት ይህንን አገኛለሁ ብላ በእጇ ያለውን የተሰጣትን ጣለች:: አምላክ የሚሆኑበትን ጥበብ የነገራቸው አስመስሎ እንዲሞቱ አደረጋቸው:: ሕይወታቸውን በሞት እንዲያጡና በሞት ቀንበር ሥር እንዲወድቁ አደረጋቸው:: ሔዋን ሆይ፣ ዲያብሎስን እንዴት አመንሽው? ምን መልካም ነገር አየሽበት? ሕጉን የሰጠው የእግዚአብሔር እውነተኛነትና ተአማኒነት እርሱ የዓለማት ፈጣሪና አስገኚ መሆኑን፣ ያ ግን ጠላት፣ ዲያብሎስ መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ አልነበረምን? እንዲያውም እንዴት ዲያብሎስ እላለሁ፣ እባብ እንደ ሆነ ነው ያየሺው:: እባብ እንዲህ የእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ እስኪነገረው ሊደርስ ይገባ ነበርን? የነገሩን ውስጠ ተንኰልነት ማወቅና መረዳት ይቻል ነበር፤ እርሷ ግን ማወቅ አልቻለችም::

እንዲህ ሲሆንም እግዚአብሔር ግን ለፍጥረቱ ያለውን እንክብካቤ በብዙ ነገር ገልጧል፣ ቸርነቱንም በብዙ ማስረጃ አሳይቷል:: ሰውን እም ኀበ አልቦ (ካለ መኖር) ኀበ ቦ (ወደ መኖር) አምጥቶ ፈጠረው፣ የሕይወት

እስትንፋስ እፍ አለበት፣ በራሱ አርአያና አምሳል ፈጠረው፣ በመሬት ላይ ባለው ነገር ሁሉ ላይ ገዢ አደረገው፣ ረዳት ሰጠው፣ ገነትን አዘጋጀለት፣ ከአንዲት ዛፍ ሲከለክለው በቀር፣ የውም ለራሱ ለሰው ጥቅም ሲል፣ ሌላውን ዛፍ ሁሉ እንዲጠቀምበት ሰጠው። ዲያብሎስ ግን በሥራው ምንም ጥሩ ነገር፣ አንዲት እንኳ፣ አላሳየም። ነገር ግን የሚያስጎመዥ ነገር በቃል ብቻ በመናገር በባዶ ተስፋ ልቧን አንሳፎ ፈታለላት። እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን መልካም አሳብና ዕቅድ በሥራው የገለጠ ቢሆንም እርሷ ግን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰይጣን የበለጠ ተአማኒ እንደ ሆነ አድርጋ አሰበች። ባዶ ቃል ብቻ እንጂ ምንም ተጨባጭ ነገር ያልሰጣትን አመነች።

ይህ መታለል ከኃይል ሳይሆን ከስንፍናና ከሞኝነት ብቻ እንደ መጣ አየህ? ይህንንም የበለጠ ለመረዳት ቅዱስ መጽሐፍ እርሷን እንዴት እንደሚወቅሳት ስማ፣ ተታልላ አይልምና፣ «ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ አይታ በላች» ይላል እንጂ። ዘፍ. 3፥6። ስለዚህ ተጠያቂነቱና ስህተቱ የእርሷ ያልተገራና ልቅ የሆነ ዕይታና ምኞት እንጂ ከሳይጣን የመጣው ማታለል ብቻ አይደለም። ድል የተነሣችው ሰይጣን በተንኮል በመናገሩ ሳይሆን ለምኞቷ በመሸነፏ ነው። ስለዚህም ምክንያት ምንም እንኳ «እባብ አሳተኝና በላሁ» ብትልም ከቅጣት አላመለጠችም፣ ጥፋቱ የራሷ ስለሆነ የመጨረሻውን ከባድ ቅጣት ከፈለች እንጂ። አለመውደቅና አለመሳሳት በእጇ ነበርና።

ይህን በበለጠ መረዳት እንችል ዘንድ የኢዮብን ነገር እንመልከት፣ ድል ከሆነው ድል ወዳደረገው እንሂድ። እጃችንን በዲያብሎስ ላይ እናነሣ ዘንድ ይህ እውነተኛ አርበኛ ታላቅ ጥንካሬና መንፈሳዊ ወኔ ይሰጠናልና። ባየነው (በአዳምና በሔዋን) ያታለለውና ድል ያደረገው እባብ ነው፣ እዚህ ግን «እግዚአብሔርን ስደበውና ሙት» ብላ የፈተነችው ሚስቱ ናት። ኢዮ. 2፥9። ሆኖም አልሰለጠነችበትም። ነገር ግን ከእባብ ይልቅ ለማሳመንና ለማሳሳት የበለጠ ቀረቤታና ኃይል ነበራት። ኢዮብ ንብረቱ ሁሉ ከወደመ በኋላ፣ ልጆቹን ሁሉ ካጣ በኋላ፣ ያለውን መልካም ነገር ሁሉ ተገፎ ራቁቱን ከቀረ በኋላ የእርሷ የማሳት ተንኮል ተጨመረበት። በዚያኛው ላይ ግን እንዲህ ያለ ምንም ነገር አልነበረም።

አዳም የልጅ ሞት አላገኘውም፣ የጠፋበት ሀብትም አልነበረም፣ ሰውነቱ በቁስል ተመትቶ በዓመድ ላይ አልወደቀም። ተድላ ደስታ ባለባት ገነት ተቀምጦ በዚያ ያለውን መልካም ነገር ሁሉ የመጠቀም ነጻነት ተሰጥቶት በደስታ እየኖረ ነበር እንጂ። በዚያ አድካሚ ሥራ፣ ተስፋ አስቆራጭ መከራ፣ ነቀፌታና ስድብ፣ ወይም በኢዮብ ላይ ከደረሰበት ስፍር ቁጥር የሌለው አስጨናቂ ነገር አንዱም አልነበረም። ሆኖም ግን ከእንዲህ ዓይነቱ





መከራና ችግር አንዱም እንኳ ሳይኖርበት ወደቀ፣ ድል ተነሣ። የውድቀቱ ምክንያት ስንፍናው እንደ ሆነ ግልፅ አይደለምን? ኢዮብ ደግሞ ይህ ሁሉ ደርሶበትና ከብዶበት ሳለ አለመውደቁና መጽናቱ ከነፍሱ ትጋት እንደ ሆነ ግልጽ አይደለምን?

5. የተወደዳችሁ ሆይ፣ ከሁሉቱም ወገን የሚጠቅማችሁን ነገር ሁሉ በሚገባ ቅሰሙ። ከስንፍናና ካለማስተዋል ብዙ ክፉ ነገሮች እንዲመነጩ አውቃችሁ አዳም ያደረገውን ስንፍና እንዳትደግሙ ተጠንቀቁ። ከጥንቃቄና ከጽናት[92] ደግሞ ምን ያህል ታላቅና ደገኛ ነገር እንዲገኝ አውቃችሁ ኢዮብን ምሰሉት። ድል አድራጊውን ሁል ጊዜ አስቡት፣ በሁሉም መከራና ችግር ብዙ መጽናናት ታገኙበታላችሁና። ያ ታላቅና ጀግና አባት በዓለም ባሉ ሰዎች ፊት ቆሞ የሚደርስባቸውን ማንኛውንም ነገር በትዕግሥት እንዲቀበሉትና ለሚመጣባቸው ፈተና እጅ እንዳይሰጡ በእርሱ ላይ በደረሰበት መከራዎች ይናገራልና።

ከኢዮብ መጽናናትን የማያገኝ ምንም ዓይነት የሰው መከራ አይኖርምና። በዓለሙ ዙሪያ ላይ ተበታትነው የሚገኙት መከራዎች ሁሉ በአንድ ላይ ሆነው በእርሱ ላይ ወርደውበታልና። ኢዮብ በዓለሙ ያለውን የመከራ ዓይነት ሁሉ እስከ መጨረሻው ተሸክሞ ጸንቶ ሲቆም በእርሱ ላይ የሚመጣውን የፈተና ድርሻ በአኩቴት የማይቀበል ሰው ምን የይቅርታ ምክንያት ይኖረዋል? እርሱ የተሸከመው የራሱን የፈተና ድርሻ ብቻ ሳይሆን በሰዎች ላይ የሚደርሰውን መከራ ሁሉ ጠቅልሎ በአንድ ላይ ነውና። የዚህን አባባሌን እውነተኛነት ትረዳ ዘንድ በእርሱ ላይ የደረሱትን መከራዎች አንድ በአንድ እንያቸው።

በመጀመሪያ በብዙዎች ዘንድ በጣም የሚያስቸግርና የሚከብድ ነው ከሚባለው ከድህነቱና ከእርሱ ጋር ተያይዘው የሚመጡትን ችግሮች እንመልከት። ሰዎች ስለ ድህነት በየቦታው ሙሾ ያወርዳሉና። ከኢዮብ የባሰ ድሀ ማን ነበር? በየመንገዱ የወደቁ፣ በደጅ የሚያድሩ ሌሎች ድሆች አሮጌም ቢሆን ቢያንስ ሰውነታቸውን የሚከድኑበት ጨርቅ ይኖራቸዋል። እርሱ ግን ራቁቱን ነበር፣ የነበረው ልብስ በተፈጥሮው የተሰጠው የሥጋው ቆዳ ብቻ ነበር። ሆኖም ይህንንም ቢሆን ሰይጣን በሁሉም በኩል በቁስል በመምታት አበላሸበት፣ አበሰበሰበት። ኢዮ. 2፥7-8።

ራሱን የሚያስጠጋበት ከማጣቱ የተነሣ የሚያድረው ሰማዩን ጣራ አድርጎ በባዶ ሜዳ ነበር። ከዚህም የበለጠ ደግሞ ሌሎች ድሆች ራሳቸው የሚያውቁት ብዙ ኃጢአትና በደል አለባቸው። እርሱ ግን ለዚህ መከራ የሚያበቃ ምን በደል እንደ በደለና ምን ኃጢአት እንደ ሠራ የሚያውቀው

[92] (Earnestness)

ነገር አልነበረውም። የበለጠ ያስጨነቀውና ግራ ያጋባው የደረሰበትን ነገር ምክንያት አለማወቁ ነበር። ሌሎቹ ሲቀጡ ቀድም እንዳልሁ ራሳቸውን የሚወቅሱበት ብዙ ምክንያት ይኖራቸዋል። ይህም ማለትም የሚቀጡበትን ምክንያት ማወቅ፣ በዚህ ምክንያት ይህ ደረሰብኝ፣ የምቀጣው ለኃጢአቴ የሚገባኝን ነው፣ ማለት በመከራ ለመጽናናት ያለው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም። ሕይወቱ ሁሉ በቅንነትና በጽድቅ የኖረ እርሱ ግን የኃጢአትን ጫፍ የነኩ ሰዎች የሚቀጡት ቅጣት ሲደርስበት ይህ መጽናኛ እንኳ የለውም።

ምእኖ ዘንድ ያሉ ድሆች ብዙዎቹ ከመጀመሪያ ጀምሮ እንዲሁ ናቸው፤ ስለዚህም ድህነትን ተለማምደውታል። እርሱ ግን ያልለመደውን ድህነት በአንድ ጊዜ ከፍጹም ባለጸጋነት ወደ ፍጹም ድህነት በመውረድ በአንድ ቅጽበት የመጨረሻ ድሀ ሆነ። የደረሰበትን ምክንያት ማወቅ የሚያጽናና እንደ ሆነ ሁሉ ድህነትንም ቀደም አድርጎ የመልመድ ዕድል ማግኘት አስተዋጽኦው ቀላል አልነበረም። እርሱ ግን እነዚህን መጽናኛዎች እንኳ አላገኘም። ሆኖም ግን አልወደቀም። የእርሱ ድህነት አቻ ያልነበረው እንደ ነበር ልብ አደረግህ? ራቁቱን ከሆነና በላዩ ላይ ጣራ እንኳ ከሌለው የባሰ ድሀ ምን ይኖራል? መሬት ላይ መተኛትን እንኳ ማግኘት አልቻለም፤ ዐመድ ላይ ወደቀ እንጂ። ስለዚህ አንተ ራስህ ድሀ ብትሆን የጻድቁን መከራ አስብ፣ በእምነት ሕሊናህን ወደ ፈጣሪህ አቅንተህ የተስፋ መቁረጥንና የመበሳጨትን ነገር ከውስጥህ ጠራርገህ አስወጣ። ይህ መቅሰፍት (ድህነት) ለብዙዎች የሌሎች ችግሮች ሁሉ መሠረትና መፍለቂያ ይመስላቸዋል።

ሁለተኛም ከዚህ በኋላ፣ አዎ፣ እንዲያውም ከዚህ በፊት የሰውነቱ ስቃይ ነው። የእርሱን ያህል ሰውነቱ በበሽታ የተጎዳና ዐቅም ያጣ ማን ይኖር ይሆን? ሰው ይህን ያህል ደዌ ሲቀበል ማን አይቶ ያውቃል? ሰውነቱ ቀስ በቀስ እያለቀ ሄደ፣ ከሥጋው እንደ ክረምት አግቢ ትል ያለማቋረጥ ይወጣበት ነበር፣ ከቆሰለው ሰውነቱ የሚወጣው ክርፋትም እርሱ ባለበት አካባቢ ለመቆም እስኪያስቸግር ድረስ በጣም የሚያስጨንቅ ነበር። ከቁስሉ መጥፎ ሽታ የተነሣ የሚሰጡትን ምግብ እንኳ መመገብ እስከማይችልበት ደረጃ ደረሰ። እንዲህ ይላልና፡- *«ምግቤ የሚያንገሸግሽና የሚያስጠላ ሆነብኝ»* ኢዮ. 6፥7።

በማንኛውም ጊዜ ቢሆን በደዌ ብትወድቅና ብትደክም ያን ቅዱስና ንጹሕ (የኢዮብን) ሰውነት አስብ። ይህን ያህል ብዙ ቁስልና መከራ እየተቀበለ ሳለም እንኳ ቅዱስ ነውና። ማንም ያለ ፍርድ አግባብ ወይም አለበቂ ምክንያት ቢታሠርና ቢገረፍ፣ ከዚያም በላይ ጎኖቹ እስኪሰነጣጠቁ ድረስ ቢፋቁና ሌላም ልዩ ልዩ ዓይነት መከራ በሰውነቱ ላይ ቢደርስ ነገሩን በሰው





ያልደረሰ ልዩ መከራ አድርጎ አያስብ፣ ይህን ቅዱስ ሲያዘክር ለሕማሙ መንገድ አይስጠው።

አይ፣ ይህ አባት ስቃዮቹን ሁሉ ያመጣበት እግዚአብሔር እንደ ሆነ ስለሚያውቅ ይህ መጽናኛ አለው የሚል ይኖራል። ነገር ግን ኢዮብን የበለጠ የረበሸውና ያበሳጨው ይህ ነው፤ ማለትም በፍጹም ልቡና በፍጹም ኃይሉ በቅንነት ያገለገለው አምላክ ፍርዱ እውነትና ርቱዕ ሲሆን በእርሱ ላይ ግን ይህን ሁሉ መከራ ማምጣቱ ነው። ለደረሰበት መከራ ምንም ዓይነት ምክንያት ሊሆን የሚችል ነገር ማግኘት አልቻለምና፤ ምክንያቱን ኋላ ሲረዳ እንዴት ዓይነት ፈሪሃ ግዚአብሔር እንዳሳየ ተመልከት። እግዚአብሔር *«አንተ ጻድቅ ትሆን ዘንድ በእኔ ትፈርዳለህን?»* ባለው ጊዜ በሕሊናው ተሰማውና *«እነሆ እኔ ወራዳ ሰው ነኝ፣ የምመልስልህ ምንድን ነው? እጄን በአፌ ላይ እጭናለሁ። አንድ ጊዜ ተናገርሁ፣ አልመልስምም፤ ሁለተኛ ጊዜ ከእንግዲህ አልናገርም።»* አለ። ኢዮ. 40፥8፤ 4-5። እንደ ገናም *«መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼህ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ።»* አለ። ኢዮ. 42፥5-6

6. ይህ (ለኢዮብ በመጨረሻ የተደረገለት) ለመጽናናት በቂ ነው ካልህ አንተም ይህን መጽናናት ታገኘዋለህ። ከእነዚህ መከራዎች አንዱ ከእግዚአብሔር እጅ ሳይሆን ከሰዎች ክፋት የተነሣ ቢደርስብህ፣ አንተ ግን እነዚህን ክፉ ነገሮች ሊያስቀራቸውና ሊከለክላቸው ይችል የነበረ፣ ነገር ግን አንተን ለመፈተን ይሆኑብህ ዘንድ የፈቀዳቸውን እግዚአብሔርን ባትነቅፍና ባታማርር አንተም እንደ እርሱ ተመሳሳይ ሽልማት ታገኛለህ። ከሰዎች የደረሱብህን ክፉ ነገሮች በአንተ ላይ እንዳይመጡብህ ሊያደርግ ይችል የነበረ እግዚአብሔርን አመስግነሃልና።

እንግዲህ ልብ አድርግ! ድህነትና በሽታ፣ ያውም ሁለቱም ባለ በሌለ የመጨረሻ ኃይላቸው በኢዮብ ላይ በአንድ ጊዜ ወድቀውበት አይተሃል። በዚህ ብርቅዬ ሰው ላይ የወደቀበትን ሌላ መከራ ማየት ትወዳለህን? አሥር ልጆችን አጣ፣ አሥሩም በአንድ ጊዜ አለቁበት፣ አሥሩም ገና በወጣትነታቸው ሳሉ፣ ሁሉም በመልካም ምግባርና ሕይወት የተዋቡ ነበሩ፣ አሟሟታቸውም በተለመደው ተፈጥሯዊ ሂደት ታመው ሳይሆን በመቅሠፍት አሳዛኝና አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ አሥሩም በአንድ ጊዜ አለቁ።

እንዲህ ያለውን ከተራራ የገዘፈ መከራ ማን እንደሚገባ አድርጎ አከናውኖ መግለፅና መናገር ይችላል? ማንም። ወንድና ሴት ልጆችን በአንድ ላይ ብታጣ ይህን ሰው ብታስታውሰው ብዙ መጽፃናትን ታገኛለህ። የደረሱበት መከራዎች እነዚህ ብቻ ናቸውን? በጓደኞቹ መጣሉና መናቁስ? «ይህ ሁሉ የደረሰብህ ኃጢአተኛ ብትሆን ነው እንጂ እግዚአብሔር ጻድቃንን እንዲህ

ባለ መከራ አይቀጣም» እያሉ በማያውቁት የእግዚአብሔር ሥራ ገብተው ያበሳጩትና ያሳዘኑትስ? በደረሰበት ነገር ሊያዝኑለት ቀርቶ መሳለቂያ አድርገውት በቁስሉ ላይ የጨመሩበት የሕሊና ጥዝጣዜስ? ይህ ሁሉ ለመሸከም የሚከብድ ነገር ነው የደረሰበት። በደረሰብን መከራ የሚወቅሱንና የሚፈርዱብን ሰዎች ከመከራው በበለጠ ነፍሳችንን ያቆስሏታልና።

የሚያጽናናው ምንም ሰው አለማግኘቱ ብቻ ሳይሆን ኋላ ደረሰበት ነገር ከሁሉም አቅጣጫ ውስጡን የሚያደሙ ነገሮች ይናገሩት ነበር። በዚህ ጉዳይ አምርሮ ሲያዝን እናየዋለን፤ እንዲህ ብሎ፦ *«ነፍሴን የምትነዘንዙ፤ በቃልስ የምታደቁኝ እስከ መቼ ነው?»* እንዲሁም ምሕረት የለሾች አላቸው፤ *«የሚያውቁኝ አጥብቀው ተለዩኝ። ዘመዶቼም ተቋረጡ፤ ወዳጆቼም ረሱኝ። ቤተሰቦቼና ሴቶች ባሪያዎቼ እንደ መጻተኛ ቆጠሩኝ፤ በዓይናቸውም እንደ እንግዳ ሆንሁ። ሚስቴ እስትንፋሴን ጠላች፤ የእናቴም ማኅፀን ልጆች ልመናዬን ጠሉ።»* ኢዮ. 19፥14-17። እንዲሁም *«ሕፃናት እንኳ አጠቁኝ፤ ሁሉም በእኔ ላይ ይናገራሉ»* አለ። 19፥18። እንደ ገናም *«አጥንቴ ከቁርበቴና ከሥጋዬ ጋር ተጣበቀ፤ ድድ ብቻ ቀረልኝ»* አለ። 19፥20። እነዚህ ነገሮች በቃል ሲሰሟቸው እንኳ ይከብዳሉ፤ በተግባር ደርሰው ሲሸከሟቸው ደግሞ እጅግ በጣም ይከብዳሉ።

የመጨረሻ ደረጃ ድህነት፤ ቆዳውን እንኳ ያላስተረፈ ጽኑ ደዌ፤ እነዚያን ያህል ብዛት ያላቸው፤ ያውም ሁሉም ደጋጎች የሆኑ አሥር ልጆችን በአንድ ጊዜ ማጣት፤ በዚህ ላይ ደግሞ የሚያጽናና ሰው አለማግኘት ብቻ ሳይሆን የሚመጡት ሰዎች የደረሰበት መከራ አይበቃው ይመስል በስድብና በነቀፋ ቁስሉ ላይ ኮምጣጤ ሲጨምሩበት፤ እንዴት ከባድ ነበር። ጠላቶቹ ብቻ ሳይሆኑ ወዳጆቹም፤ ወዳጆቹ ብቻ ሳይሆኑ ባሪያዎቹም ያሾሟጥጡትና ያሙት፤ ይስቁበትና ይቀልዱበት ነበር። መስደብና መቀለጃ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ተጸየፉት፤ ይህም ለሁለት፤ ለሦስት ወይም ለዐሥር ቀናት ሳይሆን ለብዙ ወራት ነበር።

በቀን ብቻ ሳይሆን በሌሊት እንኳ ዕፎይታ አልነበረውም። በሌሊት የሚያስፈሩትና የሚያስደነግጡት ነገሮች በጣም መብዛታቸው በቀንም መከራውን ያባብስበት ነበር። ስለዚህ እንዲህ ይላልና፦ *«ለምን በሕልም ታስፈራራኛለህ? በራእይስ ለምን ታስደነግጠኛለህ?»* ኢዮ. 7፥14። ይህን ሁሉ መከራ ምን ዓይነት ብረት የሆነ ሰው፤ ምን ዓይነት ጠንካራ ልብ ሊሸከመው ይችል ነበር? እያንዳንዱ እንኳ በራሱ ለመሸከም ከባድ ከሆነ የሁሉም አንድ ጊዜ መድረስ ምን ዓይነት መረበሽንና ግራ መጋባትን እንደሚያስከትል እስኪ አስበው። ሆኖም ግን እርሱ ይህን ሁሉ ቻለው፤ በደረሰበትና ባገኘው ነገር ሁሉ አልበደለም።





7. እንግዲህ የዚያ ታላቅ ጀግና ስቃያት ለእኛ ስህተቶች መድኃኒት ይሁኑን፤ የእርሱ መከረኛ የባሕር ላይ ጉዞ ለእኛ መከራዎች መጽናኛ ወደብ ይሁነን። በሚደርስብን በማንኛውም አደጋ ሁሉ ይህን ቅዱስ እናስበው። አንድ ሰው የዓለሙን ሁሉ መከራ ብቻውን ተሸክሞ ሲችለው እያየን እኛም የሚደርሰንን የድርሻችንን በጥብዓት ሆነን በአክእቴት ልንቀበል ይገባናል። እጂን በሁሉም አቅጣጫ ዘርግታ የተጨነቁ ልጆቿን እንደምትቀበልና እንደምታጽናና ደግ እናት ሁል ጊዜ ወደዚህ መጽሐፍ እንገስግስ። በሰዎች ላይ ከደረሰው ሁሉ የከፋና የከበደ ነገር ቢደርስብን እንኳ ከዚህ መጽሐፍ ለሁሉም የሚሆን በቂ መጽናኛ ይዘን እንመለሳለን።

«እርሱ ኢዮብ ነው፤ ስለዚህም ምክንያት ይህን ሁሉ ቻለው፤ እኔ ግን እንደ እርሱ አይደለሁም» ብትል ግን አንተን የምወቅስበትና እርሱን ደግሞ የማመሰግንበት ሌላ አዲስ ምክንያት ሰጠኸኝ ማለት ነው። ይህን ሁሉ ከእርሱ ይልቅ አንተ የበለጠ ልትሸከመው ይገባሃልና። እንዴት? ብትለኝ ምክንያቱም እርሱ የነበረው የቅድስና ሕይወት ያን ያህል ጥብቅና የተስፋፋ ባልነበረበት፤ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በዝቶ ባልተሰጠበት፤ ኃጢአትን መቃወምና መቋቋም ከባድ በነበረበት፤ በሰው ልጅ ላይ የመጣው መርገም ባልተወገደበት፤ ሞት አስፈሪ በነበረበት ከወንጌልና ከሕግ መሰጠት በፊት በነበረው ዘመን ነበርና[93]።

አሁን ግን እነዚህ ነገሮች ሁሉ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ስለ ተወገዱ ተጋድሏችን ቀላል ሆኗል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ብዙ ስጦታዎችን ከተቀበልን በኋላ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ባደረገው ቤዛነት ያስወገዳቸው ነገሮች ሁሉ በነበሩበት ና ዛሬ በዘመነ ወንጌል የምንኖር እኛ ያገኘናቸው ስጦታዎች ባልተሰጡበት ዘመን የነበረው እርሱ ከደረሰበት መድረስ ባንችል ምንም ዓይነት ማመካኛ የለንም።

ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ተገንዝበን ውጣ ውረዶችና ስቃያት ከእኛ ይልቅ ለእርሱ በጣም ከባድና አስቸጋሪ እንደ ነበሩ፤ ሆኖም ጦርነቱ በእርሱ ላይ በጣም ከባድ ቢሆንም ተጋድሎውን በድል አድራጊነት እንደ ተወጣ አስበን በእኛ ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም ነገር በትዕግሥትና በአኰቴት እንቀበል፤ እኛም እንደ እርሱ ያለ የድል አድራጊነት አክሊል እንቀበል ዘንድ፤ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነትና ሰውን መውደድ፤ ምስጋና ከእርሱ ጋር ለባሕርይ አባቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዛሬም ዘወትርም ሁል ጊዜም ለዘለዓለሙ። አሜን።

[93] ኢዮብ የነበረው የጽሑፍ ሕግ በሙሴ አማካይነት ከተሰጠበት ዘመን በፊት፤ በዘመኑ ሕገ ልቡና ነበር።

# ትምህርት ሦስት

## መግቢያ

የምሥራቁ የሮም ክፍለ ግዛት ንጉሥ የነበረው አርቃዴዎስ (395-408 ዓ.ም.) እንደ ምዕራቡ ክፍል ገዥ እንደ ወንድሙ እንደ አኖሬዎስ (395-423 ዓ.ም.) በአስተሳሰቡ ደከም ያለ ነበር። በእርሱ ዘመን የምሥራቁ የሮም ግዛት ዋናዎቹ ገዢዎች የይስሙላ እየሆኑ ዋናው ሥልጣን በሚኒስትሮቻቸው የሥልጣን ምኞትና ጥላ ሥር የወደቀበት ነበር። አርቃዴዎስ ሲነግሥ በመጀመሪያ የነበረው ዋናው ገዢ የጎል (ፈረንሳይ) ሰው የነበረው ሩፊኖስ ነበር። የሩፊኖስ ተንኰሉ፣ ዕብሪተኝነቱና የተመኘውን ነገር ሁሉ በኃይል የመውሰድ ጠባዩ ሕዝቡን በጣም እያስቆጣ ሄዶ በመጨረሻ ንጉሡ ባለበት ንግግር እያደረገላቸው በነበሩ ወታደሮች ተገደለ። የእርሱ በአርቃዴዎስ ዘንድ የነበረው ታማኝነትና ቦታ ወዲያውኑ በዩትሮጲየስ ተያዘ።

ዩትሮጲየስ የተወለደው በዘመኑ በነበረው ሥርዓተ ማኅበረሰብ መሠረት ከባሪያ ቤተሰቦች በሜሶፖታሚያ ነው። በልጅነቱና በወጣትነቱ በተለያዩ ባለቤቶች እጅ ብዙ የተዋርደና አስቸጋሪ ሥራዎችን እየሠራ አልፏል። በኋላም ጌታው የነበረ የወታደር ቤት ሹም ልጁ ስትዳር እርሱን ስጦታ አድርጐ ሰጣት። ሆኖም ይህች ሴት ዩትሮጲየስ ጉልበቱ እየደከመ ስለ ሄደ ለሌላ ሳትሸጠው ከቤቷ አስወጥ አባረረችው። ከዚያም በቁስጥንጥንያ አስቸጋሪ ሕይወት ይገፋ ጀመር። በዚያን ጊዜ የቤተ መንግሥት ሹም የነበረ አንድ ሰው አይቶት አዘነለትና በቤተ መንግሥት በዝቅተኛ ሥራ ውስጥ ቦታ ሰጠው። ይህ ወደፊት ለሚደርስበት ነገር በር ከፋች ነበር። የተሰጠውን ዝቅተኛ ሥራ በጥንቃቄና በትጋት በመሥራቱ፣ አልፎ አልፎ በሚናገራቸው የአስተዋይነትና የጥበብ አነጋገሮችና በጣም ሃይማኖተኛ መስሎ በመታየቱ የቴዎዶስዮስ ቀዳማዊን (379-395 ዓ.ም. - የአርቃዴዎስና የአኖሬዎስ አባት) ትኩረት መሳብ ቻለ።

ቀስ በቀስም በአስቸጋሪና የተወሳሰቡ ጉዳዩችና ተልእኮዎች ላይ እስኪመድበው ድረስ የቴዎዶስዮስን እምነት አገኘ። ቴዎዶስዮስ ሲሞት ዋናው የቤተ መንግሥት ጉዳይ ኃላፊና አዛዥ፣ የአርቃዴዎስ የቅርብ አማካሪና ከእርሱ የማይለይ የቅርብ ሰው ሆነ። የሩፊኖስም ዋና ዘዴኛና





ቁርጠኛ ተቀናቃኝ ሆነ። ሩፊኖስ ለአርቃዴዎስ ልጁን ለማጋባት የነበረው እቅድ ከሽፎ አርቃዴዎስ አውዶክስያን እንዲያገባ ያደረገው ይኸው ዩትሮጲየስ ነበር። ሩፊኖስ ከተገደለ በኋላ መንግሥቱ በእጁ ሥር ሆነ። ሆኖም ሥልጣኑን ከትዕቢተኛውና ከዕብሪተኛው ሩፊኖስ ይልቅ በበለጠ ዘዴ ይጠቀም ነበር። ቀስ በቀስም አደገኛ ተፎካካሪዎች ይሆናሉ ያላቸውን ሁሉ በተለያየ ሰበብ ከመንገድ በማስወጣት ወደ ሥልጣንና የኃይል ጫፍ መድረስ ጀመረ። ቤተ ክርስቲያን ወደ እርሷ የገቡትን አሳልፋ ላለመስጠትና ከጥቃትና ከቅጣት ለመጠበቅ ያላትን መብት በሕግ በመሻር የእርሱ ተጠቂ የሆኑትን የመጨረሻ የመሸሸጊያና የመጠለያ ተስፋ አሳጣቸው።[94] ይህን የቤተ ክርስቲያን መብት በዐዋጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የሻረው እርሱ ነው።

ዩትሮጲየስ ሥልጣንን ሁሉ በእጁ ካደረገ በኋላ ብዙ የመንግሥት የቢሮ ኃላፊነቶችን፣ የአገር ገዥነትንና የተለያዩ ሥልጣኖችን እንደ ጨረታ ከፍተኛ ገንዘብ ለሚያመጡት ይሰጥ ነበር። ንጉሡ አርቃዴዎስን ቀላቂል በሆኑ አጃቢዎች ዙሪያውን በማጠር፣ አእምሮዉን በተለያየ ተድላና ደስታ በማታለል ብዙ ጊዜ ወደ ባሕር ዳርቻ መዝናኛዎች በመውሰድና በዚያ ካለው ደስ የሚል አየርና መዝናኛ በቀር ሌላ ነገር እንዳያስብ በማድረግ ጥንቱንም ከቀደሙት ነገሥታት አንጻር ደከም ያለ ነው የሚባለውን ንጉሥ አርቃዴዎስን የበለጠ አዳከመው። ንጉሡ ከእርሱ በቀር ሌላ ጠንካራና ችሎታ ያለው ሰው ያለ እንዳይመስለውና ዓይኑን ወደ ሌላ እንዳያዞር አደረገው። ከትንሹ ነገር ጀምሮ እስከ ትልቁ መንግሥታዊ ጉዳይ ድረስ ሁሉም ነገር በዩትሮጲየስ ሥልጣን ሥር ወደቀ። ንጉሥ አርቃዴዎስ ግምጃ ከለበሰ አሻንጉሊት ብዙም የማይሻል ሆነ። ጃንደረባውና ባሪያ የነበረው ዩትሮጲየስ የሮማ ግዛት ግማሽ ክፍል (የምሥራቁ የሮማ ግዛት) እውነተኛው ገዥ ሆነ። በ397 ዓ.ም. ሊቀ ጳጳሳት ኔክታሪየስ ሲሞት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (እርሱ ሳይፈልግ) በቁስጥንጥንያ መንበር ላይ እንዲሾም የተደረገው በእርሱ

[94] በኦሪቱ ሕግ ሙሴ፣ ጠላቱ ያልሆነውን ባልንጀራውን ሳያውቅ የገደለ ሰው ይሸሽባቸውና ወደ አንዱ ሸሽቶ በሕይወት ይኖርባቸው ዘንድ በዮርዳኖስ ማዶ ሦስት ከተሞችን ለይቶ የመሸሸጊያና የመጠለያ ቦታዎች ብሎ ለይሟቸዋል። ወደ እነዚህ ከተሞች የገባ አይያዝም፣ አይቀጣም። ዘዳ. 4፥41-43። በሐዲስ ኪዳን ዘመንም ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ለማንም ቢሆን ተላልፎ አይሰጥም። በአንድ አገር ውስጥ ያለ የሌላ አገር ኤምባሲ ውስጥ መግባትና ወደዚያ የገባን ሰው መያዝ ያን አገር እንደመድፈር እንደሚቆጠር ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ወካይና ተምሳሌት ወደ ሆነችው ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የገባን ሰው መውሰድና ግቢዋን መድፈርም የቤተ ክርስቲያንን አምላክ እግዚአብሔርን መድፈር ነው። ቤተ ክርስቲያን ከኤምባሲዎች በጣም ትበልጣለችና። ዩትሮጲየስ በሥልጣን ዘመኑ በዐዋጅ ሽሮት የነበረው ይህንን የቤተ ክርስቲያን መብት ነበር። በኋላ ግን ከማንም በላይ ለራሱ አስፈለገው።

ምክር ነበር። ዩትሮጲየስ ስለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አስቀድሞ ይሰማ ስለ ነበር ነው። ሆኖም የቤተ መንግሥት አዳማቂና እርሱ እንደ ፈለገው የሚሆንለት ሰው ያገኝ መስሎት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን እንዲሾም አድርጐ ከሆነ በኋላ በራሱ ምክርና አስተሳሰብ በጣም ተበሳጭቶ መሆን አለበት።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን የስብከተ ወንጌል ተልእኮዎችና ሥራዎች በገንዘብ በመርዳትና በማገዝ ቤተ ክርስቲያንን የረዳ ለመምሰል ያደርጋቸው የነበሩ አንዳንድ ማስመሰሎች ሊቀ ጳጳሱቱን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን በአስተዳደሩ የሚያደርገውን ግፍና ተንኰል ከማየት ዓይኖቹን አልሸፈኑትም። በምንም ነገር ከማይደለለውና ከእውነት በቀር ለማንም ሰው ለማያደላው፣ ማንኛውንም ነገር በውጫዊ ሁኔታውና ገጽታው ሳይሆን በይዘቱና በትክክለኛ ማንነቱ ከሚገመግመው ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽና የማስጠንቀቂያ ትምህርት ነጻ ሊያደርገው አልቻለም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሀብታሞች ስለሚያደርጉት ግፍና ጭቆና አግባብ አለመሆንና ይህንን በጽኑ በማውገዝ ባስተማረ ቁጥር የነዚህ ነገሮች ዋና መገለጫና ማሳያ ዩትሮጲየስ መሆኑ ለሁሉም ሰው ግልጽ ነበር።

በመጨረሻም ዩትሮጲየስ የሮማን ምሥራቃዊ ክፍለ ግዛት ዋና ገዥነት ሥልጣን መያዝ ብቻ ስላልበቃው የክብር ስሙም እንዲሰጠው ፈለገ። ፓትሪካን እና ቆንስላ የተባሉትን የመዓርግ ስሞች ንጉሡ እንዲሰጠው በማድረግ የራሱን የውድቀት መንገድ ደኅና አድርጎ አመቻቸ። እነዚህ የመዓርግ ስሞች በዘመኑ በጣም የተከበሩ ስለ ነበሩ ጃንደረባና ባሪያ ለነበረው ሰው መሰጠታቸው በመላው የሮማ ግዛት ቁጣን ቀሰቀሰ። ዩትሮጲየስ ቆንስላ ተብሎ ተሰየመ። ከዚያም ከፍተኛው የመንግሥት ምክር ቤት (ሴኔት) አባላት፣ የሲቪልና የወታደራዊ ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ ሁሉም፣ «እንኳን ደስ አለህ» ለማለት ወደ ቤተ መንግሥት ተጣደፉ። የዩትሮጲየስን እጅና የተጨማደደ ፊቱን ሳይቀር ለመሳም ተሽቀዳደሙ። እንደ ጽኑ የሕግ አለኝታና ጠባቂ፣ የንጉሡ (የአርቃዴዎስ) ሁለተኛ አባት አድርገው በመቁጠር ተሳለሙት። በዳኛና በጦር ጀግና ምስል የተሠሩ የዩትሮጲየስ የብርና የእብነ በረድ ሀውልቶች በከተማው የተለያዩ ቦታዎች ተተከሉ። በሀውልቶቹ ላይም የቁስጥንጥንያ ከተማ ሦስተኛ መሥራች (ከቢዛስ እና ከቆስጠንጢኖስ ቀጥሎ) እንደ ሆነ የሚገልፁ ጽሑፎች ተቀርጸው ነበር። ዩትሮጲየስ





ሥልጣኑ የሚያልፍ አልመሰለውም፣ የዕለቱን እንጂ የወደፊቱን ማሰብ አልቻለም።

ከጦር ሠራዊቱ ውስጥ ትሪቢጂልድ የሚባል ታዋቂ የነበረ አንድ መኮንን ለራሱ የመዓርግ ዕድገትን፣ በሥሩ ላሉ ወታደሮች ደግሞ የተሻለ ክፍያን ጠየቀ። ይህ ጥያቄው በዩትሮጲየስ በንቀት ውደቅ ተደረገ። ትሪቢጂልድ በዩትሮጲየስ መልስ በመበሳጨቱ በሥሩ ካሉት ወታደሮች ጋር ዐመፀ። ዩትሮጲየስም ከታማኞቹ አንዱን የጦር መሪ አዘመተበት። ነገር ግን የተላከው ጦር በአሳፋሪ ሁኔታ ተሸንፎ የዩትሮጲየስ ታማኝ የነበረው የጦሩ መሪም ተገድሎ ጦሩም ተበታተነ። በዚህ ጊዜ ቁስጥንጥንያ በሽብርና በሕዝባዊ ቁጣ ሥር ወደቀች። በዚህ ጊዜ የቤተ መንግሥት ጦር አዛዥ የነበረው ሌላው ደግሞ ዩትሮጲየስ ከሥልጣን ካልወረደና ካልተባረረ በስተቀር የዓመጹን መስፋፋት ለማስቆም ምንም ማድረግ አልችልም ሲል ዐወጀ። ይህ ጥያቄም ከእርሱ (ዩትሮጲየስ) ብዙ ስድብና ንቀት ይደርስባት በነበረችው በንግሥቲቱ በአውዶክስያ ተደገፈ። በዚህ ጊዜ ዩትሮጲየስ የነበረው ሥልጣንና መዓርግ፣ ክብሩ ሁሉ በአንድ ጊዜ ተገፈፈ፣ ንብረቱ ሁሉ መወረሱ ታወጀ፣ ቤተ መንግሥቱን በፍጥነት ጥሎ ካልጠፋ ሞት እንደሚጠብቀው ተነገረው።

በአንድ ጊዜ ከሥልጣንና ከክብር ጫፍ ወደ መሬት ጥልቅ ተንኰታኩቶ የወደቀው ይህ ሰው ቀኑ ጨለመበት። በዚህ ጊዜ ወደት ይሂድ? በዚህ የመጨረሻ የጭንቀትና የችግር ጊዜ ሊሄድበት የሚችለው አንድ ቦታ ብቻ ነበር። ይኸም የቤተ ክርስቲያን ወደ እርሷ የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው አሳልፎ ያለ መስጠት መብቷ ነበር። ሆኖም ራሱ ዩትሮጲየስ ከትንሽ ጊዜ በፊት ቀደም ብሎ ባወጣው ሕግ ይህን የቤተ ክርስቲያን መብት በዐዋጅ ሽሮታል። እንዲህም ቢሆን የቤተ ክርስቲያንን የመጠጊያነት መብት የሚሽረውን ዐዋጅ ቤተ ክርስቲያን ስትቃወመው እንደ ነበር ስለሚያውቅ፣ እንዲሁም ሊቀ ጳጳሳቱ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እርሱ በዐዋጅ የሻረው የቤተ ክርስቲያን መብት ይህን ዐዋጅ ላወጣው ለራሱ ሳይቀር ጠቃሚው የነበረ መሆኑን ለማሳየት ሲል አይጨክንብኝ ይሆናል በሚል ተስፋ ዕድሉን ለመሞከር ወሰነ። በተጨማደዱ ጉንጮቹ ዕንባውን እያወረደ፣ ራሱና ግራጫ ፀጉሩ በአቧራና በጭቃ ተለውሶ የመጨረሻ አሳዛኝ በሆነ የለማኝና የደጅ ጸኝ ገጽታ ሆኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ከመቅደሱ ፊት ለፊት ያለውን መጋረጃ ገልጦ ከአንድ ዓምድ ልጥፍ ብሎ ተጠጋ።

የገቡት ወታደሮች የሙሃሪያቸው ኳኳታ ስደተኛው (ዩትሮጲየስ) በተሸሸገበት ቦታ ይሰማ ነበር። እርሱም ከንፈሮቹ እየተንቀጠቀጡ የቤተ ክርስቲያንን የማስጠጋት መብት አጥብቆ ተማጸነ። ነገር ግን እርሱ አሁን የሚማጸነውን የቤተ ክርስቲያንን ጥገኝነት የመስጠት (የመጠለያነት) መብት አጥፊ እንደ መሆኑ አልተደረገበትም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቤተ ክርስቲያን በጠላቷ ላይ እንዲህ ያለ ደገኛ በቀልን ትበቀል ዘንድ በተሰጣት እድል ደስ አለው። ዩትሮጲየስን ወደ ንዋያተ ቅድሳት ማስቀመጫ ክፍል አስገባው። ይፈልጉትና ያሳድዱት ለነበሩት ወታደሮች «ለእናንተ አሳልፌ አልሰጠውም» አላቸው። "በእኔ ሰውነት ላይ ተረማምዳችሁ ካልሆነ በስተቀር ማንም የቤተ ክርስቲያንን ግቢ ሊዳፈር አይችልም፤ ቤተ ክርስቲያን ክብሯን ለእኔ አደራ የሰጠኝ የክርስቶስ ሙሽራ ናት፣ እኔም ፈጽሞ አልከዳትም" አለ።

ከዚያም ይህን ጉዳይ ወደ ንጉሡ እንዲቀርብ በመፈለጉ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደ እስረኛ ሰይፍና ጦር በታጠቁ ወታደሮች በግራና በቀኝ ተከቦ ከቤተ ክርስቲያኑ ወደ ቤተ መንግሥት ሄደ። በዚያም በንጉሡ ፊት የቤተ ክርስቲያንን የመጠጊያነት መብት የሚሽረው ሕግ የወጣው አለ አግባብ መሆኑንና ይህን መብቷን ማንም ሊገፋት እንደማይገባ በድፍረት አስረዳ። ንጉሡ አርቃዴዎስም የወደቀውን ሚኒስትር ስደት ለማክበር ቃል ገባለት፣ በቁጣ ላይ የነበሩትን ወታደሮችም በጭንቅ ውሳኔውን እንዲቀበሉ አሳመናቸው።

ቀጣዩ ቀን እሑድ ነበር። በዚህ ዕለትም የቤተ ክርስቲያንን የመጠለያነት መብት ለመሻር የወጣውን ሕግ ጉዳይ ባለማለትና የቤተ ክርስቲያንን መብቷን ለመጠበቅና የተሰደደውን ሚኒስትር ለማዳን በቆራጥነት ከታገለው ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አንደበት ምን እንደሚነገር ለመስማት በጣም ብዙ የሆነ ሕዝብ ከመሰብሰቡ የተነሣ የቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ተጣበበ። በተግባር እስኪያዩ ድረስ እንዲህ ዓይነት ድራማዊ ትርዒት በእውነት በገሃድ መሆኑን ያመኑ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። ሊቀ ጳጳሳቱ ሁል ጊዜ የሚያስተምርበት ቦታ ላይ ሆኖ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ሲገለጥ አሳዛኙ ዩትሮጲየስ ከአንድ ዓምድ ሥር ኩርምት ብሎ ተጠግቶ ሲያዩ ከዚህ አባት የሚጣፍጥ አንደበት ምን እንደሚወጣ በጉጉት በመጠባበቅ የሁሉም ዓይን እርሱ ላይ ዐረፈ።



ሁሉ የመጨረሻ ጫፍ ላይ ከደረሰ በኂላ ሁሉንም በአንድ ቀን አጥቶ ከኂላው በጭንቀትና በሐዘን ኩርምት ብሎ በተቀመጠው በዩትሮጲየስ የተግባር ማሳያነትና ማስረጃነት ትምህርቱን ለሕዝቡ ልብ የበለጠ እንዲረዳ የሚያደርግበት ልዩ አጋጣሚ አገኘ።

ዩትሮጲየስ ለትንሽ ቀናት ያህል በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ከቆየ በኂላ በድንገት ጠፋ። በቤተ ክርስቲያን ባገኘው ጥበቃ ላይ እምነት አጥቶ በስውር ለመጥፋት ፈልጐ ይሁን ወይም የሞት ቅጣት ከሀገር በመባረር ይለወጥልኛል በሚል ተስፋ ሄዶ እጅ ይስጥ በርግጠኝነት አይታወቅም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቤተ ክርስቲያንን ትቶ ባይጠፋ ኖሮ ቤተ ክርስቲያን መቼም ቢሆን አሳልፋ አትሰጠውም ነበር ብኂል። የሆነ ሆኖ ተይዞ ወደ ቆጵሮስ ተወሰደ። ብዙም ሳይቆይ ወዲያውኑ ወደ ቁስጥንጥንያ እንዲመጣ ተደርጎ በተለያዩ በታላላቅና በታናናሽ ወንጀሎች ተከሶ የሞት ፍርድ ተፈረደበት። ወደ ኬልቄዶን ተወስዶ በዚያ አንገቱ ተቀልቶ ተገደለ። በእርሱ ታውጆ የነበረው:- *ማንም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ጥገኝነት እንዳይጠይቅና ቀድሞ የገባም ካለ ተላልፎ እንዲሰጥ* በማለት ያወጣው ዐዋጅም ከመንግሥት ሕጎች መዝገብ ተሰረዘ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዩትሮጲየስ እንዲያ መሆን ምክንያት ሁለት አስደናቂ ትምህርቶችን አስተማረ። የመጀመሪያው ትምህርት ከላይ እንደ ተገለጠው ዩትሮጲየስ ከቤተ መንግሥት ተባሮ ሕይወቱን ለማዳን ወደ ቤተ ክርስቲያን በተሰደደ ማግስት በሰንበተ ክርስቲያን (እሑድ) ቀን ነው። ሁለተኛው ደግሞ ዩትሮጲየስ የቤተ ክርስቲያንን ግቢ ትቶ ከጠፋ ከጥቂት ቀናት በኂላ ነው። የመጀመሪያው ትምህርት እንደሚከተለው ተተርጉሞ ቀርቧል። ሁለተኛው ትምህርት ከዚህ ከአንደኛው ትምህርት በዛ ያለ ሲሆን በዚህ መጽሐፍ አልተካተተም።

# ትምህርት አንድ[95]

## ጃንደረባ፣ ፓትሪካንና ቆንስላ[96] ስለ ነበረው ዩትሮጲየስ

1. "ሁሉ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነው" - ይህን ሁል ጊዜ ማስታወስና ማለት ይገባል፤ በተለይ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ የበለጠ ይህን ልንል ይገባል። የቆንስላነትህ አስደሳች ክብርና አስደናቂ አጃቢዎች አሁን የታሉ? በፊትህ የሚበሩልህ ችቦዎች የታሉ? በፊትህ የሚዘፍኑትና የሚያሸበሽቡት የውዳሴያቸውና የሽብሸባቸው ድምፅ የት ገባ? የሚደገሱት ድግሶችና የሚዘጋጁት ማዕዶች የታሉ? ይበረከቱልህ የነበሩት የቴያትር ቤቶች እቅፍ አበባና ይገለጡልህ የነበሩት ያማሩ መጋረጃዎች የት ደረሱ? በከተማ ስትንቀሳቀስ ይቀበሉህ የነበሩት ጭብጨባዎች የታሉ? በፈረስ ግልቢያና በሠረገላ እሽቅድምድም ቦታዎች የነበረው እልልታና የተመልካቾች ቁልምጫ የታለ? ሁሉም አሁን የሉም፤ ላይመለሱ በነው ጠፍተዋል። ቅጠሉን ሁሉ የሚያረግፍ ኃይለኛ ነፋስ በዛፉ ላይ ነፍሶበታል፤ ዛፉን ከሥሩ በማነቃነቅ ግንዱን ብቻ ራቁቱን አሳየን። ከነፋሱ ኃይለኛነት የተነሣ ለዛፉ አንድ ቅጠል እንካ አላስቀረለትም። ከዚያም አልፎ ከሥሩ ነቅሎ ሊጥለው ደረሰ እንጂ።

የግፍ ጓደኞችህና ግብረ አበሮችህ አሁን የት ደረሱ? የመጠጥ አጃቢዎችህና ጓደኞችህ አሁን የት ናቸው? የማዕድ ባልደረቦችህስ? ቀኑን ሙሉ ለክብርህ የሚቀዳው ወይንና የሚርመሰመሱት ጥገኞችህ፣ በማዕድ ቤት ሠራተኞችህ የፊጠራ ችሎታ እየተፈለሰፈ የሚቀርበው ልዩ ልዩ ዓይነት ጣፋጭ መብልና መጠጥስ? ሥልጣንህን ደጅ ሲጠኑና ዙሪያህን ሲከቡህ የነበሩት፣ የአንተን ትኩረት ለመሳብና ለማግኘት ሲሉ ማንኛውንም ነገር ሲያደርጉና ሲናገሩ የነበሩትስ የት አሉ? ሁሉም የሌሊት ቅዠቶች ኖረዋል። ሌሊቱ አልፎ ቀኑ በመምጣቱ ከጨለማው ጋር አብረው የጠፉ ህልሞች ብቻ ነበሩ። ወቅቱ ሲያልፍ የጠወለጉና የረገፉ የጸጌ ወራት አበባዎች ነበሩ። ያለ መስሎ ታይቶ እንደ ጠፋ

[95] (Homily I)

[96] (Patrician and Consul) እነዚህ መዓርጎች በሮማ ግዛት ዘመን በቢዛንታይን ነገሥታት በቀጥታ ለሚሾም ሰው የሚሠጡ ከፍተኛ የሥልጣን ቦታዎችና የክብር መዓርጎች ነበሩ። ፓትሪካኖች ወይም ቆንስላዎች ከንጉሡ ቀጥሎ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው ነበሩ። ነገሥታቱ ደከም ሲሉ ደግሞ የእነርሱ ሥልጣንና ፈላጭ ቆራጭነት ጎልቶ ይወጣ ነበር። ዩትሮጲየስ እንዲህ ነበር።





ጥላ፣ ወደ አየር ተኖ እንደ ጠፋ ጢስ፣ ሚሙቶ እንዳለቀ አረፋ፣ እንደ ተበጣጠሰ የሸረሪት ድር ነበሩ።

ስለዚህ ሁል ጊዜ ይህን መንፈሳዊ መዝሙር እንዘምራለን፦ "ሁሉ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነው" የሚለውን። ይህ አባባል ሁል ጊዜ በግድግዳችን፣ በልብሳችን፣ በገበያ ቦታ፣ በቤት ውስጥ፣ በመንገዶች ላይ፣ በበራችንና በመግቢያችን፣ ከዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ በእያንዳንዳችን ሕሊና ላይ ሊጻፍና ሁል ጊዜ ለተዘክሮአችን ዋና ርእስ ጉዳይ ሊሆን ይገባል። የሚያታልሉ ነገሮችና በጭምብል የተሸፈኑ ማስመሰሎች ለብዙዎች እውነታ መስለው በሚታዩበት መጠን እያንዳንዳችን ጧትም ሆነ ማታ እርስ በርሳችን ስንገናኝ በማንኛውም ጊዜ አንዱ ለሌላው፣ ሌላውም መልሶ ለአንዱ "ሁሉ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነው" ሊለው ያስፈልጋል። ሀብት ንብረት ጠፊ ነው እያልኩ ሁል ጊዜ ስነግርህ አልነበረም? ሆኖም አንተ ግን ልብ ብለህ አልሰማኸኝም።

ገንዘብ ምስጋና የለሽና ውለታ ቢስ አገልጋይ መሆኑን ስነግርህ አልነበረም? አንተ ግን ነገሩን ለማመንና ለመቀበል አልቻልህም ነበር። አሁን ግን ኃላፊና ጠፊ ብቻ ሳይሆን እንዲሁም ውለታ ቢስ አገልጋይ ብቻ ሳይሆን ሕይወት አጥፊም መሆኑን በተግባር የደረሰብህ ነገር አረጋግጧል። አሁን እንድትፈራና እንድትንቀጠቀጥ ያደረገህ ይህ ነውና። እኔ እውነቱን ስለተናገርኩ በተቆጣህ ጊዜ ሁሉ *"ከሚያቆላምጡህና ከሚያወድሱህ ሰዎች የበለጠ እኔ እወድሃለሁ"* ስልህ አልነበረምን? "በጥፋትህ እገሥጽህ የነበርኩት እኔ ከሚያጅቡህና ከሚያደንቁህ ይልቅ ላንተ አስብልህ ነበር" በእነዚህ ቃላት ላይስ *«ከጠላት መሳም ይልቅ የጓደኛ ማቁሰል ይሻላል»* የሚል ቃል አብሬ አልነገርኩህምን? ምሳ. 27፥6። የእኔን ማቁሰል በጊዜው ልብ ብለኸውና ተቀብለኸው ቢሆን ኖሮ የእነርሱ መሳም አሁን ይህን ጥፋት አያመጣብህም ነበር። የእኔ ማቁሰል ጤነኛ ትሆን ዘንድ የሚረዳህ ነበር፣ የእነርሱ መሳም ግን እንዲህ ያለ የማይድን በሽታን አመጣብህ።

ጽዋህን ይሸከሙ የነበሩት አሁን የት አሉ? በገበያ ቦታ ስታልፍ ከፊት ሆነው መንገድህን ይመሩና ያጠሩ የነበሩት አሁን የት አሉ? ውዳሴህን በሰው ሁሉ ጆሮ ሲያንቆረቁሩ የነበሩትስ አሁን የት ደረሱ? የአንተን አጃቢነት ጥለው ሸሽተዋል፣ ክድተውሃል፣ በአንተ መከራ ላይ መውደቅ የራሳቸውን ደኅንነት እያመቻቹ ናቸው። እኔ ግን እንዲህ አላደርግም። እንዲህ በገጠመህ አሳዛኝ ሁኔታ አልተውህም፣ በወደቅህ ጊዜ ተቀብልኩህ፣ ሕይወትህን ለማትረፍም ማድረግ ያለብኝን ሁሉ

አደረግሁ፣ ደኅንነትህንም ጠበቅሁ፣ ተንከባከብኩህም። እኔ እነርሱን በተመለከተ ሳስተምር በእኔ ላይ ትቆጣና ስለ እነርሱ ትቆረቆርላቸውና ታዘወትራቸው የነበሩት የቴያትር ቤቶች ሲከዱህ እንደ ጠላት የቆጠርካት ቤተ ክርስቲያን ግን እጆቿን ዘርግታ ተቀበለችህ፣ በእቅፏም ውስጥ ደበቀችህ። እንዲያም ሆኖ ለአንተ "እንዲህ ያሉ ነገሮችን ለምን ታደርጋለህ?" "ቤተ ክርስቲያንን እያስቆጣህና ራስህንም ወደ ጥልቁ እየጣልህ፣ ውድቀትህን እያፋጠንክና አወዳደቅህን እያከፋህ ነው" ማለትን አላቋረጥኩም ነበር። አንተ ግን በማስጠንቀቂያዬ ላይ ከመቆጣት በቀር ልትሰማኝ አልቻልህም። አሁን ግን የትርዒት ቦታዎች ገንዘብህን ከጨረሱ በኋላ ሰይፋቸውን ሳሉብህ። ብዙ ተንኮልህንና ቁጣህን ያደረስክባት ቤተ ክርስቲያን ግን አንተን ከገባህበት ወጥመድ ለማውጣት ካላት ፍላጎት የተነሳ በሁሉም አቅጣጫ ተፋጠነች።

2. እነዚህን ነገሮች የምለው የወደቀውን ለመርገጥና በእርሱ ላይ ለመራመድ ሳይሆን ገና ያልወደቁትንና እንዲህ ያለ ነገር ያላገኛቸውን እንዲጠነቀቁ ለማድረግ ካለኝ ፍላጎት የተነሣ ነው። የቁስለኛውን ቁስል የበለጠ ለማቁሰል ሳይሆን ገና ያልቆሰሉትን ከመቁሰል እንዲጠበቁ ለማድረግ ነው። በሞገዶች እየተማታ ያለውን ለማስጠም ሳይሆን በጥሩ ሁኔታ እየቀዘፉ ያሉትን በማዕበል እንዳይጠፉ ከመፈለግ የተነሣ ነው። ታዲያ ይህ ምን ቢደረግ ሊገኝና ተግባራዊ ሊሆን ይችላል? ይህ የሚሆነው በሰው ሕይወት ውስጥ የሚደርሱትን ተለዋዋጭ ነገሮች በማስተዋል ነው። ይህ ሰው ራሱ እንኳ በሰው ሕይወት ላይ የሚፈራረቀውን መልካምና ክፉ ነገር አስቦ ቢሆን ኖሮ ይህ ባልደረሰበት ነበር። ነገር ግን የራሱም ሕሊና ሆነ የሌሎችም ምክር በእርሱ ላይ ምንም የጠባይና የምግባር ለውጥ ሊያመጡ ስላልቻሉ አሁን ይህ ደርሶበታል።

እስኪ ባይሆን ጊዜያዊ በሆነ ሀብታችሁ የምትኩራሩና ለራሳችሁ ምናባዊ ክብርና የተለየ ቦታ የምትሰጡ እናንተ በእርሱ ላይ ከደረሰው ነገር ተምራችሁ ራሳችሁን ጥቀሙ። በዚህ ዓለም ከሰው ሕይወት የበለጠ ተለዋዋጭና ደካማ ነገር የለምና። ማንም ሰው ምንም ዓይነት ቃላትና ሐረግ ቢጠቀም የዚህን ዓለም ሕይወት ከንቱነት እውነታውን እንደሚገባ አድርጎ ለመግለጽ አይችልም። ጢስ፣ ሣር፣ ህልም፣ አበባ፣ ሌላ ሌላም ስም ቢሰጣቸው ከምንም ነገር ያነሱ ጠፊዎችና ባዶዎች ናቸው። ከዚህ ጠፊነታቸውና ከንቱነታቸው ጋርም ከፊታችን እንደምናየው ያለ ኀይለኛነት አላቸው። ጠፊዎችና ኃላፊዎች፣ ምንነት የሌላቸው ባዶዎች ሲሆኑ





ይህን ባልተረዱ ሰዎች ላይ ግን እንዲህ ያለ የማያልፍ ጠባሳና የማይጠገን ስብራት ጥለውባቸው ይሄዳሉ።

ከዚህ ሰው በላይ የከበረ ማን ነበር? በሀብቱ፣ አሉ የሚባሉ ባለ ጸጋዎች ሁሉ የማይስተካከሉት እስኪሆን ድረስ አልደረሰም? በክብር ማማ ጫፍ ላይ አልወጣም? ሁሉ በፊቱ አልተንቀጠቀጠም? ሆኖም አሁን ከእስረኛ ይልቅ አሳዛኝ ሆኗል፤ በረሃብ ከሚሰቃይ ችግረኛ የባሰ ምንም የሌለው ሆኗል። ሁል ጊዜ በፊቱ የተሳሉ ሰይፎችና የክፉዎች መቃብር እየታየው፣ ቅጣት ፈጻሚዎች እየጎተቱ ወደ ሞት ሲወስዱት እያሰበ፣ በጠራራ ፀሐይ የጭንቀት ጨለማ እየከበበው ባለፈ ዘመኑ ደስታ የሚባል ነገር አንድ ቀን እንኳ ያየ መሆኑን ማሰብ አይችልም።

ነገር ግን የምችለውን ያህል ስናገርና ቃላት ስመርጥ ብውል ሞት በድንገት ደርሶ ባሳደደው ጊዜ የደረሰበትን መከራ እንደሚገባ አድርጌ አከናውኜ ለእናንተ መናገር አልችልም። ነገር ግን እርሱ ራሱ እንደሚታይ ሥዕል ከፊታችን እያሳየን እያለ ከእኔ ምን ቃላትና ማብራሪያ ያስፈልጋል? ትናንት በኃይል አውጥተው ሊወስዱት ከመጡና እርሱም ወደ ቤተ ክርስቲያን ከገባ ጊዜ ጀምሮ ገጽታው ልክ አሁንም እንደምታዩት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሙት ሰው ገጽታ ነው። በሰውነቱ መንቀጥቀጥ፣ በአንደበቱ መያያዝ በሁሉም ነገሩ በጣም አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ነው።

3. አሁንም ይህን የምለው እርሱን ለመውቀስና በደረሰበት አሳዛኝ ሁኔታ ለመንቀፍ አይደለም፤ እናንተ ለእርሱ ያላችሁን ስሜትና አስተሳሰብ ለማለዘብና ለማለስለስ ከመፈለጌ የተነሣ፣ የተቀጣውን ቅጣት ክብደትና ሁኔታ ተረድታችሁ ይኸው የተቀበለው ቅጣት ይበቃዋል ትሉ ዘንድ እናንተን ለማሳመን እንጂ። እርሱን ወደ መቅደስ አስገብቼ በመቀበሉና አሳልፌ አልሰጥም በማለቴ ምክንያት እኔን ጥፋተኛ ለማድረግ የሚሹ ብዙ ኢሰብአዊ የሆኑ ሰዎች ከእኛ መካከል ስላሉ የልባቸውን ደንዳናነት ለማለዘብ ከመፈለጌ የተነሣ የደረሰበትን ነገር ዘርዝር አድርጌ አሳየሁ።

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ በእኔ የምትቆጡት ለምንድን ነው? ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሁል ጊዜ ጦርነትን ያውጅ የነበረ፣ የቤተ ክርስቲያንን መብት በዐዋጅ የሻረ እርሱ አሁን በእርሷ ውስጥ ተጠልሎ በመዳኑ ነው ትሉኛላችሁ። ሆኖም ግን በዚህ ነገር፣ ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔርን በጣም ልናመሰግነው ይገባናል። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያንን ኃይልና ፍቅር እንዲፈልግና በተግባር እንዲያይ የሚያስገድደው ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ ፈቅዷልና። የቤተ ክርስቲያንን ኃይል - በእርሷ ላይ ባደረሰው ጥቃትና በደል የተነሣ ይህ ታላቅ የሆነ ቅጣት ደርሶበታልና ነው።

ፍቅሯን ደግሞ ሲያጠቃትና ሲተናኮላት የነበረች እርሷ አሁን ሲገድሉት ከሚያሳድት ጋሻ ሆና በመከለል በክንፎቿ ውስጥ ተቀበለችው፤ የቀድሞ በደሉን አንዱንም ሳታስብ በጸጥታና በደኅንነት ውስጥ አስቀመጠችው፤ በፍጹም ፍቅር በእቅፎቿ ውስጥ ሰወረችው። ይህ ከማንኛውም ዓይነት ድል የበለጠ አስደናቂ ነው። ይህ ብሩህ አሸናፊነት ነው። ይህ ድል አሕዛብንም አይሁድንም ሁሉንም የሚያሳፍር ነው። ይህ የቤተ ክርስቲያንን ብሩህ ገጽ የሚያሳይ ነው። ጠላቷን እንደ ምርኮኛ ከተቀበለችው በኋላ አተረፈችው። በመከራው ጊዜ ሁሉም ሲነቅፈውና ሲጥሉው እርሷ ብቻ ልክ እንደ ርህርኅት እናት የንጉሡንም፣ የሕዝቡንም የሁሉንም ቁጣና አስፈሪ ጥላቻ በመቃወምና በመቋቋም በካባዋ ውስጥ ሰወረችው።

ይህ የምስዋዐ መቅደሱ ጌጥ ነው። የታወቀው ኃጥእ፣ ወንጀለኛው፣ ወንበዴው፣ ቀማኛው ይነካው ዘንድ የተፈቀደ የመቅደስ ጌጥ፤ ይህ እንግዳ ጌጥ ነው ትሉ ይሆናል። አይደለም! እንዲህ አትበሉ፣ አመንዝራዋ እንኳ የኢየሱስን እግር ነክታለች። እጅግ በጣም አስጸያፊና የርኩሰት ሁሉ ርኩሰት በሆነው የተበከለችው እርሷ እግሩን ስማለች። ሆኖም ይህ አድራጎቷ ኢየሱስን የሚያስነቅፈው አልነበረም፤ ለእርሱ ክብርና ምስጋና ምክንያት ሆነ እንጂ። ንጹሕ ለሆነ ለእርሱ የአመንዝራዋ ርኩሰት ያደረሰበት ምንም ነገር የለም። ነገር ግን በዝሙት የረከሰችው እርሷ ፍጹም ንጹሕ የሆነውን እርሱን በመንካቷ ነጻች፣ ተቀደሰች። ወንድሜ ሆይ፣ ስለዚህ ባለፈ በደሉ ምክንያት አሁን አትጥላው፣ ክፉም እንዲደርስበትና እንዲያገኘው አትመኝ። እኛ የተሰቀለውና *«የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው»* ያለው የእርሱ አገልጋዮች ነንና።» ሉቃ. 23፥34

ነገር ግን እርሱ የቤተ ክርስቲያንን ጥገኝነት የመስጠት (የመሰደጃነት መብት) በብዙ ዓይነት ዐዋጅና ሕግ የሻረ ነው ትላላችሁ። አዎ፣ ልክ ናችሁ፤ ሆኖም ግን አሁን ያደረገው ነገር ምን እንደ ነበር በተግባር ተምሯል፣ ራሱ ያወጣውን ሕግ ራሱ በድርጊቱ ሽሮታል፣ ለዓለሙ ሁሉ የሚታይ ሕያው ትርዒት ሆኗል። በአንደበቱ ባይናገርም በደረሰበት ነገር «እኔ እንደ ደረሰብኝ ያለ መከራ እንዳይደርስባችሁ እኔ እንዳደረግሁት ዓይነት ነገር አታድርጉ» እያለ ለሁሉም ሰው የማስጠንቀቂያ ድምፁን ያሰማል። በደረሰበት ነገር ለሁሉም መምህር ሆኗል። ቤተ ክርስቲያንም ነጸብራቅን ታፈልቃለች፣ አንበሳውን በእጇ ይዛውና አስራው ከመታየቷ የተነሣ በዓለሙ ዘንድ ታላቅ በሆነ የመፈራትና የመከበር ግርማ ትታያለች። ንጉሥ የሚከበረው ዘውዱን ደፍቶና ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ በዙፋኑ ላይ ሲቀመጥ ብቻ ሳይሆን ዓመፀኞችና ጠላቶቹ የነበሩት እጃቸው ወደ ኋላቸው ታስሮ ከንጉሡ ፊት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሲቀርቡም ነው እንጂ።





ምንም ዓይነት አስረጂና አሳማኝ ትንተና ሳያደረግ ለሕዝቡ በጉጉት መሰብሰብ እናንተ ራሳችሁ ምስክሮች ናችሁ። ዛሬ በፊታችን ያለው ትዕይንት በጣም አስደናቂ ነው፤ መሰባሰባችንም ታላቅ ነው። ዛሬ የማየው ሕዝብ ብዛት የተቀደሰውን የትንሣኤ በዓል ቀን ያህል ነውና። ስለዚህ ሰውዬው ምንም ቃል በአንደበቱ ሳይናገር ነገር ግን በድርጊቱ ከተንደ መለከት በበለጠ ጩኸት እዚህ ሰብስቧችኋል። የሰውን ሀብትና ክብር ከንቱነት ለማየት፣ የዚህን ዓለም ነገር ተለዋዋጭነትና ተገለባባጭነት በአካል ለማየት፣ ከጥቂት ቀን በፊት ሲያበራና ሲያንጸባርቅ የነበረው የአመንዝራዪቱ ፊት (በዐመፅና በቅሚያ የሚገኝ ሀብትና ክብር እንዲህ ነውና) አሁን ከማንም አሮጊት ፊት የባሰ ተጨማትሮና ተጨማዶ ለማየት ሁላችሁም ተሰብስባችኋል።

4. በሰው ላይ የሚደርስ መከራ እንዲህ ነውና፣ እንዲህ በሁሉም ላይ ሰልጥኖ ታላቅና ገናና የነበረው ሰው ከማንም ሰው ያነሰ ዋጋ ቢስና አሳዛኝ ሆኖ ይታያል። ሀብታም የሆነ ሰው ወደዚህ ጉባኤ ቢመጣ ከሚያየው ነገር ብዙ ጥቅም ያገኛል። ዓለሙን ሁሉ ሲያንቀጠቅጥ የነበረው ሰው አሁን ሰማይ ጫፍ ከደረሰ ሥልጣን በቅጽበት ወርዶ በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ በጭንቀት ገመድ ታስሮ ሲያይ የራሱን ትምክህተኝነትና ትዕቢት ይጠላል። እርሱን የሚመለከተውንና በቅዱስ መጽሐፍ የተነገረውን *«ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሣር ነው፣ ክብሩም ሁሉ እንደ ምድረ በዳ አበባ ነው»* የሚለውን፣ ወይም *«ዘመኖቹ እንደ ጢስ ናቸው»* የሚለውን፣ ወይም *«እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና፣ እንደ ለመለመ ቅጠልም ይረግፋሉና»* የሚለውን በተግባር በሚያየው ነገር ተምሮ ይሄዳል። ኢሳ. 40፥6-7፤ መዝ. 36፥2 ፤ 101፥4።

ድሀ የሆነ ሰውም ወደዚህ ትርዒት ገብቶ ሲመለከት በድህነቱ ዝቅተኝነትና ሐዘን አይሰማውም፣ ስለ ድህነቱም አይቆጭም። ነገር ግን ድሀ ስለ መሆኑ ያመሰግናል፤ ተሀውኮና አደጋ በማያንገብብበት በፀጥታ ወደብ ላይ አለና። እነዚህን ነገሮች ሲያይ የሰዎችን ሁሉ ገንዘብ ሰብስቦ ለጥቂት ጊዜ ሀብታም ሆኖ፣ ባለ ጸጋ ተብሎ፣ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ሕይወቱ በአደጋ ላይ ከሚወድቅ ባለበት ሁኔታ መኖር በጣም የቱሻለ ነገር መሆኑን ይገነዘባል። ሀብታሙም ሆነ ድሀው፣ ታላቁም ሆነ ታናሹ፣ ሁሉም ከዚህ ሰው እዚህ መጥቶ ጥገኝነት መጠየቅ የተነሣ ያገኙት ጥቅም ቀላል እንዳልሆነ አስተዋላችሁ? ሁኔታውን በማየት ብቻ እያንዳንዱ ሰው መድኃኒት አግኝቶና ተፈውሶ እንደሚመለስ ተረዳችሁ?

መልካም! ቁጣችሁን አብርጄ፣ ልባችሁን አለስልሼ ይሆን? በእርሱ ላይ የምታስቡትን ጭካኔያችሁን አጥፍቼው ይሆን? አዛኞችና ርህሩኆች እንድትሆኑ መንፈሳችሁን አነሣሥቼ ይሆን? በርግጥም ይህን ያደረግሁ ይመስለኛል። የፊታችሁ ሁኔታና ስታፈሱት የነበረው ዕንባ የዚህ ማስረጃ

ናቸውና:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንደ ዓለት ጠንካራ የነበረው ልባችሁ ወደ ሰምና ሰስላሳ አፈርነት ተለውጧል:: ስለዚህም የምሕረትን ፍሬ እናፈራ ዘንድ እንቸኩል፤ የተትረፈረፈ የሐዘኔታና የርህራኄ አዝመራን እናፈራ ዘንድ ንጉሡን በመለመን፤ ይልቁንም የንጉሡን ቁጣ እንዲያስዝበውና የምንለምነውን መልካም ነገር ሁሉ እንዲሰጠን ልቡን እንዲያራራልን እግዚአብሔርን እንማጸነው::

ይህ ሰው ለጥገኝነት ወደዚህ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ዓይነት አዲስ ነገር አልመጣም:: ወደዚህ መምጣቱን ንጉሡ እንደ ሰማ ሰውዬው በሥልጣን ዘመኑ ባደረሰው በደልና በፈጸመው ክፋት ሠራዊቱ በቁጣ ላይ የነበረና ይገደል ዘንድ ተላልፎ እንዲሰጣቸው እየጠየቁ የነበረ ቢሆንም የወታደሮቹን ቁጣ ለማለዘብ በማሰብ ረጂም ንግግር አደረገ:: ያጠፋው ጥፋት ብቻ ሳይሆን ምናልባት ያደረገው መልካም ነገርም ቢኖር ያም ግምት ውስጥ ሊገባለትና ሊታሰብለት የሚገባ መሆኑንና ከጥፋቱ ይልቅ ላደረገው መልካም ነገር የበለጠ የባለ ውለታነት ስሜት እንደሚሰማው፤ በአጠቃላይ ሰውዬው ድርጊቱ ክፉ የነበረ ቢሆንም እንደ ሰብአዊ ፍጡርነቱ ወገን በመሆኑ ይቅር ሊለው የተዘጋጀ መሆኑን ተናገረ:: እንደ ገና እየጮኹ፤ እየዘለሉና ጦራቸውን እየነቀነቁ አሁንም እንደ ገና የንጉሡን ግርማዊነት ስለ መሳደቡ ይበቀለው ዘንድ ሲያነሳሱትና ሲገፋፉት ከርህሩኅ ዓይኖቹ የዕንባ ዘለላን እያፈሰሰ ሰውዬው ለጥገኝነት የተሰደደበትን የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚሠዋበትን ቅዱስ መንበር ካሳሰባቸው በኋላ በመጨረሻ ቁጣቸውን አስታገሠ::

5. በተጨማሪም እኛን ራሳችንን ከሚመለከቱ ነገሮች ትንሽ ነገር ልጨምር:: ንጉሡ በመሰደቡ ቂም ሳይዝበት ካልተበቀለው በግላችሁ እንዲህ ዓይነት ነገር ያልደረሰባችሁ እናንተ ይህን ያህል ቁጣና የበቀል ስሜት የምታሳዩ ምን ዓይነት ይቅርታ ይገባችኋል? በበደላችሁ ሰው ላይ በቀልን የምትፈልጉ እናንተ ይህ ጉባኤ ካለቀ በኋላ እንዴት አድርጋችሁ ነው ወደ ቅዱስ ምሥጢር የምትቀርቡት? *«በደላችንን ይቅር በለን፤ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል»* የሚለውን ጸሎትስ እንዴት አድርጋችሁ ማለት ትላላችሁ? ብዙ በደል አድርሶባችኋል? ሰድቧችኋል? አዎ፤ ይህን አልክድም:: ሆኖም ግን አሁን ጊዜው የፍርድ ሳይሆን የምሕረት ነው፤ የሐተታና የምርመራ ሳይሆን የይቅርታ ጊዜ ነው::

ስለዚህ ማንም አይበሳጭ፤ አይቆጣም:: ነገር ግን እርሱን ካንዣበበበት ጥፋትና የሞት አደጋ ያድነው ዘንድ ሁላችንም እግዚአብሔርን እንለምን:: ስለ ቤተ ክርስቲያን፤ ስለ ተቀደሰው ምሥዋዕ ሲል የአንድን ሰው ሕይወት ለቤተ ክርስቲያን መባዕ አድርጎ ይሰጠን ዘንድ ርህሩኅ





የሆነውን ንጉሥ ሁላችንም አንድ ሆነን እንለምነው:: እንዲህ ብናደርግ ንጉሡ ራሱ ልመናችንን ይቀበለናል፤ ያመሰግነናልም:: እንዲያውም ከእርሱ ምስጋና በፊት ስለ መሐሪነታችንና ርህራኄያችን እግዚአብሔር አስቀድሞ ብዙ ዋጋ ይሰጠናል፤ የምንለምነውንም ያደርግልናል::

እግዚአብሔር ጨካኙንና አረመኔውን እንደሚጠላና እንደማይቀበል ሁሉ መሐሪና አዛኝ የሆነውን ደግሞ ደስ ብሎት በፍቅር ይቀበለዋል:: እንዲህ ያለው ሰው ጻድቅ ከሆነ የበለጠ የክብር አክሊል ይዘጋጅለታል፤ ኃጥእም ቢሆን ለወንድሙ በሚያሳየው ርህራኄና ሐዘኔታ ሽልማት ይሆነው ዘንድ በደሉን ይተውለታል:: *«መሥዋዕትን አይደለም፤ ምሕረትን እወዳለሁ»* ብሏልና:: ሆሴ.6.6:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን ሲፈልግና ከኃጢአት ይቅርታ የማግኛው መንገድ መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ ሲናገር ታገኘዋለህና::

በዚህም እግዚአብሔር እኛን በምሕረትና በይቅርታ እንዲመለከተን ስናደርግ ከኃጢአታችን ነፃ እንወጣለን:: በዚህ ቤተ ክርስቲያናችንን እናስጌጣለን:: እንዲሁም አዛኙ ንጉሣችን ቀድሞ እንዳልኩ ያመሰግነናል፤ ሕዝቡ ሁሉ ድርጊታችንን ያደንቃል፤ የዓለሙ ዳርቻ ሳይቀር የከተማችንን ሰብአዊነትና ደግነት ያደንቃል፤ ይህን ድርጊት የሰማ ሁሉ ያመሰግነናል:: እነዚህን መልካም ነገሮች እናገኝ ዘንድ ሁላችንም በጸሎትና በልመና በእግዚአብሔር ፊት እንውደቅ:: ምርኮኛውንና ስደተኛውን ከአደጋና ከቅጣት እናትርፈው፤ እኛ ራሳችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነትና መሐሪነት የሚመጣውን ዘለዓለማዊ ሕይወት እናገኝ ዘንድ፤ ኃይል፤ ሥልጣንና ክብር ዛሬም ዘወትርም ሁል ጊዜም ለዘለዓለም ለእርሱ ይሁን:: አሜን::

## ዋቢ ድርሳናት


1. ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገ/ሥላሴ ማ/ቤት፣ ፩፱፻፹፯ ዓ.ም
2. ስንክሳር፣ ከመጋቢት እስከ ጳጉሜን (1993ዓ.ም.) እና ከመስከረም እስከ የካቲት (1994ዓ.ም.)፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
3. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1987 ዓ.ም.
4. Ainsworth, W. F., Travels and researches in Asia Minor, Mesopotamia, Chaldea and Armenia. 2 vol. London 1842.
5. Anderson, J. G. C., A Journey of exploration in Pontus (=Studia Pontica I.). Brussels 1903.
6. Armstrong, C. B., The Synod of Alexandria and the Schism at Antioch in A.D. 362, The Journal of Theological Studies 22 (1921), 206-X21 and 347-355.
7. Bury, J. B., A History of the Later Roman Empire from the death of Theodosius I to the death of Justinian. 2 vol. London 1923.
8. Palladiana. N. II. The Dialog de Vita Chrysostomi and the Historia Lausiaca: Authorship, The Journal of Theological Studies 22 (1920-1921) 138-155.
9. Cayre, F., Manual of Patrology and History of Theology, First Volume, first and second books, 1935.
10. Cross and Livingstone (Editors), The Oxford Dictionary of the Christian Church, Oxford University Press, 1997.
11. St. John Chrysostom: Homilies on the Epistles of Paul to the Corinthians, NPNF, Volume 12, 1999.
12. St. John Chrysostom: Homilies on GALATIANS, Philippians, Colossians, Thessalonians, Timothy, Titus, and Philemon. NPNF, Volume 13, 1994.
13. St. Athnatius: Select Works and Letteres, NPNF, Volume 4, 1999.
14. Socrates: Church History from A.D. 305-438; Sozomenus: Church History from A.D. 323-425, Volume 2, 1999.
15. St. Chrysostom: On the Priesthood; Ascetic Treatises; Select Homilies and Letters; Homilies on the Statutes NPNF1-09. New York: Christian Literature Publishing Co., 1886.
16. Socrates and Sozomenus, Ecclesiastical Histories, NPNF2-02.New York: Christian Literature Publishing Co., 1886.
17. NPNF1-10. St. Chrysostom: Homilies on the Gospel of Saint Matthew, New York: Christian Literature Publishing Co., 1886
18. The Dialogue of Palladius Concerning the Life of St. John Chrysostom, Translated by Herbert Moore, 1921






## ከአሁን በፊት የታተሙ

1. ፍኖተ ቅዱሳን
2. ቃል ኪዳን በነገረ ድኅነት
3. ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ - ሕይወቱና ትምህርቱ
4. ከበረሃውያን ሕይወትና አንደበት
5. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ - ሕይወቱና ትምህርቱ

## ወደፊት የሚታተም

ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ- ሕይወቱና ትምህርቱ

## አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

**የታላቁ ቅዱስ ጳኩሚስ**
**የተጋድሎ ሕይወቱና**
**ሥርዓተ ገዳሙ**

‹‹ከእነዚህ አንዱን (ክርስቲያኖቹን) አሞጽ ወይም አብድዩ ማነው? ወይም ሐዋርያት ወይም ነቢያት ስንት ነበሩ? ብላችሁ ብትጠይቋቸው ድዳ ይመስል ዝም ይላሉ፤ ነገር ግን ስለ ፈረሶች ወይም ስለ ተሽቀዳዳሚዎች ወይም ስለ ሌሎች ትርዒት አቅራቢዎች ወይም ስለ ተወዳዳሪዎች ብትጠይቋቸው የንግግር ጥበብ ከተማሩት ባላነሰ ግልጽነት፣ በጥንቃቄና በስሜት ሆነው ይመልሳሉ።››

(ከውስጥ ገጽ)

‹‹የክርስቶስን አካል ልታከብሩት ትወዳላችሁ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ራቁቱን ሆኖ እያያችሁት አትለፉት፣ በየመንገዱ ራቁቱን ሆኖ በብርድ እየተሰቃየ አለና፤ ራቁቱን ሆኖ በብርድ እየተሰቃየ አልፋችሁት መጥታችሁ ከዚህ ከቤተ መቅደስ በብርና በወርቅ ላስጊጥህ አትበሉት። ... ወንድምህ በረሃብ እየተሰቃየና እየሞተ ቅዱስ ደሙ የሚቀዳበት ጽዋ በወርቅ ቢለበጥና ቢንቆጠቆጥ ጥቅሙ ምን ላይ ነው? አስቀድመህ የወንድምህን ረሃብ በማጥገብና ጥሙን በማርካት ጀምር፣ ከዚያ በኋላ በተረፈህ ገንዘብ ቤተ መቅደሱንና ንዋያተ ቅድሳትን እንዲህ ማስጌጥ ትችላለህ።››

(ከውስጥ ገጽ)

‹‹የቆንስላነትህ አስደሳች ክብርና አስደናቂ አጃቢዎች አሁን የታሉ? በፊትህ የሚበሩልህ ችቦዎች የታሉ? ... በከተማ ስትንቀሳቀስ ይቀበሉህ የነበሩት ጭብጨባዎች የታሉ? ... ስልጣንህን ደጅ ሲጠኑና ዙሪያህን ሲከቡህ የነበሩት፣ የአንተን ትኩረት ለመሳብና ለማግኘት ሲሉ ማንኛውንም ነገር ሲያደርጉና ሲናገሩ የነበሩትስ የት አሉ? ሁሉም አሁን የሉም፤ ላይመለሱ በነው ጠፍተዋል። ...

‹‹ሁሉም የሌሊት ቅዠቶች ኖረዋል። ሌሊቱ አልፎ ቀኑ በመምጣቱ ከጨለማው ጋር አብረው የጠፉ ህልሞች ብቻ ነበሩ ። ወቅቱ ሲያልፍ የጠወለጉና የረገፉ የጽጌ ወራት አበባዎች ነበሩ። ያለ መስሎ ታይቶ እንደ ጠፋ ጥላ፣ ወደ አየር ተኖ እንደ ጠፋ ጢስ፣ ሟሙቶ እንዳለቀ አረፋ፣ እንደ ተበጣጠሰ የሸረሪት ድር ነበሩ። ስለዚህ ሁል ጊዜ ይህን መንፈሳዊ መዝሙር እንዘምራለን፡- ‹ሁሉ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነው› የሚለውን።››

(ከውስጥ ገጽ)

እሌኒ ማ.ቤ.ኃ.የተ.የግ.ማ.

ዋጋ ብር 25.00